፳፰ ጉባዔ ምሳሌያተ ወገዐረ ተዝካር፡

፳፱ ጉባዔ ምሳሌያተ እስመ ለቀደምት፡

፴ ጉባዔ ምሳሌያተ ወእመቦ ዐራቢ ዕፀ ዘያስተርኢ፡

፴፩ ጉባዔ ምሳሌያተ ወአንተሰ አምላክነ ኄር፡

፴፪ ጉባዔ ምሳሌያተ በረድኒ ወአስሐትያ ቆሙ ወጸንዑ፡

፴፫ ጉባዔ ምሳሌያተ ለእንታክቲ ሌሊት አእመ ርዋ አበዊነ፡

፴፬ ጉባዔ ምሳሌያተ ቃለ መክብብ፡

፴፭ ጉባዔ ምሳሌያተ ቦ ለኵሉ ዘመን፡

፴፮ ጉባዔ ምሳሌያተ ዕቀብ እግሪከ፡

፴፯ ጉባዔ ምሳሌያተ ይኄይስ ስም ሠናይ እምቅብዕ መዓዛ፡

፴፰ ጉባዔ ምሳሌያተ ነዓ ብላእ ኅብስተከ፡

፴፱ ጉባዔ ምሳሌያተ አሌ ለኪ ሀገር እንተ ንጉሥኪ ወሬዛ፡

## የመጽሐፈ ዳንኤል ጉባዔ

፩ ጉባዔ ታሪክ፡

፪ ጉባዔ ወሀሎ አሐዱ፡

፫ ጉባዔ እመ ሠላሳ ዓመተ መንግሥት፡

፬ ጉባዔ በካልዕ ዓመተ ዓመት መንግሥት፡

፭ ጉባዔ እመ አሠርቱ ወሰመንቱ፡

፮ ጉባዔ መቆመ አዛርያ፡

፯ ጉባዔ ወኢሐደገ ወዓልት፡

፰ ጉባዔ ይቤ ናቡከደነፆር፡

፱ ጉባዔ ብልጣሶር ገብረ ለመገብቱ፡

፲ ጉባዔ ወዳርዮስ ሜዶናዊ ነግሠ፡

፲፩ ጉባዔ በቀዳሚ ዓመተ መንግሥቱ ለብልጣሶር፡

፲፪ ጉባዔ ወአመ አሠርቱ ወሠለስቱ ዓመተ መንግሥቱ ለብልጣሶር፡

፲፫ ጉባዔ በቀዳሚ ዓመተ መንግሥቱ ለዳርዮስ፡

፲፬ ጉባዔ በሠላስ ዓመተ መንግሥቱ ለቂሮስ፡

፲፭ ጉባዔ ታሪክ ወአነ በዓመት ቀዳሚ ዘዳርዮስ፡

፲፮ ጉባዔ ወወለተ አንስትያ ትትወነብ፡

፲፯ ጉባዔ ወውእተ አሚረ ይትነሣእ ሚካኤል መልአክ፡

፲፰ ጉባዔ እምድኅረ ሞተ እስጥያኪስ፡

# መጽሐፈ ኢዮብ

## መቅድም ፤

ኢዮብ ማለት አበባ ፣ ጨረቃ ማለት ነው፤ አሕዛብ ለልጆቻቸው ስም ሲያወጡ በአማረ በአማረ ነገር ነውና፣ ይህም ኢዮብ አብርሃምን የሚመስል በት፣ ከአብርሃም የሚበልጥበት ግብር አለው፤ አብርሃምን የሚመስልበት አብርሃም እንግዳ ይቀበል ነበር፤ ኢዮብም እንግዳ ይቀበል ነበር ፤

ወለኵሉ ዘመጽአ ርኅው አንቀጸ ቤትየ ፣

ኆኅተ ቤትየም ይላል፤ ወበአፍአ ኢኀደረ ነግድ ብሎ እንዲያ መጣው ከአብርሃም የሚበልጥ በት ግብር አብርሃም ሚስቱ ሣራ ሳለች ከአጋር እስማኤልን ወልዷል፤ ሚስቱ ከሞተች በኋላም ከኬጡራ ፮ ልጆች ወልዷል፤ ኢዮብ ግን ሚስቱ፣ ባርከ ለእግዚአብሔር ወሙት፣ ብላ በዚህ ምክንያት ብትቀሠፍበት እንደ ዘመነ ሐዲስ በአንዲት ፀንቶ የሚኖር ሁኗል ፣ ይህም ኢዮብ ጥመት የሌለበት ቅን፣ ኃጢአት የሌለበት ንጹሕ፣ ሐሰት የሌለበት እውነተኛ፣ እግዚአብሔርን የሚፈራ፤ የሚያመልክ በፍጹም ልቡናው ከክፉ ሥራ ሁሉ የሚርቅ ደግ ሰው ነበር ፯ ወንዶች ልጆች ፫ ሴቶች ልጆች ነበሩት፤ አሁን ግምብ ተንዶ አጠፋቸው የሚል ነውና እንደ አር እስት ተናግሮታል፤ ፯ ሺህ የከብት መንጋ ነበረው ፤ አንድ ሁለት ብሎ ቆጥሮ፤ አንድም በረቱን ቆጥሮ ፫ ሺህ የበግ መንጋ ነበረው ፤ አንድ ሁለት ብሎ ቆጥሮ፤ አንድም በረቱን ቆጥሮ ፭፻ ግመል፣ ፭፻ ጥማድ በሬ፣ ፭፻ ባዝራ ወደልጋዝም ይሉታል ፤ ይህን ያህል ገንዘብ ነበረው፤ ባሮቹም እጅግ ብዙ ነበሩ፤ አሳርሶ አስነግዶ የሚያገኘው እጅግ ብዙ ነበር ፤ አንድም ኀታው ፣ ኀተራው፣ እሪቁ ብዙ ነበር ፤

ወውእቱሰ ብእሲ ኄር በብሔረ ጽባሕ በምሥራቀ ፀሐይ ፣

ኢዮብ ግን በፀሐይ መውጫ በምሥራቅ የሚኖር ደግ ሰው ነበር፤ አንድም እምሥራቀ ፀሐይ ይላል፤ በፀሐይ መውጫ ከነበሩ ሰዎች ይልቅ በብሔረ ጽባሕ የሚኖር ደግ ሰው ነበር ፤

ወየሐውሩ ደቂቁ ወይትጋብኡ ኅቡረ፣

ልጆቹ ሒደው በአንድነት ይሰበሰቡ ነበር፣ ከባለጌ ልጅ ሲለይ ነው፤ የባለጌ ልጅ የሆነ እንደሆነ አንዱ ሲወጣ አንዱ ሲገባ ነው፤ እሱ ግን ሥርቶ፣ ቀጥቶ አሳድጓቸዋልና በአንድነት ይወጡ ይገቡ ነበር ፤

ወይገብሩ ምሳሐ ኰሎ አሚረ ፤

ሁል ጊዜ ምሳ ጋሬዳ ያደርጉ ነበር፡ የኢዮብ ልጆችስ ምሳ ጋሬዳ አያደርጉም ብሎ ሠርቀ ወርኀን ያደርጉ ነበር ፡

ወይነሥኡ ሠሳሰ አኀቲሆን ይብልዓ ወይስተያ ምስሌሆሙ ፤

ከነሱ ጋራ ይበሉ ይጠጡ ዘንድ ሦስቱን እህቶቻቸውን ይዘው ይሔዱ ነበር፤ አንድም ሦስቱን እህቶቻቸውን ይዘው ይሔዱ ነበር፤ ከነሱ ጋራ እንደነሱ ይበሉ ይጠጡ ነበር ፡

ወተፈጺሞ መዋዕለ ግዕዘሙ ይፌንዎሙ ኢዮብ ቅድመ እግዚአብሔር፤

በዓል የሚያደርጉበት ቀን ከተፈጸመ በኋላ ኢዮብ በእግዚአብሔር ፊት ያሰናብታቸው ነበር፡

ወያስተሠሪ ሎሙ ፤

ኃጢአታቸውን ያስተሠርይላቸው ነበር፡ ወይገይሥ በጽባሕ የተሳለፈ ነው ፡

ወያበውዕ መሥዋዕተ በእንቲአሆሙ በኍልቆሙ ፡ ወ፩ደ ላህመ በእንተ ኃጢአተ ነፍሱ ፤

የኔ የኢዮብ ልጆች ሠርቼ ቀጥቼ አሳድጌያቸው ይበድላሉን ምንም በገቢር ኃጢአት ባይሠሩ በሐልዮ ሳይሠሩ አይቀሩም ብሎ ፲፭ በነግህ፤ ፲፭ በሠርክ ይሰዋ ነበር፡ እሱ ከነሚስቱ ፩ድ ይሰዋ ነበር፤ በኍልቆሙ ያለውስ አይመችም ብሎ ለሰዎች ይሰጧል ፯ቱ ወንዶች ልጆች ከነሚስቶቻቸው፤ ፲፬ት ሴቶች ልጆቹ ከነባሎቻቸው፤ እሱ ከነሚስቱ ፳፪ ፤ ፳፪ በነግህ ፳፪ በሠርክ ይሰዋ ነበር ፡

ወይገይሥ በጽባሕ ወያበውዕ መሥዋዕተ ወያስተሠሪ ሎሙ ፤

ወይፌንዎሙ ቅድመ እግዚአብሔር ሲል ነው ፡

ወእምድኅረ ይእቲ ዕለት መጽኡ መላእክተ እግዚአብሔር ወቆሙ ቅድመ እግዚአብሔር ፤

ከዚች ቀን በኋላ መላእክት መጥተው በእግዚአብሔር ፊት ቆሙ፤ ሰይጣንም መጥቶ ከነሱ ጋራ በቦታው ቆመ፡ ለሰይጣን ምን ቦታ አለው ቢሉ እነሆ ዛሬ ለቋሚ ለለጓሚ ኀሰር ቦታ እንዳለው ኀሠር ቦታ አለውና፡ እግዚአብሔር ሰይጣንን ከወዴት መጣህ አለው፤ ሰይጣን የመጣበት ለጌታ ጠፍቶት አይደለም፡ ሊያናግረው ነው እንጂ፤ ሰይጣንም መለሰ፤ እንዲህ አለ፤ ከሰማይ በታች አራቱን ማዕዘን ዞሬ ሁሉን ኃጢአት አሠርቼ፤ ጣዖት አስመልኬ ወዳጅ፤ አሳጥቼህ መጣሁ አለው፤ እግዚአብሔርም ነገሩ በኢዮብ እንደሆን



የውቃልና ሁሉን ብታስት በወዳጄ በኢዮብ ላይ ክፉ ነገር እንዳታደርግ እወቅ አለው፤ ሰይጣንም መለሰ፤ እንዲህ አለ፤ ኢዮብ በከንቱ ያመለከኝ ይመስልሃል? አለው ፤ ገንዘቡን በዚህ ዓለም አብዝተህለታልና ስለዚህ ነው እንጂ፤ በከንቱ ያመለከኝ ይመስልሃልን፤ ነገር ግን እደ መዓትህን አምጥተህ ገንዘቡን ሁሉ አጥፋበትና ፤

እመ ውስተ ገጽከ ኢባረከከ ፤

ፊት ለፊት ባይሰድብህ ታይ፤ ይሰድብሃል እንጂ አለው፤ ከዚህ በኋላ ያለውን ገንዘቡን ሁሉ ሰጥቼሃለሁ፤ ነገር ግን እሱን አትንካ አለው፤ ሰይጣንም እንደተሾመ፤ እንደተሸለመ ደስ እያለው ወጣ ፤ ከዚህ በኋላ በአሕዛብ አድሮ ገንዘቡን ያጠፋበት ጀመር ፡

ወመጽአ ዘይዜንዎ ለኢዮብ ፤

ለኢዮብ ወሬ የሚነግረው መጣ በሬዎችህ ተጠምደው ሲያርሱ፤ ባዝሮችህ በአጠገባቸው ተሰማርተው ሳለ የሚማርኩ ሰዎች መጥተው ማረኳቸው፤ ብላቴኖችህንም በሰይፍ ገደሉ ፤ እኔ ብቻዬን ቀረሁ፤ ይህን ልነግርህ መጣሁ አለው ፤ ጃን ገበሩን መስሎ መጥቶ ነግሮታል ፤

ወእንዘ ዘንተ ይዜንዎ መጽአ ካልዕመ ዘይዜንዎ ፤

ይህን ሲነግረው ሁለተኛ ወሬ የሚነግረው መጣ ፤ እሳት ከሰማይ ወርዶ በጎችህን አቃጠለቻቸው፤ ብላቴኖችህን አጠፋቻቸው አለው ፤ እኔ ብቻዬን ዳንኹ፤ ይህን ልነግርህ መጣሁ፤ በግ መልከኛውን መስሎ መጥቶ ነግሮታል ፤

ወእንዘ ዘንተ ይዜንዎ መጽአ ሣልስመ ዘይዜንዎ ፤

ይህን ሲነግረው ሦስተኛ ለኢዮብ ወሬ የሚነግረው መጣ፤ በፈረስ የተቀመጡ ፫ቤት ጭፍራዎች ብዙ ሠራዊት ላሞችህን ግመሎችህን ከበው ማረኳቸው፤ ብላቴኖችህን በሰይፍ መትተው ገደሏቸው፤ እኔ ብቻየን ቀረሁ፤ ይህን ልነግርህ መጣሁ አለው፤ ላም ራሱን መስሎ መጥቶ ነግሮታል ፡

ወእንዘ ዘንተ ይዜንዎ መጽአ ራብዕመ ዘይዜንዎ ፤

ይህን ሲነግረው ፬ኛ ወሬ የሚነግረው መጣ፤ ወንዶች ልጆችህ ሴቶች ልጆችህ፤ በታላቅ ወንድማቸው ቤት በአንድነት ሲበሉ ሲጠጡ ድንገት ዕኑዕ ነፋስ ከምድረ በዳ ተነሥቶ አራት ማእዝን ያለውን ቤት ገፍቶ ጣለው፤ ይህስ በአንድ ወገን ያሉት ይቀራሉ ብሎ አራቱን

www.ethiopianorthodox.org

ማእዝን ገፍቶ ጣለው፤ በልጆችህ ላይ ወደቀ ሞቱ፤ እኔ ብቻ ዳንሁ፤ ይህን ልነግርህ መጣሁ አለው፤ ሰይፍ ጃግሬውን መስሎ መጥቶ ነግሮታል፤ ከዚህ በኋላ ኢዮብ ይህን በሰማ ጊዜ እግዚአብሔር ቢሽረኝ አልሻርም እላለሁ ? ብሎ ልብሱን ቀደደ አሰለበ ፤

ወይቤ ዕራቅየ ወፃዕኩ እምከርሠ እምየ ወዕራቅየ እገብእ ውስተ ምድር፣

ጥንቱን ከናቴ ማኅፀን ለአንገቴ ፈትል፣ ለወገቤ ጨርቅ ሳልይዝ ተወለድሁ፤ ዛሬም ለአንገቴ ፈትል ለወገቤ ጨርቅ ሳልይዝ ወደ መቃብር እመለሳለሁ፤ እግ ዚአብሔር ሰጠ፤ እግዚአብሔር ነሳ፤ እኔ ምን ዕዳየ የሰጠ ቢነሣ የለውም ወቀሳ እንዲሉ ፤

ወእምዝ እምድኅረ ይእቲ ዕለት መጽኡ መላእክተ እግዚአብሔር ወቆሙ ቅድሜሁ ፣

እግዚአብሔር ወሀበ ወእግዚአብ ሔር ነሥአ ካለባት ቀን በኋላ ትእግሥቱን ለማሣረግ መላእ ክት መጥተው በፊቱ ቆሙ፣ ሰይጣንም መጥቶ በፊቱ ቆመ፣ አራቱን መዓዝን ዞሬ ኃጢአት አሠርቼ ፣ ጣዖት አስመልኬ፣ ወዳጅ አሳጥቼህ መጣሁ አለው፤

ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሰይጣን ሁቅኬ ላዕለ ኢዮብ ቍልዔየ ፣

እግዚአብሔር ሰይጣንን በወዳጄ በኢዮብ ላይ ክፉ ነገር እንዳታ ደርግ እወቅ አለው፤ በዚህ ዓለም እንደሱ ያለ ኃጢአት የሌለበት ንጹሕ፣ ሐሰት የሌለበት እውነ ተኛ ፤

ወዓዲ የዋህ ፣

ዳግመኛም እንደሱ ያለ ዕጉሥ የለምና ፤

አንተሰ ትቤ ታኀጕሎ ንዋዮ በከንቱ እመ ኢያእኩተከ ፣

አንተ ግን እንደ አሕዛብ ደም አፍስሶ፣ ስብ አጢሶ ባያመሰግ ንህ ገንዘቡን ታጠፋበት ዘንድ ላጥፋበት አልህ፤

ወተሰጥዎ ሰይጣን ለእግዚአብሔር ወይቤ ማዕስ ቤዛ ማዕስ ፣

ሰይጣን መለሰለት፣ እንዲህ አለ፤ ቁርበት ለቁርበት ቤዛው ነው፤ ጫማ ለጠጠር፣ ጋሻ ለጦር እን ዲሉ፣ እንደዚህም ሁሉ ኢዮብ እንጂ በገንዘቤ ከእግዚአብሔር ጋራ ታረቅሁበት አለህ አለው ፤

ወባሕቱ ፈኑ እዴከ ወግሥሥ አእፅ ምቲሁ ወሥጋሁ ፣

ነገር ግን እደ መዓትህን አምጥ ተህ ሥጋውን የሚያሳብጥ፣ አጥ ንቱን የሚቀጠቅጥ ደዌ አምጣ በትና ፊት ለፊት ባይሰድብህ ታያለህ አለው ፤

ናሁ መጠውኩከ ውስተ እዴከ ሥጋሁ ወዳዕሙ ነፍሶ ዑቅ ፣

ሥጋውን ሰጥቼሃለሁ፤ ነገር ግን ነፍሱን ከሥጋው እንዳትለይ እወቅ አለው፤ ደስ እያለው ወጣ፤



ወአኀዞ ለኢዮብ ዝልጋሴ እምእግሩ እስከ ርእሱ ፣

ከዕለታት አንድ ቀን በአደባ ባይ ተቀምጦ ነገር ሲሰማ ይህስ ጊዜውም አይደል ብሎ በአዳ ራሽ ተገኝቶ ሲያበላ፤ ሲያጠጣ ብሂሞትን መስሎ ከአፉ፣ ከአፍ ንጫው እንደ ጢስ ያለ ትጉል ጉል እያለ መጥቶ እፍ አለበት፤ ከእግሩ እስከ ራሱ ደዌ ሥጋ እንደ ቀሚስ አለበሰው ፤

ወነሥአ ገልዐ ወአኀዘ ይሕክክ ቍስሎ ፣

ጥፍሩ ውልቅ ውልቅ እያለ ቢወ ድቅበት ገል አንሥቶ ቍስሉን ያክ ጀመረ ፤

ወነበረ አፍአ እም ሀገር ፣

ከከተማ ወጥቶ በአፍአ ተቀ መጠ፤ ስለምን ቢሉ ያለፈ ያገ ደመውን፣ የወጣ የወረደውን መድኃኒት ለመጠየቅ ነው ፤

ወሰሚያሙ ፫ቱ አዕርክቲሁ ለኢዮብ ኵሎ ዘረከቦ ለኢዮብ ፣

ሦስቱ ወዳጆቹ ኢዮብን ያገኘ ውን መከራ ሰምተው በከብቱ ጥፋት እግዚአብሔር ይርጠ ብህ፣ በልጆቹ ሞት እግዚአብ ሔር ያጥናህ፣ ከደዌህ ይፈው ስህ ለማለት መጡ ፤

ነጸርዎ እምርኁቅ ወኢያእመርዎ ፣

ከሩቅ አይተው አላወቁትም ልብልብ ግንድ መስሏልና ሰባት ቀን ዝም ብለው ሰነበቱ፤ እጅግ ዕኑዕ የሆነ መከራውን አይተዋ ልና ፤

ወእምድኅረዝ ከሠተ ኢዮብ አፉሁ፣

ኢዮብ ከሰባት ቀን በኋላ ነገር ጀመረ ወከሠተ አፉሁ ጴጥሮስ እንዲል ፤

ወረገማ ለዕለት እንተ ባቲ ተወልደ፣

የተወለደባትን ቀን ረገማት፤ ዕለ ቲቱን ቢረግማት የምትጐዳ ፣ ባይረግማት የምትጠቀም ሁና አይደለም፤ ዕንዓ ኀዘን ያናግረዋል እንጂ፤ አንድም እግዚአብሔርን ባማ ክህደት፣ መላእክትን ባማ ኃጢአት ይሆንብኛል ብሎ የተ ወለደባትን ቀን ረገመ ፤ ከዚህ በኋላ በከብቱ ጥፋት እግዚአብ ሔር ይርጠብህ፤ በልጆቹ ሞት እግዚአብሔር ያጥናህ ለማለት መጥተው ነበር፤ ሰይጣን ልቡና ቸውን ወደ ጥመት መልሶት ሦስቱም ወዳጆቹ እየተፈራረቁ ይከራከሩታል፤ ኢያርመምኩ ወኢያዕረፍኩ ትላለህ እንጂ ፤

ተዘከር ከመ አልቦ ንጹሕ ዘተኀጕለ፣

የጠፋ ጻድቅ ንጹሕ ሰው እንደ ሌለ አስብ ፤ ሎጥን ፣ ኖኅን ፣ አብርሃምን ጠፋ አለው ፤

ሶበሁ ሰብእ ውእቱ ዘይትዋቀሰኒ እምሖርኑ ኀቡረ ውስተ ዓውድ ፣

የሚከራከረኝ ሰው ቢሆን አን ድነት ወደ አደባባይ በሔድን

www.ethiopianorthodox.org

ነበር፤ ሶበሁ ቦ ዕሩየ ዘይፈትሕ ለነ፣ አስተካክሎ የሚፈርድልን ቢኖር ፤

ወያዐምዕ ማዕከሌነ እምተአተተ ዝንቱ በትር እምኔየ ፣

በሁለታችን መካከል የሚሰማ ዳኛ ቢኖር፣ ቀኝና ግራ ሁነን ተከራክረን ይህ ደዌ ለኢዮብ አይገባውም አሰኝቼ መከራው ከኔ በራቀልኝ ነበር ይላል፤ ኢዮብ ራሱን አርቆ እነዚያ ሲናገሩ እሱ ሲመልስ እንደ ሰለቹት አይቶ ፤

መኑ እምጸሐፎ ለነገርየ ወይልክዎ ውስተ መጽሐፍ ዘለዓለም ፣

ነገሬን ለዘለዓለሙ በብራና ማን በጻፈው ነበር ፤

ወውስተ ምጽሐለ ሐፂን ወዐረር ፣

በብርት በብረት ሰሌዳ ማን በጻፈልኝ?፣ በብረት በብርት የተጻፈ እንዳይጠፉ፣ እንዳይ ጠፉ አድርጎ ማን በጻፈልኝ ነበር ፣ እንዲህ ሲል ሰምቶ ኤልዩስ ጽፎታል፤ ኤልዩስ የእ ኅቱ ልጅ ነው ፤ አንድም ጋሻ ጃግሬው ነው ፤

ወነደገ ኢዮብ ነገረ ወአርመሙ እሉ ፫ቱ አዕርክቲሁ ፣

ኢዮብ ነገሩን ተወ ፤ ሦስቱ ወዳጆቹም ዝም አሉ ፤

እስመ ይጼደቅ ኢዮብ በቅድሜ ሆሙ ፣

ኢዮብ በፊታቸው ይመጻደቅ ነበርና ተዉት ይመጻደቅበት ብለው ዝም አሉ ፤ አንድም ይረታቸው ነበርና አልመለሱለ ትም ፤

ወተምዐ ኤልዩስ ወልደ ብርክያል፣

የብርክያል ልጅ ኤልዩስ ተቆጣ፤

ወተምዓ ለኢዮብ በሕቁ ፣

ኢዮብን ለምን ጻድቅ ነኝ ፣ ንጹሕ ነኝ ትላለህ ብሎ በጥ ቂቱ ተቆጣው ፤

ወተምዖሙ ጥቀ ለ፫ቱ አዕርክቲሁ፣

እናንተስ ጻድቅ ሰው ኢዮብን እንደ ሌባ፣ እንደ ቀማኛ ኃጥእ ነህ ለምን ትሉታላችሁ ? በገ ቢር ባትሠራ በሐልዮ ሳት ሠራ ቀረህ? በሉት እንጂ ብሎ ፫ቱን ወዳጆቹን እጅግ ተቆጣ ቸው ፤ ጌታም የነዚያን ነገር ሲጠላ የእሱን ነገር ተቀብሎ ታል ከዚህ በኋላ፤

ወተሰአሎ እግዚአብሔር ለኢዮብ በደመና ወበዓውሎ ፣

እግዚአብሔር ኢዮብን በደመና በነፋስ አድሮ ተናገረው፤ መጀመ ሪያ በዮርዳኖስ ተጠመቅ አለው፤ ተጠመቀ፤ ከደዌው ተፈውሷል፣ በሁለተኛው ኃይሉ ጸንቷል ፣ በሦስተኛው እንደ እከክ ያለው



ረግፎለታል፤ የሚጠይቅ እየመ ሰለ ብዙ ስነ ፍጥረት ነግሮታል፤

ቅንት ሐቌከ ከመ ብእሲ ፣

ኢዮብ እንደ ሰው ሁኖ አግኝ ቼው ተከራክሬው ብትል እኔም እንደ ሰው ሆኜ መጥቻለሁና በዓለ አእምሮ እንደ መሆንህ ወገብ ልቡናህን አጽና ማለት መጣሁልህ ታጠቅ አለው ፤

ወተሰጥዎ ኢዮብ ለእግዚአብሔር ወይቤ አአምር ከመ ኵሎ ትክል ወኵሉ ይትከሃለከ ወአልቦ ዘይስዓ ነከ ፣

ኢዮብ ለእግዚአብሔር መለሰ፤ እንዲህ አለ፤ ሁሉ እንዲቻልህ የሚሳንህ እንደሌለ አውቃለሁ አለው፣ ከዚህ በኋላ የቀደመ ገንዘቡን ሁሉ እጥፍ እጥፍ አድ ርጎ ሰጥቶታል፤ ከብቱ ፯ሺህ ነበር ፲ ከ፬ ሺህ ሁኗል፤ በጎቹ ፫ ሺህ ነበሩ፣ ፮ ሺህ ሁነዋል፤ ጥማዱ ፭፻ ነበር፣ ሺህ ሁኗል፤ ባዝሮቹ ፭፻ ነበሩ፣ ሺህ ሁነ ዋል፤ ግመሎቹ ፭፻ ነበሩ፣ ሺህ ሁነዋል፤ ፯ ወንዶች ልጆች፣ ፫ ሴቶች ልጆች ተወለዱለት፤ ልጆ ቹን ግን እጥፍ አድርጎ አልመ ለሰለትም፤ ስለምን ቢሉ በነፍስ ሕያዋን ስለሆኑ ፤ ኋላም የሚያ ስነሣቸው ስለሆነ፣ ኢዮብ ከተ

ፈወሰ በኋላ ፻፵ ዘመን ኖረ፤ የኖረው መላ ዘመኑ ፪፻፵፰ ዘመን ነው ፤

ወርአየ ኢዮብ ደቂቆ ወደቂቀ ደቂቁ ፣

ኢዮብ የልጅ ልጁን አይቶ በተፈጥሮ የተሰጠውን ዘመኑን ፈጽሞ አርፏል ፤

ወከመዝ ትርጓሜሁ እመጽሐፈ ሦርያ ፣

ትርጓሜ ስሙ ይላል፤ ከሦርያ ቋንቋ ወደ ዕብራይስጥ የተመ ለሰው ይህ ነው፤ ሙሴ ምድያምን በወጋ ጊዜ የደገኘው የኢዮብ መጽሐፍ ከዚህ አለ አሉት፤ እሱ ከሦርያ ወደ ዕብራይስጥ መልሶታል ፤ አንድም ዳዊት ኤዶምያስን በወጋ ጊዜ የደገ ኘው የኢዮብ መጽሐፍ ከዚህ አለ አሉት፤ እሱ ከሦርያ ወደ ዕብራይስጥ ቋንቋ መልሶታል፤ ስሙንም ሳይቀር እጥፍ አድር ጎለታል፤ ኢዮብ ማለት አበባ ጨረቃ ማለት ነበር ፤ ፍሬ ፀሐይ ሲል ኢዮብ ብሎታል ፤

ወሐምስ ውእቱ ኢዮብ እምአብር ሃም፣

ይኸውም ኢዮብ ለአብርሃም ፳ኛ ትውልድ ነው፤ አብርሃምን ትቶ ይስሐቅ፣ ኤሳውን፣ ኤሳው ራጉኤልን ፣ ራጉኤል ዛራን ፣

www.ethiopianorthodox.org

ሕፍትም ኢዮብን የትዕግሥት አብነት እያደረጉ ወስደውታል፤ ይህንንም ጻፈው አለው፤ ተጽፎ ሲነበብ፣ ሲተረጐም ከነቢያት እስከ ሐዋርያትም ደረሰ፤ ሐዋርያትም ለቀሌምንጦስ ሰማንያ አንዱን መጽሐፍ ቆጥረው ሲሰጡት አንድ መጽሐፈ ኢዮብ ብለው አስረክበውታል፤ ይህም መጻፉ ለከንቱ አይደለም፤ እኛ ልንገሠዕበት እኛ ልንመከርበት ነው፤ ወኵሉ ዘተጽሕፈ ለተግሣፀ ዚአነ ተጽሕፈ ከመ በትዕግሥትነ ወበተወክሎ መጽሐፍ ንርከብ ተስፋነ እንዲል፤ ይህ አርእስት ነው፤ ፲፱ ለመጻሕፍት አርእስት ሲሰጡ አርእስት ሰጥተውታል፤ እሱ ግን ነገሩን ወሀሎ ፩ብእሲ ብሎ ያመጣል ::

## ምዕራፍ ፩

አንደኛው ምዕራፍ ይህ ነው::

፩፡ ወሀሎ ፩ ብእሲ በብሔረ አውስጢድ ዘስሙ ኢዮብ ፣

አውስጢድ በሚባል አገር ስሙ ኢዮብ የሚባል ፩ድ ሰው ነበር፤ ስለምን በዋዌ ጀመረ ቢሉ መጻሕፍት ይቀድሙታልና አንዱ መጽሐፍስ ላንዱ መጽሐፍ ዋዌ አይሆነውም ብሎ መጽሐፍ ምሥጢር ይጠነቅቃል እንጂ አንድና ብዙ ፣ ሩቅና ቅርብ ፣ ሴትና ወንድ አይጠነቀቅምና፤ ወሀሎ ፩ዱ ብእሲ ዘእምነ አርማቴም ዘእም ደብረ ኤፍሬም ዘመሴፋ ዘስሙ ሕልቃና ፣

ወሀሎ ፩ ብእሲ በሀገረ ባቢሎን ዘስሙ ኢዮአቄም እንዲል አውስጢድ ከተማው ነው፤ መላው ኤዶምያስ ይባላል፤ በሀገረ ዖጽ፣ አስ ይላል ፤

ወውእቱ ብእሲ ራትዕ ፣

ይኸውም ጥመት የሌለበት ቅን፤

ወንጹሕ ፣

ኃጢአት የሌለበት ንጹሕ ፤

ወጻድቅ ፣

ሐሰት የሌለበት ዕውነተኛ ፤

ወፈራሄ እግዚአብሔር ፣

እግዚአብሔርን የሚፈራ፣ የሚያመልክ ፩ ሰው ነበር ፤

ወይትገሐሥ ምስለ ልቡ እምኵሉ ምግባር እኩይ ፣

ከክፉ ሥራ ሁሉ ከልቡ ፈጽሞ የሚርቅ፣ ሰው በልቡ በጎ ቢሆን በአፉ፣ በአፉ በጎ ቢሆን በልቡ በጎ አይሆንምና ምግባሩን ጨምሮ ጻፈ፤ ይህ የመጣበት መከራ ለፈተና ነው እንጂ በኃጢአቱ አይደለምና ፤



፪፡ ወቦቱ ፯ቱ ደቂቅ ወሠላስ አዋልድ ፣

፫ት ሴቶች ልጆች፣ ፯ት ወንዶች ልጆች ነበሩት ፤

እንስሳሁኒ ፸፻ ፣

፯ት ሺህ ላም ነበረው፣ አንድ፣ ሁለት ፣ ሦስት ብሎ ቈጥሮ ፤ አንድም በረቱን ቈጥሮ ፤

፫፡ ወአባግዒሁኒ ፴ ምዕት ፣

፫ት ሺህ የበግ መንጋ ነበረው አንድ ፣ ሁለት ፣ ሦስት ብሎ ቈጥሮ አንድም በረቱን ቈጥሮ፤

ወአግማሊሁኒ ፭፻ ፣

፭ት፻ቶ ግመል ነበረው፤ አንድ፣ ሁለት ፣ ሦስት ብሎ ቈጥሮ ፤

ጽምደ አልሕምቲሁኒ ፭፻ ፣

አምስት መቶ ጥማድ በሬ ነበረው፤

አእዱጊሁኒ አዕኑስ ፭፻ ፣

አምስት መቶ ባዝራ ነበረው፤ አንድ ፣ ሁለት ፣ ሦስት ብሎ ቈጥሮ ፤ አንድም መንጋውን ቈጥሮ ፤

፬፡ ወብዙኅ አግብርቲሁ ጥቀ ፣

ባሮቹ እጅግ ብዙ ነበሩ፤ አንድም ወብዙኅ ግበሪሁ ይላል፣ አራሹ ብዙ ነበር ፤

ወዓቢይ ተግባሩ በዲበ ምድር ፣

ደርቡ ግምቡ ብዙ ነበር፤ አንድም አሣርሶ አስነግዶ የሚያገኘው ገንዘቡ ብዙ ነበር፤ ባለጸግነቱን ሁሉ ቈጠረ፤ ይህን ሁሉ ቢያጠፋበት አልካደም ለማለት ፤

ወውእቱ ብእሲ ኄር በብሔረ ጽባሕ በምሥራቀ ፀሐይ ፣

ጽባሕና ምሥራቅ አንድ ወገን ነው፤ ይኸውም በፀሐይ መውጫ የሚኖር ደግ ሰው ነበር፤ አንድም እምኵሉ ደቂቀ ጽባሕ ፣ ከምሥራቅ ሰዎች ይልቅ ደግ ሰው ነበር፤ አንድም በደወለ ኤዶምያስ ዘአረብም ይላል ፤

፭፡ ወየሐውሩ ደቂቁ ፣ .

የተባለፈ ነው፤ ልጆቹ ይሔዱ ነበር ፤

ወይትጋብኡ ኅቡረ ወይገብሩ ምሳሐ ኵሎ አሚረ ፣

አንድ ሁነው ተሰብስበው ሁል ጊዜ ምሳ ጋሬዳ ያደርጉ ነበር፣ የኢዮብስ ልጆች ምሳ ጋሬዳ አያደርጉም፤ አንድ ጊዜ በልተው፣ አንድ ጊዜ ጠጥተው ነው የሚኖሩ ብሎ በዓል ያደርጉ ነበር ፤

ወይነሥኡ ሠላሰ አኃቲሆሙ ይበልዓ ወይሰትያ ምስሌሆሙ ፣

፫ቱን እኅቶቻቸውን ይዘው ከነዚያ ጋር ይበሉ ይጠጡ ነበር፤ አንድም ይብልዓ ወይስተያ ይላል ከነዚያ ጋር ይበሉ ይጠጡ ዘንድ፤

፮፡ ወተፈጺሞ መዋዕለ ግዝኦሙ ፣

በዓል የሚያደርጉበት ቀን ከተፈጸመ በኋላ ፤

ይፌንዎሙ ኢዮብ ቅድመ እግዚአ
ብሔር ፤

ኢዮብ ወደ ቤተ እግዚአብሔር ይሰዳቸው ነበር ፤

ወያስተሥሪ ሎሙ ፤

ኃጢአታቸውን ያስተሠርይላቸው ነበር ፤

ወይገይሥ በጽባሕ ፤

የተላለፈ ነው ገሥግሦ ይሔድ ነበር ፤

ወያበውእ መሥዋዕተ በእንቲአሆሙ በኍልቆሙ ፤

ስለሳቸው በቊጥራቸው ፲፩ በነግህ ፲፩ በሠርክ ይሠዋ ነበር፤ አንድም ፭፻ በነግህ፣ ፭፻ በሠርክ ይሠዋ ነበር፣ ወይገይስ በጽባሕ ወያበውእ መሥዋዕተ በኍልቆሙ ወያስተሥሪ ሎሙ ወይፌንዎሙ ቅድመ እግዚአ ብሔር ብሎ መግጠም ነው፤ ከዚያ በኋላ ኃጢአታቸውን ያስ ተሠርይላቸው ነበር ፤

፯፡ ወ፩ደ ላሕመ በእንተ ነፍሱ ፤

ስለሚስቱና ስለሱ አንድ ላም ይሠዋ ነበር ፤

፰፡ ወይብል ኢዮብ ለእመቦ ዘይሄ ልዩ ደቂቅየ እኩየ ላዕለ እግዚአብ ሔር ፤

የእኔ የኢዮብ ልጆች ቀጥቼ ሠርቼ አሳድጌያቸው ይበድላሉን ምንም በገቢር ባይበድሉ በሐልዮ ሳይበድሉ አይቀሩም ብሎ ፲፩ በነግህ፣ ፲፩ በሠርክ ይሠዋ ነበር ፤

ወከመዝ ይገብር ኢዮብ በኵሉ መዋ ዕለ ሕይወቱ ፤

ኢዮብ በሕይወት በኖረው ዘመን ሁሉ ፲፩ በነግህ ፲፩ በሠርክ ይሠዋ ነበር ፤

፱፡ ወእምድኅረ ይእቲ ዕለት መጽኡ መላእክተ እግዚአብሔር ፤

በዓል ከአደረገባት ቀን በኋላ መሥዋዕቱን ጸሎቱን ለማሳረግ መላእክት መጡ ፤

ወቆሙ ቅድመ እግዚአብሔር ፤

በእግዚአብሔር ፊት ቆሙ ፤

ወመጽአ ሰይጣን ወቆመ ምስሌሆሙ ፤ ፨

በመካኑ ሰይጣንም መጥቶ ከነ ዚያ ጋር በቦታው ቆመ፤ ለሰይ ጣን ምን ቦታ አለው ቢሉ ዛሬ በነገሥታት ቤት ለቋሚ፣ ለለ ጓሚ የሚቆምበት ኀሡር ቦታ እንዳለው ለሱም ኀሡር ቦታ አለ ውና፤ አንድም በሐልዮ መጣ፤ አንድም በአስሕቶ ፀና ፤

፲፡ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሰይጣን እምአይቴ መጻእከ ፤

እግዚአብሔር ሰይጣንን ከወ ዴት መጣህ አለው፣ ጠፍቶት አይደለም፣ ሊያናግረው ነው እንጂ፤ አንድም ለምንት መጻ



እከ ምንት አምጽአከ ለምን መጣህ? ምን አመጣህ አለው፡

ወተሰጥዎ ሰይጣን ለእግዚአብሔር ወይቤሎ ፤

ሰይጣን ለእግዚአብሔር መለሰ ለት፣ እንዲህ አለው ፡

ዖድክዋ ለኵላ ምድር ወአንሶሰውኩ ታሕተ ሰማይ ፤

ከሰማይ በታች ያለች ይችን ዓለም ዞሬ፣ ኃጢአት አሠርቼ፣ ጣዖት አስመልኬ ፣ ወደጅ አሳ ጥቼህ መጣሁ አለው ፡

፲፩፡ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሰይ ጣን ሁቅኬ አልቦ ዘትሔሊ ላዕለ ቍልዔየ ኢዮብ ፤

ነገሩ በኢዮብ እንደሆነ ያውቃ ልና እግዚአብሔር ሰይጣንን በወዳጁ በኢዮብ ላይ ክፉ ነገር እንዳታስብ እወቅ አለው ፡

እስመ አልቦ ዘከማሁ በዲበ ምድር ፤

በዚህ ዓለም እንደሱ ያለ ሌላ የለምና ፡

ብእሲ ንጹሕ ወጻድቅ ፤

ኃጢአት የሌለበት ንጹሕ ፤ ሐሰት የሌለበት እውነተኛ ፡

ወፈራሄ እግዚአብሔር ፤

እግዚአብሔርን የሚፈራ የሚያ መልክ ፡

ወይትገሐሥ እምኵሉ ምግባር እኩይ፤

ከክፉ ሥራ የሚርቅ እንደሱ ያለ ሌላ የለምና ፡

፲፪፡ ወተሰጥወ ሰይጣን ቅድመ እግዚአብሔር ፤

ሰይጣንም በእግዚአብሔር ፊት መለሰ ፡

ወይቤ ቦኑ በከንቱ ያመልኮ ኢዮብ ለእግዚአብሔር ፤

በውኑ ኢዮብ በከንቱ እግዚአ ብሔርን የሚያመልከው ይመ ስልሃል ማለት በከንቱ የሚያ መልከኝ ይመስልሃል ፡

አኮኑ እስመ አንተ መላእከ ሎቱ ፤

አንተ ገንዘቡን መልተህለታልና ስለዚህ ነው እንጂ ፡

እምውስጡ ፤

እንደ ጎንደር ያለውን ፡

ወእምአፍአሁ ቤቶ ፤

እንደ ጠዳ ያለውን ቤቱን፡ አን ድም እንደ ጎንደር እንደ ጠዳ ያለ ቤቱን መልተህለታልና ፡

ወኵሎ ዘዓውዶ ፤

እንደ አረንጎ፣ እንደ ይባባ ያለ ውን መልተህለታልና ፡

ወባረክ ተግባረ እደዊሁ ፤

አሳርሶ፣ አስነግዶ የሚያገኘውን አብዝተህለታልና ፡

ወአብዝኀከ እንስሳሁ በዲበ ምድር፣

በዚህ ዓለም ከብቱን አብዝተ ህለታልና ስለዚህ ነው እንጂ በከንቱ ያመልከኝ ይመስልሃልን፡

www.ethiopianorthodox.org

፲፩፥ ወባሕቱ ፈኑ እዴከ ፤

ነገር ግን እጅ መዓትህን አም ጣበትና ፡

ወግሥሥ ኵሎ ዘቦ ፤

ያለውን ገንዘቡን ሁሉ አጥፋብ ትና ፤

ዳዕሙ እመ ውስተ ገጽከ ኢባረከከ፤

ፊት ለፊት ባይሰድብህ ታያለህ ይሰድብሃል እንጂ፤ አንድም ፊት ለፊት ባይሰድብህ ታይ ዘንድ ግሥሥ ኵሎ ዘቦ፤ አንድም በአፉ እንጂ ባይሰድብህ በልቡ ያማሃል፤

፲፪፥ ወእምዝ ይቤሎ እግዚአብሔር ለሰይጣን ናሁኬ ኵሎ ዘቦ መጠ ውኩከ ውስተ እዴከ ፤

ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር ሰይ ጣንን እነሆ ገንዘቡን ሁሉ ሰጥ ቼሃለሁ ፤

ዳዕሙ ኪያሁ ኢትግሥሥ ፤

እሱን ብቻ አትንካ አለው፤ አን ድም እሱን ብቻ አትንካ እንጂ ገንዘቡን ሰጥቼሃለሁ ፤

ወወጽአ ሰይጣን እምነበ እግዚአብ ሔር ፤

እንዘ ይትፌሣሕ ያለበት ነው፤ ሰይጣን እንደ ተሾመ፤ እንደ ተሸለመ ደስ እያለው፤ ከእግዚአ ብሔር ዘንድ ወጣ፤ ከዚህ በኋላ በአሕዛብ እያደረ ገንዘቡን ሁሉ ያጠፋበት ጀመረ ፤

፲፫፥ ወሀለዉ በይእቲ ዕለት ደቂቁ ለኢዮብ ወአዋልዲሁኒ ይበልዑ ወይ ሰትዩ በቤተ እኁሆሙ ዘይልሕቅ ፤

በዚች ቀን የኢዮብ ልጆች ሴቶ ችም ወንዶችም በታላቅ ወንድ ማቸው ቤት ይበሉ ይጠጡ ነበር ፤

፲፬፥ ወመጽአ ዘይዜንዎ ለኢዮብ ፤

ለኢዮብ ወሬ የሚነግረው መጣ፤

ወይቤሎ ዕምደ አልሕምቲከ እንዘ የሐርሱ ፤

በሮችህ ተጠምደው ሲያርሱ፤

ወአእዱጊክኒ አዕኑስ እንዘ ይትርዓዩ ጥቃሆሙ ፤

አህዮችህ በአጠገባቸው ተሰማር ተው ሳለ ፤

፲፭፥ ወመጽኡ እለ ይፄውዉ ወማህ ረክዎሙ ፤

የሚማርኩ ሰዎች መጥተው ማረ ኳቸው ፤

ወቀተሉ ደቂቀከ በመጥባሕት ፤

ብላቴኖችህን በሰይፍ ገደሉ፤

ወአነ ባሕቲትየ ተረፍኩ ወመጻእኩ እዜኑከ ፤

እኔ ብቻዬን ዳንኩ፤ ይኸን ልነግ ርህ መጣሁ፤ ጃን ገበሩን መስሎ ነግሮታል፤ አንድም እሱ ብቻ ቀርቶ ነበርና መጥቶ ነግሮ ታል ፤



፲፮፥ ወእንዘ ዘንተ ይዜንዎ መጽአ ካልዕመ ዘይዜንዎ ፤

ይህን ሲነግረው ሁለተኛ ወሬ የሚነግረው መጣ ፤

ወይቤሎ ለኢዮብ እሳት ወድቀት እምሰማይ ወዓውአየት ዓባግዒከ ፤

ኢዮብን እሳት ከሰማይ ወርዳ በጎችህን አጠፋቻቸው ፤

ወበልዓቶሙ ለኖሎትክኒ ኅቡረ ፤

እረኞችህንም በአንድነት አጠ ፋቻቸው አለው ፤

ወአነ ባሕቲትየ ተረፍኩ ወመጻእኩ እዜኑከ ፤

እኔ ብቻዬን ቀረሁ፤ ይህን ልነግ ርህ መጣሁ አለው፤ በግ መልከ ኛውን መስሎ ነግሮታል፤ አንድም እሱ ብቻ ቀርቶ ነበርና መጥቶ ነግሮታል፤ ለሰይጣን እሳት ማው ረድ ይቻለዋል? ቢሉ እሱ ካለ አዎን ይቻለዋል ፤

፲፯፥ ወእንዘ ዘንተ ይዜንዎ መጽአ ሣልስመ ዘይዜንዎ ፤

ይህን ሲነግረው ሦስተኛ ወሬ የሚነግረው መጣ ፤

ወይቤሎ ለኢዮብ መስተፅዕናነ አፍ ራስ ፫ቱ ወሠራዊት ብዙኃን አገቱ አልሕምቲከ ወአግማሊከ ፤

በፈረስ የተቀመጡ ፫ ቤት ጭፍራ ብዙ ሠራዊት ግመሎ ችህን ላሞችህን ከበቡ አለው ፤

እግዚአብሔር ቢጣላኝ ነው እንጂ በፈረስ የተቀመጡ ፫ ቤት ጭፍራ ድል ይነሱኝ ነበር? አንድም በፈረስ የተቀመጡ ፫ አበጋዞች ብዙ ሠራዊት ላሞች ህን ከበቡ አለው፤ እግዚአብሔር ቢጣላኝ ነው እንጂ በፈረስ የተቀመጡ ፫ አበጋዞች ላንድ ለኔ ያመጣብኝ ነበር ? አለ ፤

ወማህረኩ ወቀተሉ ደቀከ በመጥባ ሕት ፤

ከብትህን ማረኩ፤ ብላቴኖችህን በሰይፍ ገደሉ ፤

ወአነ ባሕቲትየ ተረፍኩ ወመጻእኩ እዜኑከ ፤

እኔ ብቻዬን ዳንሁ፤ ይህን ልነግ ርህ መጣሁ አለው፤ ላም ራሱን መስሎ መጥቶ ነግሮታል፤ አን ድም እሱ ብቻ ቀርቶ ነበርና መጥቶ ነግሮታል ፤

፲፰፥ ወእንዘ ዘንተ ይዜንዎ መጽአ ራብዕመ ዘይዜንዎ ፤

ይህን ሲነግረው አራተኛ ወሬ የሚነግረው መጣ ፤

ወይቤሎ ለኢዮብ ደቂቅከ ወአዋል ዲከ እንዘ ይበልዑ ወይሰትዩ በቤተ እኁሆሙ ዘይልሕቅ ፤

ኢዮብን እንዲህ አለው፤ ወንዶች ልጆችህ ሴቶች ልጆችህ በታ ላቅ ወንድማቸው ቤት ሲበሉ ሲጠጡ ፤

www.ethiopianorthodox.org

ግብተ መጽአ ዓቢይ ነፋስ እምገዳም ወጐድአ ለቤት እንተ ፬ቱ መዓዝ ኒሁ ፤

ከምድረ በዳ ዕኑዕ ነፋስ ድንገት ተነሥቶ አራት መዓዝን ያለውን ቤት ነቀነቀው፡ አንድም በአራት መዓዝኑ ነቀነቀው፡ በአንድ ወገን ያሉት ያመልጡኛል ብሎ ፡

፳፩፡ ወወድቀ ቤት ዲበ ደቅከ ወሞቱ ፤

ቤቱ በልጆችህ ላይ ወደቀ ፤ ሞቱ ፡

ወአነ ባሕቲትየ ድኅንኩ ፤

እኔም ብቻዬን ዳንሁ፤ ይህን ልነግርህ መጣሁ፤ የታላቅ ልጁን ሰይፍ ጃግሬ መስሎ መጥቶ ነግሮታል፡ አንድም እሱ ብቻ ቀርቶ ነበርና መጥቶ ነግሮታል፡ ሰይጣን በዚህ ሁሉ መመሰል ይቻለዋል? ቢሉ አዎን እሱ ካለ ይቻለዋል ፡ አንድም ሠራዊተ ዲያብሎስ ብዙ አይደሉምን አንዱ በአንዱ ፤ አንዱ በአንዱ ይመሰላል፤ ስለምን አንድ ጊዜ ያልነገረው ቢሉ ኃዘን ይፅናበት ብሎ አንድ ጊዜ ቢነግረው ኃዘን አይፀናበትም ነበርና፤ ስለምን የገንዘቡን ጥፋት በፊት፤ የልጆቹን ሞት በኋላ ነገረው ቢሉ ኃዘን ይፅናበት ብሎ በፊት የልጆቹን ሞት ነግሮ ኋላ የገንዘቡን ጥፋት ቢነግረው ገንዘብ መሰብሰቡ ለልጅ አልነበረም ብሎ ኃዘን አይፀናበትም ነበርና፡

፳፪፡ ወእምዝ ሰበ ሰምአ ኢዮብ ዘንተ ነገረ ተንሥአ ኢዮብ ፤

ከዚህ በኋላ ኢዮብ ይህን ነገር በሰማ ጊዜ ተነሣ ፡

ወገደፈ ሐሜለቶ ፤

ሻሹን መሐረሙን ጣለ ፡ አንድም አክሊሉ ይላል፡ ዘውዱን አወረደ ፡

ወሠጠጠ አልባሲሁ ወላፀየ ስእርተ ርእሱ ፤

ልብሱን ቀደደ አሰለበ፤ ራሱን ላጨ ፡

ወወድቀ ዲበ ምድር ወሰገደ በገጹ፤

እግዚአብሔር ቢሽረኝ አልሻርም እላለሁ ብሎ በምድር ተንከባለለ፤ ሰገደ፤ ዛሬ የተሻረ ሰው ሰግዶ እንዲሔድ፡

፳፫፡ ወይቤ ዕራቅየ ወፃእኩ እምከርሠ እምየ ወዕራቅየ እገብእ ውስተ ምድር ፤

ጥንቱን ለእንገቴ ፈትል፤ ለወገቤ ጨርቅ ሳልይዝ ከናቴ ማሕፀን ወጣሁ፤ ዛሬም ለእንገቴ ፈትል ለወገቤ ጨርቅ ሳልይዝ ወደ መቃብር እወርዳለሁ፡ አንድም ለእንገቴ ፈትል ለወገቤ ጨርቅ ሳልይዝ ከናቴ ከምድር ተገኘሁ፡ ዛሬም ለእንገቴ ፈትል ለወገቤ ጨርቅ ሳልይዝ ወደ መቃብር እወርዳለሁ አለ ፡

እግዚአብሔር ወሀበ ወእግዚአብሔር ነሥአ ፤

እግዚአብሔር ሰጠ እግዚአብሔር ነሣ ፤ እኔ ምን ዕዳዬ ፡

ወኮነ ከመ እግዚአብሔር ፈቀደ ፤

እግዚአብሔር በኔ እንደ ወደደ ሆነ፤ ጌታ ሁን እንዳሻህ ትሆን እንዲሉ፤ አንድም እግዚአብሔር እንደ ወደደ መከራው ተደረገብኝ፤ አንድም እግዚአብሔር የወደደው መከራ ተደረገብኝ ፤

ወባሕቱ ይኩን ቡሩክ ስሙ ለእግዚአብሔር ፤

የእግዚአብሔር ስሙ ክቡር ምስጉን ይሁን ፡

፳፬፡ ወበዝ ኲሉ ዘረከቦ አልቦ ዘአበሰ ኢዮብ ቅድመ እግዚአብሔር፤

በዚህ ባገኘው መከራ ሁሉ ኢዮብ በእግዚአብሔር ፊት የበደለው የለም፤ አንድም ወኵሉ ዘረከቦ ይላል፤ ይህ ያገኘው መከራ በኃጢአቱ አይደለም ለፈተና ነው እንጂ፤

ወኢወሀበ ዕበደ ለእግዚአብሔር ፤

እግዚአብሔርን ጠላቱን አይጎዳ ወዳጁን አይጠቅም አላለም ።

## ምዕራፍ ፪

ሁለተኛው ምዕራፍ ይህ ነው፡

፩፡ ወእምዝ እምድኅረ ይእቲ ዕለት መጽኡ መላእክተ እግዚአብሔር ወቆሙ ቅድመ እግዚአብሔር ፤

እምዝና እምድኅረ አንድ ወገን ነው፤ እግዚአብሔር ወሀበ ወእግዚአብሔር ነሥአ ካለባት ቀን በኋላ ትዕግሥቱን ለማግረግ መላእክት መጥተው በእግዚአብሔር ፊት ቆሙ ፡

ወመጽአ ሰይጣን ወቆመ ምስሌሆሙ ቅድመ እግዚአብሔር ፤

ሰይጣንም ከነዚያ ጋራ መጥቶ በእግዚአብሔር ፊት ቆመ ፡

፪፡ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሰይጣን እምአይቴ መጻእከ አንተ፤

እግዚአብሔር ሰይጣንን አንተ ከወዴት መጣህ አለው ፡

ወይቤ ሰይጣን ሶቤሃ ቅድመ እግዚ አብሔር ሖርኩ መትሕተ ሰማይ ወአንሶሰውኩ ኵለሄ ወመጻእኩ ፤

ሰይጣን በእግዚአብሔር ፊት ያን ጊዜ እንዲህ አለ፤ ከሰማይ በታች አራቱን መዓዝን ዞሬ ኃጢአት አሠርቼ ጣዖት አስመልኬ ወዳጅ አሳጥቼህ መጣሁ አለ ፡



www.ethiopianorthodox.org

፫፡ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሰይጣን ሁቅኬ ላዕለ ኢዮብ ቍልዔየ ፡

እግዚአብሔር ሰይጣንን በወዳጁ በኢዮብ ላይ ክፉ ነገር እንዳ ታደርግ እወቅ አለው ፡

እስመ አልቦ ዘከማሁ በዲበ ምድር ብእሲ የዋህ ፤

በዚህ ዓለም እንደሱ ያለ ደግ ሰው የለምና ፡

ጻድቅ ወንጹሕ ፤

ኃጢአት የሌለበት ንጹሕ ፡ ሐሰት የሌለበት እውነተኛ ፡

ወፈራኄ እግዚአብሔር ፡

እግዚአብሔርን የሚፈራ የሚ ያመልክ ፡

ወይትገሐሥ እምኵሉ እኩይ ፡

ከክፉ ነገር የሚርቅ እንደሱ ያለ ሌላ የለምና ፡

ወዓዲ የዋህ ፤

ዳግመኛም ዕጉሥ ፡

ወአንተሰ ትቤ ታኅጒሎ ንዋዮ በከ ንቱ እመ ኢያእኰተከ ፤

አንተ ግን በከንቱ ገንዘቡን ታጠ ፋበት ዘንድ ባያመሰግንህ እስተ ታያለህ አልህ፡ አንድም እንደ አሕዛብ ኃጢአት ሠርቶ ጣዖት አምልኮ ባያመሰግንህ በከንቱ ገንዘቡን ታጠፋበት ዘንድ ግሥሥ ኰሉ ዘዐ አልህ፡ አንድም ፊት

ለፊት ባያመሰግንህ ታዩ ዘንድ ሳጥፋበት አልህ ፡

፬፡ ወተሰጥዎ ሰይጣን ለእግዚአብሔር ወይቤ ማዕስ ቤዛ ማዕስ ፡

ሰይጣን ለእግዚአብሔር መለሰ እንዲህ አለ ቁርበት ለቁርበት ቤዛው ነው ፡ ሙሚሚ ለጠጠር ፤ ጋሻ ለጦር እንዲሉ፡

ኵሎ ዘአጥረየ ሰብእ ይሁብ ቤዛ ነፍሱ ፤

ሰው በገንዘቡ ሰውነቱን ይቤዠ ዋል፡ እንደዚህም ሁሉ ገንዘቢ ለሰውነቱ ቤዛ ሆነኝ አለህ ፡

፭፡ ወባሕቱ ፈኑ እዴከ ፡

ነገር ግን እደ መዓትህን አምጣ በትና ፡

ወግሥሥ አእዕምቲሁ ወሥጋሁ ፡

አጥንቱን የሚቀጠቅጥ ሥጋውን የሚያሳብጥ ደዌ አምጣበትና ፡

ዳዕሙ እመ ውስተ ገጽከ ኢባረከከ፡

ፊት ለፊት ባይሰድብህ ታያለህ ይሰድብሃል እንጂ ትርጓሜው እንዳለፈው ነው፡

፮፡ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሰይጣን ናሁ መጠውኩከ ሥጋሁ ወዳዕሙ ነፍሶ ዑቅ ፤

እግዚአብሔር ሰይጣንን እነሆ ሥጋውን ሰጥቼሃለሁ ነፍሱን ከሥጋው እንዳትለይ እወቅ አለው ፡



፯፡ ወወጽአ ሰይጣን እም ኀበ እግዚ አብሔር ፤

ሰይጣን ከእግዚአብሔር ዘንድ ደስ ብሎት ወጣ ፡

ወአኀዞ ለኢዮብ ዝልጋሴ እኩይ እምእግሩ እስከ ርእሱ ፤

በአደባባይ ተቀምጦ ነገር ሲሰማ፡ አንድም በአዳራሽ ተቀምጦ ሲያበላ፤ ሲያጠጣ ይህስ ጊዜው አይደለም ብሎ በከብቱ ጥፋት እግዚአብሔር ይርጠብህ፤ በል ጆቹ ሞት እግዚአብሔር ያጥናህ የሚለው ሰው ሲወጣ ሲገባ አይቶ ይህስ ተድላ ደስታ ሆነው ብሎ ብሔሞትን መስሎ ከዓይኑ፤ ከአ ፍንጫው እንደ ጢስ ያለ ትግ ልግል እያለ ሔዶ እፍ አለ በት፤ ኢዮብንም ከእግሩ እስከ ራሱ ድረስ ጽኑዕ ደዌ ያዘው ፡

፰፡ ወነሥአ ገልዐ ወአኀዘ ይሔክክ ቍስሎ ፤

ጥፍሩ ውልቅ ውልቅ እያለ ቢወ ድቅበት ገሉን አንስቶ ቍስሉን ያክ ጀመረ ፤

ወነበረ አፍአ እም ሀገር ፤

ከከተማ ወጥቶ በአፍአ ጎጆ ሰርቶ ተቀመጠ፤ በከብቱ ጥፋት እግዚ አብሔር ይርጠብህ ፤ በልጆቹ ሞት እግዚአብሔር ያጥናህ ፤ ከደዌህ ይፈውስህ የሚለው ሰው ሲወጣ ሲገባ አይቶ ይህም ተድላ

ደስታ ሆነው ብሎ ቍስሉን እንዲሸት አደረገበት፡ ከከተማ ወጥቶ በአፍአ፡ ጎጆ ሠርቶ ተቀ ምጧል፡ አንድም ከወጣ ከወረ ደው ሰው መድኃኒት ለመጠ የቅ ፡

ወሰከበ ውስተ መሬት ወሐመድ ፤

አመድ ነስንሰው ገል ደቁሰው በማጥን አድርገው አስተኝተው ታል፡ አንድም ደዌው አመድ ያስመስለዋልና፡

፱፡ ውነሊፎ ብዙኅ መዋዕል ትቤሎ ብእሲቱ ዓዲኑ ትፀንሐ በየውሃት ፤

ከብዙ ዘመን በኋላ ሚስቱ እን ዲህ አለችው፡ በሞኝነት ፀንተህ ዳግመኛ ደጅ እጠናዋለሁ ትላ ለህ ፡

ባርኮ ለእግዚአብሔር ወሙት ፤

ስትዞር ውላ የሰውን ልቡና ሰይ ጣን አጽንቶባት ስትመለስ የቀ ደመ ብላቴን ጌታዋን መስሎ ሰይጣን ሲንከባለል አገኘችው፡ ምን ሁነሃል አለችው፡ የእኔ ያስ ደንቅሻልን ዐሐይ አያይሽ የነ በር የኢዮብስ ሚስት ስንኳ እን ዲህ ሁነሻል፤ ቢሆን ያድንሃል ያለዚያ ይገድልሃል እግዚአብ ሔርን ስደበውና ሙት በዪው አላት፡ ቢሆን ያድንሃል ያለዚያ ይገድልሃል እግዚአብሔርን ስደ በውና ሙት አለችው ፡ በዚህ ምክንያት ተቀሥፋለች ፡

www.ethiopianorthodox.org

እስከ ማዕዜኑ ትትዔገሥ ፤

እስከ መቼ ድረስ ትታገሣለህ፡

ወትብልኑ እጸንሕ መዋዕለ ኅዳጠ፤

ጥቂት ቀን ደጅ እጠናዋለሁ ትላለህን ፤

ወዓዲ እትዔገሥ ፤

ዳግመኛም መከራውን እታገሠ ዋለሁ ትላለህን ፤

ወእሴፎ ሕይወትየ ፤

ሕይወትን አገኝ ዘንድ ተስፋ አደርጋለሁ ትላለህን ፤

፲፡ ናሁ ማሰነ እምድር ዝክርከ ፤

አንተ አለህልኝ እንዳልል እነሆ አጠራርህ ከዚህ ዓለም ጠፋ ፤

ደቂቅየኒ ወአዋልድየኒ ሞቱ ፤

ልጆች አሉኝ እንዳልል ወንዶች ልጆቼ ፤ ሴቶች ልጆቼ ሞቱ ፤

ከርሠ ዚአየ ሐመ በሕማመ ማኅ ምም ፤

በከንቱ አማጥሁ ፤

ወሠራሕኩ ወፃመውኩ በከንቱ ፤

ሳልረባ፤ ሳልጠቅም በከንቱ ደከ ምሁ ፤

፲፩፡ ወአንተሂ ትነብር ውስተ መግል ወዕፄያት ፤

አንተም በመግል ተውጠህ በዕ ፄያት (በትሎች) ተከበህ ትኖ ራለህ ፤

ወእነሂ አዓውድ ወእትሃል ፤

እኔም እየዞርሁ እቀላውጣለሁ፡ አንድም ተለል ተለል እላለሁ፡

ወእሐውር እምብሔር ብሔረ ወእም ቤት ቤተ ፤

ከአንዱ ሀገር ወደ አንዱ ሀገር፤ ከአንዱ ቤት ወደ አንዱ ቤት እሔዳለሁ ፤

ወእጸንሕ እምነግህ እስከ የዓርብ ፀሐይ ፤

ከነግህ ጀምሮ ፀሐይ እስኪገባ ድረስ እቆያለሁ አገኛለሁ የሚል ሰው ይዘገያልና ፤

ከመ አእርፍ እምፃማየ ወእምሕማምየ ዘላዕሌየ ይእዜ ፤

በኔ ላይ ካለ ከድካሜ ከደዌየ አርፍ ዘንድ ከታማሚው አስታ ማሚው እንዲሉ፡ አንድም ከረ ኃብ አርፍ ዘንድ፡ አንድም ከድ ካም፤ ከመከራ አርፍ ዘንድ ፤

ወባሕቱ ንብብ ቃለ ላዕለ እግዚአብ ሔር ወሙት ፤

ነገር ግን እግዚአብሔርን ስደበ ውና ሙት ፤

፲፪፡ ወነጸራ ፤

በዓይነ መዓት አያት፡ አንድም አስተውሎ አያት፡ ከአፍ ጠለፍ አድርጎ መናገር አይገባምና ፤



ወይቤላ ከመ አሐቲ እም አብዳት አንስት ተናገርኪ ፤

የኔ የኢዮብ ሚስት ቀጥቼ ሠርቼ አሳድጌሽ ነበር፡ ከሰነፎች ሴቶች እንደ አንዲቱ ሴት ተናገርሽ ፤ አንድም ሥርዓት ካልተሠራላ ቸው ከአሕዛብ ሴቶች እንደ አንዲቱ ተናገርሽ ፤

ሠናይቶሰ ነሣዕነ እምነበ እግዚአብ ሔር ወእኪቶሰ ሶበ በጽሐተነ ኢንት ዔገሥኑ ፤

ተድላውን ደስታውን ከእግዚአ ብሔር ዘንድ አገኘነ፤ መከራውስ በመጣ ጊዜ አንታገሥምን፡ አን ድም ድኅነቱን ፤ ጤናውን አገ ኘነ ፤ ደዌውን አንቀበልምን ፤

ወበኵሉ ዝ ዘረከቦ አልቦ ዘአበሰ ኢዮብ ቅድመ እግዚአብሔር ፤

በዚህ ባገኘው መከራ ሁሉ ኢዮብ በእግዚአብሔር ፊት የበደለው በደል የለም፡ አንድም ወኵሉ ዘረከቦ ይህ ያገኘው መከራ በኃ ጢአቱ አይደለም፤ ለፈተና ነው እንጂ፡

፲፫፡ ወሰሚዖሙ ፫ቱ አዕርክቲሁ ኵሎ እኩየ ዘረከቦ ለኢዮብ መጽኡ ኀቤሁ እምብሔሮሙ ፤

ሦስቱ ወዳጆቹ ኢዮብን ያገኘ ውን መከራ ሰምተው ከሀገራ ቸው ወደሱ ሊጠይቁት መጡ፡

እሉ እሙንቱ ኤልፋዝ ቴማናዊ ንጉሥ ፤

የቴማን ንጉሥ ኤልፋዝ ፤

ወበልዳዶስ አውኬናዊ መስፍን ፤

የአውኬን ሹም በልዳዶስ ፤

ወሳፍር አሚናዊ ፤

የአሜን ሰው ሳፍር እነዚህም ኤልፋዝ በልዳዶስ ሳፍር ናቸው፡

ወመጽኡ ኀቤሁ ኅቡረ ከመ የሐው ዕዎ ወይናዝዝዎ ፤

በክብቱ ጥፋት እግዚአብሔር ይርጠብህ፤ በልጆቹ ሞት እግዚ አብሔር ያጥናህ፤ ከደዌህ ይፈ ውስህ ብለው ያረጋጉት፤ ያፅና ኑት ዘንድ አንድ ሁነው ወደሱ መጡ ፤

፲፬፡ ወርእይዎ እምርኁቅ ወኢያ እመርዎ ፤

ከሩቅ አይተው አላወቁትም፤ መልኩ በደዌ ተለውጧልና ፤

ወአውየዉ በዓቢይ ቃል ወጸርሑ ወበከዩ ፤

ቃላቸውን አሰምተው ጮኹ አለቀሱ ፤

ወሠጠጡ አልባሲሆሙ ወወደዩ ሐመደ ዲበ ርእሶሙ ፤

ልብሳቸውን ቀደዱ፤ አሰለቡ፤ ትቢያ በራሳቸው ላይ ነሰነሱ፡

www.ethiopianorthodox.org

፲፫፡ ወነበሩ ሰቡዓ መዋዕለ ወሰቡዐ ለያልየ ፤

፯ት መዓልት ፯ት ሌሊት ተቀመጡ ፡

ወአልቦ ዘነበበ እምኔሆሙ ፤

ከነዚያ የተናገረ የለም ፡

እስመ ርእዩ መቅሠፍቶ ዓቢየ ጥቀ፤

እጅግ ጽኑዕ ጭንቅ የሆነ ደዌ ውን አይተዋልና ።

## ምዕራፍ ፫

ሦስተኛው ምዕራፍ ይህ ነው፤

### ገባዔ

፩፡ ወእምድኅረዝ ከሠተ ኢዮብ አፉሁ ፤

፯ት ቀን ሳይናገሩ ሰንብተዋል፤ ከ፯ት ቀን በኋላ ሰይጣን ልቡናቸውን ከበጎነት ወደ ክፋት መልሶት ያለ ኃጢአቴ ለምን አመጣብኝ ትላለህ፤ በገቢር ባትሠራ በሐልዮ ሳትሠራ ቀረህ፤ ያመጣብህ በኃጢአትህ ነው አሉት ፡ ከዚህ በኋላ ኢዮብ ነገር ጀመረ፤ ወከሠተ አፉሁ ጴጥሮስ እንዲል ፡

ወረገማ ለዕለት እንተ ባቲ ተወልደ፤

መላእክትን ባማ ኃጢአት፤ እግዚአብሔርን ባማ ክህደት ይሆንብኛል ብሎ የተወለደባትን ቀን ረገማት ፡

፫፡ ወይቤ ለትጥፋዕ ይእቲ ዕለት እንተ ባቲ ተወለድኩ ፤

የተወለድኩባት ቀን ትጥፋ አለ፡

ወሌሊታኒ እንተ ባቲ ይቤሉ ተባዕት ውእቱ ፤

ለናቴ ለባሰራስ ወንድ ልጅ ተወለደልሽ ብለው የተናገሩባት ሌሊቷም ትጥፋ አለ ፡

፬፡ ለትጽልም ይእቲ ዕለት ወኢይትነሥኣ እግዚአብሔር በላዕሉ ፤

ይች ዕለት ትጥፋ በሰማይ ያለ እግዚአብሔር ከዕለታት አይቍጠራት ፡

ወኢይምጻእ ብርሃን ውስቴታ ፤

ብርሃን አይምጣባት ፡

፭፡ ወይርከባ ጽልመት ወይድፍና ጽላሎተ ሞት ፤

ኃዘን ጽኑዕ መከራ ያግኛት ፡

ወይምጽኣ ቆባር ፤

ጭጋግ ይምጣባት ፡

ርግምተ ለትኩን ይእቲ ዕለት ፤

ይህች ዕለት የተረገመች ትሁን፤ ምነው እሷ ትጎዳለች? እንዲህ ያለ ቢሉ ፤ ያልሆነ ያልሆነ ነገር የሚያናግር ደዌ ይዞት ሳለ አልካደም ለማለት ፡



፮፡ ወይምጽኣ ጽልመት ለይእቲ ሌሊት ፤

በዚች ሌሊት መከራ ይምጣባት ፡

ኢተሀሉ ውስተ መዋዕለ ዓመት ፤

ዓመቱ ፫፻፷፭ ቀን ተብሎ ሲቈጠር አትቈጠር ፡

ወኢትትኈለቍ ምስለ መዋዕለ አውራኅ ፤

ከ፯ቱ ዕለታት፤ ከ፴ው ቀን ጋራ አንድ ሁና አትቈጠር ፡

፯፡ ለይእቲ ዕለት ፃዕር ለይርከባ ፤

ይችን ቀን ጭንቅ መከራ ያግኛት ፡

ወኢይምጻእ ውስቴታ ፍሥሓ ወሐሤት ፤

ተድላ ደስታ አይደረግባት ፡

፰፡ ጸዐሙ ይርግማ ዘረገማ ለይእቲ፤

ጥንቱን የረገማት እግዚአብሔር ጨርሶ ይርገማት እንጂ ባይረግማትማ እኔ እገኝባት ነበርን፡ አንድም አዳምና ሔዋን ዕፀ በለስን የበሉባትን ቀን የረገማት እግዚአብሔር ጨርሶ ይርገማት እንጂ፡ አንድም ዕለተ ዓርብን የረገማት እግዚአብሔር ጨርሶ ይርገማት እንጂ፤ አዳምና ሔዋን ዕፀ በለስን የበሉባት ቀንና ዕለተ ዓርብ አንድ ነው፡ አንድም ዕለተ ምጽአትን የረገማት እግዚአብሔር ጨርሶ ይርገማት እንጂ አጋንንት መናፍቃን ፍዳ ይቀበሉባታልና ፡

ዘሀሎ ይምትሮ ለዓቢይ አንበሪ ፤

ብሔሞትን ያሳለፈው ዘንድ ያለው፡ አንድም አናምርት ይላል፤ ብሔሞትን፤ ሌዋታንን ያሳለፋቸው ዘንድ ያለው፡ አንድም ክርስቶስ ዲያብሎስን በመስቀል ድል ይነሣው ዘንድ ያለው፡ አንድም ለዓበይት አናምርት ይላል፤ አጋንንትን ያጠፋቸው ዘንድ ያለው እግዚአብሔር ይርገማት እንጂ ፡

፱፡ ለይጽለሙ ከዋክብቲሃ ለይእቲ ሌሊት ፤

የዚች ሌሊት ከዋክብቶቿ ይጥፉ፡

ወይንበሩ ኀበ ኢይሬእዩ ብርሃነ ፤

ብርሃን ከማያዩበት ቦታ ይኑሩ፡ አንድም ኢይሬእዩ ብርሃነ ይላል፤ ብርሃንን ከማያዩበት ቦታ ይኑሩ፡

፲፡ እስመ ኢዐፀወ አንቀጸ ከርሣ ለእምየ ፤

የናቴን ማኅፀን አልዘጋምና እንደ ቦአስጥቂስ፤ ቦአስጥቂስ የሚባል ፈላስፋ ነበረ፤ ባሏ ከንግድም፤ ከዘመቻም እንደሆነ ሔዶ ሳለ ከጉልማሳ ሚስት ደረሰ፤ ፀነሰች፡ በሚወለድበት ወራት ሌሊት ወጥቶ ቢያይ ኮከቡ ከኀሠር ቦታ ሆኖ አየው፡ ይህን ጊዜ የሚወለ

www.ethiopianorthodox.org

ደው ኀሡር ይሆናል ብሎ ጭንና ጭናን ገጥሞ አሥሮ ተዋት፤ ፪ኛ ወጥቶ ቢያይ ከክቡር ቦታ ሆኖ አየው፤ ይህን ጊዜ የሚወለደው ክቡር ይሆናል ብሎ ፈታት ፤ ቢወለድ ሽቅብ ቍልቍል የሚያይ ሆኗል፣ ይኸውም እስክን ድር ነው ይላሉ ፤

ወኢይርአዩ ቤዘ እንዘ ይሠርቅ ፣

ኢይርአዩ ቤዘ ቤዝ እንዘ ይሠ ርቅ ብሎ መግጠም ነው፣ ኮከብን አይዩ ፤ አንድም ኮከብ ሲወጣ አይዩ ፤

ዘኢያእተቱ ሕማመ እምአዕይንትየ፣

መከራውን ከኔ ያላራቁ ፤

፲፤ ለምንት በውስተ ከርሥ ኢሞትኩ፣

በናታቸው ማኅፀን የሞቱ ሕፃ ናት ብዙ ናቸው፤ በናቴ ማኅፀን ለምን ያልሞትሁ፤ አንድም በናቴ ማኅፀን ብሞት ባማረ በተገባ ነበር፤ አንድም በናቴ ማኅፀን ብሞት ይህ ሁሉ መከራ ባላገኘ ኝም ነበር ፤

ወወፂእየ እምከርሥ ዘኢተህጐልኩ ሶቤሃ ፣

ይህማ እናትህን ትዳፋት የለም ትሉኝ እንደሆነ፣ ከናቴ ማኅፀን በወጣሁ ጊዜ ለምን ያልሞትሁ፣ ብሞት ባማረ በተገባ ነበር፤ አን ድም ብሞት ይህ ሁሉ መከራ ባላገኘኝም ነበር ፤

፲፩፤ ለምንት ፀንሀ ብረክየ ፣

ሲድሁ የሞቱ ብዙ ናቸው፤ ስድህ ለምን ያልሞትሁ፤ አንድም ስድህ ብሞት ባማረ በተገባ ነበር፤ አን ድም ስድህ ብሞት ይህ ሁሉ መከራ ባላገኘኝም ነበር ፤

ወለምንት ተሐፀንኩ በጥብ ፣

የናታቸው ጡት አንዝዟቸው የሞቱ ሕፃናት ብዙ ናቸው፤ የእ ናቴ ጡት አንዝዞኝ ለምን ያል ሞትሁ፤ አንድም የእናቴ ጡት አንዝዞኝ ብሞት ባማረ በተገባ ነበር፤ አንድም ብሞት ይህ ሁሉ መከራ ባላገኘኝም ነበር ፤

፲፪፤ ሶበ ሰከብኩ አሚሃ እምአርመ ምኩ ወሶበሂ ኖምኩ አሚሃ እም አዕረፍኩ ፣

ሰከብኩና ኖምኩ ፣ አሚሃና አሚሃ፣ አርመምኩና አዕረፍኩ አንድ ወገን፣ ብሞት ያን ጊዜ ከመከራው በአረፍኩ ነበር ፤

፲፫፤ ምስለ ነገሥት እለ መከሩ እኩየ በምድር ፣

ምነዋ ቢያነግሥህ ትሉኝ እንደ ሆነ በዚህ ዓለም ክፉ ምክር ከመ ከሩ ነገሥታት ጋራ ለምን ያል ሞትሁ፣ ብሞት ባማረ በተገባ ነበር፤ አንድም ብሞት ይህ ሁሉ መከራ ባላገኘኝም ነበር ፤ ስለ ትሕትና እለ መከሩ እኩየ አለ፤



ወኰነኑ በመጥባሕት ፣

በመባሕትም ይላል፣ በሥልጣን ከሚገዙ ከሚሠሩ ፤

፲፬፤ አው ምስለ መላእክት ፣

አለቃ ቢያደርግህ ምነዋ ትሉኝ እንደሆነ፣ ከአለቆች ጋራ ለምን ያልሞትሁ ብሞት በአማረ በተ ገባ ነበር፤ አንድም ብሞት ይህ ሁሉ መከራ ባላገኘኝም ነበር ፤

ወአብዕልትኒ እለ አብዝኅዎ ለወርቅ ወመልዑ አብያቲሆሙ ብሩረ ፣

ባለጸጋ ቢያደርግህ ምነዋ ትሉኝ እንደሆነ ፣ ቤታቸውን ብር ከመሉ፣ ወርቅን ከአበዙ ከባለ ጸጎች ጋራ ለምን ያልሞትሁ፣ ብሞት ባማረ በተገባ ነበር፤ አን ድም ብሞት ይህ ሁሉ መከራ ባላገኘኝም ነበር ፤

፲፭፤ ወሶበኒ ኮንኩ ከመ ዣዕዣዕ ዘአ ድኀፀቶ ማኅፀነ እሙ ፣

የናቱ ማኅፀን አስወርዳ እንደጣ ለችው እንደ ጭንጋፍ ብሆን በአማረ በተገባ ነበር ፤

፲፮፤ ህየ የኀድጉ ኃጥአን ድንጋፄ ፣

ኃጥአን ድንጋፄን በመቃብር ይተዋሉ፣ መቃብር እንጂ በኀ ነገር ነው፤ አንድም ድንጋፄን በሰው ልቡና ይተዋሉ፣ እገሌ ፈርያን ነው፤ እገሌ ሰናክሬም ነው ማለትን፤ አንድም አደንግ ፆቶሙ ይላል፤ ሰው ማስደንገጣ ቸውን በመቃብር ይተዋሉ፣ የሥ ጋውን አልፈውታልና ፤

ወይውዕዩ በመቅሠፍተ መዓቱ ፣

ተቆጥቶ በአመጣው መቅሠፍት ይጠፋሉ ፤

፲፯፤ ወህየ የዓርፉ እለሂ ተዕዕኑ በሥ ጋሆሙ ኀቡረ እምፍጥረተ ዓለም ፣

ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ በሥጋ ቸው የተጨነቁ ሰዎች በመቃ ብር ያርፋሉ ፤

፲፰፤ ንዑሳንሂ ወዓቢያን ህየ ሀለዉ የዓርፉ ፣

ታናሹም ታላቁም በመቃብር አሉ ፤

ሕፃናትሂ እለ ኢርእዩ ብርሃነ ፣

ተወልደው ብርሃን ሳያዩ የሞቱ ሕፃናት፤ አንድም ዘኢፈለጡ ብር ሃነ ይላል፣ ይህ የፀሐይ ብርሃን ነው፣ ይህ የእሳት ብርሃን ነው፤ ብለው የማይለዩ ሕፃናት በመ ቃብር አሉ ፤

ወኢሰምዑ ድምፀ ዘያንሶሱ ህየ ሀለዉ፣

የሚመላለስ የሰውን ድምፅ ያል ሰሙ ሕፃናት በመቃብር አሉ፤

፲፱ ገብርሂ ዘአድለወ ለእግዚኡ ህየ ሀሎ፣

አተላው ለኔ፣ ጥሩው ለጌታዬ፣ ብሎ የሚያደላ ባርያ በመቃብር አለ፤ አንድም ገብርሂ ግዑዝ እም

www.ethiopianorthodox.org

እግዚኦ ይላል፣ ከጌታው ነፃ የወጣ ባርያ በመቃብር አለ፡ አን ድም ለጌታው የሚያደላ ጻድቅ በመቃብር አለ፡ ይኄይሰነ ናድሉ ለእግዚአብሔር እምነ አድልዎ ለሰብእ እንዲል፡ አንድም ግዑዝ እምእግዚኦ ኃጢአት ቢሠራ ጣዖት ቢያመልክ ጌታው ይሆን ከነበረ ከዲያብሎስ ነፃ የወጣ ምዕመን በመቃብር አለ፡ መቃ ብር እንጂ በጎ ነው ፡

፲፱፡ ለምንት ወሀብኮሙ ብርሃነ ለም ሩራን ፣

ለኀዙናን ሲል ነው፡ በከብታችን ጥፋት በልጆቻችን ሞት እርር ምርር ብለን ለአዘነ ለኛ ደስታ ውን ለምን ሰጠኸን፣ በዛሬው መከራ የቀድሞው ተድላ ደስታ፣ በቀድሞው ተድላ ደስታ የዛ ሬው መከራ ያልተጨመረበት፡

ወሕይወት ለጽዑራነ ነፍስ ፣

ልቡናችን ለአዘነ ለኛ ሕይወትን ለምን ሰጠኸን ፡

፳፡ እለ ይትሜነይዎ ለሞት ወኢይ ረክብዎ ፣

ሞትን ለምንለምነው ለማናገ ኘነው ፡

ወይፍርህዎ ከመ መድፍን ፣

የተቀበረውን ወርቅ በመነጥር በጠልሰም በአልስጣላብ እንዲ ፈልጉ ለምንፈልገው ፡

ወይትፌሥሑ ለእመ አድምዕዎ ፣

ብናገኘው ደስ ለሚለን ደስታ ውን ለምን ሰጠኸን ፡

ዕረፍቱ ለሰብእ ሞት ፣

የሰው እረፍቱ ሞት ነው፣ ሞት የሰው ዕረፍቱ ነው፡ ሞት እንጂ በጎ ነገር ነው ለማለት ፡

ወዓፀዎ እግዚአብሔር እምኔሁ ፣

ሞትን ከኔ አራቀው ገንዘብ መስ ሎት ፡

፳፩፡ ወእምድኅረ ማዕረርየ ረከበተኒ መቅሠፍት ፣

በከብት፣ በንብረት ከተዘጋጀሁ በኋላ መከራ አገኘችኝ፡ አንድም እምድኅረ ምረርየ ይላል፣ በከ ብቴ ጥፋት እርር ምርር ብዬ ካዘንሁ በኋላ የልጆቼ ሞት አገ ኘኝ፡ አንድም በልጆቼ ሞት እርር ምርር ብዬ ካዘንሁ በኋላ የአካሌ ጥፋት አገኘችኝ፡ አንድም እምቅድመ ተአርሮትየ ይላል፣ በሞት ከመታጨዴ አስቀድሞ የከብቴ ጥፋት፣ የልጆቼ ሞት፣ የአካሌ ጥፋት አገኘችኝ፡ አንድም እምቅድመ ማዕረር ይላል፡ ገን ዘቤ ተመልሶልኝ ከደዌዬ ተፈ ውሼ ደስ ከሚለኝ አስቀድሞ፡ አንድም ኋላ በመንግሥተ ሰማይ ደስ ከሚለኝ አስቀድሞ የልጅ የአካል ጥፋት አገኘችኝ ፡

የግል ቤተ መጻሕፍት



፳፪፡ እበኪ በእንተ ግሩም ዘረከበኒ፣

የከብት ጥፋት ስለአገኘኝ ፡

ወፍርሃት እንተ ኢተኃዘብኩ ፣

ያልጠረጠርኋት የልጅ ሞት ስለአገኘችኝ ፣

ወእንተ ኢሐለይኩ ተጻደቀተኒ ፣

ያላሰብኋት የአካሌ ጥፋት ስለ አገኘችኝ አለቅሳለሁ ፡

፳፫፡ ኢያርመምኩ ፣

ከጸሎት፣ ከአኰቴት ዝም አላ ልሁም ፡

ወኢያዕረፍኩ ፣

ከመሥዋዕት፣ ከምጽዋት አላረ ፍኩም፡ አንድም ኢያርመምኩ፣ ከመሥዋዕት ከምጽዋት ዝም አላ ልሁም ፡

ወኢያዕረፍኩ ፣

ከቀዊም ከሰጊድ አላረፍሁም፡

ወኢድኀንኩ ፣

ነገር ግን ከመከራው አልዳን ሁም ፡

ወበጽሐኒ መቅሠፍት ፣

የከብት ጥፋት ደረሰብኝ፡ ወመ ንሱት፣ የልጅ ጥፋት ደረሰብኝ፡ አንድም የልጅ ጥፋት፣ የአካሌ ጥፋት ደረሰብኝ ።

## ምዕራፍ ፬

አራተኛው ምዕራፍ ይህ ነው፡

ጉባዔ

፩፡ ወተሰጥዎ ኤልፋዝ ቴማናዊ ወይቤ ፣

የቴምና ሰው ኤልፋዝ እንዲህ አለ ፡

፪፡ ኢታብዝኅ ነቢበ እንዘ አንተ በፃማ ፣

አንተ በመከራ ተይዘህ ሳለ መቀ ባጠርን አታብዛ ፡

አብዝኆ ንባብ ምንት ይበቍዓከ ፣

አንተ በመከራ ተይዘህ ሳለ ነገር ማብዛት ምን ይረባሃል ? ምን ይጠቅምሃል ፡

፫፡ አንተ ዘእምገሠፅከሙ ለብዙኃን፣

አንተ ብዙ ሰዎችን ስትገሥፃ ቸው፡ አንድም ብዙ ሰዎችን ትገ ፅሥፃቸው ዘንድ ይገባህ የነበረ አንተ እንዲህ ያለ ነገር ትናገ ራለህ? አንድም እመ ገሠፅከሙ ገዘኮሉ እምኢረከበከ፣ ብትገሥፃ ቸው ይህ ሁሉ መከራ ባላገኘ ህም ነበር ፡

ወእምናዘዝከ ዕደወ ድኩማነ ፣

ድኩማን አእምሮን ስታረጋጋ ቸው፡ አንድም ታረጋጋቸው ዘንድ ይገባህ የነበረ አንተ እንዲህ ያለ ነገር ትናገራለህ? አንድም

www.ethiopianorthodox.org

እመ ናዘዝከሙ ብታረጋጋቸው ይህ ሁሉ መከራ ባላገኘህም ነበር ፤

፬፡ ወእምአንሣዕከሙ በነገርከ ለድውያን ፤

ድውያን አእምሮን በነገርህ ክታነሣቸው ፤ እንድም ታነሣቸው ዘንድ ይገባህ የነበረ አንተ እንዲህ ያለ ነገር ትናገራለህ ? እንድም እመ አንሣዕከሙ ብታነሣቸው ይህ ሁሉ መከራ ባላገኘህ ነበር ፤

ወእምአጽናዕከ ብርከ ሥዑናን ፤

ስዑናን አእምሮን ክታፀናቸው፤ እንድም ታፀናቸው ዘንድ ይገባህ የነበር አንተ እንዲህ ያለ ነገር ትናገራለህ? እንድም እመ አፅናዕከሙ ብታፀናቸው ይህ ሁሉ መከራ ባላገኘህም ነበር ፤

፭፡ ወይእዜሰ እስመ መጽአከ ሕማም፤

ዛሬ ግን መከራ መጥቶብሃልና፤

ወገሠሠከ ለከ ለሊከ ተዐንብዘ ገባእከ እንከ ፤

ቍስለ መከራ ደርሶብሃልና አእምሮህን ታጣ ዘንድ አእምሮ ወደማጣት ተመለስህ ፤

፮፡ ቀዳሚሁ አኮኑ ዕበድ ውእቱ ፍርሃትከ ወተስፋከ ፤

ጥንቱስ አባቶችህ የሚያመልኩትን አምላክ አመልከዋለሁ፤ እፈራዋለሁ ማለትህ ተስፋህ ከንቱ አይደለምን ፤

ወእኩይ ፍኖትከ ፤

ሥራህም ክፉ ነው ፤

፯፡ ተዘከር ከመ ንጹሕ አልቦ ዘተኃጕለ ፤

ያለ ኃጢአቴ አመጣብኝ ይላልና ንጹሕ ሰው የጠፋ እንደሌለ አስብ፤ ኖኅን፤ ሎጥን አብርሃምን ጠፉ ? ፤

ወኢይጠፍኡ ጻድቃን ወኢይሠረዉ፤

ኢያርመምኩ ወኢያዕረፍኩ ብሎ ነበርና ጻድቃንስ ፈጽመው አይጠፉም ፤

፰፡ ወበከመ ርኢነ እለ የሐርስዋ ለኃጢአት ፤

እንደ አየነ፤ እንደ ሰማነ መጠን ኃጢአትን በሐልዮ የሚሠሯት፤

ወይዘርዕዋ መቅሠፍተ የአርኑ ሎሙ፤

በገቢር የሚሠሯት ሰዎች መከራን ይቀበላሉ ፤

፱፡ ወይትኃጐሉ በትእዛዘ እግዚአብሔር ፤

በእግዚአብሔር ትእዛዝ በሥጋ ይጎዳሉ ፤

ወይማስኑ በመቅሠፍተ መዓቱ ፤

ተቈጥቶ በአመጣው መቅሠፍት በነፍስ ይጠፋሉ ፤

፲፡ ጣኅረ አንበሳ ፤

የኢዮብ መፈራት ፤



ወንቃወ አንበሳዊት ፤

የሚስቱ መፈራት ፤

ወግርማ አክይስት ጠፍኣ ፤

የመኳንንቱ መፈራት ጠፋ ፤

፲፩፡ ስኪዕትኒ ሐልቀ ኃጢአ ዘይበልዕ ፤

የሰውን ገንዘብ የሚበላ ገብረ ጉንዳን የሚበላው አጥቶ ጠፋ፤ አንተም የሰውን ሁሉ ገንዘብ እየዘረፍህ በላህ፤ በዚህ ምክንያት መጣብህ ሠራዊቶችህም ጠፉ ፤

ወዕጕለ አናብስትኒ ተኀለቁ በበይናቲሆሙ ፤

ጣኅረ አንበሳ ወንቃወ አንበሳዊት ብሎ ነበርና የኢዮብ ልጆች አንገት ለአንገት ተያይዘው አለቁ፤ አንድም ወመጽአ ነፋስ ግብተ ብሎ ነበርና የኢዮብ ልጆች ግምብ ተጭኗቸው አለቁ ፤

፲፪፡ ሶበሰ አሐተ ጽድቀ ገበርከ ዘኮሉ እምኢረከበከ ፤

ኢያርመምኩ ወኢያእረፍኩ፤ ትላለህ እንጂ አንድ በጎ ሥራ ሠርተህ ቢሆን ይህ ሁሉ መከራ ባላገኘህም ነበር፤ በነቤየ ነገር ይትነሣእ፤ በኔ ዘንድ ነገር ይጀመራል፤ ነገር ጀማሪ ኤልፋዝ ነውና፤ አንድም በነቤከ ነገር ይትነሣእ፤ በአንተ ዘንድ ነገር ይጀመራል ይለዋል ኤልፋዝ ኢዮብን፤ ነገር ጀማሪ ኢዮብ ነውና፤ ወትሰምዕ ዕዝንየ ቃለ እምኔሁ፤ እምኔከ ሲል ነው፤ ኤልፋዝ ኢዮብን ጆሮዬ ካንተ ነገር ትሰማለች ይለዋል፤ አንድም ኢዮብ እኔ አንተን መስየሃለሁ? ጆሮዬ ነገርን ከእግዚአብሔር ትሰማለች፤ አንድም ኢዮብ እኔ እንዳንተ ጠለፍ አድርጌ እናገራለሁ ? ዕዝነ ሥጋዬ ከዕዝነ ልቡናዬ ነገርን ትሰማለች ፤

ቀዳሚሁኒ ኢየአምኖ ለዘይነግረኒ ፤

ጥንቱንም ኢዮብ ጻደቀ ብሎ የነገረኝን አላምነውም ነበር፤ አባይ ዋሾ የቦለዱ የዛራ ልጅ ኢዮብ ጻደቀ አለው ነበር ?

፲፫፡ ግርማ ሌሊት ወመጽአኒ ይመጽእ ለሰብእ ግብተ ፍርሃት ፤

አጋንንት መከራ ፍርሃት ግርማ ሌሊት ድንገት መጣብህ ፤

፲፬፡ ወአኀዘኒ ድንጋፄ ወረዓድ ፤

የደዌህን ጽናት ባየሁ ጊዜ ድንጋፄ ፍርሃት ያዘኝ ፤

ወበሕቁ አንቀልቀሉ አእፅምትየ ፤

አጥንቶቼ ፈጽመው ተነዋወጡ፤

፲፭፡ ውኀለፈት ነፍስየ እምገጽየ ፤

አእምሮዬ ከገጸ ልቡናዬ ጠፋች፤

www.ethiopianorthodox.org

ወአንሶጠጠኒ ሥዕርተ ርእስየ፤

የራሴ ጠጒር ስግጥጥ ስግጥጥ አደረገኝ ፡

፲፮፡ ተንሣእኩ ወኢያእመርኩክ ፤

ከሀገሬ ተነሥቼ መጣሁ፤ አላወቅሁህም ፡

ነጸርኩክ ወኢጠየቁክ ፤

አየሁህ አልተረዳሁህም ፡

ነጸርኩክ ወአልብከ ራእይ ቅድመ አዕይንትየ ፤

አየሁህ በፊቴ መልክ የለህም መልኩ ተለውጧልና ፡

ጸዕሙ ጽላሎትክ እሬኢ ፤

ቢጋርህን አያለሁ እንጂ፡ አንድም በጥላ መመሰልህን፡ አንድም በወርቅ በመስሉት ምስል መመስልህን አያለሁ እንጂ ፡

ወቃለከ እሰምዕ ፤

ቃልህን እሰማለሁ እንጂ ፡

፲፯፡ ወባሕቱ ዓይኑ ውእቱ መዋቲ ዘይነጽሕ በቅድመ እግዚአብሔር ፤

ነገር ግን ፈራሽ በስባሽ የሚሆን ሰው በእግዚአብሔር ፊት የሚነጻ ማነው ? ፡

ወዓይ ሰብእ ዘይጸድቅ በተግባሩ ፤

በሥራው የከበረ ሰው ማነው፡

፲፰፡ ለላዕካኑ ጥቀ ኢይትአመኖሙ፤

መላእክትንስ ስንኳ ልቡናቸው፡ አንድም ንጽሕናቸው የማይታመናቸው ከሆነ ፡

ወለመላእክቲሁኒ ዕፁበ ይትሄዘቦሙ፤

ለመላእክት ልቡናቸው ንጽሕናቸው ከተጠራጠራቸው የተጠራጠራቸው ፡

፲፱፡ እፎኬ ለእለ ይነብሩ አብያተ መሬት ፤

በሥጋ በዚህ ዓለም ለሚኖሩ ሰዎች እንደምን አይጠራጠራቸው ? አንድም በመቃብር ለምንኖር ለኛ እንደምን አይጠራጠረን ?

ወንሕነኒ እምነ ፩ዱ ጽቡር ፤

ከአንድ ከአዳም፤ ከአንድ ከመሬት ለተፈጠርን ለኛ እንደምን አይጠራጠረን ?

ወይረክቦሙ ብልዐተ ዕፄ ፤

የዕፄ አበላል የሚያገኛቸው፡ አንድም የዕፄ አበላል ያገኘናል ፡

፳፡ ወኢይሄልዉ እምነግህ እስከ ሠርክ ፤

ኑ በአላቸው ጊዜ ከነግህ እስከ ሠርክ አይቆዩም፡

እስመ ስዕኑ አድኅኖ ነፍሶሙ ወረዲአ ርእሶሙ ተኀጕሉ ፤

ሰውነታቸውን ማዳን ራሳቸውን መርዳት ተስኗቸዋልና አይቆዩም፡ አንድም ሰውነታቸውን ማዳን ራሳቸውን መርዳት ተስኗቸዋልና ጠፉ ፡



፳፩፡ ወነፍሖሙ ነፋስ ወተኀጕሉ ፤

ነፋስ፤ አንድም መከራ መጣባቸው፤ ጠፉ ፡

እስመ አልቦሙ ጥበብ ፤

የሚድኑበት ጥበብ የላቸውምና::

## ምዕራፍ ፭

አምስተኛው ምዕራፍ ይህ ነው፡

፩፡ ጸውዕ እስኩ እመቦ ዘየወሥአከ፤

ከጻድቅ ሰው መልአክ አይለይም ለሙሴ መልአከ ገጽ እየነገረው ኩፋሌን እንደጻፈ፡ አንድም ከመላእክት ጻድቅ ነኝ ብሎ የሚመልስልህ አለ እንደሆነ እስቲ ተጣራ፤ አንድም ንጹሕ ነኝ ብሎ የሚመልስልህ አለ እንደሆነ እስቲ ተጣራ ፡

ወእመቦ እመላእክቲሁ ቅዱሳን ዘትሬኢ ፤

ዘትሰምዕ ሲል ነው፤ ከቅዱሳን መላእክት ጻድቅ ነኝ፤ ንጹሕ ነኝ ሲል የምትሰማው አለ እንደሆነ፡

፪፡ እስመ ለአብድ መዓት ይቀትሎ ፤

ሰነፍን የራሱ ቍጣ ይገድለዋልና እንደ አኪጦፌል፡

ወዕቡድኒ ይመውት በቅንዓት ፤

የሰነፍ ሰነፍ ባልንጀራዬ ተሾመ ተሸለመ ብሎ በቅንዓት ይሞታል ፡

፫፡ አንሰ ርኢኩ በቈለ ሥርዎሙ ለአብዳን ፤

የሰነፎች የአባትነታቸውን ጽናት እኔ አየሁ ፡

ወበጊዜሃ ጠፍዐት ንብረቶሙ ፤

ለጊዜው እንዲህ አልሁ እንጂ አኗኗራቸው ያን ጊዜ ጠፋች ፡

ወወጽአ እምሕይወቶሙ ፡

ከሕይወታቸው ተለዩ ፡

፬፡ ወለውሉዶሙኒ ይኩርዕዎሙ በአናቅጽ ፤

ልጆቻቸውንም በአደባባይ ራስ ራሳቸውን ይቀጠቅጧቸዋል ፡

ወየመነዝዝዎሙ ወአልቦ ዘያድኅኖሙ፡

አጽንተው ይይዟቸዋል፤ የሚያድናቸው የለም ፡

፭፡ ዘእሙንቱ ዘገቡ ጻድቃን ይበልዑ ፡

ይኸውም ልማድ ነው፡ ኃጥአን የሰበሰቡትን ጻድቃን ይበሉታል፡

ወሉሙስ ትዐብዮሙ እኪት ፡

እነሱን ግን መከራ ታጠፋቸዋለች ወይትመሰው ኃይሎሙ የኀልቅ ብዕሎሙ ይደክም ኃይሎሙ ሲል ነው፡ ባለጸግነታቸው ይጠፋል፤ ኃይላቸው ይደክማል፡

www.ethiopianorthodox.org

፮፡ እስመ አኮ እምድር ዘይወጽእ ሃማ ፤

በደዌ መድከም ከምድር የሚገኝ አይደለምና ፡

ወአኮ እምውስተ አድባር ዘይበቍል ሕማም ፤

መከራ ከተራራ የሚገኝ አይደለምና ማለት ከምድር እንደ ሰርዶ ከሰማይ እንደ በረዶ የሚገኝ አይደለምና ፡

፯፡ ሰብእሰ ይትወለድ ለሥራሕ ፤

ሰው ግን መከራ ሊቀበል ይፈጠራልና በኃጢአትህ የመጣብህን መከራ አንተ ተቀበለው እንጂ ማን ይቀበልልሃል ፡ አንድም በደዌ መድከም ከምድር ከባሕርይዋ የሚገኝ አይደለምና፤ መከራም ከተራራ ከባሕርይዋ የሚገኝ አይደለምና፤ ሰው ግን በተስማሚ ሰውነቱ መከራ ሊቀበል ተፈጥሯልና፤ በተስማሚ ሰውነትህ አንተ ተቀበለው እንጂ ማን ይቀበልልሃል ፡

ወዕጕለ አዕዋፍ ያሌዕሉ ያፈ ፤

ወአዕዋፍ ያሌዕሉ ዕጕለ ያፍ ሲል ነው፡ አዕዋፍ የሰውን ገንዘብ እየዘረፉ ልጆቻቸውን ያሳድጋሉ፡ አንተም የሰውን ገንዘብ እየዘረፍህ በልተህ በዚህ ምክንያት መከራ መጣብህ ፡

፰፡ ወባሕቱ ለእግዚአብሔር እስዕሎ፤

ነገር ግን ኢዮብ እኔ እንዳንተ አይደለሁም፡ እግዚአብሔርን እለምነዋለሁ፡ አንድም ለእግዚአብሔር፤ እግዚአብሔርን እለምነዋለሁ በል ፡

፱፡ ወእጼውዖ ለእግዚአ ኵሉ ለዘገብረ ዓቢያተ ወክቡራተ ወመንክራተ ዘአልቦ ሁሌቍ ወአልቦ ኍልቈ ፤

ቍጥር ስፍር የሌለው ድንቅ ድንቅ፤ ክቡር ክቡር፤ ዕፁብ ዕፁብ ሥራ የሠራ አሠረ ባሕርዩ የማይመረመር የሁሉ ጌታ እግዚአብሔርን እለምነዋለሁ፡ አንድም እለምነዋለሁ በል ፡

፲፡ ዘይሁብ ዝናመ ላዕለ ምድር ፤

ዝናሙን በምድር ላይ የሚያዘንም እሱ ነው ማለት በደመና ቋጥሮ፤ በነፋስ ጭኖ የሚያመጣው እሱ ነው ፡

ወይፌኑ ማየ መትሕተ ሰማይ ፤

ዝናሙን ከሰማይ በታች በዚህ ዓለም ያዘንማል ፡

፲፩፡ ዘያሌዕሎሙ ለትሑታን ፤

ትሑታን ሰዎችን ከፍ ከፍ የሚያደርጋቸው እሱ ነው፡ አንድም አዝርእትን፤ አትክልትን ከፍ ከፍ ቅየሚያደርጋቸው እሱ ነው፡ አንድም ዝናማትን እንዲዘንሙ የሚያደርጋቸው እሱ ነው ፡



ወይኔሥኦሙ ለግዱፋን ፤

በመከራ የወደቁትን ሰዎች የሚያነሣቸው እሱ ነው፡ አንድም አዝርዕትን፤ አትክልትን የሚያነሣቸው እሱ ነው፡ አንድም ዝናማትን እንዲዘንሙ የሚያደርጋቸው እሱ ነው ፡

፲፪፡ ወይመይጥ ምክሮሙ ለእለ በጕሕሉት ፤

በጉሕሉት (በክዳት በተንኰል) ያሉትን ሰዎች ምክራቸውን የሚለውጥ እሱ ነው፡ ወለእመኒ ለቢያር ዕጉለ ጕሕሉት አሦር ይጼውዖ እንዲል፡

ወኢይገብራ ርቱዓ እደዊሆሙ ፤

እደ ልቡናቸው የቀና ሥራ አይሠራም ፡

፲፫፡ ዘይእኅዞሙ በምክሮሙ ለጠቢባን ፤

በምክራቸው ምክንያት አዋቆች ነን የሚሉትን በፍዳ የሚይዛቸው እሱ ነው ፡

ወያጠፍዕ ሕሊናሆሙ ለእለ ይጸፍርዋ ለምክር ፤

ምክርን አጽንተው የያዙ ክፉ አሳባቸውን የሚያጠፋ እሱ ነው፡

፲፬፡ መዓልተ ይረክቦሙ ጽልመት፤

በአፍኣ ባለጸግነት ሳሉ መከራ ያገኛቸዋል ፡

ወያረምስሱ ቀትረ ከመ ዕውር ወከመ ሌሊት ፤

ደህነኛ በሌሊት፤ ዕውር በቀን እንዲዳብስ ይዳብሳሉ ፡

ወይትኃጐሉ በውስተ ቀትል ፤

በሰልፍ ይጠፋሉ ፡

፲፭፡ ወየመስጥ ድኩም እምእደ ኃያል ፤

እንደዚህም ሁሉ አንተ ጠፍተህለት ደካማው ከኃይለኛ እጅ ይድናል ፡

እስመ ዕቡስኒ ቦቱ ተስፋ ፤

ለዕቡስሂ ሲል ነው፡ ለደካማው አለኝታ አለውና ፡

ወይትፌጸም አፉሁ ለዓማፂ ፤

የሸፋፊው አፉ ይዘጋል ፡

፲፮፡ ወባሕቱ ብፁዕ ብእሲ ዘእግዚአብሔር ገሠፆ ፤

ነገር ግን እግዚአብሔር መከራ አምጥቶ የገሠጸው ሰው ንዑድ ነው ክቡር ነው፡

ወኢታስተዕሕብ ተግሣጸ እግዚአብሔር ፤

ተግሣጸ እግዚአብሔርን አታቃል ፤ አትናቅ ፡

፲፯፡ እስመ ውእቱ ያቄስል ፤

እሱ በመከራ ያቆስላልና ይኸን አይሻውም ፡

www.ethiopianorthodox.org

ወካዕበ ይፌውስ ፣

ዳግመኛ ያድናልና ፡

ይቀሥፍሂ እዴሁ ወይሠሃል ፣

በሥልጣኑ ይገርፋል ፣ ይቅር ይላል፡

፲፰፡ ስድሰ ያድኅነከ እመንሱት ፣

ስድስት ጊዜ ከሞት ያድንሃል፡

ወበሳብዕት ኢትገሥሠከ እኪት ፣

በ፯ኛው ከደዌህ ያድንሃል ፡ ስንክሣር ፴ዘመን አለ ፡ ከዚህ ፯ ዘመን አለ፣ አይጣላም ቢሉ አይጣላም፡ ከዚያ መላ ዘመኑን፣ ከዚህ የፀናበትን ለይቶ ተናገረ፡ አንድም ፴ው ፯ ፣ ፭ ይሆናል አንድ ነው፡ አንድም በኃደሉ ትዕግሥትህ ከደዌህ ያድንሃል፣ በፍጹም ትዕግሥትህ ከሞት ያድንሃል ፡ አንድም ወደፊት ያመጣዋል፡

፲፱፡ እመሂ ረኃብ ያድኅነከ እሞት፣

ቀጠናም ቢመጣብህ ከሞት ያድንሃል እንጂ ፡

ወበውስተ ፀብእሂ ያነግፊከ እምእደ ኵናት ፣

እምአፈ ኵናት ሲል ነው፡ በሰልፍም ጊዜ ከጦር እንደበት ያድንሃል ሁለት ፡

፳፡ ወይሜውረከ እመቅሠፍተ ልሳን፣

ከነገረ ሠሪ አንደበት ይሠውርሃል ፡ ሦስት ፡

ወኢትፈርኅ እምእኪት እንተ ትመጽእ ፣

ከምትመጣብህ መከራ አትፈራም ፡ አራት ፡

፳፩፡ ወትስሕቆሙ ለኃጥአን ወለዓማፅያን ፣

በኃጥአን፣ በዓማፅያን ትዘብት ባቸዋለህ ፡ አምስት፡

ወኢትፈርኅ እምአራዊተ ሐቅል ፣

ከምድረ በዳ አራዊት የተነሣ አትፈራም ማለት ከአሕዛብ የተነሣ አትፈራም ፡ ስድስት ያለው ይህ ነው ፡

ወይሰነዓወከ አራዊተ ገዳም ፣

የምድረ በዳ አራዊት ከአንተ ጋራ ይስማማሉ ማለት አሕዛብ ይገዙልሃል፡ ሳብዕም ያለው ይህ ነው ፡

፳፪፡ ወሰቤሃ ተአምር ከመ ዳኅን ቤትከ ፣

ወገንህ ደህና እንደሆነ ያን ጊዜ ታውቃለህ ፡

ወአልቦ ዘይትነከይ እምንብረትከ ፣

ከገንዘብህ የሚጠፋ የለም ፡

፳፫፡ ወትጤይቅ ከመ ብዙኅ ዘርዕከ፣

የልጅ ልጅህ ብዙ እንዲሆን ትረዳለህ ፡



ወደቂቅከኒ ከመ ሣዕረ ጊያት ሥዑር፣

ልጆችህም እንደ አማገረ እንደ መስከ ሣር ይሆናሉ፡ ያ እንዲ ወደድ ይወደዳሉ ፡

፳፬፡ ወተአቱ መቃብሪከ ዘህሉከ ፣

በብዕል ሲል ነው፡ በባለጸግነት ሳለህ ሳታጣ ትሞታለህ ፡

ከመ ዕክለ ማዕረር ሥዑር ፣

እንደ አማገረ፣ እንደ በጀ መከር እህል ፡

ወከመ ክምር ዘኵሉ ጊዜ ይነሥኡ ኅምኔሁ ፣

ሁል ጊዜ እየዘረፉ የሚወስዱት ክምር እንደማያልቅ ሳታጣ ትሞታለህ ፡

፳፭፡ ናሁ ዝ አሠር ዘአቅጻዕነ ወዝንቱ ዘሰማዕነ ፣

እነሆ ያስወኃነው ወግ የሰማነው ወሬ ይህ ነው፡ ኃጥአን እንዲጠፉ ጻድቃን እንዳይጠፉ ፡

ወአንተ ባሕቱ አእምር ዘገበርከ ፣

ነገር ግን አንተ ያደረግኸውን እወቅ ማለት በኃጢአቴ መጣብኝ በል፡ አንድም ጻድቅ ሰው እንዳይጠፋ ኃጥእ እንዲጠፋ እወቅ ::

## ምዕራፍ ፮

ስድስተኛው ምዕራፍ ይህ ነው፡

ገባዔ

፩፡ ወእደ ተናገረ ኢዮብ ተሰጥወ ወይቤ ፣

ኢዮብ ከተናገረ ዘንድ መለሰ፣ እንዲህ አለ ፡

፪፡ ናሁ ፩ዱ እምኔከሙ ይደልዋ ለመቅሠፍትየ ፣

እነሆ ከናንተ አንዱ ኤልፋዝ ለመከራዬ ይገባታል ፡

ወይነሥእ ኀቡረ በመዳልው ለሕማምየ ፣

ከናንተ ፩ዱ ልቡናውን እንደ ሚዛን አድርጎ ቢመዝናት እንዲህ ባላላችሁኝም ነበር፡ ስለምን እንዲህ አለ፡ የተናገረው ኤልፋዝ አይደለም ቢሉ እነዚያም እንዳ ይተዉት ያውቃልና፡ አንድም ከናንተ አንዱ ኤልፋዝ በሰውነቱ ቢቀበላት እንዲህ ባላለኝም ነበር፡ አንድም ከናንተ አንዱ ኤልፋዝ በሰውነቱ ሊቀበላት ትገባዋለች፡ እስመ ይከብድ እምኆፃ ባሕር፣ ነገራችሁ ከባሕር አሸዋ ይከብዳልና ፡

፫፡ ወባሕቱ ሐሰተ ይመስል ነገርየ ዘእሙን ፣

ነገር ግን የታመነው ነገሬ ሐሰት ይመስላል፣ የሰው ቀኀል የግንድ ይመስል እንዲሉ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ናሁ አሕፃሁ ለእግዚአብሔር ኣዕለ ሥጋየ ፤

የእግዚአብሔር አሕፃ መዓቱ በሰውነቴ ላይ ነው ፤ አንድም አሕፃው ዕፄ በሰውነቴ ላይ ነው፤

ወኀምዙ ይሰርበኒ ደምየ ፤

ኀምዘ መዓቱ ፤ አንድም ኀምዙ ዕፄ ደሜን ያደርቀዋል ፤

ሶበ እእኅዝ እንብብ ይደጕፀኒ ሥጋየ፤

ልናገር በጀመርሁ ጊዜ ሰውነቴን ይወጋኛል፤ አላናግር ይለዋልና ፤

፭፡ ቦኑ ለከንቱ ይነቁ ሐለስትዮ በውስተ ሐመልማል አኮኑ እንዘ የኀሥሡ ዘይበልዕ ፤

ረድኤተ እግዚአብሔር ሳይለየው ተለየኝ፤ በኃጢአቱ መጥቶበት ሳለ ያለ ኃጢአቴ አመጣብኝ ይላል ይሉታልና፤ የምድረ በዳ አህያ በልምላሜ መካከል ሳለ በውኑ በከንቱ ይጮኻልን፤ የሚበላው ሲሻ አይደለምን ፤

ወይነቁኑ ላሕም እንዘ ይበልዕ ውስተ ጎል ወይቀምሕ ፤

በበረት የሚበላው፤ የሚቅመው ሳለ (በሬ) ላም በከንቱ ይጮኻልን፤ ያለ ኃጢአቴ ቢመጣብኝ ረድኤተ እግዚአብሔር ቢለየኝ ነው እንጅ ፤

፮፡ ወይትበላዕኑ እክል ዘእንበለ ጼው፤

እህል ያለ ጨው ይበላልን፤ መበላትስ እንዳይበላ የለም፤ በውኑ ጣዕም አለው? ለኔስ ነገር ጣዕም አለው ?፤

ወቦኑ ጣዕም ለሐሪፈ ሐመልማል ዘይሰመይ ሕጥሜ ፤

በሌላ ቋንቋ ሕጥሜ ለሚባል ለጎመን ዘር ጭማቂ በውኑ ጣዕም አለው? እንደዚህስ ሁሉ ረድኤተ እግዚአብሔር ሳይለየኝ ተለየኝ እላለሁ ?፤

ወቦኑ ጣዕም ለነገር ከንቱ ፤

ለከንቱስ ነገር ጣዕም አለው ? ያለ ኃጢአቴ ቢመጣብኝ ረድኤተ እግዚአብሔር ቢለየኝ ነው እንጂ ፤

፯፡ ኢይክል አእርፎ ነፍስየ ፤

ሰውነቴን ከመከራ ማሳረፍ አልችልም፤ አንድም ሰውነቴ ከመከራ ማረፍ አይቻላትም ፤

ወእሬኢ ንስሐተ ሥጋየ ከመ ብሕባሔ አንበሳ ፤

እንደ አንበሳ ክርፋት የሆነ የሰውነቴን ክርፋት አያለሁ ፤ አንድም እንደ አንበሳ ኃይል የሆነ የሰውነቴ ኃይል ወደ ድካም መመለሱን አያለሁ ፤

፰፡ ሶበ ይመጽአኒ ጻሉትየ ፤

አትታገሥም ይሉታልና ልመናዬ ደዌን ይዞ ሲመጣ እንደ



ምን ልታገስ፤ አንድም ልመናዬ ዋጋዬን ይዞ ሲመጣልኝ ልታገሥ እንጂ እንደምን ልታገሥ ፤

ወይሁበኒ እግዚአብሔር ተስፋየ ፤

ዝም አትልም ይሉታልና ተስፋዬ ደዌን ሲያመጣብኝ እንዴት ዝም ልበል፤ አንድም ተስፋዬ ድኅነቴን በአመጣልኝ ጊዜ ዝም ልበል እንጂ ፤

፱፡ ወአኀዘ እግዚአብሔር ወፈጸመ፤

ተዘከር ከመ ንጹሕ አልቦ ዘተኀጕለ ብሎ ነበርና እግዚአብሔር በኔ ጀምሮ በኔ ጨረሰ፤ አንድም አኀዘ፤ በከብቴ ጥፋት፤ ወፈጸመ በልጆቼ ሞት ፤ አንድም አኀዘ በልጆቼ ሞት፤ ወፈጸመ፤ በአካሌ ጥፋት ጨረሰ፤ ወቀተለኒ ለዝሉፉ፤ ፈጽሞ አጠፋኝ ማለት ከከብት፤ ከልጅ፤ ከአካል ለየኝ፤

፲፡ ወሶበ ተሐንፀ ዝህርየ ፤

መቃብር ሲቆፈርልኝ እንዴት ዝም ልበል፤ አንድም መቃብር በተቆፈረልኝ ጊዜ ዝም ልበል እንጂ፤ አንድም ወሶበ ተሐንፀ ዓውድየ ይላል፤ ዙሪያዬ ሲቆፈር እንዴት ዝም ልበል ማለት የከብት፤ የልጅ፤ የአካል ጥፋት ሲያገኝኝ ፤

ወእትመየየጥ ውስተ ዓረፋቲሁ ፤

በማጥኑ ስመላለስ፤ አንድም በዘንግ ይለኩታልና፤ አንድም ከፍና ዝቅ ያደርጉታልና ፤

ወኢይምሕክ ፤

ያለ ኃጢአቴ አመጣብኝ ማለትን፤ አንድም መሐሪ ወመስተሣህል ነው ማለትን አልሸልግም ፤

እስመ ኢሐሰውኩ ቃለ አምላኪየ ቅዱስ ፤

ክቡር የሚሆን የፈጣሪዬን ሕግን አላፈረስሁምና፤ አንድም መሐሪ መሆኑን አልካድሁምና ፤

፲፩፡ ምንትኑ ኃይልየ ከመ እትዓገሥ፤

ዝም በል ይሉታልና ዝም እል ዘንድ ኃይሌ ምንድ ነው፤

ወምንትኑ መዋዕልየ ከመ ታስተአገዝዝ ነፍስየ ፤

ሰውነቴ ትጽናና ዘንድ ዘመኔ ምንድ ነው ፤

፲፪፡ ቦኑ ኃይለ ዕብን ኃይልየ ፤

መከራውን እታገሥ ዘንድ በውኑ ኃይሌ የደንጊያ ኃይል ነው?፤

ወሚመ ዘብርትኑ ሥጋየ ፤

መከራውን እታገሥ ዘንድ ሥጋዬ የብርት ወገን ብረት የብረት ወገን ብርት ነው? ያ እሳቱን፤ ፍላቱን፤ መዶሻውን መታገሥ ይቻለዋል፤ መከራውም እንደዚያ ነውና፤

፲፫፡ አኮኑ ቦቱ ተወከልኩ ፤

በሱ ያመንሁ አይደለሁም፤ አንድም በሱ አምኛለሁና ፤

www.ethiopianorthodox.org

ርኅቀ እምኔየ ረድኤቱ ፣

ለምንት ርኅቀ ሲል ነው፡ ረድ ኤቱ ከኔ ለምን ራቀ ፡

፲፫፡ ወተሐየየኒ ማህሉ ፣

ይቅርታውስ ለምን ቸል አለኝ፡

ወኢነጸረኒ እግዚአብሔር ወኢሐወ ፀኒ፣

እግዚአብሔር በዓይነ ምሕረት ለምን አላየኝ? አልተመለከተኝ? በረድኤት ለምን አልጎበኘኝ?፡

፲፬፡ አዘመደየኒ ኢየእመሩኒ ፣

ነጸርዎ ወኢየእመርዎ ፣ ብሎ ነበርና ዘመዶቼም አላወቁኝም፡

ከመ ውኂዝ ዘነጽፈ ወከመ ማዕበል ዘኃለፈ፣

ኩንኩ ይቤ ያለበት ነው፡ ጎርፍ ማዕበል ለጊዜው እንዲያስፈራ ኋላ እንዳያስፈራ ፡

እልኩቱ እለ ይፈርሁኒ እሙንቱ ይስ ሕቱኒ ፡

ይፈሩኝ የነበረ እነዚህ ይዘብቱ ብኛል ፡

፲፭፡ ከመ በረድ ወከመ አስሐትያ ዘጠግዐ ፣

በረድ፣ ውርጭ እንዲረጋ ረግቶ እንዲሰነብት ፡

ወእምዝ ተመስወ መዊቶ ወኢተአውቀ ኀበ ነበረ ፣

ከዚህ በኋላ ቀልጦ እንዲጠፋ፣ የነበረበት እንዳይታወቅ ፡

፲፮፡ ከማሁ አነሂ ወጻእኩ እምኮሉ ወተነገሉኩ ፣

እንደዚህም ሁሉ እኔም ከልጅ፣ ከከብት ተለየሁ፣ ጠፋሁ፡

ወወጻእኩ እምቤትየ ፣

ወነበረ አፍአ ብሎ ነበርና ከቤቴ ወጣሁ ፡

፲፯፡ ተአምሩ ማዕዘሙ ለቴማናን ፣

ኤልፋዝን ይነካል፣ በኃጢአትህ መጣብህ ይሉታልና ፍዳ መቀ በል በኃጢአትማ ከሆነ የቴማንን ሰዎች ግብራቸውን ታውቁታላ ችሁ ፡

ወእከየሙ ለሳባን ፣

ሳፍርን ይነካል፣ የሳባንን ሰዎች ክፋታቸውን ታውቁታላችሁ፡

ወተዓውሮቶሙ ፡

ሕገ እግዚአብሔርን ቸል ማለታ ቸውን ታውቁታላችሁ፡

፲፰፡ ወርቱዕስ ይትሐፈሩ እለ ይት ዌከሉ በንዋዮሙ ወበአብያቲሆሙ ፣

አገባብስ በገንዘባቸው፣ በቤታ ቸው የሚታመኑ ሰዎች ይፈሩ፡

፲፱፡ ከመ አንትሙ መጻእክሙ ዘእን በለ ምሕረት ፣

እናንተ ያለ ርኅራኄ መጥታ ችሁ ፡



ወርእየክሙ ቍስልየ ወኢፈራኅክሙ፣

ቍስሌን አይታችሁ አልፈራች ሁም ፡

፳፡ በእንተ ምንት በሁ ዘሰዓልኩክሙ፣

እንዲህ የምትሉኝ ስለምን ነው? እርዱኝ ብዬ የለመንኋችሁ መለ መን አለ ?፡

ወሚመ ኃይለ ዚአክሙ ተመነይኩ፣

ወይስ ብዕላችሁን፣ ሠራዊታች ሁን ተመኘሁን ፡

ከመ ታድኅኑኒ እምፀርየ ወታንግፉኒ እምእደ ዘይኄይሉኒ ፣

ከጠላቴ ታድኑኝ ዘንድ፣ ከሚበረ ታቱብኝ እጅ ታስጥሉኝ ዘንድ፡

፳፩፡ መሐሩኒ ወአነ አጸምአክሙ፣

ይቅር በሉኝ፡ አንድም ንገሩኒ የበደልሁት አለ እንደሆነ ንገ ሩኝ፣ አደምጣችኋለሁ ፡

ወእመቦ ዘስሕትኩ አጠይቁኒ ፣

የበደልሁት አለ እንደሆነ አስረ ዱኝ ፡

እስመ ሐሰተ ይመስለክሙ ነገርየ ዘእሙን ፣

የታመነው ነገሬ ሐሰት ይመስ ላችኋልና ፡

፳፪፡ ዘአኮ በነቢክሙ ዘእስዕል ኃይለ፣

ከናንተ ዘንድ ሠራዊትን፣ ብዕልን የምለምን አይደለሁም፡

ወነባቤ ነገርክሙ ኢያስሕተኒ ፣

የነገራችሁም ማረጋጋት ደስ አያ ሰኘኝም ፡

ወኢይሔውዘኒ ማዕማዕ ቃልክሙ ፣

ጣዕመ ቃልክሙ ሲል ነው፡ እኛ እንጂ የከተማ ሰዎች ነን፣ ነገር አከናውኖ መናገር ይቻለናል ማለታችሁ ደስ አያሰኘኝም ፡

እስመ ስሐቅሙ ዲበ ዕጓለ ማውታ፣

እናት አባቱ ጥለውት በሞተ ዘብታችኋልና ፡

ወተሳለቅሙ ላዕለ ርእስክሙ ፣

በወዳጆችሁ በኔ ዘብታችኋልና፡

፳፫፡ ወይእዜኒ ነጺርየ ገጽክሙ እንዘ ኢይኄስወክሙ ኀበሩ ዲዕሙ ወኢተ ዓምዑ ፣

አሁንም ፊታችሁን አይቼ ሳል ፈራችሁ ተቀመጡ እንጂ አት በድሉ አልኋችሁ ፡

ወበጽድቅ ካዕበ ተናገሩ ፣

ዳግመኛ እውነት ተናገሩ ፡

፳፬፡ እስመ አልቦ ቃለ ዓመፃ ውስተ ልሳንየ ፣

በአንደበቴ ሐሰት ነገር የለምና፡

ወጥበበ ይነግር አፉየ ፣

አፌም ጥበብ የሚሆን ነገር ይና ገራል ።

# ምዕራፍ ፯

ሰባተኛው ምዕራፍ ይህ ነው፤

፩፡ ቀዳሚሁ አኮኑ ጽኣሉት ውእቱ ሕይወቱ ለሰብእ ዲበ ምድር ።

አኮኑ ጽኣሉተከ እሬዒ ብሎ ነበርና ማን አሰት ብሎሃል ጥን ቱንም ሰው በዚህ ዓለም ለወርቅ ለብር የመሰሉት ሰም ነው፤ ጥላ ጊት ይረዝማል፣ ኋላ ያጥራል ደግሞ ይረዝማል፣ ደግሞ ያጥ ራል ።

ወንብረቱኒ ከመ አሳብ ዘለለዕለቱ፣

አነዋወሩም እንደ ዕለት ምንደኛ ነው፣ የዕለት ምንደኛ ቀኑ በደ ረሰ ጊዜ ልዋል ልደር እንዳይል፤ አንድም እኔ ከገባሁ ገንዘቡ በዛ ብሎ ልውሰድ እንዳይል፣ ሰውም ከከፈን በቀር ምንም ይዞ አይሔድም ።

፪፡ ወእመ አኮ ከመ ገብር ዘአድለወ ለእግዚኡ ወያጸምዕ ጸሎቶ ።

ይህም ባይሆን መናኛው ለኔ፣ ማለፊያው ለጌታዬ፣ አተላው ለኔ፣ ጥሩው ለጌታዬ ብሎ የሚ ያደላ ባርያ ለጌታው ሹመት፣ ሽልማት ስጥልኝ ብሎ እንዲ ለምን፣ በተሾመ ጊዜ ምንም ምን እንዳያስበው፣ ሰውም በሞተ ጊዜ ከገንዘቡ ምንም ምን ይዞት የሚ ሔድ የለም፤ አንድም ጽኣሉቶ ይላል ጌታው ጥላ ሰፍሮ እንዲ ልከው ከዚያ እልፍ እንዳይል ሰውም ና ባለው ጊዜ አይውልም አያድርም ፤

አው ከመ ገባኢ ዘይሴፎ አስቦ ።

ወይስ ደመወዙን አገኛለሁ ብሎ ተስፋ እንደሚያደርግ ምንደኛ፤

፫፡ ከማሁ አነሂ ተዓገሥኩ አውራኀ ከንቶ ።

እንደዚህም ሁሉ ከንቱ የሆኑ አውራኀን ታገሥሁ፣ እሱ ከንቱ ስለሆነባቸው ነው ፤

ሌሊተኒ ተውኅበኒ ሊተ ፃዕር ።

ሌሊት ቍርጥማት ተሰጠኝ፤ ሰው ቀን ሲጽር፣ ሲግር እንዲውል እሱም ሌሊት ሲጽር ሲግር ያድ ራልና ፤

፬፡ እመ ኖምኩ እብል ማዕዜ ይጸ ብሕ ።

በተኛሁ ጊዜ እንጂ መች ይነጋ ይሆን እላለሁ፣ ብርሃን ቢያይ፣ ከሰው ጋራ ቢነጋገር ይሻለው ይመስለዋልና ፤

ወእመ ነቃሕኩ እብል ካዕበ ማዕዜ ይመሲ ።

በተነሣሁ ጊዜ ዳግመኛ መች ይመሽ ይሆን እላለሁ፤ ብርሃን ማየቱን፣ ከሰው ጋራ መነጋገሩን ብተወው ይሻለኝ ይመስለዋልና፤



፭፡ ጸገብኩ ሕማመ እምንግህ እስከ ሠርክ ።

ከንግህ እስከ ሠርክ ድረስ መከ ራውን ጠገብሁ ፡ ምነው ፴ ዘመን አይደለምን ቢሉ፣ ያው እየመሸ እየነጋ ነውና ፡

ወበኍልቍ ሥጋየ በዕጺያት ወመግል፣

ሥጋዬ በዕጼያት ተከቦ በመግል ተውጦ ሸተተ፣ ከረፋ ፤

ወሐለቁ እንዘ አሐክክ ጸውበ ወእም ጻንጼ ።

የጕረበውን ስልጥ፣ ያበጠውን ሳፈርጥ ደከምሁ ፡

ወሐመደ ኮንኩ ።

አመድ ሆንሁ ፡ ገል ደቁሰው፣ አመድ ነስንሰው በማጥን አድር ገውታልና ፡ አንድም ደዌው አመድ ያስመስለዋልና ።

፮፡ ቀሊለ ኮነት ሕይወትየ ከመ ነገረ ዘየአንም ።

አፍአሬ እንደ ነገረ ሠሪ ነገር የተናቀች ሆነች፤ አንድም የነገረ ሠሪ ነገር እንዲናቅ የተናቀች ሆነች ፡

ወተኀጕልኩ በተሰፋየ ከንቱ ።

ከንቱ ነገርን ተስፋ በማድረግ ጠፋሁ ፡

፯፡ ተዘከር ከመ ነፋስ ይእቲ ሕይወ ትየ ።

ሰውነቴ እንደ ነፋስ እንደሆነች አስብ፤ በደዌ ፈጥና ጠፍታለችና፤

ወኢትገብእ እንከ ዓይንየ ትርአይ ሠናየተ ።

ዓይኔ ተድላውን ፣ ደስታውን ታይ ዘንድ እንግዲህ ወዲህ አት መለስም ፡

፰፡ ወኢይሬኢ ዓይነ ዘይሬእየኒ ።

የሚያየኝን ሰው ዓይን አላይም፤ አንድም የሚያየኝ ሰው ዓይን በቀደመ መልኬ ፡ አያየኝም መልኩ በደዌ ተለውጧልና ፡

ወእመሂ ነጸረኒ ኢይሄሉ እንከ ።

ቢያየኝም በቀደመ መልኬ አል ገኝም፤ አንድም ይህ ደዌ ከኔ ጋራ አይኖርም ፤

፱፡ ከመ ደመና ዘተነጽሐ እምሰማይ ኢይገብእ ።

የተበተነ፣ ከሰማይ የወረደ ዝናም እንዳይመለስ ፤

እስመ እምከመ ወረደ ሰብእ ውስተ መቃብር ኢየዓርግ እንከ ።

ሰው ወደ መቃብር ከወረደ በኋላ አይመለስም ፤

፲፡ ወኢይገብእ ውስተ ቤቱ ወኢየአ ምር እንከ መካኖ ።

ወደ ቤቱ አይመለስም፣ ቦታ ውን በመኖር አያውቀውም ፡

፲፩፡ ወበእንተዝ አነሂ ኢይምህክ አፉየ፣

ስለዚህ እኔም ማረኝ ማረኝ ማለ ትን አልተውም ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወአነብብ ሃዕረ መንፈስየ ወእከሥት ምሬረ ነፍስየ ዘላዕሌየ ፤

የሰውነቴን መከራ የልቡናዬን ኀዘን ገልጬ እናገራለሁ ፤

ከመ ባሕር ኮነ አንብዕየ ፤

እንባዬ እንደ ባሕር ሆነ ፤

፲፪፡ ባሕርኑ አነ ወሚመ ቀላይ ፤

እኔ ባሕር ነኝ? ወይስ ወንዝ ነኝ፤ ባሕር ወንዝ ማዕበሉን፤ ሞገዱን ይችላል እንደዚያ መከራውን እችለዋለሁን ፤

እስመ አዘዝከ ዓቃቤ ላዕሌየ ፤

አምጻእከ ሲል ነው ፤ ደዌ አምጥተህብኛልና ፤

፲፫፡ እቤ አራትየኑ እንጋ ይናዝዘኒ፤

አልጋዬ ያረጋጋኝ ይሆን እንጃ አልሁ፤ ወያልሕየኒኑ ምስካብየ፤ ምኝታዬ ያሳርፈኝ ይሆን፤ አን ድም ወያልሕበኒሁ ይላል፤ ምኝ ታዬ ያልበኝ ይሆን ደርበው ደራ ርበው ያለብሱታል አይሞቀው ምና ፤

፲፬፡ ወትጌርመኒ በሕልም ፤

በሕልም ታስፈራኛለህ፤ ብሔሞ ትን የላከው እሱ ነውና፤ ወታደ ነግፀኒ በራእይ በነጽሮተ አጋን ንት ታስደነግጠኛለህ ፤

፲፭፡ ወኮነ ሥልጣን ለነፍስየ እመን ፈስየ፤

ከነፍሴ ለሥጋዬ ሥልጣን ተሰ ጠው፤ ቀድሞ ነፍስ እለይ እለይ ትል ነበረ፤ ዛሬ ግን ሥጋው እለይ እለይ ትላለችና፤ አንድም፡ ወኮነ ሥሉጠ ይላል፤ ዲያብሎስ በነፍስ በሥጋዬ የሠለጠነ ሆነ፡ በሥጋው ደዌ አምጥቶበታል፡ በነፍሱ ባርኮ ለእግዚአብሔር ብሎታልና፤

ወአ ሞቶን ለአዕይንትየ ፤

ዓይኖቼንም በዕንባ አፈሰሳቸው ዕንባ፤ አንድም ደዌ ሥጋ ዓይን ያጠፋልና ፤

ቦኑ ለዓለም አሐዩ ከመ እትዓገሥ ፤

መከራውን እታገሥ ዘንድ በውኑ ለዘለዓለም እኖራለሁ ? ፤

ርኅቀ እምኔየ ከንቱ ውእቱ ሕይወ ትየ ፤

ከንቱ የሚሆን አኗኗሬ ጠፋ፡ አንድም ረድኤቱ ከኔ ራቀ፡ አንድም እምሕይወትየ ሕይወቴ ከእግዚአብሔር ራቀ ፤

፲፯፡ ምንትኑ ውእቱ ሰብእ ከመ ታዕብዮ ፤

ሰውን ታከብረው ዘንድ ምንድ ነው ፤

ወከመ ተሐውፆ ልቦ ፤

ልቡናውን ትመረምረው ዘንድ፡

፲፰፡ አው ከመ ትቀህዮ እስከ ይበጽሕ ኀቤከ ፤

ከእግዚአብሔር ጋራ በተከራከ ርሁ እስቲል ድረስ፤ አንድም በረ ድኤት ወደ አንተ እስቲመጣ ድረስ ፤



አው ከመ ትኩንኖ በውስተ አራቱ፤

በደዌ ዳኛ፤ በአልጋ ቁራኛ ይኑር ብለህ ትፈርድበት ዘንድ ሰው ምንድን ነው ፤

፲፱፡ እስከ ምንትኑ ኢታሴሕተኒ ፤

የማታማርፈኝ ምን እስቲሆን ድረስ ነው? አንድም እስከ ማዕ ዜኑ፤ የማታሳርፈኝ እስከ መቼ ድረስ ነው ? ፤

እስከ እውህጥ ምራቅየ እንዘ የሐን ቀኒ ፤

ምራቄን እስክውጥ ድረስ ሲያን ቀኝ ነው? ፤ አንድም ሲያንቀኝ ምራቄን እስክውጥ ድረስ ነው?፤

፳፡ ወእመሂ አነ አበስኩ ምንተ እንከ እክል ገቢረ ለከ ፤

ብበድልስ ለአንተ ምን ማድረግ ይቻለኛል ፤

አ ዘተአምር ልበ ዕጓለ እመሕያው ለምንት ረሰይከኒ ለመቅሠፍት ለከ፤

የሰውን ልቡና መርምረህ ለምታ ውቅ ለአንተ ስገዛ በከንቱ ለመ ከራ ለምን ሰጠኸኝ ? ፤

ወለምንት ፈጠርከኒ በአምሳሊከ ፤

ንግበር ሰብአ ብለህ በአንተ አም ሳል ለምን ፈጠርኸኝ ?

አነሁ ዳዕሙ ከበድኩከ ፤

ብዙ ኃጥአን በዚህ ዓለም ይኖ ራሉ፤ ከብዙ ኃጥአን እኔ በዛኁ ብህ ? ፤

፳፩፡ ወለምንት ኢገበርከ በዘይትረሳእ ኃጢአትየ ፤

ኃጢአትስ ብሠራ ኃጢአቴ እን ዲዘነጋልኝ ለምን ያላደረግህ?፡

ወበዘይነጽሕ ጌጋይየ ፤

እምጌጋይየ ሲል ነው፡ ከኃጢ አቴ በምንጻ ገንዘብ ፤

ወይእዜሰ እወርድ ውስተ ምድር ኀበ ኢይነቅሕ እንከ ፤

ዛሬ ግን ወደማልመለስበት ወደ መቃብር እወርዳለሁ ።

## ምዕራፍ ፰

ስምንተኛው ምዕራፍ ይህ ነው፡

ጉባዔ

፩፡ ኀበ ተናገረ በልዳዶስ አውኬናዊ ወይቤ ፤

አውኬናዊ በልዳዶስ ከተናገረ ዘንድ እንዲህ አለ ፤

፪፡ እስከ ምንትኑ ትነብብ ከመዝ መንፈሰ ነቢብኑ ውስተ አፉከ ፤

ምን እስቲሆን ድረስ ትናገራለህ፡ አንድም እስከ ማዕዜኑ ይላል፤ እስከ መቼ ድረስ ትናገራለህ፤ ቀባጥር ቀባጥር የሚል ጋኔን አድ ሮብሃል? አንድም እውቀትህ በአ ፍህ ነው እንጂ በልብህ የለምን፤

፫፡ ቦኑ እግዚአብሔር ይኄንን በዓመፃ፤

ያለ ኃጢአቴ አመጣብኝ ይላልና በውኑ እግዚአብሔር ያለ ኃጢ አት በሐሰት ይፈርዳልን ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወፈጣሬ ኵሉ የሀውኮኑ ለጻድቅ ፤

ሁሉን የፈጠረ እግዚአብሔር ጻድቁን በመከራ ያውከዋልን፤

፬፡ እመሰኬ ደቂቅከ አበሱ ቅድሜሁ ወፈነወ በእንተ ኃጢአቶሙ ፤

ልጆችህ በፊት በድለው እንደ ሆን ስለ ኃጢአታቸው ፍዳውን አመጣባቸው፤ እንድም በኃጢ አታቸው ፍዳውን አምጥቶባ ቸው እንደሆን ፤

፭፡ ወአንተሰ ጊሥ ኀበ እግዚአብሔር ወጸሊ ፤

አንተ ግን በጸሎት ወደ እግዚ አብሔር ገሥግሥ ለምን፤

፮፡ እመ ጻድቅ ወንጹሕ አንተ ይሰም ዓከ ስዕለተከ ፤

አንተ ጻድቅ ንጹሕ ከሆንህ ልመ ናህን ይሰማሃል ፤

ወየዓሥየከ ፍጡነ ፍዳ ጽድቅከ ፤

የምግባርህን ዋጋ ፈጥኖ ይሰጥ ሃል ፤

፯፡ ወአመ ውሁድ ቀዳሚትከ አልቦ ኍልቈ ለደኃሪትከ ፤

የቀደመው ገንዘብህ ጥቂት ኖሮ እንደሆን ኋላ የሚሰጥህ ገንዘብ ቊጥር ስፍር የለውም፤ አንድም የቀደመው ዘመን ተድላ አንሶህ እንደሆን ኋላ የሚሰጥህ ዘመን ተድላ ቊጥር ስፍር የለውም ፤

፰፡ ወከመዝ ይብል ኢዮብ ይትከሃለ ኒኑ እዕርግ ሰማየ ወእስርቅ መዛግብ ቲሁ ወዕመቀ ምድር፤

ኢዮብ ወደ ሰማይ ወጥቼ ወር ቁን፤ ብሩን፤ ወደ ጥልቅ ምድር ወርጄ ኀታውን፤ ኀተራውን እወ ስድ ዘንድ ይቻለኛል? አለ ብሎ ከጌታ ጋራ ያጣላዋል፤ የወታደር አነጋገር ነው ፤

ከማሁ ተሰዓሎሙ ለቀደምት አበው፤

አሁን እንደተናገርሁት ከአንተ አስቀድመው የነበሩትን አእሩግ የጻድቃንን የኃጥአንን ዜና ጠይ ቃቸው ፤

ወሕትቶሙ ለአበው በበሕዘቢሆሙ፤

በየወገናቸው አበውን መርምራ ቸው ፤

፱፡ ዛሬት ንሕነ ወኢነአምር ፤

እኛ እንደ ሸረሪት ወተር ነን፤ እንኖር እንሞት አናውቅም ፤

ወጽላሎት ውእቱ ሕይወትነ በዲበ ምድር ፤

አኗኗራችን በዚህ ዓለም እንደ ጥላ ነው፤ ጥላ ጥዋት ይረዝማል ማታ ያጥራል ፤

፲፡ ወእሙንቱ ይሜህሩከ ወይነግሩከ፤

እኒህ ያስተምሩሃል ይነግሩሃል፤

ወያወጽኡ ለከ ነገረ እምልቦሙ ፤

ነገሩን ከልቡናቸው አውጥተው ይነግሩሃል ፤



፲፩፡ ይበቊልኑ ዛዕር ዘእንበለ ማይ ወይልሕቅኑ ሐመልማል ዘእንበለ ይስ ቅይዎ ፤

አልተማርሁምና ተሠዓሎሙ ትለኛለህ ትለኝ እንደሆነ፤ ዛር ያለ ውሀ ይበቅላል? ተክልስ ውሀ ሳያጠጡት ይለመልማል? አንተስ ሳትማር ማወቅ ይቻልሃል ?

፲፪፡ ወእንዘ ሀሎ ውስተ ሥርው ዘእ ንበለ ይግምድዎ ኵሉ ዛዕር ዘኢይ ሰቲ ማየ ይየብስ ፤

ውሀ የማይጠጣ ዛር ሁሉ ከሥሩ ጋራ ሳለ እንዲደርቅ አእምሮ ጠባይዕ ቀንቶለት ሳለ አእምሮ ጠባይውን አጥሞ የማይማር ሰው እንዲጠፋ ፤

፲፫፡ ከማሁ ደኃሪቶሙ ለኵሎሙ እለ ይረሥዕዎ ለእግዚአብሔር ፤

እንደዚህም ሁሉ ክፉ መልካም ለይተው የሚያውቁበት ዕውቀት ተሰጥቷቸው ሳለ እግዚአብሔ ርን የሚዘነጉ ሰዎች ይጠፋሉ ፤

ወትጠፍእ ተስፋሆሙ ለረሲዓን ፤

ሕገ እግዚአብሔርን የዘነጉ ሰዎች አለኝታቸው ትጠፋለች፤

፲፬፡ ምዝቡር ውእቱ ቤቱ ወዛሬት ይከውኖ ማኅደሮ ፤

ቤቱ ማኅደሩ አንድ ወገን ነው፤ ቤቱ የፈረሰ ይሆናል፤ አንድም ማደሪያው የሸረሪት ወተር ይሆ ናል ፤

፲፭፡ ወእመሂ አፅንዖ ለቤቱ ኢይቀ ውም ፤

ቤቱን በከብት ላይ ከብት ጨምሮ ቢያጸናው አይፀናም፤

ወዘወጠነሂ ኢይፌጽም ፤

የጀመረውን መንግሥት አይፈ ጽምም ፤

፲፮፡ ወሰሕቡብ ውእቱ ቤቱ በታሕተ ፀሐይ ፤

ወዛሬት ይከውኖ ማኅደሮ ብሎ ነበርና ከፀሐይ በታች ያለ ቤቱ ይሻግታል ማለት የተፈታ ይሆ ናል ፤

ወውስተ ገነቱ ልምላሜሁ ይየብስ፤

በተክሉ ውስጥ ያለ ልምላሜው ይደርቃል ማለት ተድላው ደስ ታው ይጠፋል ፤

፲፯፡ ወበእከዩ የኀልቅ ኃይሉ ፤

በክፋቱ ኃይሉ ይደክማል፤ አን ድም ባለጸግነቱ ይጠፋል፤

ወማዕከለ ያላዕት ይበይት ፤

ወወጽአ አፍአ ብሎ ነበርና በሣ ጥን ይኖራል ፤

ወውስተ ሐዝሐዝ የሐዩ ፤

በእዝኅ ረግረግ ተውጦ ይኖራል፤

፲፰፡ ወእመሰ ውህጠ ምድር ወሐሰዎ ኢርኢኩ ዘከመዝ ፤

አገር የተቀበለው እግዚአብሔርን የካደው እንደ አንተ ያለ አላየ

www.ethiopianorthodox.org

ሁም፤ አንድም መቃብር ከተቀበለው በኋላ ያዳነው እግዚአብሔርን የካደው እንደ አንተ ያለ አላየሁም ፤

እስመ ከማሁ ይትገፈትዑ ረሲዓን፣

ሕገ እግዚአብሔርን የዘነጉ ሰዎች አሁን እንደ ተናገርሁት ይጠፋሉ፤ አንድም እንዲህ ይጠፋሉና ፤

፲፱፡ ወካልዕ ይበቍል እምድር ፣

በዚህ ዓለም እሱ ሙቶ ሌላ ይነግሣል ፡

፳፡ ወእግዚአብሔርሰ ኢይገድፎ ለየዋህ ፣

እግዚአብሔር ግን ደጉን ሰው በመከራ አይጥለውም ፤

ወኢያፀንዕ እደ እኩያን ፣

የኃጥአንን የክፉዎችን ሰዎች ሥልጣን አያፀናም ፡

ወኢይትሜጠ መባዓ ኃጥአን ፣

የኃጥአንን መባ አይቀበልም ፤ አንድም የኃጥአንን ጸሎታቸውን አይቀበልም ፤

፳፩፡ ወአፈ ራትዓን ይመልዕ ሰሐቀ፣

ወሰሐቅሙ ብሎ ነበርና እውነት ነው፤ የቅኖች ሰዎች አፋቸው ደስ ይለዋል ፤

ወየአንግግ ከናፍሪሆሙ ፣

ይየብባ ሲል ነው፣ ከንፈሮቻቸውም ያመሰግናሉ፤

ወጸላዕቶሙሰ ይለብሱ ኀፍረተ ፣

ጠላቶቻቸውም ኃፍረት እንደ ልብስ ይለብሳሉ ፤

ወይጠፍዕ ቤተ ኃጥአን ፣

የኃጥአን ወገን ይጠፋል ።

## ምዕራፍ ፱

### ዘጠነኛው ምዕራፍ ይህ ነው፤

### ገባዔ

፩፡ ወአደ ተናገረ ኢዮብ ተሰጥወ ወይቤ ፣

ኢዮብ ከተናገረ ዘንድ እንዲህ አለ፤ አንድም ሲገባው ሲመልስ እንዲህ አለ ፤

፪፡ አማን አአምር ከመ ከመዝ ውእቱ ፣

እውነት ነው፤ ኃጥእ እንዲጠፋ ጻድቅ እንዳይጠፋ አውቃለሁ፤

ወእፎ ይከውን ንጹሐ በቅድመ እግዚአብሔር ፣

ጻድቅ ነኝ፣ ንጹሕ ነኝ የሚል ሰው ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት እንደምን ጻድቅ፣ ንጹሕ ይሆናል፡



፫፡ ወእመሂ ፈቀደ ይትዋቀሥ ኢይሠጠዎ አሐተ ቃለ እም ፻ ፣

ሰው ከእግዚአብሔር ሊከራከር ቢወድ ከሰው እልፍ ውርድ እግዚአብሔር አንድ ጭብጥ ቃል አይመልስለትም፣ ነገሩን ይንቅበታል፡ አንድም ሰው ከእግዚአብሔር ጋራ ሊከራከር ቢወድ ከእግዚአብሔር እልፍ ውርድ ሰው አንድ ጭብጥ ውርድ ቃል መመለስ አይቨንለትም ፡

፬፡ ጠቢበ ምክር ውእቱ ወዐቢየ ኃይል ፣

ምክር አዋቂ ይባላል፣ ገናና ኃያል ይባላል ፡

መኑ ውእቱ እኩየ ከዊኖ ዘቆመ ቅድሜሁ፣

ክፉ ሆኖ በፊቱ የቆመ ማነው? ሰብአ ትካትን፣ ሰብአ ሰዶምን ናቸው ?

፭፡ ዘያንቀለቅሎሙ ለአድባር ወኢየሬእይዎ ፣

ተራሮችን የሚያነዋውጣቸው እሱ ነው፡ በምን ኃጢአታችን ነው አይሉትም፡ አንድም ነገሥታቱን የሚያነዋውጣቸው እሱ ነው ፡ ረቂቀ ባሕርይ ነው ፡ ሲያጠፋ አይታይም ፡

ወይገፈትዖሙ በመዓቱ ፣

ተቆጥቶ የሚያጠፋቸው እሱ ነው ፡

፮፡ ወያድለቀልቃ እመሠረታቲሃ ለምድር ፣

ምድርን ሥር መሠረቷን የሚያነዋውጣት እሱ ነው ፡

፯፡ ወለሰማይ የሀውኮን ለአዕማዲሃ፣

አዕማዲሃ ለሰማይ ሲል ነው፡ እሉእሙንቱ አእማደ ሰማይ፣ የሚላቸውን የሚያሳልፋቸው እሱ ነው ፡

፰፡ ወየሐውር መልዕልተ ባሕር ከመ ዘዲበ ምድር ፣

በምድር ምሉዕ እንደሆነ በባሕር ምሉዕ ነው፡ አንድም ፴፫ ዓመት በምድር ላይ እንደሔደ በባሕረ ጥብርያዶስ ሔደ ፡

ዘሰፍሖ ለሰማይ ባሕቲቱ ፣

ሰማይን ብቻውን የዘረጋው እሱ ነው፡ አንድም ያለ ምሰሶ ያፀናው እሱ ነው ፡

፱፡ ዘይብላ ለወርኅ ኢትሥርቂ ፡

ጨረቃን በጠፍ ጊዜ እንዳታበራ የሚያደርጋት፡ አንድም የሚያሳልፋት እሱ ነው ፡

ወገጸ ከዋክብት የሐትም ፣

ከዋክብትን የፈጠረ፡ አንድም ከዋክብትን የሚያሳልፋቸው እሱ ነው ፡

ዘገብሮ ለትርያ ወአስተጋብአ ፣

ዓቢይ ኮከብን የፈጠረ፣ ገንዘብ ያደረገው እሱ ነው ፡

www.ethiopianorthodox.org

ወለደብራንሂ ፣

ንዑስ ኮከብን የፈጠረው እሱ ነው፤ አንድም ዘገብሮ ለትርያ ፈጣን ኮከብን የፈጠረ እሱ ነው ወለደብራንሂ፣ ዳተኛ ኮከብን የፈ ጠረ እሱ ነው፤ አንድም ዘገብሮ ለትርያ፣ የአጥቢያ ኮከብን፣ አስ ታርቦሽሽ ኮከብን የፈጠረ እሱ ነው፤ አንድም ዘገብሮ ለትርያ እነሦስቶን፣ ወለደብራንሂ እነስ ድሰቶን የፈጠረ እሱ ነው፤

ወይኄልቆሙ ለከዋክብተ ጽባሕ ፣

በምሥራቅ ያሉትን ከዋክብት የሚቆጥራቸው እሱ ነው ፤

፲፡ ዘይገብር ዓቢያተ ዘአልቦ ኍልቈ፣

ቍጥር ስፍር የሌለው ድንቅ ድንቅ ሥራ የሚሠራ እሱ ነው፤

፲፩፡ እመሂ ተዓደወኒ ኢይሬእዮ ፣

ከወደ ኋላዬ መጥቶ ቀድሞኝ ቢሔድ አላየውም ፤

ወእመኒ ኀለፈ ኢየአምሮ ፣

ከወደፊቴም መጥቶ አልፎኝ ቢሔድ አላውቀውም ፤

፲፪፡ ወእመኒ ውእቱ አዕተተ መኑ ያገብዕ ፣

እሱ በሞት ቢያርቅ በሕይወት የሚመልስ ማነው፤

ወመኑ ዘይብሎ ምንተ ገብርከ ፣

ምን አደረግህ የሚለው ማነው? አንድም ማን ብሎ ፤

፲፫፡ ወእግዚአብሔር ውእቱ ኢተመ ይጠ እመቅሠፍትየ ፣

ኦ... እግዚአብሔር በኔ መከራ ከማምጣት አልተመለሰም ፤

ወእምኔሁ ተቀጽዑ አናምርት ዘበታ ሕተ ሰማይ ፣

ከሰማይ በታች ያሉ ብሂሞት ሌዋታን በሱ ትእዛዝ ተወሰኑ፤

፲፬፡ እፎኬ ይሰምዓኒ ቃልየ ወይፌ ክሮ ፣

ውርድ የሚነዛ ጭብጥ የሚመ ልስ ማነው ፤

፲፭፡ ወእመሂ ጸዋዕኩ በጽድቅ ወኢይ ሰምዓኒ እስዕል ፍትሐ ዚአሁ፣

በእውነት ብለምነው ባይሰማኝ ቸርነቱን እለምናለሁ እንጂ ሌላ ምን አደርጋለሁ ?

፲፮፡ ወእመኒ ጸዋዕኩ ወአውሥአኒ ኢየአምን ከመ ሰምዓኒ ፣

ብለምነውም ቢሰማኝ በምግባሬ እንደ ሰማኝ አላምንም ፤

፲፯፡ ዓውሎሁ ይቀጠቅጠኒ ፣

እሱ አጠፋኝ እንጂ ማን አጠ ፋኝ? አንድም ረቂቅ መቅሠፍቱ አጠፋኝ እንጂ ማን አጠፋኝ ? ወመጽአ ነፋስ ብሎ ነበርና ፤



፲፰፡ ወብዙኃ አቍሰለኒ በከንቱ ወኢ ኀደገኒ ከመ አዕርፍ ፣

በከንቱ ኃጢአቴ ብዙ መከራ አመጣብኝ፣ ከመከራው አርፍ ዘንድ አልተወኝም ፤

ወአጽገበኒ ኀምዘ ፣

ኀምዘ መዓቱን አጠገበኝ ፤

፲፱፡ እስመ ዕኑዓ ይእኀዝ መኑ ይት ቃወማ ለኰነኔሁ ፣

አያያዘ ዕኑዕ ነውና ፍርዱን የሚ ቀዋወማት ማነው ?

ወእመሂ አመፀ አፉየ እምጽድቅ ፣

አፌ ከእውነተኛው ሕግ ወጥቶ ቢበድል ፤

ወእመሂ አሕፀፅኩ ዕፁብ ይረክበኒ፣

ሕገ እግዚአብሔርን ባፈርስ ጭንቅ መከራ ያገኘኛል፤ አንድም ዕፁፍ ይላል፣ ዕፅፍ መከራ ያገኘ ኛል ፤

፳፡ ንጹሕ አነ ወኢየአምር ነፍስየ ፣

እኔ ንጹሕ ነኝ፣ ሰውነቴ የምት ሠራውን አላውቅም፤ አንድም እንዳዒ ለነፍስየ ይላል፣ ሰውነቴ የምትጠራጠርበት ዕዳዋን አላ ወቅሁትም ፤

ዳዕሙ ጠፍአት ሕይወትየ ፣

አነዋወሬ ጠፋች እንጂ ፤

፳፩፡ ወባሕቱ እቤ ዓቢይ ወኃያል ይፌኑ መቅሠፍተ ፣

ነገር ግን ገናና ኃያል የሚሆን እሱ መቅሠፍትን ያመጣል ፤

እስመ እኩይ ሞቶሙ ለኃጥአን ፣

የኃጥአን ሞታቸው ጽኑዕ ነውና፤

ወይስሕቅዎሙ ለጻድቃን ፣

ከዚህ አስቀድሞ በጻድቃን ይዘብ ቱባቸዋል ፤

ወይገብዑ ውስተ እደ ኃጥአን ፣

ጻድቃን በኃጥአን እጅ ይወድ ቃሉ ፤

ወይከድንዎ ገጸ መደልዋን ፣

ግብዞች ኃጥአን ምድርን በብዛት በኃጢአት ይሸፍኗታል ፤

ወለምንትኑ አነ ፣

እኔ ምንድን ነኝ? ከመሠወራ ቸው ወይስ ከብዛታቸው ነኝ ?

፳፪፡ ወሕይወትየኒ ትቀልል እምረ ዊፀ እለ አምሠጡ ወኢይረክቦሙ እንከ ፣

ከመ ዘአምሠጡ እምረዋዕያን ኮነት ሕይወትየ ሲል ነው፤ ሰው ነቴ ከአዳኞች ከአመለጡ ከሚ ዳቋ፣ ከፌቆ ይልቅ ትቀላለች፣ እንግዲህ ወዲህም እንደማላገ ኛቸው ፤

፳፫፡ ወእመቦ ሐመር አሠረ ፍኖቱ ኢይትአመር ፣

በባሕር የሚሔድ መርከብ የሔ ደበት እንዳይታወቅ ፤

www.ethiopianorthodox.org

አው ንስር ዘይሠርር ወየኀሥሥ ዘይ በልዕ ፣

የሚበላውን የሚሻ በአየር የሚ ሔድ አሞራ የሔደበት ፍለጋው እንዳይታወቅ፣ ከማሁ ኮነት ሕይ ወትየ ወጠፍአት አኗኗሬ እንደ ዚህ ጠፋች ፡

፳፯፡ ወእመሂ ነበብኩ አልቦ ዘይበ ቍዕ ፣

ብናገርም የሚረባኝ የሚጠቅመኝ የለም ፡

ወድቀ ገጽየ በገዓር ፣

ገጸ ልቡናዬ አዘነ ፡

ወአንቀልቀሉ ኵሉ መለያልይየ ፣

ሕዋሳቶቼ ሁሉ በመከራ ተነዋ ወጡ ፡

አእመርኩ እንከሰ ከመ ኢየኀድገኒ ከመዝ ፣

እንግዲህ ወዲህስ በመከራ እን ዳይተወኝ እንዲያድነኝ አወቅሁ፡

፳፱፡ እመሰኬ ኃጥዕ አነ ለምንት ኢሞትኩ ፣

ኃጥእ ነህ ይሉታልና ኃጥእስ ብሆን ለምን ያልሞትሁ ?

፴፡ እመኒ ተሐፀብኩ ወነጻሕኩ ከመ በረድ ፣

በማየ ንስሐ ታጠብሁ ፣ እንደ በረድ ነጻሁ ባልሁ ጊዜ ፡

፴፩፡ ወአንጻሕከኒ አደውየ በሕቁ ትጠ ምዓኒ ውስተ ርስሐት ፣

ቃሌን ከመበደል እጄን ከመግ ደል አነጻሁ ባልሁ ጊዜ ፈጽሞ ኃጢአተኛ /አደፈኛ/ ተባልሁ፣ አንድም መከራ ተቀበልሁ ፡

ወአስቆረረኒ ልብስየ ፣

ልብሴ ተጸየፈኝ ማለት ልብስና ቁስል አይስማማምና፡ አንድም ልቡናዬ ተጸየፈኝ ፡

፴፪፡ ሰበኡ ሰብእ ውእቱ ዘይትዋ ቀሰኒ እምሐርነ ውስተ ዓውድ ፣

መከራ አምጥቶ የሚከራከረኝ ሰው ቢሆን ወደ አደባባይ ብን ሔድ ?

፴፫፡ ወሰበሁ ቦ ኅሩይ ዘይፈትሕ ለነ፣

የሚፈርድልን የተመረጠ ዳኛ ቢኖር፡ አንድም ዕሩየ ይላል፣ አስ ተካክሎ የሚፈርድ ዳኛ ቢኖር?

ወያጸምዕ ማዕከለ ፪ኤነ ፣

ሁለታችንን ቢሰማን ?

እምተአተተ ዘንተ በትር እምኔየ ፣

ይህ ደዌ ለኢዮብ አይገባውም አስኝቼ በእግዚአብሔር ባስፈረ ድሁበት ነበር፡ መከራውም ከኔ በራቀ ነበር ፡

፴፬፡ ወእምኢመጽአኒ ግርማሁ ፣

ግርማ መዓቱም ባልመጣብኝም ነበር፡ አንድም ወእምኢፀብዓኒ ግርማ መዓቱ ባላጠፋኝም ነበር፡



፴፭፡ ወእነግር እንከ ወኢይፈርሆ ፣

ግፌን መናገር አልፈራም፡ ወአ ልቦ ዘአአምር በዘትዔዓር ነፍስየ ሰውነቴ በምትጨነቅ ገንዘብ የምትጨነቅበትን አላውቅም ።

## ምዕራፍ ፲

አሥረኛው ምዕራፍ ይህ ነው፣

፩፡ በዘትዔዓር ነፍስየ እምዕውብ አወ ሥእ ቃልየ ፣

ሰውነቴ በምትጨነቅበት ገንዘብ በጭንቅ እናገራለሁ ፡

ወእነብብ እንዘ ትጠወቅ ነፍስየ መሪረ ፣

ሰውነቴ በመከራ እየተጨነቀች እናገራለሁ ፡

፪፡ ወእብሎ ለእግዚአብሔር ኃጥአ ኢትምሐርኒ ወለምንት ከመዝ ኰነንከኒ፣

እግዚአብሔርን ኃጥእስ ብሆን አትምረኝም? ሳልበድል ለምን ፈረድህብኝ እለዋለሁ ፡

፫፡ ይኄንየከሁ እመ አበስኩ ፣

ብበድል ይሻልሃልን ሳልበድል መከራ ያመጣህብኝ፡ አንድም ሠናይኑ፣ ብበድል ይሻልሃልን መከራ ሲፀናበት ይበድላልና ፡ አንድም ሠናይኑ ሰብ ትገፍዕ ገፋዒ፣ ብትባል ይሻልሃልን ፡

እስመ ፣ ተሐየይከ ተግባረ እደዊከ ወነጸርከ ምክረ ረሲአን ፣

የሰይጣንን ምክር ሰምተህ የእ ጅህ፣ የቃልህ ፍጥረት የምሆን እኔን ቸል ብለኸኛልና ፡

፬፡ ቦኑ ዓይነ ሰብእ ለከ ፣

በውኑ የሰው ዓይን አለህ ?

ወከመ መዋቲ ትኔጽር ወትሬኢ ፣

እንደ ሰው አስተያየት ታያለህን ሰው በዓይን ጥቅሻ፣ በከንፈር ንክሻ ጠላቱን ይጎዳል ፡

፭፡ ወመዋዕሊከኒ ከመ ዘ ሰብእኑ ውእቱ ፣

ዘመንህስ እንደ ሰው ዘመን ነውን ሰው ሳይቀድመኝ ልቅደመው ይላል ፡

ወዓመቲከኒ ከመ ዘዕጓለ እመሕያው፣

ዘመንህስ እንደ ሰው ዘመን ነውን ሰው ዛሬ ሳጥፋው እንጂ ኋላማ እሞት የለም ይላል፡ አንተም እንደዚያ ነህን፡

ከመ ትኅሥሣ ለኃጢአትየ ወትሕትት ጌጋይየ ፣

ኃጢአቴን፣ በደሌን ትሻ ትመ ረምር ዘንድ ፡

፯፡ ተአምር ከመሰ ኢአበስኩ ፣

እንዳልበደልሁስ ታውቃለህ ፡

ወባሕቱ መኑ ውእቱ ዘያመስጥ እምደኪ ፣

ነገር ግን ከሥልጣንህ የሚያመ ልጥ ማነው ፡

www.ethiopianorthodox.org

፰፡ እደዊከ ፈጠራኒ ወገብራኒ ፤

አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ በነ
ፍስ በሥጋ ፈጠሩኝ፤ አንድም
ፈጠራኒ በነፍስ በሥጋ፣ ገብራኒ
ገንዘብ አደረጉኝ ፤

ወእምዝ አፍለስከኒ ወነጸሕከኒ ፤

ከዚህ በኋላ በደዌ ለወጥኸኝ በመ
ከራ ጣልኸኝ ፤

፱፡ ተዘከር ከመ እምዕቡር ፈጠርከኒ
ወታገብዓኒ ካዕበ ውስተ መሬት ፤

ከመሬት፤ አንድም ከአዳም እንደ
ፈጠርኸኝ ዳግመኛ ወደ መሬት
እንድትመልሰኝ አስብ ፤

፲፡ ወከመ ሐሊብ ሀለብከኒ ወከመ
ግብነት አርጋዕከኒ ፤

እንደ ወተት አለብኸኝ፣ እንደ
እርጎ አረጋኸኝ ማለት ከዚህ
ቀድሞ ካባቴ አብራክ ወደ እናቴ
ማኅፀን እንድጣል አደረግኸኝ፤

፲፩፡ ወአልበስከኒ ሥጋ ወማዕሰ ፤

ሥጋ ቁርበት አለበስኸኝ፣ በነፍስ
መደብ ቁሞ እንዲህ አለ ፤

ወአሠርከ በአሥራው አዕዕምትየ ፤

አጥንቴንም በአሥራው አፀናህ፤

፲፪፡ ወወሀብከኒ ሣህለ ወምሕረተ ፤

በናቴ ማኅፀን ይቅርታን፣ ቸርነ
ትን ሰጠኸኝ ማለት እናቴ የበላ
ችው ተጭኖ፣ የጠጣችው እንገዘ፣
እንዳይገድለኝ አደረግኸኝ ፤

ወሐውፆትከ ዐቀበኒ መንፈስየ ፤

በረድኤት መጐብኘትህ ሰውነ
ቴን ጠበቀኝ ፤

፲፫፡ ወዝንቱ ኵሉ በኀቤከ ሀሎ አእ
ምር ከመ ኵሎ ትክል ፤

እንዲህ አድርጎ መጠበቅ ከአንተ
ዘንድ አለ፣ ዛሬም ብትጠብቀኝ
ይቻልሃል፤ አንድም ይህ የአካሌ
መቆረጥ ከአንተ ዘንድ አለ፣ አሁ
ንም ብታድነኝ ይቻልሃል፤ አን
ድም ይህን ሁሉ መከራ ኋላ
በሥጋ ትቀበለዋለህ ፤

ወአልቦ ምንትኒ ዘይስአነከ ፤

ምንም ምን የሚሳንህ የለም ፤

፲፬፡ ወሶበሂ አበስኩ እምአይቀብከኒ፤

ብበድልስ ባልታገሥኸኝም ነበር፤

ወእምኢአንጻሕከኒ እምኃጢአትየ ፤

ኃጢአትስ ብሠራ ባላነጻኸኝም
ነበር ፤

፲፭፡ ወእመሂ አበስኩ አሌ ሊተ ፤

አልበደልሁም እንጂ ብበድልስ
ለኔ ወዮልኝ እንጂ አንተ ምን
ትጎዳለህ ?፤

ወእመሂ ጸደቁ ስዕንኩ አንቃዕድዎ፤

እውነተኛ ሆንሁ ባልሁ ጊዜ ወደ
አንተ አቅንቶ ማየት ተሳነኝ ፤

ጸገብክዋ ለኃሣር ፤

መከራን ጠገብኋት ፤



፲፮፡ ከመ አንበሳ ዘተሠግረ ወዘተ
ቀትለ ዘኢይትነከር ከማሁ ኮንኩ ፤

በወጥመድ የተያዘ፣ የሞተ አን
በሳ እንዳይደነቅ፣ እኔም እንደ
ዚያ ሆንሁ፤ ምን አንክሬ እንዲሉ፤

ወካዕበ ተአትተኒ በሞት ወበሕቁ
ትጠስየኒ፤

ዳግመኛ በሞት ታርቀኛለህ ፤
ፈጽመህ ታጠፋኛለህ ፤

፲፯፡ ወእምጥንቱ ካዕበ ተሐትተኒ ፤

ዳግመኛ ከጥንቱ ጀምሮ ትመ
ረምረኛለህ ማለት ከወዴት ነበ
ርህ፣ ምን አደረግህ ትለኛለህ፤

ወአምጻእከ ላዕሌየ ዓቢየ መቅሠፍተ
ወፈኖከ ላዕሌየ መንሱተ ፤

ላዕሌየና ላዕሌየ አንድ ወገን ፤
በኔ ላይ ጽኑዕ መቅሠፍት ጥፋት
አመጣህብኝ፤ አንድም መቅሠ
ፍት የልጆቼን ሞት ወመንሱት
የአካሌን ጥፋት አመጣህብኝ ፤

፲፰፡ ለምንት እንከ ኢሞትኩ ሶበ
ታወጽአኒ እምከርሠ እምየ ፤

እንዲህ ከሆነ ከናቴ ማኅፀን ባወ
ጣኸኝ ጊዜ ለምን አልሞትሁ ፤

ወኢትርአየኒ ዓይን ፤

ዓይን ከታየኝ፤ አንድም ዓይን
እንዳታየኝ ፤

ወእኩን ከመ ኢተፈጠርኩ ፤

ስፈጠር፤ አንድም እንዳልተፈጠ
ርሁ ስሆን ፤

፲፱፡ ወለምንት ተፈጢርየ ውስተ
መቃብር ዘኢወረድኩ ፤

ከተፈጠርሁ በኋላ ወደ መቃ
ብር ለምን አልወረድሁ፣ ብወ
ርድ ይህ ሁሉ መከራ ባላገኘኝም
ነበር ፤

ወወጺእየ እምከርሥ ዘኢተነጉልኩ
ሰቤሃ ፤

ከናቴ ማኅፀን በወጣሁ ጊዜ ያን
ጊዜ ለምን አልሞትሁ፤ አንድም
ያን ጊዜ ብሞት ይህ ሁሉ መከራ
ባላገኘኝም ነበር ፤

፲፱፡ አኮኑ ውሑድ መዋዕለ ሕይወ
ትየ ኅድገኒ አዕርፍ ሕቀ ፤

በሕይወቴ የምኖረው ዘመን
ጥቂት ነውና ጥቂት አርፍ ዘንድ
ተወኝ ፤

፳፩፡ ዘእንበለ እሑር ኀበ ኢይገብዕ
ብሔረ ጽልመት ወቆባር ብሔረ ጽል
መት ዘለዓለም ኀበ አልቦ ብርሃን፣

ብሔረ ጽልመትና ብሔረ ጽል
መት አንድ ወገን፣ ብርሃን ወደ
ሌለበት ጨለማ፣ ጭጋግ ወደ
አለበት ወደ መቃብር ሳልሔድ፤

ወኢይሬዒ ብርሃነ ወሕይወተ መዋቲ፣

የሞተ ሰው ብርሃንን የማያይ
በት ሕይወትን የማያገኝበት ።

www.ethiopianorthodox.org

# ምዕራፍ ፲፩

## አሥራ አንደኛው ምዕራፍ ይህ ነው ፤

### ጉባዔ

፩፡ ወአደ ተናገረ ሳፍር አሜናዊ ወይቤ ፣

ሳፍር ከተናገረ ዘንድ መለሰ ፤ እንዲህ አለ ፤

፪፡ በከመ ብዙኀ ትነብብ ከማሁ ትሰምዕ ፣

አንተ እንደምትናገረው ያለ ብዙ ነገር ትሰማለህ ፤

በብዝኃ ነቢብከኑ ዘትጸድቅ ይመስለከ ፣

ነገር በማብዛት የምትረታኝ ይመስልሃል ? አንድም በነገር ብዛት የምትረታኝ ይመስልሃል፤

፫፡ ቡሩክ ዘይትወለድ እምአንስት ዘኅዳጥ መዋዕሊሁ ፣

ዘመኑ ጥቂት የሆነ ከሴቶች የሚወለድ ሰው ርጉም ነው፤ አንተም ርጉም ነህ ፤ አያ ? ምን ርጉም ነህ ? ምን ጥፉ ነህ ?

ኢታብዝኅ ነቢበ እስመ አልቦ ዘይትዋቀሠከ ፣

ሶበሁ ሰብእ ዘይትዋቀሰኒ ብሎ ነበርና የሚከራከርህ የለምና መቀባጠርን አታብዛ፤ አንድም እንዘ አልቦ፣ የሚከራከርህ ሳይኖር ነገር አታብዛ ፤

፬፡ ወኢትበል ንጹሕ አነ በምግባርየ ወጻድቅ አነ በቅድሜሁ ፣

ወእመኒ ተሐፀብኩ ወነጻሕኩ ብሎ ነበርና በሥራዬ ንጹሕ ነኝ በፊቱ ጻድቅ ነኝ አትበል ፤

፭፡ እፎመ ይትናገረከ እግዚአብሔር ወይከሥት ከናፍሪሁ ምስሌከ ፣

ከእግዚአብሔር ጋራ በተከራከርህ ያልህ እግዚአብሔር ከንፈሩን ገልጦ ከአንተ ጋራ እንደምን ይናገራል ?

ወይነግረከ ኃይላ ለጥበብ ፣

ዓለሙን እንደፈጠረ ውርድ ብትጠይቀው ጭብጥ እንደምን ይመልስልሃል ?

እስመ ዕፁፍ ውእቱ ዘላዕሌከ ፣

በአንተ ላይ ያለ መከራ ዕፅፍ ድርብ ነውና እንዲህ ትላለህ እንጂ፤ አንድም ዕፁብ ይላል፤ በአንተ ላይ ያለ ደዌ ጭንቅ ነውና ፤

፮፡ ሶበሁ ተአምር ከመ ረከበከ ዘይደልወከ እምኀበ እግዚአብሔር በኃጢአትከ ፣

ብታውቅስ ከእግዚአብሔር ታግኘህ ይህ መከራ በኃጢአትህ ነው፤ አንድም በኃጢአትህ ከእግዚአብሔር ታግኘህ መከራ የሚገባህ ነው፤ አንድም በኃጢአትህ ያገኘህ ይህ መከራ ከእግዚአብሔር ታግ ነው፤ አንድም



ይህ የመጣብህ መከራ በኃጢአትህ እንደሆነ ብታውቅስ ፤

ወአሠሮሂ ለእግዚአብሔር ትረክብ፣

አሠረ ፍትሑን ታውቃለህ፤ አንድም መከራ እንዳገኘህ ብታውቅስ አሠረ ባሕርዩን መርምረህ ታገኛለህ ፤

ሀሎከኑ ቀዲሙ አመ ይፈጥር ዓለመ ወልዑለ ሰማየ ወትሑተ ምድረ ፣

ከእግዚአብሔር ጋራ በተከራከርህ ያልህ ዓለምን፣ ሰማይን፣ ትሑት ምድርን በፈጠረ ጊዜ ኖረሃልን ፤

፯፡ ወምንተ ትሬሲ ፣

ምን ታደርግ ኑሯል ?

ወምንተ ተአምር ፣

እኛ የማናውቀው ምን ታውቃለህ ?፤

ዕመቃ ለቀላይ ፣

የቀላይ ጥልቅነቷን ምን ታውቃለህ? አንድም የቀላይ ጥልቅነቷን ምን ታውቅ ነበር? አንድም የቀላይን ጥልቅነት ታውቃለህን፤

፰፡ ወኑኃ ለሰማይ ፣

የሰማይ ምጥቅነቷን ?

ወስፍሐ ለምድር አውራኃባ ለባሕር፣

የምድርን ወርዷን፣ ቁመቷን፣ የባሕርን ስፋቷን ምን ታውቅ ነበር ? አንድም ምን ታውቃለህ ? አንድም የምድር ወርዷን የባሕር ስፋቷን ታውቃለህን ፤

፱፡ ወእመ ገፍትዖ ለኵሉ መኑ ምንተ ገበርከ ዘይብሎ ፣

ሁሉን ቢያሳልፈው ምን አደረግህ የሚለው ማነው፤ አንድም ማን ብሎ ፤

፲፡ እስመ ለሊሁ የአምር ግብረ ኃጥአን ወእመ ርእየ ዓመፃ ኢያረምም፣

የኃጥአንን ሥራ እሱ ያውቃልና ክፉ ነገርንም ቢያይ ከመፍረድ ዝም አይልም ፣

ወብእሲ ለባዊ ይሌብዎ ፣

አንተ ልብ ባታደርግ እኔ ልብ አደርገዋለሁ ፤

፲፩፡ ሰብእሰ ኃሣሤ ንባብ ውእቱ ፣

ሰውስ ነገር ፈላጊ፣ ነገር ወዳጅ ነው፣ አያ ምን ነገር ፈላጊ ነገር ወዳጅ ነህ ?

መዋቲ ዘይትወለድ እምአንስት ከመ አድግ ይመስለኒ ፣

ከሴቶች የሚወለድ ሟች ሰው አህያ ይመስለኛል ፣ አንተም አህያ ነህ ፤

፲፪፡ ወአንተሰ ትብል ንጹሕ ልብየ ወተዓቢ እዴከ ኀቤሁ ፣

አንተ ግን ልቤ ንጹሕ ነው ትላለህ ፤ ወዲህም ቃልህን ወደሱ ከፍ ከፍ ታደርጋለህ ፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፫፡ ሶበሰ ዓመፃ ኢሀሎ ውስተ እዴከ ፣

በእጅህ መግደል በቃልህ መበደል ባይኖር ፡

ወእመ ኢያንበርከ ጽልሁተ ውስተ ልብከ ፣

በልቡናህ ቂም ተንኮል ካላኖርህ፣

አማሃ ይበርህ ገጽከ ከመ ዘተሐጽበ በማይ ንጹሕ ፣

ጽሩይ ሲል ነው ፡ በጠራ ውሀ እንደ ታጠበ ፊትህ ያበራል ማለት ዋጋህን ያን ጊዜ ይሰጥሃል ፡

፲፬፡ ወትከውን ስቁየ እማይ ፣

ከማየ ረድኤቱ የረካህ ትሆና ለህ ፡

ወአእትት ርስሐተ ወኢትፍራህ እንከ ፣

ኢትፈርህ ሲል ነው፤ ኃጢአቱን አንተ አርቅ እንግዲህ ወዲህ መከራውን አትፈራውም ፡

፲፭፡ ወትረስዓ ለሕማምከ ከመ ሞገድ አንተ ኃለፈት ወኢትደምዕ እንከ ፣

መከራኸን ትዘነጋታለህ፣ ጎርፍ ፈጥና እንድታልፍ እንዳትሰማ መከራህን ትረሳታለህ ፡

ወጸሎትከሂ ከመ ኮከበ ጽባሕ ፣

ልመናህም እንደ አጥቢያ ኮከብ ነው፤ ያ ደስ እንዲያሰኝ ደስ የሚያሰኝ ዋጋ ይዞ ይመጣልሃል፤ በዚህ ዓለም የሚያገኘው ክብር ነው ፡

ወትሠርቅ ሕይወትከ ከመ መዓልት፣

ትመጽእ ሲል ነው፤ ሕይወትህ እንደ ፀሐይ ደስ በማሰኘት ትመጣለች ማለት በወዲያው ዓለም የሚያገኘው ክብር ነው፤

፲፮፡ ወትትአመን ከመ ትረክብ ተስፋከ ፡

አለኝታህን እንድታገኝ ታምናለህ ፡

ወትነብር ጻህነ ዘእንበለ ኀዘን ወትካዝ ፣

ያለኀዘን ያለ ትካዝ በተድላ በደስታ ትኖራለህ ፡

፲፯፡ ወተአርፍ እንከ ወአልቦ ዘይፀብዓከ ፣

እንግዲህ ወዲህ ከመከራው አርፈህ ትኖራለህ፣ የሚጣላህ የለም፤

ወይመጽኡ ብዙኃን ወይገንዩ ለከ ፣

ብዙ ሰዎች ይመጣሉ፣ ለአንተ ይገዙልሃል ፡

፲፰፡ ወተኃልቅ መድኃኒቶሙ ለኃጥአን ፣

የኃጥአን ድኅነታቸው ትጠፋለች፤

ወየኃጕሉ ተስፋሆሙ ፣

ይህም ልማድ ነው፣ ባለጸግነታቸውን ያጣሉ ፡

ወይትመሰዋ አዕይንተ ረሲዓን ፣

ሐገ እግዚአብሔርን የዘነጉ ሰዎች ዓይናቸው በሞት ይጠፋል ።



# ምዕራፍ ፲፪

## አሥራ ሁለተኛው ምዕራፍ ይህ ነው ፡

፩፡ ወአደ ተናገረ ኢዮብ ወተሰጥወ ወይቤ ፣

ኢዮብ ከተናገረ ዘንድ መለሰ እንዲህ አለ፤ አንድም ሲገባው ሲመልስ እንዲህ አለ ፡

፪፡ አንትሙኑ ሰብእ አንትሙ ፣

ሰብእሰ ኃማሜ ንባብ ከመ አድግ ብሎ ነበርና እናንተም ሰዎች ናችሁ፣ አህያ ናችሁ፤ አንድም እናንተም ሰዎች ናችሁን ከሰው ትቆጠራላችሁ ?

ወበኀቤክሙኑ ጻዕሙ ተሠልጠት ጥበብ ፣

ጥበብ ስትመጣ ስትመጣ በናንተ ተከማችታለች ? አንድም ጥበብስ በናንተ ዘንድ ጨርሳ ጠፍታለቺ ?

፫፡ ወአነሂ ብየ ልብ ከማከሙ ፣

እኔም እንደናንተ ዕውቀት አለኝ፤

እስመ አልቦ ከመ እግዚአብሔር ፣

እንደ እግዚአብሔር ያለ ፈታሒ በጽድቅ ኰናኒ በርትዕ የለምና፤ አንድም እንደ እግዚአብሔር ያለ ንጹሐ ባሕርይ የለምና ፡ አንድም እንደ እግዚአብሔር ያለ መሐሪ ወመስተሣህል የለምና ፡

ሰሐቀ ለቢጹ ይከውን ፣

በኃጢአቱ እግዚአብሔር ፈርዶበት አንዱ ላንዱ መዘበቻ ይሆናል፤ አንድም ከደዌዬ ተፈውሼ ለዘመዶቼ ተድላ ደስታ እሆናለሁ፤

ወሰሐቀ ጻድቅ ንጹሕ ፣

በኔ በኢዮብ መዘበት ከውነት ንጹሕ ነው፤ አንድም በኔ ተድላ ደስታ መዘበት ከሐሰት ንጹሕ ነው ፡

፭፡ ብእሲ ጻድቅ ወንጹሕ ሥላቀ ኮነ በዕድሜ መዋዕሊሁ ፣

ጻድቅ ንጹሕ የሚሆን ኢዮብ ባለ በዘመኑ ሁሉ መዘበቻ ሆነ፤ አንድም ኢዮብ ቢኖር ቢኖር መዘበቻ ሆነ ፡

፮፡ ወአጽንሕዎ ያርስሕዎ ባዕዳን ፣

ያስርሕዎ ያሕዝንዎ ይላል፣ ያሳዝኑት ዘንድ ሰነፎች የስድብ መጠን አቆዩት፣ ንጉሥ በመጣ ጊዜ ሊል ማጾ ፍሪዳው ማገሩ ይቈየው ነበር፣ ለኔ ግን የስድብ መጠን አቆዩኝ ፡

ወከመ ያውድቁ ቤቶ ኃጥአን ፣

አሕዛብ ቤቱን ገንዘቡን ያጠፉ ዘንድ፤ አንድም አጋንንት ቤተ ምግባሩን ያፈርሱ ዘንድ፤

፯፡ ወባሕቱ እኩያን ኢይበሉ ኄራን ንሕነ እለ ያምዕዕዎ ለእግዚአብሔር፣

ነገር ግን እግዚአብሔርን የሚያሳዝኑ እኒህ ክፉዎች በጎ ሰዎች ነን አይበሉ ፡

www.ethiopianorthodox.org

አኮኑ ውእቱ ወየሐትቶሙ ፤

በጎ ሰዎች ነንማ እንዳይሉ እሱ የሚመረምራቸው አይደለምን፤

፯፤ ተሰአሎሙ ለእንስሳሂ ለእመ ይነግሩከ ፤

እኔንስ አህያ ብለኸኛልና ይነግሩህ እንደሆነ እንስሳትን ጠይቃቸው ፤

ወለአዕዋፈ ሰማይኒ ለእመ ያየድዑከ፤

አዕዋፍን ጠይቃቸው ይነግሩህ እንደሆነ፤ አንድም እስቲ እነዚያን ጠይቃቸው ይነግሩህ እንደሆነ፤ አህያ ያልኸኝ እኔ እነግርሃለሁ እንጂ ፤

፰፤ ተናገራ ለምድር ለእመ ትፌክር ለከ ፤

ምድርንም ጠይቃት ፤ ውርድ ብትጠይቃት ጭብጥ ትመልስልህ እንደሆነ ፤

ወለእመ ይነግሩከ ዓሣተ ባሕር ፤

ዓሣተ ባሕርም ይነግሩህ እንደሆነ ጠይቃቸው ፤

፱፤ መኑ የአምር ዘንተ ኵሎ ከመ እደ እግዚአብሔር ገብረ ፤

ይህን ሁሉ መከራ ያመጣብህ ሥልጣነ እግዚአብሔር እንደሆነ ማን ያውቃል ፤

፲፤ እስመ ውስተ እዴሁ ነፍሰ ኵሉ ሕያው ወመንፈሰ ኵሉ ሰብእ፤

የሰው ሁሉ ልቡና የሰው ሁሉ ሰውነት በሱ እጅ በሱ ሥልጣን ተይዟልና ፤

፲፩፤ ዕዝን ነገረ ይፌልጥ ወጕርዔ እክለ ይጥዕም ፤

ጆሮ ነገርን ይለያል፤ ጉሮሮ የእህል ጣዕም ያውቃል ፤ የነገር ጣዕም በጆሮ ፤ የእህል ጣዕም በጉሮሮ እንዲሉ ፤

፲፪፤ በብዝኃ ዓመታትኑ ትትረከብ ጥበብ ወበብዝኃ ንብረት ትምህርት፤

እንደዚህስ ሁሉ ዘመን በማብዛት ብዙ ዘመን በመኖር ጥበብ ትምህርት ትገኛለችን፤ አንድም ሳይማሩ ብዙ ዘመን በተማሪ ቤት ቢኖሩ ጥበብ ትምህርት ትገኛለችን ፤

፲፫፤ ወባሕቱ ኵሉ እምኀበ እግዚአብሔር ፤

ነገር ግን ሁሉ ከእግዚአብሔር ዘንድ ይገኛል፤

ወሎቱ ምክር ወአእምሮ ወኃይል ፤

ምክር ዕውቀት ኃይል የሱ ገንዘብ ነው ፤

፲፬፤ ወለእመ ውእቱ ነሠተ መኑ የሐንፅ ፤

በሞት ቢያፈርስ በሕይወት የሚያድን ማነው ፤

ወለእመኒ አዐወ ላዕለ ሰብእ መኑ ያርኁ ፤

በመቃብር ቢዘጋ ከፍቶ የሚያወጣ ማነው ፤



፲፭፤ እመ ከልዐ እምሰማይ ዝናመ ያየብሳ ለምድር ፤

እንደ ኤልያስ ጊዜ ዝናሙን ከሰማይ ቢከለክል ምድርን ያደርቃታል ፤

ወእመ ኃደጋ ትማስን ወትትገፈታዕ፤

ዝናሙን ማዝነም ቢተዋት ፈጽማ ትጠፋለች፤ አንድም እንደ ማየ አይኅ ጊዜ አብዝቶ ቢያመጣባት ፈጽማ ትጠፋለች ፤

፲፮፤ እስመ እምኀቤሁ ኃይል ወጽንዕ ፤

ኃይል ጽንዕ መገኛው ከሱ ነውና፤

ወእንቲአሁ ጥበብ ወምክር ፤

ጥበብ ምክር የሱ ገንዘብ ነው፤

፲፯፤ ወይሬስዮሙ ለመካርያን ወይዒወዉ ፤

የጦር ምክር እናውቃለን የሚሉትን እንዲማረኩ የሚያደርጋቸው እሱ ነው ፤

ወይወስዶሙ ለመኳንንተ ምድር ፤

መኳንንቱን አስማርኮ የሚወስዳቸው እሱ ነው ፤

፲፰፤ ወያነብሮሙ ለነገሥት ዲበ መናብርት ፤

ነገሥታቱን በዙፋን ላይ የሚያስቀምጣቸው እሱ ነው፤ እንደ ሕዝቅያስ ፤

ወያቀንቶሙ ቅናተ ዘኃይል ውስተ ሐቋሆሙ ፤

ኃይልን እንደዝናር የሚያስታጥቃቸው እሱ ነው፤

፲፱፤ ወይፌንዎሙ ለማርያን ወይዒወዉ ፤

ሟርተኞችን ተማርከው እንዲሄዱ የሚያደርጋቸው እሱ ነው፤

ወይገፈትዖሙ ለኃያላነ ምድር ፤

ኃያላኑን የሚያጠፋቸው እሱ ነው ፤

፳፤ ወይመይጥ ምክሮሙ ለመሐይምናን ፤

የእስራኤልን ነገራቸውን በሚለውጡ በነሰናክሬም መዓት፤ መቅሠፍት ያመጣባቸዋል፤ አንድም ለእስራኤል አስበ ጸሎታቸውን የሚሰጣቸው እሱ ነው ፤

ወየአምር ምክረ ሊቃናት ፤

የአለቆችን ምክር የሚያውቅ እሱ ነው ፤

፳፩፤ ወያመጽእ ሎሙ ኃሣረ ለመሳእክት ፤

በነሰናክሬም አለቆች ጕስቁልና የሚያመጣባቸው እሱ ነው ፤

ወይሠሃሎሙ ለትሑታን ፤

ትሑታን እስራኤልን ይቅር የሚላቸው እሱ ነው ፤

www.ethiopianorthodox.org

፳፪፡ ወይከሥት ዕሙቃተ እምጽል
መት ፤

የተሠወረውን መርምሮ የሚያ
ውቅ እሱ ነው ፤

ወያወጽእሙ ውስተ ብርሃን እምጽል
መት ወጽላሎተ ሞት ፤

ሞት ጽኑዕ መከራ ካለበት ወደ
ተድላ፣ ወደ ደስታ የሚያወጣ
ቸው እሱ ነው ፤

፳፫፡ ወየአወክኮሙ ለአሕዛብ ወይት
ኃጐሉ ፤

አሕዛብን በሞት ተግ ተግ የሚ
ያደርጋቸው ፤ አንድም የሐው
ኮሙ ቢል የሚያውካቸው እሱ
ነው፣ ይጠፋሉ ፤

ወይሠርዮሙ ለአሕዛብ ወይመርሆሙ፣

አሕዛብን ለጥፋት ይሠራቸዋል
ወደ ጥፋት ይመራቸዋል ፤

፳፬፡ ወይመይጥ ምክሮሙ ለመላእ
ክተ ምድር ፤

ያለቆችንም ምክር ይለውጥባቸ
ዋል ፤

ወያዔይሎሙ ፍኖተ ዘኢያእመሩ፣

የማያውቁትን ጎዳና ያዞራቸዋል
እንደ እስራኤል ፵ ዘመን ይዞሩ
እንደነበሩ ፤

፳፭፡ ወያመረስሱ ውስተ ጽልመት
ወአኮ ውስተ ብርሃን ፤

በተድላ በደስታ ያይደለ በመከራ
ተይዘው ይዳብሳሉ ፤

ወይተንትኑ ከመ ስኩር ፤

እንደሰከረ ሰው በመከራ ይፍገ
መገማሉ ፡፡

## ምዕራፍ ፲፫

### አሥራ ሶስተኛው ምዕራፍ ይህ ነው ፤

፩፡ ናሁ ዝ ዘርእየት ዓይንየ ፤

እነሆ ዓይኔ ያየችው ይህ ነው፤
አለ በዘመኑ የተደረገው ፤

ወዘሰምዓት ዕዝንየ ፤

ጆሮየም የሰማችው ይህ ነው
አለ፤ ከሱ በፊት የተደረገው፤

፪፡ ወአአምር ዘከመ ተአምሩ አን
ትሙ ፤

ወብእሲ ለባዊ ይሌብዎ ብሎ
ነበርና እናንተ እንደምታውቁት
ዕውቀት አውቃለሁ ፤

እምኔክሙሰ ኢየዓብድ ፤

ከናንተ ግን አልሰንፍም ፤

፫፡ ወባሕቱ አንሰ ኀበ እግዚአብሔር
እነግር ፤

ነገር ግን በደሌን ለእግዚአብሔር
እናገራለሁ ፤

ወእትዋቀስ ቅድሜሁ እመ ፈቀደ፣

ቢወድልኝ በፊቱ እከራከራለሁ፤

፬፡ አንትሙሰ ዓቀብተ ሥራይ ዘዓ
መፃ ፤

እናንተስ እንደማያውቅ ባለመድ
ኃኒት ናችሁ፤ እንገም፣ እንተኩስ



እያሉ ሰውን እንደሚያውኩ
ናችሁ፤ አንድም የናንተስ መድ
ኃኒታችሁ ዐመፅ ነው ማለት
በኃጢአቴ መጣብኝ በል ማለት
ነው ፤

ወመናግዛን ለእኪት ኵልክሙ ፤

ሁላችሁም ለበጎ ነገር ያይደለ
ለክፉ ነገር የምታረጋጉ ናችሁና፤

፭፡ ኢይረትዓኒ አጽምዕክሙ ፤

ነገራችሁን እሰማችሁ ዘንድ ደስ
አያሰኘኝም ፤

እስመ ጠፍዓት ጥበብ እምኔክሙ፣

ጥበብ ከናንተ ጠፍታለችና ፤

፮፡ ስምዑኒ ቅሥተ አፉየ ፤

ካፌ የወጣ ጠብ ክርክርን ስሙ፤

ወአጽምዑኒ ፍትሐ ከናፍርየ ፤

ካፌ የወጣውን ፍርድ ስሙኝ፤

፯፡ ወይእዜኒ አኮኑ ቅድመ እግዚአብ
ሔር ትነብቡ ወታየድኡ ጕሕሉተ
ቅድሜሁ ፤

እግዚአብሔርን እንወደዋለን
ትላላችሁ፣ ወዲህ ተንኮል የሚ
ሆን ነገር በፊቱ ትናገራላችሁ፤
አንድም እንወድሃለን ትሉኛላ
ችሁ፣ ወዲህ ጽድቄን ትሠው
ራላችሁ ፤

ወትትገኃሡ እምኔሁ ፤

ከሱ ትርቃላችሁ ፤

እስኩ ለሊክሙ ፍትሑ ፤

እስኪ እናንተ ፍረዱት ፤

፰፡ ሠናይሰ ሶበ የሐትቱክሙ ፤

ሳይጠይቋችሁ ሳይመረምሯችሁ
ትናገራላችሁ እንጅ ሲጠይቋ
ችሁ ሲመረምሯችሁስ ብትመ
ልሱ በጎ ነገር ነበር፤ አንድም
ሠናይኑ ሥላሴ፣ እንደኔ ያለ
መከራ አምጥተው ቢመረምሯ
ችሁ መልካምን ነው ?

እንዘ ኵሎ ትገብሩ ኪያሁ ተኃሥሡ፣

ይህን ሁሉ እያደረጋችሁ እናመ
ልከዋለን ትላላችሁ ፤

፱፡ በምንትኑ ታስተማስልዎ ከመ
ትትዋቀሱ ሎቱ ፤

ትከራከሩለት ዘንድ በምን ትመ
ስሉታላችሁ ባላዋቂ ነው ?

ለገጽሰ ታደልዉ ወለፌ ተኃብዑ ፤

እናመልከዋለን ትላላችሁ ወዲህ
ኃጢአት ትሠራላችሁ፤ አንድም
እንወድኻለን ትላላችሁ ወዲህ
ምግባሬን ትሠውራላችሁ ፤

፲፡ ቀዳሚሁ አኮኑ ኃይሉ ያፈርህ
ክሙ ፤

ጥንቱን ኃይሉ የሚያስፈራችሁ
አይደለም ?

ወይመጽአክሙ ግሩም እምኀቤሁ ፤

ግሩም የሆነ መዓት፣ መቅሰፍት
ይመጣባችኋል ፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፩፡ ዘለፋክሙሂ ኃላፊ ከመ ሐመድ፤

የምትሳደቡት ስድብ እንደ አመድ ነው፤ አንድም አመድ እንዳይረባ እንዳይጠቅም አይረ ባም ፤

ወሥጋክሙኒ መሬት ፤

ሥጋችሁም ፈራሽ በስባሽ ነው፤ እንደ አመድም ዝርው ነው፤

፲፪፡ ተጸመሙ እንብብ ወእስሐት እምሕምዝ ፤

ዝም በሉ፤ ተናግሬ ከመከራው ልረፍ፤ ብናገር የሚሻለኝ ይመ ስለዋልና ፤

፲፫፡ ወአስተጋብዕ ሥጋየ በስነንየ ፤

ሥጋዬን በጥርሴ ይገርፏታለሁ፤ ነፍ ሴን በጥርሴ ይገርፏታለሁ እንዲሉ፤

ወአጠውቃ ለነፍስየ በእዴየ ፤

ሰውነቴን በእጄ አስጨንቃታ ለሁ ፤

፲፬፡ ወእመ ተመጠውክዋ በኃይል ወእመ አኮሰ እምኢተንሥአት ፤

ተዕናንቴ ላስነሳት ባልተነሳችም ነበር ፤ አንድም እምተነሥአት ነፍሴ ከሥጋዬ በተለየች ነበር ፤ አንድም እምተነሥኦታ ሥጋዬን ነፍሴ በተለየቻት ነበር ፤

ወእመ አኮ እነግር ወእወቅስ ቅድሜሁ፤

ነገር እንደኔ ከሆነ፤ እንደናንተ ካልሆነ እናገራለሁ ፤ በፊቱ እከ ራከራለሁ ፤

፲፭፡ ወዝንቱ ይኩነኒ መድኃኒተ እስመ ኢይበውዕ ቅድሜሁ ትምይንት ፤

ይህ መከራው መድኃኒት ይሁ ነኝ በፊቱ ተንኮል የለምና ፤

፲፮፡ ስምዑኒ ቃልየ አነ እነግረክሙ እንዘ ታፀምዑኒ ፤

እመ ታፀምዑኒ ሲል ነው፤ ብታ ደምጡኝ እነግራችኋለሁ ፤ ነገ ሬን ስሙኝ ፤

፲፯፡ ናሁ አነ ቀረብኩ ኀበ ፍትሕየ፤

እነሆ እኔ ይፈርድልኛል ወደ ማለት ቀረብሁ ፤ አንድም ዳኛ አግኝቼ ተከራክሬ ወደማለት ቀረብሁ፤

ወአአምር አነ ከመ ታስተርኢ ጽድ ቅየ ፤

ምግባሬ ዋጋዬን እንድታሰጠኝ አውቃለሁ ፤

፲፰፡ ወመኑ ውእቱ ዘተዐአረ ከማየ ከመ እፀመም ወአርምም ይእዜ ፤

ዝም በል ይሉታልና ዛሬ ዝም እል ዘንድ እንደኔ በመከራ የተ ጨነቀ ማነው ?

ወእከውን ከመ ዓብድ ወእትኃባዕኑ እምገጽከ ፤

እንግዲህስ እንደ አላዋቂ እሆና ለሁ? ከገጸ መዓትህ እሰወራለ ሁን ፤





፲፱፡ አእትት እምኔየ እዴከ ወኢያጥ ውቀኒ ግርማከ ፤

እደ መዓትህን ከኔ አርቅ፤ ግርማ መዓትኽ እንዳያስጨንቀኝ ፤

፳፡ ወትጼውዓኒ ወአነ እሰጠወከ ፤

በሞት ትጠራኛለህና እኔንም ና ባልከኝ ጊዜ እመጣለሁ ፤

ወእመሂ ተናገርከኒ ወአነ አወሥአከ፤

ምንተ ገበርከ ባልከኝ ጊዜ እኔ እመልስልሃለሁ ፤

፳፩፡ ወሚመጠን እማንቱ ኃጣውእየ ወአበሳየ አርዕየኒ ምንት እማንቱ ፤

ኃጢአቶቼ ምን ያህል ናቸው ምን ያህል እንደሆኑ ግለጽልኝ፤ አንድም ንግረኒ ፤ ምን ያህል እንደሆኑ ንገረኝ፤

፳፪፡ ወለምንት ትሜውር እምኔየ ወትሬስየኒ ፀላዒከ ፤

ከኔ ከወዳጅህ ዕዳየን ለምን ትሠ ውራለህ፤ ወዳጅህ እኔን እንደ ጠላት ለምን ታደርገኛለህ፤ አን ድም ረድኤትህን ከኔ ለምን ትሠውራለህ ፤

፳፫፡ ከመ ቈጽል ዘይትነገፍ እምነፋስ ተሐፍሰኒ ፤

ከነፋስ የተነሣ ቅጠል እንዲረ ግፍ በመከራ ታጠፋኛለህ ፤

ወከመ ነፋስ ታሠርረኒ ፤

እንደ ነፋስ ብር ብር ታደርገ ኛለህ ፤

ሣዕረኑ ወብርዓ ዘይየብስ ትዴግን፤

የሚደርቅ ሳር ገለባን ትከተላለ ህን ? ያ እንዲደርቅ የምጠፋ አይደለምን ፤

፳፬፡ እስመ ጸሐፍከ እኪይየ ላዕሌየ፤

ኃጢአቴን ቆጥረህብኛልና ፤

ወዓቀብከ ሊተ ኵሉ ኃጢአተ ዘእም ንዕስየ አቅነትከኒ ፤

በሕፃንነቴ የሠራሁትን ኃጢአ ቴን አስበህብኛልና፤ አስጉረጉ ስኸኝ፤ አንድም ደዌውን እንደ ዝናር አስታጠቅኸኝ ፤

ወአቀምከነ ለእገርየ ውስተ ጻሕፅ፤

እግሮቼን በመከራ አቆምኻቸው፤

፳፭፡ ወሜምከ ኵሉ ምግባርየ ፤

ሥራዬን ሁሉ አሰብህ ፤

ወሰበ ቆመት እግርየ ውስተ ጻህዕ ኃደገኒ ፤

እግረ ልቡናዬ በሕግ ፀና ባል ሁህ ጊዜ በመከራ ጣልከኝ፤

፳፮፡ ወአብለይከኒ ከመ ዝቅ አው ከመ ልብስ ዘተበልዓ እምቍንቍኔ፤

እንደ አረጀ እርዋት አደረግኸኝ ወይም ብል እንደበላው ልብስ አጠፋኸኝ ፡፡

www.ethiopianorthodox.org

# ምዕራፍ ፲፬

## አሥራ አራተኛው ምዕራፍ ይህ ነው ፤

፩፡ መዋቲ ዘይትወለድ እምአንስት፣

ከሴቶች የሚወለድ ሟች ሰው ርጉም ነው ፤

ወኅጻጥ መዋዕሊሁ ወምሉዕ መቅሠፍቱ ፣

ዘመኑ ጥቂት፣ መቅሠፍቱ ብዙ ነው ፤

፪፡ ወይፈሪ ከመ ጽጌ ወይወድቅ ወየኃልፍ ከመ ጽላሎት ወኢይሄሉ እንከ ፣

እንደ አበባ ይረግፋል፣ እንደ ጥላ ያልፋል፣ ከዚያ በኋላ አይኖርም፤

፫፡ ለዝኒ አንተ ሐተትከ ወሎቱኒ አባዕከ ቅድሜከ ይትዋቀስ ፣

እንዲህ የሚሆን ሰውን በመከራ መረመርከው እሱን ከእግዚአብሔር ጋራ በተከራከርሁ እንዲል አደረግኸው ፤

፬፡ ወመኑ ይነጽሕ እምርስሐት ወኢመኑሂ ፣

ማንም ማን ከኃጢአት የሚነፃ ማነው ፤

ወዘአሐተ ዕለተ ሐይወ በዲበ ምድር፣

ከተወለደ ጀምሮ ኃጢአት ሳይሠራ የሚኖር ማነው ? ከተወለደስ ጀምሮ ኃጢአት አይሠራም ብሎ ለኃጢአት ከበቃ በኋላ ፤ አንድም ኃጢአት ሠርቶ አንድ ቀን የሚውል ማነው ፤

፭፡ እስመ ኍልቌ አውራኂሁ በኀቤከ ፣

የዘመኑን ቍጥር አንተ ታውቀዋለህና ፤

ወትሁቦ ዕድሜሁ ወኢየኃልፍ እምኔሁ ፣

ይህን ያህል ዘመን ኖረህ ፣ ና ፣ ብለህ ታዘዋለህ ፣ ከትእዛዝህ አልፍ አይልም ፤

፮፡ ረኃቅ እምኔሁ ከመ ያዕርፍ ፣

አርፍ ዘንድ መከራውን አርቅልኝ ፤

ወይትዓቀባ ለሕይወቱ ከመ አሳብ፣

ሰውነቱን እንደ ዕለት ምንደኛ ይጠባበቃታል ፤

፯፡ ዕፅኒ ቦቱ ተስፋ ተገዚሞ ዳግመ ይፈሪ ወይሠርፅ ኃይሉሂ ኢየኃልቅ፣

ለዕፅኒ ሲል ነው ፤ እንጨትም ከተቈረጠ በኋላ ዳግመኛ ያፈራል ፣ ይለመልማል ፣ ልምላሜውም አይደርቅም ፣ ፍሬውም አያልቅ ተብሎ ተስፋ አለው ፤

፰፡ ወእመሂ ረስአ ውስተ ምድር ሥርው ፣

ሥሩ በምድርም ቢያረጅ ፤



እመሂ ሞተ በውስተ ኰኵሕ ፣

በዐለቱ ደንጊያ ውስጥ ቢደርቅም ፤

እመዓዛ ማይ ይሠርፅ ወይፈሪ ከመ ሐዲስ ተክል ፣

ከለቆው ዝናም፣ ከውሀ ጥላላት የተነሣ እንደ አዲስ ተክል ይለመልማል ያፈራል ተብሎ ተስፋ አለው ፤

፱፡ ሰብእሰ እምከመ ሞተ ይጸይዕ፣

ሰው ግን ከሞተ በኋላ ይሸታል፤

ወእምከመ ሞተ መዋቲ ኢይሄሉ እንከ ፣

ከሞተ በኋላም እነሣለሁ ብሎ ተስፋ አያደርግም ፤

፲፡ ባሕርኒ ቦ ተስፋ ሶበ ይቀብል ወፈለግኒ ይነጽፍ ወይየብስ ፣

ለባሕርኒ ሲል ነው ፤ ባሕርም ከጎደለ በኋላ ይመላል ተብሎ ፈሳሹ ውሀ ከደረቀም በኋላ ይፈሳል ተብሎ ተስፋ አለው፤

፲፩፡ ሰብእሰ እምከመ ኖመ ኢይነቅሕ እንከ እስከ አመ የኃልፍ ሰማይ፣

ሰው ግን ከሞተ በኋላ ሰማይ እስኪያልፍ ድረስ አይነሣም፤

ወይነቅሑ እምንዋሞሙ ፣

ተኝቶ እንደ መነሣት ዘግይቶ እንደ መክበር ከምድር ይነሣሉ፤

፲፪፡ እምሐየሰኒ ሶበ ውስተ መቃብር ዓቀብከኒ ፣

ከዚህ ሁሉ መከራ በመቃብር አኑረህ ብትጠብቀኝ በተሻለኝ ነበር ፣

ወእምኃባዕከኒ እስከ ይቈርር መዓትከ፣

መዓትህ እስቲርቅ ድረስ በመቃብር ብትሠውረኝ በተሻለኝ ነበር ፤

ወእምዓቀብከኒ እስከ አመ ትዜክረኒ፣

በትንሣኤ ዘጉባኤ እስክታስበኝ ድረስ በመቃብር በጠበቅኸኝ በተሻለኝ ነበር፤ መቃብር እንጂ በጎ ነገር ነው ለማለት ፤

፲፫፡ ሶበሰ የሐዩ ሰብእ እምድኅረ ሞተ ፈጺሞ መዋዕለ ሕይወቱ እምተዓገሥኩ እስከ አመ እትወለድ ዳግመ፣

ሰው ዘመኑን ፈጽሞ ከሞተ በኋላ የሚነሣ ቢሆን ዳግመኛ እስክፈጠር ድረስ መከራውን በታገስሁ ነበር ፤

፲፬፡ ወእም አውሥዕኩከ ጊዜ ጸዋዕከኒ፣

ና ባልኸኝ ጊዜ በመጣሁ ነበር፤

ወኢትመንን ተግባረ እደዊከ ፣

የእጅህ ፣ የቃልህ ፍጥረት የምሆን እኔን አትናቅ ፤

፲፭፡ ኍለቌኑ ኃጢአትየ አሐተኒ አልቦ ዘረሣዕከ ሊተ ኃጢአትየ ወአበሳየ ፣

ኃጢአቴን ቆጠርህ፣ ከኃጢአቴ ከበደሌ አንዲትስ ስንኳ የዘነጋሕብኝ የለም ፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፯፡ ወሐተምኩ ውስተ ቍናማቲሁ ጌጋይየ ወኮሎ ዘአበስኩ ዘላዕሌየ፤

በኔ ላይ ያለ የበደልሁትን በደል ሁሉ ኃጢአቴን በልቡናህ ቆጠርህ ፤

፲፰፡ ከመ ደብር ዘንህለ ወወድቀ ፤

ኮንኩ ያለበት ነው፤ እንደፈረሰ አምባ ሆንኩ፤ አንድም ኃጢአቴን እንደፈረሰ ግንብ አድርግልኝ፤ አንድም እንደፈረሰ አምባ መሆኔን አይተህ ይቅር አልከኝ፤

ወኰኵሕኒ ይበሊ በውስተ ምንባሩ፤

ዐለቱም ደንጊያ በቦታው ያረጃል፤ መሸበቱ ማርጀቱ ነው ፤ ይህን ሁሉ መከራዬን አይተህ ኃጢአቴን እንደዚህ አድርግልኝ ፤

፲፱፡ ዕብነኒ ይለምዕ እማይ ፤

ደንጊያም ከውሀው የተነሣ ያድጣል፤ ማጻጡ ማርጀቱ ነው ፤

ማይሂ ይደፈን በማዕከለ ምድር ልሁል፤

ግዙፍ ሲል ነው፤ ውሀውም ከፍ ባለ ምድር መካከል ውስጥ ለውስጥ ይሄዳል፤ ውስጥ ለውስጥ መሄዱ ማርጀቱ ነው፤ እንደዚህም ሁሉ መከራዬን አይተህ ኃጢአቴን እንደዚያ አድርግልኝ፤

ወአኅጐልከ ትዕግሥቶ ለሰብእ ፤

ትዕግሥቴን አይተህ አልራራህልኝም ፤

፳፡ ወተአትቶ ለዝሉፉ ወይማስን፤

በሞት ታርቀዋለህ፤ ፈጽሞ ይጠፋል ፤

ወሜጥከ ገጸከ ኀቤሁ ወመሰጥኮ ፤

ገጸ መዓትህን ወደሱ መለስህ፤ በሞት ወሰድኸው ፤

፳፩፡ እመኒ ደቂቀ በዝኁ ኢይሬዕዮሙ፤

ልጆቹም ቢበዙ አያያቸውም ፤ ሙተዋልና ፤

ወእመሂ ኅዳጣን ኢየአምሮሙ ፤

ጥቂቶችም ቢሆኑ በመኖር አያውቃቸውም ፤

፳፪፡ ዳዕሙ ሥጋሁ ያማስን ነፍሱሂ ለሕይወት ፤

ሥጋው ይጠፋል እንጂ ነፍሱ ለሕይወት ትሆናለች ።

## ምዕራፍ ፲፭

አሥራ አምስተኛው ምዕራፍ ይህ ነው ፤

፩፡ ወተሠጥወ ኤልፋዝ ቴሜናዊ ወይቤ ፤

የቴሜን ሰው ኤልፋዝ መለሰ፤ እንዲህ አለ ፤

፪፡ ቀዳሚሁ ለጠቢብ ያወሥእ ዘይሄሊ መንፈሰ ፤

ያወሥእ መንፈሰ ዘይሄሊ መንፈስ ብሎ መግጠም ነው፤ የብልህ ሰው መጀመሪያ ነገሩ ልቡናው



ያሰበውን ይናገራል፤ እንደ አንተ ጠለፍ አድርጌ አልናገርም፤ አንድም የብልህ ሰው ነገሩ እንዲህ ነው ፤ ልቡናው ያሰበውን ነገር ይናገራል ፤

ወአጽገብካ ፃዕረ ለከርሥነ ፤

አንተ ስትናገር እኛ ላንተ እንመልስ ስንል ሰውነታችንን መከራ አጠገብኻት ፤

፫፡ ወትወቅስ ነገረ ከንቶ ወትነብብ ዘኢይበቍዕ ፤

በከንቱ ከእግዚአብሔር ጋራ በተከራከርሁ ነበር እያልኽ የማይረባ ነገር ትናገራለህ ፤

፬፡ አኮኑ ለሊከ ኢፈራህከ ከመ ትንብብ ዘከመዝ ነገረ ቅድመ እግዚአብሔር ፤

እንዲህ ያለ ነገር በእግዚአብሔር ፊት ትናገር ዘንድ አልፈራህ ምና ፤

፭፡ መጠንከ እምቃለ አፉከ ፤

ከአፍህ የሚወጣ ነገር መጠንህ አይደለም ነገርህ ሲበዛ ነው፤ አንድም ኢመጠንከ ፤ መጥነህ አልተናገርህም፤ አንድም ኢመጠንከ መጠንህ አይደለም ፤

ወኢፈለጥከ ነገረ ዓበይት ፤

የደጋጎችን የነአብርሃምን ነገር ለይተህ አላወቅህም ፤

፮፡ ወይዘልፈከ ቃለ አፉከ ወአኮ አነ ፤

ከእግዚአብሔር ጋራ በተከራከርሁ ማለትህ ይዘልፍሃል፤ እኔ የምዘልፍህ አይደለም ፤

ወከናፍሪከ ማኅተትከ ፤

ከከንፈርህ የወጣ ነገር ያስፈርድብሃል ፤

፯፡ ቦኑ እምሰብእ ቀደምከ ተፈጥሮ፤

ከእግዚአብሔር ጋራ በተከራከርሁ ያልህ ከሰው ሁሉ አስቀድመህ በውኑ ተፈጥረሃልን ፤

አው ከመ አስሐትያኑ ጠጋዕከ ፤

ወይስ እንደ ውርጭ ረግተህ ተገኝተሃልን ፤

፰፡ ወትእዛዘ እግዚአብሔርኑ ሰማዕከ ፤

ለይኩን ብርሃን ሲል ሰምተሃልን ፤

ቦኑ ኀቤከኑ ተዘግበት ጥበብ ፤

ጥበብስ ስትመጣ ስትመጣ ባንተ ዘንድ ተከማችታለች ?

፱፡ ወምንተ ተአምር ዘኢነአምር ንሕነ ፤

እኛ የማናውቀው አንተ ምን ታውቃለህ ?

ወምንተ ትሌቡ ዘኢንሌቡ ንሕነ፤

እኛ ልብ የማናደርገው አንተ ልብ የምታደርገው ምንድን ነው?

www.ethiopianorthodox.org

፲፡ ወሬዛኒ ፣

የሕፃን አዋቂ ብትል ኤልዩስ አለ ፤

ልሒቅኒ ፣

የሽማግሌ አዋቂ ብትል ሳፍር አለ ፤

ወአዕሩግኒ በነቤነ ሀለዉ ፣

ኤልፋዝ በልዳዶስ በኛ ዘንድ አሉ ፤ አንድም የሕፃን አዋቂ ብትል ሳፍር አለ ፤ የሽማግሌ አዋቂ ብትል፣ ኤልፋዝ አለ፣ ወአዕሩግኒ በነቤነ ሀለዉ በል ዳዶስ ኤልፋዝ አሉ ፤

ወዘይረስዕ እምአቡከ በመዋዕሊሁ ፣

በዘመኑ ካባትህ የሚበልጥ ኤል ፋዝ አለ ፤

፲፩፡ ወእመሂ አበስከ ተቀሠፍከ ኀዳጠ፣

ጥቂትም ብትበድል በዚያው መከራ ተቀበልህ ፤

ወኢኮነ ዝ ነገር ዘነበብከ በአምጣንከ፣

ይህ የተናገርኸው ነገር መጠ ንህ አይደለም ፤

፲፪፡ እፎኑ እንከ ተሀበለ ልብከ ከመ ትትቀሣዕ በቅድመ እግዚአብ ሔር ፣

ከእግዚአብሔር ጋራ በተከራከ ርሁ እያልኸ ልቡናህ እንደምን ደፈረ ፤

ወምንተ ርእየ አዕይንቲከ ፣

ከመ ትትቀሣዕ በመዓት ቅድመ እግዚአብሔር፣ በመዓት ተቆጥቶ መዓት ቢያመጣብህ በእግዚአ ብሔር ፊት ትከራከር ዘንድ ዓይኖችህ ምን አዩ ፤

ወዘከመዝ ነገረ ታወጽእ እምአፉከ፣

ከእግዚአብሔር ጋራ በተከራከ ርሁ ብለህ ትናገር ዘንድ ፤

፲፫፡ መኑ መዋቲ ዘይነጽሕ እምኃ ጢአት ወመኑ ጻድቅ ዘይትወለድ እምአንስት ፣

ወዲያውስ ንጹሕ ነኝ፣ ጻድቅ ነኝ የምትል ከኃጢአት የሚነፃ ሰው ማነው? ከሴቶችስ የሚወለድ ጻድቅ ማነው ?

ለቅዱሳን ጥቀ ኢይትአመኖሙ ፣

ለመላእክትስ ስንኳን ንጽሕና ቸው አይታመናቸውም ፤

ሰማይኒ ኢኮነ ንጹሐ በቅድሜሁ ፣

ሰማይም በፊቱ ንጹሕ አይደለም እለፍ ቢለው በምን ኃጢአቴ አይልም ፤

፲፬፡ ኀድግሰ ሰብእ ርኩሰ ወርሱሐ ዘይሰርባ ለኃጢአት ከመ ስታይ ፣

ኃጢአትን እንደመጠጥ አብዝቶ የሚሠራት ሕሡር ርኩስ የሚ ሆን ሰውንስ ተውና፤ አንድም ይትኃደግሰ ሰብእ ርኩስ ይላል፤



ኃጢአትን አብዝቶ የሚሠራት ኅሡር ርኩስ የሚሆን ሰውስ ይቅርና ለመላእክትስ ስንኳ ንጽ ሕናቸው አይታመናቸውም፤

፲፭፡ ስምዓኒ እንግርከ ወአይድዕከ ዘርኢኩ ወዘነገሩ ጠቢባን ፣

ጠቢባን የተናገሩትን ፤ እኔ ያየ ሁትን እነግርህ ዘንድ ስማኝ ፤

ወኢኃብኡ ለውሉዶሙ አበዊሆሙ፣

አባቶቻቸው ለልጆቻቸው ሊሆን ያልሠወሩትን እነግርህ ዘንድ ስማኝ ፤

እስመ ለባሕቲቶሙ ተውህበት ምድር፣

ደቂቀ ሴት ናቸው፤ ምድር ለነሱ ብቻ ተሰጥታቸው ነበርና ፤

ወኢኃለፈ ካልዕ ሕዝብ እምኔሆሙ፣

ከሳቸው አስቀድሞ ሌላ ወገን አልነበረምና ፤

፲፮፡ ኵሉ መዋዕሊሁ ለኃጥእ ይት ኀዘብ ፣

ኃጥእ ባለ ዘመኑ ሁሉ ይጠራ ጠራል ፤

መዋዕሊሁኒ ወዓመታቲሁኒ በኍልቍ ይትወሀቦ ፣

ቀኑም ዘመኑም በቍጥር ይሰ ጠዋል ፤

፲፯፡ ለኃያል ትግርምቱ ያወድቆ ፣

የእግዚአብሔር ግርማ መዓቱ ኃይለኛውን ያጠፋዋል፤ አንድም ኃይለኛ ሰው በሰው ዘንድ መገ ረሙ ራሱን ያጠፋዋል፤ የነምር ጅራት አይዙም፣ ከያዙም አይ ለቁም እንዲሉ ፤ አንድም ሌላ ውን ያጠፋል ፤

እመ ተሰፈወ ዳህነ ይነብር ይትገፈ ታዕ ፣

በተድላ በደስታ ይኖር ዘንድ ተስፋ ባደረገ ጊዜ ይጠፋል ፤

፲፰፡ ወአልቦ ተስፋ ወጺአ እምጽል መት ፣

ከመከራ የሚወጣበት ተስፋ የለ ውም ፤

ወተአዘዘ ወድዓ ውስተ እደ ሐፂን፣

ሞቱ በጦር ይሆን ዘንድ ፈጽሞ ታዘዘ፤ አንድም ሞቱ በደዌ ይሆን ዘንድ ደዌውን እድ አለው ፤ ጨምድዶ ይይዘዋልና ፤

፲፱፡ ወተውህበ መብልዓ ለአንስርት፣

ለዕዌያት ምግብ ሁኖ ተሰጠ፤ አንድም ገንዘቡ ለአሕዛብ ተሰጠ የልጆቹ ሥጋ አልተቀበረምና ፤

ወኢየአምር ለሊሁ ከመ ድቀት ትፀ ንሖ ዕለተ መቅሰፍት ወጽልመት ፣

ድቀት ያለውን መቅሠፍት፣ ጽል መት አለው፤ ጽኑ መከራ ደጅ እንዲጠናው አያውቅም፤

፳፡ ወያጸድፎ ሕማም ወምንዳቤ ከመ መልአክ ዘይቀድም ተሰይሞ ወየኃ ሥር፣

መከራ ፀዋትወ መከራ እንዲ ያጠፋው አያውቅም፤ አስቀድሞ

www.ethiopianorthodox.org

የተሸመ ስማያዝ እንደጕሰቈለ፤ አንድም ዲያብሎስ እንደ ጕሰ ቈለ ፤

እስመ አዕበየ እደሁ ቅድመ እግዚ አብሔር ፤

ስማያዝ ፡ አንድም ዲያብሎስ በእግዚአብሔር ፊት ቃሉን ከፍ ከፍ አድርጓልና ፡

ወአግዘፈ ክሣዶ ቅድመ እግዚአብሔር ዘኵሎ ይመልክ ፤

ሁሉን በሚገዛ በእግዚአብሔር ፊት ክሣደ ልቡናውን አጽንቷ ልና ፡

፲፩፡ ወትረውፅ ኃሣሩ ቅድሜሁ ፤

ጕስቍልናው ተገልጣ በፊቱ ትገናኘዋለች፡ አንድም ትል በፊቱ ትመላለሳለች ፡

ወውስተ ራህበ ዘባኑ ኃይሉ ፤

የትል ሠራዊት በጀርባው ይመ ላለሳሉ ፡

፲፪፡ ወይከድኖ ሞት ለገጹ በኃሊ ፎቱ ፤

ሞት እግር መንገዱን መጥቶ ፊቱን ይሸፍነዋል ፤ አንድም ለአኅልፎቱ እሱን ለማኅለፍ መጥቶ ፤

ወይጠብቆ ውስተ ሐቌሁ ፤

ደዌ አስጨንቆ ይይዘዋል ፤

ወይነብር ውስተ አህጕረ ሐቅል ፤

ወነበረ አፍአ ብሎ ነበርና በም ድረ በዳ ይኖራል ፤ አንድም በማጥን አስተኝተውታልና ፡

ወይበይት ውስተ አብያት ምዝቡር፤

በፈረሰ ቤት ያድራል ፤

ወዘውእቱ አስተዳለወ ባዕድ ይበልዖ፤

እሱ ያዘጋጀውን ሌላ ይበላዋል፡

፲፫፡ ይብዕልዋ ወኢይጌንዲ ብዕሉ፤

ይከብራል ባለጸግነቱ አይዘገ ይም ፡

ወኢይገብር ጽላሎተ በዲበ ምድር፤

በዚህ ዓለም አምሳል መርገፍ አያደርግም ማለት ልጅ አይተ ካም ፡

፲፬፡ ወኢየመሥጥ እምጽልመት ፤

ከመከራ አያመልጥም ፡

ለሥርውሂ ነፋስ ያየብሳ ፤

አባትነቱን መዓት መቅሰፍት ያጠፋዋል ፤

፲፭፡ ወይወድቅ ፍሬሁ ወኢይሴፎ ሐይወ ፤

ልጁ ይጠፋል በሕይወት አይኖ ርም ፤

፲፮፡ ወዘተሰፈወሂ የመሥጥ ወይጠ ፍዕ ትውክልቱሂ በጊዜሁ ፤

ዘተሰፈወና ትውክልት ፩ድ ወገን ነው፤ የታመነው ባለጸግነቱ በጊ ዜው ጊዜ ፈጥኖ ይጠፋል፤



ወኃይሉሂ ኢይጸንዕ ፤

ኃይሉም አይጸናም ፤

፲፯፡ ወይትበላዕ ቆሁ በምዕር ወይወ ድቅ ከመ ፍሬ ዘይት ፤

በሕፃንነቱ ሳለ ይቀሰፋል ፤ አን ድም ልጁ ይቀሰፋል እንደ ዘይት ፍሬ ይጠፋል ፤

፲፰፡ ማኅተቶሙ ለኃጥአን ሞት ፤

ኃጥአንን እየመረመረ የሚያጠ ፋቸው ሞት ነው፤ አንድም ማኅ ቶቶሙ ለኃጥአን ይላል፡ የኃጥ አን ሞታቸው ተድላ ደስታ ነው ፡

እሳት ያውዒ ቤተ እለ ይነሥኡ ሕል ያነ በዓመፃ ፤

እሳት ወድቀት እምሰማይ ብሎ ነበርና ማማለጃ የሚቀበሉ ሰዎ ችን ቤት በእሳት ያጠፋዋል ፤

፲፱፡ ይፀንሱ ፃዕረ በከርሦሙ ፤

በገቢር፣ በሐልዮ፣ ኃጢአት ይሠ ራሉ ፤

ወትመልዕ ከርሦሙ ጕኅሉተ ፤

ፍዳ ይቀበላሉ ።

## ምዕራፍ ፲፱

አሥራ ስድስተኛው ምዕራፍ ይህ ነው ፡

ገባኤ

፩፡ ኀበ ተናገረ ኢዮብ ተሰጥወ ወይቤ፤

ኢዮብ ከተናገረ ዘንድ መለሰ፤ እንዲህ አለ፡ አንድም ሲገባው ሲመልስ እንዲህ አለ ፡

፪፡ ብዙኃ ሰማዕኩ ዘከመዝ መናገሥን ለእኪት ፤

እንደ እናንተ ለክፉ ነገር የሚያ ጽናና አላየሁም፡ አንድም ጻድቅ እንዳይጠፋ ኃጥእ እንዲጠፋ ሰማሁ፤ አንድም ሁላችሁ ለክፉ ነገር የምታጽናኑ ናችሁ ፡

፫፡ ወኮልክሙ ኮሉ ዘመጽአክሙ ትነብቡ ዘእንበለ ዓቅም ፡

ሁላችሁም ያለመጠን አገኝ ባጣ ትናገራላችሁ ፡

ወምንት አጽሐብኩክሙ ከመ ትትዋ ሥኡኒ ፤

ትከራከሩኝ ዘንድ ምን ስጡኝ ብዬ ዘበዘብኋችሁ ፡

፬፡ አነሂ ዘከመ ትብሉ አወሥአክሙ፤

እኔም እንደተናገራችሁት እመ ልስላችኋለሁ ፤

በነፍስክሙኑ ትቤዝውዋ ለነፍስየ ፤

ሰውነቴን በሰውነታችሁ ታድኗ ታላችሁን፤ አንድም ምን አልኋ

www.ethiopianorthodox.org

ችሁ፣ ሰውነቴን በሰውነታችሁ አድኗት አልኳችሁ ?

፬፡ ወእነግረክሙ ነገረ ወአሐውስ ርእስየ ለክሙ ፣

እንዘ አሐውስ ሲል ነው፤ ራስ ለነገር ያግዛልና ራሴን እየነቀነ ቅሐ ነገር እናገራለሁ፤

፭፡ ወሶበሁ ብየ ኃይል ውስተ አፉየ እምኢምህኩ ከናፍርየ ፣

ዕውቀት ባፌ ቢኖር በከንፈሬ መናገርን ባልሸለግሁም ነበር፤

ወእምአነየስኩ ዘእነብብ ፣

አሻሽየ በተናገርሁ ነበር ፤

፮፡ ወእመሂ ነበብኩ ኢይጥኢ ቊስልየ ፣

ብናገርም ከደዌዬ አልፈወስም፤

ወእመሂ አርመምኩ ይብዕሰኒ ሕማምየ ፣

ዝምም ብል ደዌዬ ይብስብኛል፤

፯፡ ይእዜሰ ግማዳተ ዓብድ ወቅንማባተ ረሰይከኒ ፣

ዛሬ ግን የሰነፍ አባል የአጣሪ ቅንጣቢ አደረግኸኝ ፤

፰፡ ወኮነት ስምዓ እኪዮትየ ፣

በመከራ መያዜ ለኃጢአቴ ምስክር ሆነች ፤

ወተንሥአት ላዕሌየ ሐሰትየ ፣

ኃጢአቴ መከራ ይዛ በጠላትነት ተነሣችብኝ ፤

ወተዋቀሰተኒ ቅድመ ገጽየ ፣

በፊቴ ተከራከረችኝ ፤

፱፡ ወተምዒዖ በመዓቱ ነጽሐኒ ፣

ተቆጥቶ በመከራ ጣለኝ ፤

ወሐቀየ ስነኒሁ ላዕሌየ ፣

ትእምርተ ፀብዕ ነው፤ አጽንቶ ተጣላኝ፣ በኔ ላይ ጥርሱን አፋጨ፤

ወአሕፃሁኒ በዲቤየ አመክረ ፣

አኅፃ መዓቱን በኔ ላይ ፈተነ ፤

፲፡ ለከዋኒ አዕይንትየ ፣

ዓይኖቹ ብርሃን አጥተው ፈዘዙብኝ ፤

ወኅቡረ ሮጹኒ አሕዛብ ፣

ዕዌያት ፤ አንድም አጋንንት አንድ ሁነው ከበቡኝ ፤

፲፩፡ ወመጠወኒ ውስተ እደ ዘይትኌዘበኒ ፣

ከዛሬ ነገ ያጠፉናል ብለው ለሚጠራጠሩኝ ለአሕዛብ ሰጠኝ ፤ አንድም ይስትን አይስትን ብለው ለሚጠራጠሩኝ ለአጋንንት ሰጠኝ ፤

ወበሕቁ አጽደፈኒ በብረክየ ፣

ፈጽሞ በጉልበቴ ጣለኝ፣ በጉልበቱ የወደቀ እንዳይድን የማልድን ሆንሁ ፤



፲፪፡ ወገደፈኒ እግዚአብሔር እንዘ ጸህነ እነብር ፣

በተድላ በደስታ እኖራለሁ ስል እግዚአብሔር በመከራ ጣለኝ ፤

ወገደፈኒ እግዚአብሔር ለፀዋጋን ፤

እግዚአብሔር ለአሕዛብ ፤ አንድም ለዕዌያት ለአጋንንት ሰጠኝ፤

ወበሥእርተ ድማኅየ መሐወኒ ፣

ማኽል ራሴን ነቀለኝ ፣ ማኽል ራሱን የተነቀለ እንዳይድን የማልድን ሆንሁ ፤

ወአቀመኒ ከመ መጠራ ወከመ ቃፍ አስተሐይፅ ከመ ሰብአ ዓይን፣

እንደ ትከሻ፣ እንደ ጊጤ ሕጉን እንደ ጉበኛ ስመለከት፤ አንድም ሕጉን እንደ ትከሻ እንደ ጊጤ ስመለከት እንደ ጉበኛ በዓይነ መዓት ተመለከተኝ ፤

፲፫፡ እስመ በኵያንው ወግዓኒ ፣

በዕዌ ወግቶኛልና ፤

ወይረግዙኒ ኵልያትየ ወኢይምሕሩኒ፣

አሕዛብ አጋንንት ኩላሊቴን ይወጉኛል አያዝኑልኝም፣ ኵላሊቱን የተወጋ እንዳይድን እኔም የማልድን ሆንሁ ፤

ወተክዕወት ውስተ ምድር ሐሞትየ፣

ሐሞቴ በምድር ላይ ፈሰሰች፣ ሐሞቱ የፈሰሰ ሰው እንዳይድን እኔም የማልድን ሆንኹ ፤

፲፬፡ ወበጽሐኒ ድቀት በዲበ ድቀት፣

በመከራ ላይ መከራ መጣብኝ በከብት ጥፋት ላይ የልጆች ሞት፤

ወሮጹ ላዕሌየ ኃያላን ፣

ዕዌያት አሕዛብ አጋንንት በኔ ላይ ሰለጠኑ ፤

፲፭፡ ሠቀ አስተጣበቀ ላዕለ ማዕስየ፣

ደዌውን በሰውነቴ ላይ አስታጠቅኸኝ፤ አንድም ከመ ሠቅ ዘአስተጣበቁ፣ ደዌው እንደማቅ ይኰሰኩሰዋልና ፤

ወተሠልጠት ሕማምየ በውስተ መሬት ፣

ደዌዬ በመሬት ሰለጠነች፤ ገል ደቁሰው፣ ትቢያ ነስንሰው በሣጥን አድርገውታልና ፤

፲፮፡ ትነድድ ከርሥየ በብካይ ፣

ሰውነቴ በልቅሶ ተናደደች ፤

ወውስተ ቀራንብትየ ጽላሎተ ሞት እሬኢ ፣

በቅንድቤም የሞትን ጥላ አያለሁ፣ ብሂሞትን መስሎ ይታየኛልና ፤

፲፯፡ ወአልቦ ዓመፃ ውስተ እደውየ፣

በእጄ መግደል፣ በቃሌ መበደል የለም ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወንጹሕ ጸሎትየ ፤

ጸሎቴም ከቂም ከበቀል ንጹሕ ነው ፤

፲፱፡ መሬትኑ ይከድነኒ ሥጋዩ ፤

አፈር እንደሆንሁ እቀር ይሆን፧

ወይትከዓው ደምየ ፤

ደሜ እንደፈሰሰ ይቀር ይሆን፧

ወኢይረክብኑ ብሔረ ሶበ አአወዩ ፤

ለምኜ የምድንበት አገር አላገኝ ይሆን ? አገርማ ምነዋ ግፌን የምነግረው ሰው አላገኝ ይሆን?

፳፡ ይእዜኒ ናሁ ሰማዕትየ ውስተ ሰማይ ፤

አሁንም ምስክሬ በሰማይ ያለ እግዚአብሔር ነው ፤

ወየአምር ሊተ ዘውስተ አርያም ፤

በሰማይ ያለ እግዚአብሔር ግፌን ያውቅልኛል ፤

፳፩፡ ኃለፈት ጸሎትየ ኀበ እግዚአብሔር ፤

ልመናዩ ከእግዚአብሔር ዘንድ ደረሰች ፤

ወታንጸፈጽፍ ዓይንየ ቅድሜሁ ፤

ዓይኔም በፊቱ ዕንባን ታፈሳለች ፤

፳፪፡ ሶበሁ ያስተዋቅሥዎ ለሰብእ ምስለ እግዚአብሔር ከመ ዕጓለ እመ ሕያው ምስለ ቢጹ ፤

ሰው ከባልንጀራው ጋራ እንዲከራከር ሰውን ከእግዚአብሔር ጋራ የሚያከራክር ቢኖር ፤

ይመጽአኒ ዓመታት ኍልቃት ፤

ይህ ደዌ ለኢዮብ አይገባውም ተብሎ የተቈጠሩ ብዙ ዘመናት በመጡልኝ ነበረ ፤

፳፫፡ ወአሐውር ፍኖተ ኀበ ኢይገብዕ ፤

ወደማልመለስበት ወደ መቃብር እሔዳለሁ ።

## ምዕራፍ ፲፯

### አሥራ ሰባተኛው ምዕራፍ ይህ ነው ፤

፩፡ ያዔዕረኒ ዘያወጽኣ ለነፍስየ ፤

ነፍሴን ከሥጋዩ የሚለያት ዕዔ፡ አንድም መልአከ ሞት ያስጨንቀኛል፡ አንድም ነፍሴን የሚለያት ጌታ ነው ፤

እትሜነዮ ለመቃብር ወኢየደምእ፤

መቃብርን እመኘዋለሁ አላገኘውም ፤

፪፡ እንዘ እልሕስ ሠራሕኩ ፤

ከጤና በደዌ፤ ከሕይወት በሞት ስሰደድ ደከምሁ ፤

ወምንተ እሬሲ ፤

ምን አደርጋለሁ ፤

ሰረቁኒ ነኪራን ንዋይየ ፤

ዕዔያት አካሌን፤ አሕዛብ ገንዘቤን ፤ አጋንንት ምግባሬን ሰረቁኝ ፤



፫፡ ወመኑ ውእቱ ዘይመይጣ ለእዴየ ፤

አሕዛብን ሳጥፋቸው ባልሁ ጊዜ ሥልጣኔን የሚመልሳት ማነው አንድም ልስጥ ልመጽውት ባልሁ ጊዜ እጄን የሚመልሳት ማነው፤

፬፡ እስመ ኅብዕዎ ለልቦሙ እምሠናይ ፤

ልቡናቸውን ከበጎ ነገር መልሰውታልና ፤

ወበእንተዝ ኢያሌዕሎሙ ፤

ስለዚህ ነገር ከፍ ከፍ አላደርጋቸውምና እንዲህ ይሉኛል እንጂ አንድም በክብር በአእምሮ ከፍ ከፍ አላደርጋቸውምና ፤

፭፡ ወይሚህርዎ እከየ ለልቦሙ ፤

ለልቡናቸው ክፉ ነገር ያስተምሩታል ፤

ወተመስዋ አዕይንትየ በእንተ ደቂቅየ ፤

ወመጽአ ዓቢይ ነፋስ ብሎ ነበርና ስለ ልጆቼ ሞት ሳለቅስ ዓይኖቼ ጠፉ ፤

፮፡ ወረሰይከኒ ነገረ ለአሕዛብ ወኮንክዎሙ ሰሐቀ ወሥላቀ ፤

ለአሕዛብ ተረት አደረግኸኝ መሳቂያ መዘበቻ ሆንኋቸው፤

፯፡ ወያራ አዕይንትየ እምአንብዕ፤

ዓይኖቼ ከእንባ የተነሣ ከማየት ተከለከሉ ፤

ወፈድፋደ አስቈረረኒ ኮሉ ፤

ሰው ሁሉ ፈጽሞ ተጸየፈኝ ፤

፰፡ ወተአመንከዋ ለዛቲ ወቀበበተኒ፤

ባለጸግነቴን ታመንኋት፤ ወዲያው አጣኋት፤ አንድም ጸሎቴን ታድነኛለች ብዬ ታምኛት ነበር አላዳነችኝም ፤

ወርቱዕሰ ትግባዕ ሳዕለ ኃጥአን ፤

አገባብስ ይች መከራ ወደ ኃጥአን ትመለስ ዘንድ ይገባል ፤

፱፡ ወባሕቱ እትአመን ከመ እገብዕ በፍኖትየ ፤

ነገር ግን በሠራሁት ሥራዩ ወደ ባለጸግነት እንድመለስ አውቃለሁ ፤

እስመ ንጹሐት እደውየ እረክባ ለትፍሥሕትየ ፤

ቃሌ ከመበደል ፤ እጆቼ ከመግደል ንጹሐን ናቸውና ተድላዩን ደስታዩን አገኛታለሁ ፤

፲፡ ወህለወክሙ ትርአዩኒ ኵልክሙ ወትምጽኡ ኀቤየ ፤

ረድኤት ስትሹ መጥታችሁ ገንዘቤ ተመልሶልኝ ከደዌዩ ተፈውሼ ታዩኝ ዘንድ አላችሁ ፤

እስመ አልቦ ርትዕ ዘእረክብ ኀቤክሙ ፤

በናንተ ዘንድ የማገኘው የቀና ነገር የለምና ፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፩፡ ወኀልቃ መዋዕልየ እንዘ ጽዩ አት ፤

ዘመኖቼ ሸተተዉ ከርፍተዉ ጠፉ፣ እሱ ስለሸተተባቸው ነው፤

ወተበትከ ሥርወ ልብዩ ፤

የልቡናዬ ሥር ተቆረጠ ፣ ሥሩ የተቆረጠ እንዳይድን የማልድን ሆንሁ ፤

፲፪፡ መዓልተ ሌሊተ ኮነኒ ፤

ቀኑ ሌሊት ሆነብኝ ማለት ደጅ ዘግተውበት ይሔዳሉና ፤

ወጽልመት ውስተ ገጸ ብርሃን ገብ ዓኒ ፤

ጨለማው ብርሃን ወደመሆን ተመለሰብኝ አለ፣ ዕንቅልፍ አይ ወስደውምና ፤

፲፫፡ ወእመሂ ጐንደይኩ ዳዕሙ መቃ ብር ቤትየ ፤

በዚህ ዓለም ብዘገይ ነገር ግን መቃብር ቤቴ ነው፤ ውሎ ውሎ ከቤት፣ ኑሮ ኑሮ ከመሬት እን ዲሉ ፤

ወውስተ ጽልመት ተነጽፈ ምስካብየ፣

መኝታዬ በጨለማ ሆነ ፤

፲፬፡ ለሞትሂ አቡየ እብሎ ፤

ሞትን አባቴ እለዋለሁ፤ አባት እንዲወደድ እወደዋለሁ ፤

እምየሂ ወአኃውየ ዕጌያት እሙንቱ፣

እናት ወንድም እንዲወደድ ዕጌ ያትን እወዳቸዋለሁ አለ፣ ዋጋ ያሰጡታልና ፤ እንድም እናት ወንድም ከበው እንዲያስታምሙ ከበው ይዘውታልና ፤

፲፭፡ አይቴ ውእቱ እንከ ተስፋየ ፤

እንግዲህ ወዲህ አለኝታዬ ወዴት ነው ፤

እፌእያኑ ዓዲ ለሠናይትየ ፤

ዳግመኛ ተድላ ደስታዬን አያት ይሆን ፤

፲፮፡ ወትወርድኑ ኀቡረ ውስተ መሬት ምስሌየ ፤

ከኔ ጋራ ወደ መቃብር ትወርድ ይሆን ፤

ወንደፌንኑ ኀቡረ ውስተ መሬት ፤

አንድ ሁነን በመቃብር እንቀ በር ይሆን ማለት ሳላጣ እሞት ይሆን ።

## ምዕራፍ ፲፰

አሥራ ስምንተኛው ምዕራፍ ይህ ነው ፤

### ጉባዔ

፩፡ ኀበ ተናገረ በልዳዶስ ተሰጥወ ወይቤ ፤

በልዳዶስ ከተናገረ ዘንድ መለሰ እንዲህ አለ ፤

፪፡ እስከ ምንትኑ ኢታረምም ፤

ዝም የማትል ምን እስቲሆን ድረስ ነው? አንድም ዝም የማ ትል እስከ መቼ ድረስ ነው ፤



ተአገሥ ንንግርከ ንሕነኒ ፤

እኛም እንነግርህ ዘንድ ዝም በል ፤

፫፡ ለምንትኑ ከመ እንስሳ አርመምነ ቅድሜከ ፤

በፊትህ እንደ እንስሳ ዝም ያልን ልንመስልህ ነው እንጂ ላንመስ ልህ ዝም ያልን ይመስልሃል ?

፬፡ ይደልዋ ለመቅሠፍትከ ፤

መከራ ባንት ልትመጣ ይገባ ታል፤ አንድም ትደልዋ ለመቅ ሠፍትከ ለመከራህ ትገባታለህ አንድም ይደልወከ መቅሠፍትከ መከራ ባንት መምጣት ይገባ ዋል ፤

ምንትኑ አንተ ለእመ ሞትከ ፤

ለሞትሂ አቡየ እብሎ ብሎ ነበ ርና አንተ ብትሞት ምንድነው? አንድም አንተ ሞትክና ምን ይሁን ? ምን ይደረግ ?

አልቦኑ ዘይኄይስ እምኔከ በታሕተ ሰማይ ፤

ለሞትሂ አቡየ እብሎ እምየሂ ወአኃውየ ዕጌያት ብሎ ነበርና ከሰማይ በታች በዚህ ዓለም ካንተ የሚበልጥ የለምን ፤

ይወድቁኑ አድባር እመሠረቶሙ ፤

አንተ ሞትህና ተራሮች ያልፉ ሉን፤ አንድም ይደቁኑ ፣ አንተ ሞትህና ተራሮች ያልፉን? አን ድም ስንኳን አንተ ተራሮች ያልፋሉ ፤

፭፡ ወይጠፍዕ ብርሃነ ኃጥአን ፤

የኃጥአን ተድላ ደስታቸው ይጠ ፋል፣ ያንተም እንደዚያው ጠፋ፤

ወኢይትከበት እከዮሙ ፤

ክፋታቸው አይሠወርም ፤

፮፡ ወብርሃኖሙ ጽልመተ ይከው ኖሙ ፤

ተድላቸው ደስታቸው በመከራ ይለወጥባቸዋል ፤

ይጌግጹ ወማኅቶቶሙ ትጠፍዕ ፤

ተግ ተግ ይላሉ፣ ተድላ ደስታ ቸው ትጠፋለች፤ አንድም ማኅ ተቶሙ ይላል፣ ከዚህ ይህ ቀረ እያሉ ኃጢአት መሥራታቸው ትቀራለች ፤

፯፡ ወይነሥኡ ንዋዮ ትሑታን ፤

እሱ ሙቶ ገንዘቡን ባለጾች ይወስዱታል ፤

ወትድኀዕ ምክሩ ፤

ምክሩ ትጠፋለች ፤

፰፡ ወትወርድ እግሩ ውስተ መሥገ ርት ወትትአሠር በመሥገርት ፤

ውስተ መሥገርትና በመሥገ ርት አንድ ወገን ነው፤ ሰውነቱ በመከራ ትያዛለች ፤

www.ethiopianorthodox.org

፱፡ ወይመጽእ መሥገርት ላዕሌሁ፤

መከራ ይመጣበታል ፤

ወይመጽኡ ጽኑዓን ላዕሌሁ ፤

ጠላቶቹ ፡ አንድም አጋንንት ወደሱ ይመጣሉ ፤

፲፡ ወኅቡዕ ውስተ ምድር ሐብሉ ፤

አንጋዳው በመሬት የተሠወረ ነው ማለት መከራ በሰውነቱ የተሠወረ ነው ፡

ወይስሕብዎ እምፍኖቱ ፤

ከጐዳናው እየጐተቱ በሞት ይወ ስዱታል ፡

፲፩፡ ወያጠፍዎ ሕማም እምዓውዱ፤

መከራው ወገኖቹን ያጠፋል፤

ወመጽኡ ብዙኃን ታሕተ እገሪሁ በዓ ቢይ ረሀብ ፤

ብዙ ሰዎች በጽኑ ረሀብ ተይ ዘው ያበላናል ያጠጣናል ብለው መጡ፤ ሳታበላ ሳታጠጣ ሰደድ ኻቸው፤ አንተም በዚህ ምክን ያት መከራ መጣብህ ፤

፲፪፡ ወጽኑሕ ሎቱ ኃጣር ዕፁብ ፤

ጽኑ መከራ ደጅ ይጠናዋል፤ የእ ግሩ አገዳ ይበሰብሳል ፤

፲፫፡ ወይበልዖ ሞት ምስናዮ ፤

ገንዘቡን አሕዛብ፤ ሰውነቱን ዕፄ ያት፤ ምግባሩን አጋንንት ያጠ ፉታል ፤

፲፬፡ ወይነቅዑ እምሥጋሁ ዕፄያት፤

ዕፄያት ከአካሉ ይፈስሳሉ ፤

ወትፀንዕ ምንዳቤሁ ወይትቤቀሎ እግዚአብሔር ፤

መከራው ትፀናለች፤ እግዚአብ ሔር ይበቀለዋል ፤

፲፭፡ ወይትአያ ውስተ ቤቱ በሌሊት፤

በሌሊተ መከራ ተይዞ ሳለ፡ አን ድም በመቃብር ይዘጋል፡

ወይዘርዎ ምስናዮ ፈጣሪሁ ፤

ፈጣሪው ገንዘቡን፡ አንድም ሥጋ ውን ያጠፋዋል ፡

፲፮፡ ወይየብስ ሥረዊሁ እምታሕቴሁ፤

አባትነቱ ይጠፋል ፤

ወይወድቅ ፍሬሁ እምላዕሌሁ ፤

ልጁ፤ የልጅ ልጁ ይጠፋል ፡

፲፯፡ ወይጠፍዕ እምድር ዝክሩ ፤

አጠራሩ ከዚህ ዓለም ይጠፋል፤ ይኸውም ልማድ ነው፤ ያንተም እንዲህ ይጠፋል ፤

ወይርሕቅ ስሙ ነዋኀ ፤

ስሙ ፈጽሞ ይጠፋል ፤

፲፰፡ ወያፈልስዎ እምብርሃን ውስተ ጽልመት ፤

ከተድላ ከደስታ ወደ መከራ ወደኀዘን ይወስዱታል ፤



ወአልቦ ዘይምሕሮ እምሕዝቡ ፤

ከወገኖቹ ለሱ የሚራራለት የለም፤ አንድም እሱ ለወገኖቹ አያዝ ንም ፡

፲፱፡ ወኢይድኅን ቤቱ በታሕተ ሰማይ ፤

ከሰማይ በታች ያለ ቤቱ፡ አን ድም ወገኑ ይጠፋል ፤

ወባዕድ ይዴሎ በንዋየ ዚአሁ ፤

በሱ ገንዘብ ሌላ ተድላ ደስታ ያደርግበታል ፤

፳፡ ወገዓረ ነዳይ በእንቲአሁ ፤

ኀቤሁ ሲል ነው፤ ድኃው ያበላ ኛል ያጠጣኛል ብሎ በሱ ጮኸ በት ፤

ወአንከርዎ ዓበይትኒ ፤

ደጋጎችም አደነቁት ፤

፳፩፡ ከመዝ ውእቱ ቤተ ዓማፅያን፤

ሕገ እግዚአብሔርን ያፈረሱ ሰዎች ቤታቸው፤ ወገናቸው እን ዲህ ይጠፋል ፤

ወዝውእቱ ግዕዞሙ ለእለ ኢየአምርዎ ለእግዚአብሔር ፤

እግዚአብሔርን በሕግ በአምል ኮት የማያውቁት ሰዎች ግብሩ ቸው ይህ ነው ።

## ምዕራፍ ፲፱

አሥራ ዘጠነኛው ምዕራፍ ይህ ነው ፡

ገባዔ

፩፡ ኅበ ተናገረ ኢዮብ ተሰጥወ ወይቤ፤

ኢዮብ ከተናገረ ዘንድ መለሰ፤ እንዲህ አለ ፤

፪፡ እስከ ምንትኑ ታሔዕርዋ ለነፍስየ፤

ሰውነቴን ምን እስቲሆን ታደክ ሚታላችሁ፤ አንድም እስከ መቼ ድረስ ታስጨንቋታላችሁ ፡

ወትቀትሉኒ በነገርክሙ ፤

ምንትኑ አንተ ለእመ ሞትከ ብሎ ነበርና በነገራችሁ እስከ መቼ ድረስ ታጠፉኛላችሁ ፡

፮፡ አእምሩ ዳዕሙ ከመ እግዚአብ ሔር ዘንተ ይሬስየኒ ፤

እንዲህ ያደረገኝ እግዚአብሔር እንደሆነ እወቁ እንጂ፡ አንድም ነገር ግን እግዚአብሔር እንደ ሆነ እወቁ፡

ትትላከኩዩኒ ወኢተሐፍሩ ትቀሙ ላዕለ ነፍስየ ፤

ትከራከሩኛላችሁና በጠላትነት ስትነሱብኝ አታፍሩም ፡

፯፡ አሆ እንከ አነ አበስኩ አማን ፤

ይህ ሁሉ ኃጥእ ነኝ በል ብላ ችሁ አይደለም የምታደክሙኝ እነሆ እኔ በእውነት በደልሁ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ወነቤየ ኃደረት እበድ ወነበብኩ ቃለ ዘኢየአምር ፣

ስንፍና በኔ አደረች፡ ከእግዚአብሔር ጋራ በተከራከርሁ ብዬ ተናገርሁ ፡

ወነገርየኒ ዕበድ ወአከሰ ዘእዘልፍ ፣

ነገሬ የስንፍና ነገር ነው፡ እናንተን የምነቅፍ አይደለም ፡ አንድም ነገር ግን እናንተን ደስ ይበላችሁ ብዬ ነው እንጂ ራሴን የምዘልፍ አይደለም ፡

፭፡ አሌ ሊተ በላዕሌየ ዳዕሙ ተዓብዩ አፉክሙ ፣

ኃጢአትስ ብሠራ እኔ ወዮልኝ፣ እንጂ እናንተ ምን ዕዳችሁ ፡ አንድም እንደበታችሁን ከፍ ከፍ አድርጋችሁ ትናገሩላችሁና ለኔ ወዮልኝ ፡

ወትትቄናደዩ ብየ ወትዘረክዩኒ ፣

ትጫወቱብኛላችሁ፣ ትሰድቡኛላችሁና ወዮልኝ ፡

፮፡ አእምሩ ዳዕሙ ከመ እግዚአብሔር ዘሆከኒ ፣

ነገር ግን በመከራ ያወከኝ እግዚአብሔር እንደሆነ ዕወቁ፡

ወአንሐ መዓቶ ላዕሌየ ፣

መዓቱን በኔ ላይ አበዛ፣ አፀና፡

፯፡ ናሁ እሠርሕ በኒስ ፣

እነሆ በፀብ በክርክር ደከምሁ፡

እነግር ወአዓወዩ ወአልቦ ዘይፈትሕ ሊተ ፣

ግፌን እናገራለሁ፣ እጮኻለሁ የሚፈርድልኝ የለም ፡

፰፡ ወተሐንፀ ዓውድየ ፣

ዙሪያዬ ታነፀ ፡

ወአልብየ ምንሳፍ ፣

መቃብሩን የሚያሳልፈኝ የለም፡ አንድም ተሐፅረ ዓውድየ ይላል የከብት፣ የልጅ ጥፋት አገኘኝ፣ መከራውን የሚያርቅልኝ የለም፡

ወአንጦልዓ ውስተ ገጽየ ጽልመት፣

መከራ ፊቴን ሸፈነኝ ፡

፱፡ ወሰለበኒ ትርሚትየ ፣

ሽልማቴን ገፈፈኝ፣ ደዌና ሽልማት አይስማማምና ፡

ወአእተተ አክሊልየ እምርእስየ ፣

ዘውዴን ከራሴ አራቀ፡ አንድም ተድላውን ደስታውን ከኔ አራቀ፡

፲፡ ወመሐወኒ እንተ ኵለሄ ወአልሖስ ፣

እንዘ እልሕስ ሲል ነው፡ ከጥዒና በደዌ ፣ ከሕይወት በሞት ስሰደድ ፣ በልጅ፣ በከብት ጥፋት ነቀለኝ ፡

ወገዘማ ከመ ዕፅ ለሕይወትየ ፣

ሰውነቴን እንደ እንጨት ቆረጣት ፡



፲፩፡ ወረሰየኒ ለኃያል መቅሠፍት ፣

ለጽኑ መከራ አሳልፎ ሰጠኝ ፣ አንድም ኃያል እግዚአብሔር ለመከራ ሰጠኝ ፡

ወረሰየኒ ከመ ፀር ፣

እኔን ወዳጁን እንደጠላት አደረገኝ ፡

፲፪፡ ወኅቡረ መጽአ ላዕሌየ መዓቱ፣

መዓቱ በኔ ላይ አንድ ሆኖ መጣ፡ የልጅ፣ የከብት የራሱ ጥፋት፡

ወዓገቱኒ ውስተ ፍናውየ እለ ይጸንሑኒ ፣

ከዛሬ ነገ ያጠፋናል ብለው የሚጠብቁኝ አሕዛብ ከበቡኝ፡ አንድም ዕዬየት ከበቡኝ፡ አንድም ይስትን አይስትን ብለው የሚጠብቁኝ አጋንንት ከበቡኝ፡

፲፫፡ ወአኃውየኒ ተናከሩኒ ወአብደሩ ነኪረ እምኔየ ፣

ወንድሞቼም ባዕድ ሆኑኝ፣ ከኔ ይልቅ ሌላውን ወደዱ ፡

ወአዕርክትየኒ ኢመሐሩኒ ፣

ወዳጆቼም አላዘኑልኝም ፡

፲፬፡ ወአዝማድየኒ ኢየንከሩኒ ፣

ዘመዶቼም መከራዬን አይተው አላደነቁኝም ፡

ወእለሂ የአምሩ ስምየ ረስዑኒ ፣

ስሜን የሚያውቁ ሁሉ ዘነጉኝ፡

፲፭፡ ወእለሂ ቅሩባንየ ኢይፈቅዱ ይርአዩኒ ፣

አቅራቢያዎቼ የሚሆኑ ሁሉ ሊያዩኝ አይወዱም ፡

ወከመ እምካልዕ ሕዝብ ያመስሉኒ፣

ከሌላ እንደተወለድኩ ያስመስሉኛል ፡

፲፮፡ ለነባሪየኒ እጼውዖሙ ወይጸመሙኒ ፣

ቤተሰቦቼን ውሀ በቅል፣ እሳት በገል ያመጡልኝ ዘንድ እጠራቸዋለሁ፣ ቸል ይሉኛል ፡

፲፯፡ ለብእሲትየኒ እትጋነይ ላቲ ወእየውሃ ፣

ሚስቴንም እማልዳታለሁ፣ አለዝባታለሁ፣ ቸል ትለኛለች፡

፲፰፡ ወአሰተበቍዖሙ ለደቂቀ ገዛዕየ ወአስተምህር ሎሙ ወቀብዑኒ ለዓለም ፣

የቤተሰቦቼን ልጆች እማልዳቸዋለሁ፣ እለምናቸዋለሁ፣ ፊጽመው ቸል ይሉኛል፣ ተስፋ ቆረጡብኝ፡

ወሶበሂ እትነሣእ የሐምዩኒ ፣

ተኝቼም በተነሣሁ ጊዜ ሲያሙኝ አገኛቸዋለሁ፡ አንድም ተበረታትቼም ብነሣ ይህ ዘብዛባ ተነሣ ይሉኛል ፡

፲፱፡ ወእለሂ የአምሩኒ ያስቈርሩኒ፣

የሚያውቁኝ፣ የሚወዱኝ ሁሉ ይጸየፉኛል ፡

www.ethiopianorthodox.org

እለሂ አፈቅሮሙ ተንሥኡ ላዕለ ነፍስየ ፤

የምወዳቸውም ሰዎች በሰውነቴ ላይ በጠላትነት ተነሡ ፡

፳፡ ወይትቤዐል ማዕስየ ምስለ ሥጋየ ፤

የነዚያስ ይቅርና ሰውነቴ እየተቆራረጠ ወደቀ ፡

የሐቅየኒ አዕፅምትየ ፤

አጥንቴን ይፈጨኛል ፡

፳፩፡ መሐሩኒ መሐሩኒ አዕርክትየ እስመ እደ እግዚአብሔር ውእቱ ዘገሠሠኒ ፤

በመከራ የዳሰሰኝ የእግዚአብሔር እጅ ነውና ፡ ወዳጆቼ ይቅር በሉኝ ፤ ይቅር በሉኝ ፡

፳፪፡ ለምንት ታሠርሑኒ አንትሙ ከመ እግዚአብሔር ፤

እግዚአብሔር በመከራ እንዳደከመኝ ለምን ታደክሙኛላችሁ ፡

ወኢትጸግቡኑ እምሥጋየ ፤

ምንት አንተ ለእመ ሞትከ ብሎ ነበርና ብሞት ሥጋዬን የምት በሉኝ ነው፡ አንድም ብታሙኝ ብታሙኝ አትጠግቡምን፡ አን ድም ገንዘቤን ብትወስዱ ብት ወስዱ አይበቃችሁም ፡

፳፫፡ መኑ እምጸሐፎ ለነገርየ ወይል ክዖ ውስተ መጽሐፍ ዘለዓለም ውስተ ምጽሐለ ሐፂን ወዓረር ፤

ሲሰለቹት አይቶ ነገሬን ለዘለዓ ለም በሚኖር፡ በርሳስ በብረት ሰሌዳ ማን በጻፈው ነበር፤ በዚህ ጊዜ ኤልዩስ ተነሥቶ ጽፎታል፡

፳፬፡ ወእመ አኮ ይገልፍዎ ውስተ ኩኵሕ፤

ይሕም ባይሆን ባለት ደንጊያ ማን በቀረፀው ነበር፡ በብረት፤ በደንጊያ የተቀረፀ እንዳይጠፋ አድርጎ ማን በቀረፀልኝ ነበር ፡

፳፭፡ አአምር ባሕቱ ከመ ኢየገምሮ ቤት ለዘሀለዎ ይፈውሰኒ ሕያው ፤

ነገር ግን በሥጋ ያድነኝ ዘንድ ያለው እግዚአብሔር የሚሰጠ ኝን ገንዘብ ቤት እንዳይችለው አውቃለሁ ፡ አንድም በነፍስ ያድነኝ ዘንድ ያለው እግዚአብ ሔር በሰውነቱ እንጂ በመለኮቱ ዓለም እንዳይወስነው አውቃለሁ፡

ዘይቀውም ድኅረ ውስተ ምድር ፤

በዚህ ዓለም ኋላ የሚደረግ ፡

፳፮፡ ወእንዘ ሀሎኩ ዓዲ ዲበ ምድር ይትቄለጥ ማዕስየ ፤

ዳግመኛ በዚህ ዓለም ሳለሁ ሰው ነቴ በሕይወት ይለወጣል፡

ዝኒ እምነበ እግዚአብሔር መጽአኒ፤

ይህ ሀብተ ትንቢቱ ከእግዚአ ብሔር ዘንድ መጣልኝ፡ አንድም



ዝኒ መጽአኒ እምነበ መጽአኒ ይላል፡ ይህ ሀብተ ትንቢቱ ከመ ጣልኝ ከእግዚአብሔር ሀብተ ፈውስ መጣልኝ ፡

፳፯፡ ዘለልየ አአምር ፤

እኔ የማውቀው ከሱ በቀር ሰው ነቱን የሚያውቀው ሌላ የለምና፡

ዘዓይንየ ርእየት ወአኮ ባዕድ ፤

ትንቢቱን የተናገርሁ እኔ ነኝ ሌላ የተናገረው አይደለም ፡

ሠለጡኒ ኵሉ ውስተ ሕዕንየ ፤

ሥላሴ ብዕሉንም ደዌውንም አስጐረጐሱኝ ፡

፳፰፡ እመሰ ትብሉ ምንተ ንነግር ቅድሜሁ ፤

በፊቱ ምን እንናገራለን ትሉ እንደሆነ ፡

ወንረክብ ሥርወ ነገር ሎቱ ፍርሀዎ አንትሙ ለኃሣር ፤

ታሪክ ተርከን፤ ጥቅስ ጠቅሰን የምንነግረው ወዴት እናገኛለን ትሉ እንደሆነ መከራውን ፍሩት እናንተም ለኃሣር ትሆናላችሁ፡

፳፱፡ እስመ መቅሠፍት ትመጽአሙ ለኃጥአን አሚሃ የአምሩ ከሎ እከዮሙ እምአይቴ ዘበጽሖሙ ፤

በኃጥአን መከራ ትመጣባቸዋ ለችና ያን ጊዜ መከራውን ሁሉ ከየትም እንዳመጣባቸው ያው ቃሉ ::

## ምዕራፍ ፳

ሐያኛው ምዕራፍ ይህ ነው፡

ጉባዔ

፩፡ ነበ ተናገረ ሳፋር ተሰጥወ ወይቤ፤

ሳፋር ከተናገረ ዘንድ መለሰ፤ እንዲህ አለ፡ አንድም ሲገባው ሲመልስ እንዲህ አለ ፡

፪፡ ኢኃዘብኩከ ትንብብ ከመዝ ፤

እንዲህ ያለ ነገር ትናገራለህ ብዬ አላሰብሁም እንዲህ ያለ አዋቂ ነህ ?

ወአልቦ ዘትኄይስ እምኔየ አእምሮ፤

ነገር ግን በዕውቀት ከኔ አትበ ልጥም፡ አንድም ምንም ከኔ አት በልጥም፡ አንድም ነገሩ እንዲህ አላዋቂ ነህ ?

፫፡ ስምዓኒ ጥበበ ትምህርትየ ፤

በትምህርት ያገኘሁትን ጥበቤን ስማኝ ፡

ወያወሥአኒ መንፈስ ሕሊናየ ፤

የልቡናዬ ዕውቀት ይመልስል ኛል ማለት እንደ አንተ ጠለፍ አድርጌ አልናገርም ፡

፬፡ ቦኑ ዘተአምር ዘከመዝ እምቅድ ሚከ ወእምአሚከ እምአመ ተፈጥረ ሰብእ ዲበ ምድር ፤

ከእግዚአብሔር ጋራ በተከራከ ርሁ ያልሕ ከአንተ አስቀድሞ

www.ethiopianorthodox.org

ወኢያደምእ ፍትወቶ ፤

የሚወደው ባለጸግነቱን አያገኘውም ፤

፳፩፡ ወአልቦ ትራፍ ለብዕሉ ፤

ከገንዘቡ የሚቀርለት የለም ፤ አንድም ከገንዘብህ የሚቀርልህ የለም ፤

በእንተዝ ኢትሠምር ሠናይቱ ፤

ስለዚህ ተድላ ደስታው የበጀች አትሆንም፤ አንድም ባለጸግነቱ አትፀናም ፤

፳፪፡ ወአመ ይቢ ሠለጥኩ አሚሃ ይትመነደብ ፤

ፈጽሜ ከበርሁ ባለ ጊዜ ያን ጊዜ በመከራ ይጨነቃል ፤

ወይመጽእ ኵሉ ሕማም ዘያጸግባ ለከርሡ ፤

ሰውነቱን የሚያስጨንቅ መከራ ይመጣበታል ፤

፳፫፡ ወይትዌስክ መቅሠፍተ መዓቱ፤

የጌታ መዓቱ መቅሠፍቱ ቀጥሎ ቀጥሎ ይመጣበታል ፤

ወይተግህ ላዕሌሁ ዘየሐምም ፤

መከራ የሚያፀናበት ሰይጣን ዕፄ አሕዛብ በሱ ላይ ይተጋል ፤

፳፬፡ ወኢያመሥጥ እምእደ ኵናት፤

እምአፈ ኵናት ሲል ነው ፤ ከጦር አንደበት አያመልጥም፤

ወይበረብሮ ቀስተ ብርት ፤

ቀስት ይነድፈዋል ፤ አንድም ትል ይበላዋል ፤

፳፭፡ ወየኃልፍ ሐፅ ውስተ ሥጋሁ፤

በሰውነቱ ፍላፃ ይወረወራል፤ አንድም በሥጋው ትል ይፈላበታል፤

ወያንሶሱ እኩይ ውስተ ነፍስቱ ፤

በሰውነቱ ትል ይመላለስበታል፤

ወበላዕሌሁ ዘያደነግፆ ፤

የሚያስደነግጠው ብሔሞት ይመጣበታል ፤ አንድም ዕፄ ይመጣበታል ፤

፳፮፡ ወይጸንሖ ኵሉ ጽልመት ፤

መከራ ደጅ ይጠናዋል ፤

ወይበልዖ እሳት ዘአንደደ ፤

የሠራው ኃጢአት ያጠፋዋል፤

ወይትጋየያ ኀረቤቱ ፤

በገንዘቡ ኀረቤቱ ያጌጥበታል ፤ አንድም ኀረቤቱ ይለገድበታል ማለት ይዘብትበታል ፤

፳፯፡ ወይከሥት ሰማይ ጌጋዮ ፤

ወወረደት እሳት እምሰማይ ብሎ ነበርና ሰማይ ኃጢአቱን ይገልጥበታል ፤ አንድም ሰማያዊ እግዚአብሔር ኃጢአቱን ይገልጥበታል ፤

ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ቤተ መጻሕፍት



ወምድርኒ ኢትነሥእ ፤

ምድርም አትቀበለውም ማለት ልጆቹ አልተቀበሩምና፤ አንድም ምድርኒ ትትነሣእ ላዕሌሁ ይላል አሕዛብ ገንዘቡን ይወስዱበታል፤

፳፰፡ ወሞት ይስሕባ ለቤቱ ለዝሉፉ፤

ሞት ወደቤቱ ተስቦ ይገባል ፤ አንድም ወይስሕቦ ሞት እም ቤቱ፤ ሞት ከወገኖቹ ለይቶ ስቦ ጎትቶ ይወስደዋል፤

ወትመጽእ ዕለተ መንሡት ፤

ዕለተ መከራ ትመጣበታለች፤

፳፱፡ ዝውእቱ መክፈልቱ ለብእሲ ኃጥእ እምኀበ እግዚአብሔር፤

ከእግዚአብሔር ዘንድ ታዞ የሚመጣበት የኃጥእ ሰው ጽዋዓ ተርታው፤ እድል ፈንታው ይህ ነው፡

ወንዋዩሂ ዘአጥረዮ እምኀበ ፈጣሪሁ፤

ትጠፍዕ ያለበት ነው፤ ከፈጣሪው ዘንድ ያገኘው ገንዘቡ ይጠፋል።

## ምዕራፍ ፳፩

ሐያ አንደኛው ምዕራፍ ይህ ነው ፤

### ጉባዔ

፩፡ ወአደ ተናገረ ኢዮብ ወተሰጥወ ወይቤ ፤

ኢዮብ ከተናገረ ዘንድ መለሰ፤ እንዲህ አለ ፤

፪፡ ስምዑኒ ወአዕምዑኒ ነገርየ ፤

እኛ እናረጋጋዋለን እንዳትሉ ነገሬን ስሙኝ ፤ አድምጡኝ ፤

፫፡ ከመ ኢትበሉ ንሕነ ንናዝዞ አርምሙ እንግርክሙ ፤

እኛ እናጽናናዋለን እናረጋጋዋለን እንዳትሉ እነግራችሁ ዘንድ ነገሬን ስሙ ፤

እስመ ዘትስሕቁኒ ዘእኮ ሰብእ ዘይዛለፈኒ ፤

ይህን የምትዘብቱብኝን ደዌ የመጣብኝ እግዚአብሔር ነው እንጂ ሰው አይደለምና እነግራችሁ ዘንድ ስሙ ፤

ወእፎ ዘኢይትመዓዕ ፤

እንዴት አልቈጣ ፤

፭፡ ትኔጽሩኒ ወታነክሩኒ ፤

እኔን አይታችሁ ታደንቃላችሁ፡

ወትትመላትሁ በእደዊክሙ ፤

በእጃችሁ ትጠቃቀሱብኛላችሁ፤

፮፡ እመሂ ተዘከርኩ ተዘለፍኩ ፤

ከእግዚአብሔር ጋራ በተከራከርሁ ብልም በዚያውም ፍዳዬን ተቀበልሁ፤

ወኀዱር ውስተ ሥጋየ ፃዕር ፤

ቁርጥማት በሰውነቴ ጸንቶ ይኖራል ፤

www.ethiopianorthodox.org

፯፡ ለምንት ኃጥአን የሐይዉ ፤

ፍዳ መቀበልማ በዚህ ዓለም ከሆነ ኃጥአን በተድላ በደስታ ለምን ይኖራሉ ?

ወይረስዑ ውስተ ብዕሎሙ ፤

በባለጸግነታቸው እንደምን ፀን ተው ይኖራሉ ፤

፰፡ እመሂ ዘርዑ ይሠምር በቅድሜ ሆሙ ፤

ቢዘሩስ በፊታቸው የበጀ ለምን ይሆናል ?፤

ወውሉዶሙኒ ይመልዑ ዓይነ በቅድ ሜሆሙ ፤

ልጆቻቸው በፊታቸው ምሉዕ ይሆናሉ፤ አንድም ዓይን ሙሉ ልጅ ለምን ይወልዳሉ፤

፱፡ ወአብያቲሆሙኒ ምሉዕ ፤

ቤታቸው ባለጸግነትን መልቶ ለምን ይኖራል ፤

ወአልቦ ዘያደነግፆሙ ፤

ምነው የሚያስደነግጣቸው የለም ፤

ወኢይመጽአሙ መቅሠፍት እምኀበ እግዚአብሔር ፤

ምነው ከእግዚአብሔር ዘንድ ታዞ መዓት መቅሠፍት አይመ ጣባቸው ፤

፲፡ ወአልሕምቲሆሙኒ ኢይመክና፤

ምነው ላሞቻቸው አይመክኑ፤

ወጽኑሳቲሆሙኒ ኢያድኀፃ ፤

ምነው የፀነሱትን አያስወርዳ ቸው ፤

ወይድኅና በኀርሶን ፤

ምነው ባራስነት ሳሉ ይድናሉ፤

፲፩፡ ወይዜወሩ ከመ አባግዕ ዘለዓለም፤

እንደ በግ ተጠብቀው ለምን ይኖራሉ ፤

ወደቂቆሙኒ ይትዋነዩ ወይነብሩ ወይ ሰነቅዉ ፤

ልጆቻቸውስ መሰንቆውን፤ በገና ውን እየመቱ ለምን ይዘፍናሉ?

፲፪፡ ወይትፌሥሑ በቃለ ማኅሌ ቶሙ ፤

በልጆቻቸው ዘፈን፤ አንድም በራ ሳቸው ዘፈን ለምን ደስ ይላቸ ዋል ፤

፲፫፡ ወፈጸሞሙ መዋዕሊሆሙ እንዘ ይትፌግዑ ውስተ ምስካበ ሲኦል ይነ ውሙ ፤

ነገር ግን ለጊዜው እንዲህ አልሁ እንጂ ደስ ብሏቸው ሳሉ በተፈ ጥሮ የተሰጣቸውን ዘመን ጨር ሰው በመቃብር ይጋደማሉ ፤

፲፬፡ ወይቤልዎ ለእግዚአብሔር ረኃቅ እምኔነ ፤

እግዚአብሔርን ይወዱታል እን ዳልል ከኛ ራቅ ይሉታል፤



ኢንፈቅድ ንርአይ ፍኖተከ ፤

ሕግህን እንጠብቅ ዘንድ አንወ ድም ፤

፲፭፡ ምንተ ይክል ከመ ንትቀነይ ሎቱ ፤

ለሱ እንገዛለት ዘንድ ምን ማድ ረግ ይቻለዋል ፤

ወምንት ይበቍዓነ ከመ ንሑር ኀቤሁ፤

በሕግ በአምልኮት ወደሱ እንቀ ርብ ዘንድ ምን ይረባናል፤ ምን ይጠቅመናል ይላሉ ፤

፲፮፡ ወውስተ እደዊሆሙ ሀለወት ሠናይቶሙ ፤

እንዲህ እያደረጉ ባለጸግነታቸው ፀንታ ትኖራለች ፤

ወኢይኔጽር ምግባሮሙ ለኃጥአን ፤

የኃጥአንን ባለጸግነታቸውን አያ ጠፋም ፤

፲፯፡ ወባሕቱ ትጠፍዕ ማኅበሮሙ ለረሲዓን ፤

ነገር ግን ለጊዜው እንዲህ አልሁ እንጂ ሕገ እግዚአብሔርን የዘ ነጉ ሰዎች ወገናቸው ትጠፋ ለች ፤

ወትበጽሖሙ ዕልወቶሙ ፤

ኃጢአታቸው መከራ ይዛ ትመ ጣባቸዋለች ፤

ወይበጽሖሙ ምንዳቤ ወመቅሠፍት፤

መከራ ፤ ፀዋትወ መከራ ትመ ጣባቸዋለች ፤

፲፰፡ ወይከውኑ ከመ ሐሠር ዘቅድመ ገጸ ነፋስ ፤

በነፋስ ፊት እንዳለ ገለባ ይሆ ናሉ ፤

ወከመ ፀበል ዘይነሥእ ነፋስ ዓውሎ፤

ነፋስ ዓውሎ እንደሚበትነው ትቢያ ይሆናሉ ፤

፲፱፡ ወኢይረክቡ ንዋዮሂ ደቂቆ ፤

የክፉ ሰው ልጆች ገንዘቡን አያ ገኙትም ፤

ወይትቤቀሎሙ እግዚአብሔር ወየአ ምር ሶቤሃ ፤

ጌታ ተበቅሎ ያጠፋቸዋል፤ ያን ጊዜ በኃጢአቱ እንደመጣበት ያውቃል ፤

፳፡ ወይሬእያ አዕይንቲሁ እንዘ ይረ ግዝዎሙ ለደቂቁ በቅድሜሁ ፤

ልጆቹን በፊቱ እየወጉ ሲጥሏ ቸው ዓይኖቹ ያያሉ፤ እንደ ሴዴ ቅያስ ፤

ወእግዚአብሔርኒ ኢያድኀኖሙ ፤

እግዚአብሔርም አያድናቸውም፤

እስመ እንተ ፈቀደ ይገብር በቤቱ ፤

ሰው በቤቱ የወደደውን ያደ ርግ ነበርና፤ አንድም እግዚአብ

www.ethiopianorthodox.org

ሐር በወገኖቹ የወደደውን ያደ
ርጋልና ፤

፳፡ ወይቀብላ እምኍልቄ አውራ
ኂሁ ፣

ዘመኖቹ ከቍጥር ይጐላሉ ፤
ሰባ፣ ሰማንያ ዘመን ተሰጥቶት
ሳለ በሀያ ፣ በሠላሳ ዘመን ይቀ
ሠፋል ፤

፳፩፡ ቀዳሚሁ አኮኑ እግዚአብሔር
ውእቱ ዘይሜህር ምክረ ወጥበበ ፣

ጥንቱንስ ምክርን፣ ጥበብን የሚ
ያስተምር እግዚአብሔር አይደ
ለም ? ማን አሌ ብሎሃል ፤

ወውእቱ ይትቤቀሎ ለቀታሌ ነፍስ፣

ነፍስ ገዳይን ተበቅሎ የሚያጠ
ፋው እሱ ነው ፤

፳፪፡ ወዘሰ ይመውት በብዝኃ የዋሃቱ
እንዘ ይትፌሣሕ ወይዴሎ፣

በውስጥ በአፍአ ደስ ብሎት
በበጐነት ሳለ የሚሞት ፤

ወበውስጡሂ ምሉዕ ስብሐ ፣

ወርቁም ብሩም በቤቱ መልቶ
ሳለ ፤

ወይትከዓው አንጕዑ ፣

ማሩ ቅቤው ሲፈስ ፤ አንድም
ባለጸግነቱ መልቶ ተርፎት ሲያ
በድር ፤

፳፫፡ ወይመውት በምሬረ ነፍሱ ፣

ልቡ አዝኖ ሳለ የሚሞት አለ፤

እንዘ ኢይበልዕ ሠናየ ወኢምንተኒ፣

ምንም ምን የላመ፣ የጣመ ሳይ
ቀምስ፣ የሞቀ የደመቀ ሳይለ
ብስ የሚሞት አለ ፤

፳፬፡ ወከሎሙ ኅቡረ ይነውሙ ውስተ
ምድር ፣

ነገር ግን እንዲህ የሚያደርጉ
ትም ሰጥተው መጽውተው በል
ተው ጠጥተው የሞቱትም ሁሉ
በመቃብር ይጋደማሉ ፤

ወይደፍንዎሙ ዕፄያት ፣

ዕፄያት (ትሎች) ይከቧቸዋል ፤

፳፭፡ ወይእዜኒ አእመርኩ ከመ ተሀ
ቢለክሙ ትቁሙ ላዕለ ነፍስየ ፣

አሁንም ተደፋፍራችሁ በጠላት
ነት በሰውነቴ ላይ እንድትነሡ
አወቅሁ ፤

፳፮፡ ወትብሉ አይቴ ውእቱ ቤተ
መልአክ ፣

ያለቃ የኢዮብ ቤት ወዴት ነው
ትላላችሁ ፤

ወአይቴ ውእቱ ማኅደሪሆሙ ለአብ
ድንተ ኃጥአን ፣

የልጆቹስ መቃብር ወዴት ነው
ትላላችሁ ፣ አልተቀበሩምና ፤

፳፯፡ ተሰአልዎሙ ለኃላፍያነ ፍኖት፣

ጐዳና የሚሄዱትን ጠይቋቸው፤
አንድም ከዚህ ዓለም በሞት
የሚሄዱትን ጠይቋቸው ፤



ወትእምርቶሙ ኢይረክቡ ፣

ምልክቱን አያገኙም ፤ አንድም
ምልክቱን አታገኙም ፣ መጠየ
ቁም የለ፣ መመለሱም የለ ፤

፳፰፡ እስመ ዕለት እኪት ትጸንሖ
ለኃጥእ ፣

ኃጥእን ሰው ዕለተ ሞት ዕለተ
መከራ ትጠብቀዋለችና ፤

ወይወስድዎ ለዕለተ መንሡት ፣

ወደሚጠፋበት ይወስዱታል ፤

፳፱፡ መኑ ይዜንዎ ቅድሜሁ ፍኖቶ፣

ከሱ አስቀድሞ የሚሆነውን የሚ
ነግረው ማነው፤ አንድም እምድ
ኅሬሁ ይላል፤ ከሱ በኋላ ልጅህ
አለቀሰ፣ ቤትህ አፈሰሰ ብሎ
የሚነግረው ማነው ፤

ወመኑ ይፈድዮ ዘለሊሁ ገብረ ፣

ፍዳውን የሚያመጣ ማነው ቢሉ
የሠራው ኃጢአቱ ነው፤ አንድም
የፈጠረው ፈጣሪው ነው፤ አን
ድም ፍዳውን የሚያመጣው
ማነው? የሠራው ኃጢአቱ፣ የፈ
ጠረው ፈጣሪው አይደለምን ፤

፴፡ ወይወስድዎ ኀበ መቃብሩ ፣

ወደሚቀብሩበት ቦታ ይወስዱ
ታል ፤

ወውስተ ነፍቀ ይተግሀ ፣

በሣጥኑ ትል ይፈላል ፤

፴፩፡ ወያስጥሞ ኀዝኃዘ ፈለግ ፣

የእዝኅ ረግረግ ያስጥመዋል ፤

ወይወጽኡ ኵሉ ሰብእ ድኅሬሁ ወቅ
ድሜሁኒ ዘአልቦ ኍልቍ ፣

ቍጥር ስፍር የሌላቸው ሰዎች
ዋይ ሸሸ ተበላሸ እያሉ በፊቱ
በኋላውም ይሄዳሉ ፤

፴፪፡ ለምንትኑ በከ ትጌሥጹኒ ፣

በኃጢአቴ መጣብኝ በል እያላ
ችሁ ለምን ትዘልፉኛላችሁ ፤

በኀቤክሙሰ አልብየ ዕረፍት ፣

በናንተ ዘንድ ዕረፍት የለኝም።

## ምዕራፍ ፳፪

ሐዩ ሁለተኛው ምዕራፍ ይህ
ነው ፤

ጉባዔ

፩፡ ኀበ ተናገረ ኤልፋዝ ወተሰጥወ
ወይቤ ፣

ኤልፋዝ ከተናገረ ዘንድ መለሰ፣
እንዲህ አለ ፤

፪፡ ቀዳሚሁሰ አኮኑ እግዚአብሔር
ውእቱ ዘይሜህር ምክረ ወጥበበ ፣

ቀዳሚሁ አኮኑ እግዚአብሔር
ዘይሜህር ምክረ ወጥበበ ብሎ
ነበርና ጥንቱንስ ማን አሌ ብሎ
ሃል ምክርን ጥበብን የሚያስተ
ምር እግዚአብሔር አይደለም?

፫፤ ወምንተ ያጽሕቅ ለእግዚአብሔር ለእመ አንተ አንጻሕከ ምግባሪከ ፡

አንተ ሥራህን ንጹሕ ካደረግሕ ባንተ መከራ ለማምጣት እግዚ አብሔርን ምን ያተጋዋል? አን ድም አንተ ሥራህን ንጹሕ ብታ ደርግ ለእግዚአብሔር ምን ግዳጅ ይፈጽምለታል? ለራስህ ነው እንጂ ፡

ወምንተ ይረብሖ ለእመ አንተ አር ታዕከ ፍናዊከ ፡

አንተ ሥራህን ካቀናህ ባንተ መከራ ማምጣት ለእግዚአብሔር ምን ይረባዋል? ምን ይጠቅመ ዋል፤ አንድም አንተ ሥራህን ብታቀና ለራስህ ነው እንጂ ለእግዚአብሔር ምን ይረባዋል? ምን ይጠቅመዋል ?

፬፤ ይትሐሰበከኑ ወይትዋቀሠከኑ ፡

ከእግዚአብሔር ጋራ በተከራከ ርሁ ያልህ ከምንስ ከምን ይቈጥ ርሃል? ካንተ ጋራ ይከራከራልን፤

ወየሐውርኑ ይሳነን ምስሌከ ፡

ካንተ ጋራ ይከራከር ዘንድ ይሄ ዳልን ፡

፭፤ ቀዳሚሁ አኮኑ ብዙኅ ውእቱ እከ ይከ ፡

ጥንቱን ክፋትህ ብዙ ነውና ስለዚህ ነው እንጂ ፡

ወአልቦሙ ኊልቍ ለኃጣውኢከ ፡

ኃጢአትህ ስፍር ቍጥር የለው ምና ስለዚህ ነው እንጂ፤

፮፤ ወአኃዝኮ በከንቱ ፡

ከእግዚአብሔር ጋራ ተከራክሬ ማለትን በከንቱ አጽንተህ ያዝ ኸው ፡

ወሰለብኮ ልብሶ ለዕሩቅ ፡

ያለብሰኛል ብሎ ቢመጣ ድኃ ውን ልብሱን ገፍፈኸው፣ ከሆነ በኋላ ለዕሩቅ አለ ፡

፯፤ ማየ ጥቀ ኢያስተይኮ ለፅሙዕ፣

የተጠማውን ሰው ውሀ ስንኳ አላጠጣኸውም ፡

ውኄድኮ አፍዕሞቶ ለርኁብ ፡

የሚበላውን ቀማኸው ፡

ወብእሲ ዘይዘርዕ ሎቱ ምድረ ገጸ መዳልው ያነብር ውስቴታ ፡

ምድርን የሚዘራ ሰው ድምበር አያፈርስም አንተ ግን ድምበር አፈረስህ፣ በዚህ ምክንያት መከራ መጣብህ፤ አንድም ምድርን የሚ ዘራ ሰው አሥራቱን ይሰጣል፤ አንተ ግን አስቀረህ፣ በዚህ ምክ ንያት መከራ መጣብህ፤ አንድም ምድርን የሚጠመን ሰው የም ድር ደሙን፣ ዕርቦውን ገመታ ውን ይሰጣል፤ አንተ ግን አስቀ ረህ ፡ በዚህ ምክንያት መከራ



መጣብህ ፡ አንድም ምድርን የሚያርስ ሰው የገበሬ አበሉን ሲሰውን ፡ ዕርቦውን ይሰጣል ፡ አንተ ግን ውረድ ከማማው፣ ውጣ ከአውድማው ብለህ ሰደ ድኸው፣ በዚህ ምክንያት መከራ አመጣብህ ፡

፰፤ ወበ እለሂ አንከርከ ገጸሙ ፡

ፊታቸውን አይተህ ያደላህላቸው ባለጸጎች አሉ ፡

ወጸላእከ ነዳየ በዲበ ምድር ፡

በፍርድ ፡ በምጽዋት ጊዜ ድኃ ውን ጠላኸው ፡

፱፤ ወአውጻእኮን ዕራቆን ለዕቤራት፣

ያለብሰናል ብለው ቢመጡ ባል ቴቶችን ራቁታቸውን ሰደድኻ ቸው ፡

ወአጽዓርኮ ለእጓለ ማውታ ፡

እናት አባቶቻቸው የሞቱባቸውን መከራ አጸናህባቸው ፡

፲፤ በእንተ ምንትኑመ ዓገተከ መሣ ግር ፡

ይህ ሁሉ መከራ የመጣብህ በምን ምክንያት ይመስልሃል፤

ወሮዱከ ፀባዒት ኃያል ፡

አሕዛብ፤ አንድም ዕዬያት የከበ ቡህ በምን ይመስልሃል? በኃጢ አትህ አይደለም ?፤

፲፩፤ ብርሃንከኒ ጽልመተ ኮነከ ፡

መዓልት ሌሊት ኮነኒ ብሎ ነበ ርና ተድላህ ደስታህ በመከራ ተለወጠ ፡

ወደፈነከ ማይ እንዘ ትነውም ፡

ተኝተህ ሳለ የእዝኅ ውሀ አሰጠ መህ ፡

፲፪፤ ኢኮነሁ ብውህ ልዑል ዘፈቀደ ይግበር ፡

ልዑል እግዚአብሔር የወደደውን ያደርግ ዘንድ የሠጠን አይደ ለም፣ አንድም፤ ኢኮነኑ መባሕት ሎቱ ፡ የወደደውን ያደርግ ዘንድ ለልዑል እግዚአብሔር ሥልጣን የለውምን ?

ወየኃሥሮሙ ለፀዓልያን ፡

የሚሳደቡትን ሰዎች ያዋርዳቸ ዋል ፡

፲፫፤ ወትቤ ምንተ የአምር ኃያል፣

ኃያል እግዚአብሔር ምን ያው ቃል አልህ ፡

ወበላዕለ ጽልመትኑ ይኴንን ፡

ባለ አዋቂነት ይፈርዳልን አልህ፤ አንድም ሳያውቁ በሥሩት ኃጢ አት ይፈርዳልን፤

፲፬፤ ወደመና ይሜውሮ ፡

ደመና ይጋርደዋል አልህ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ዓውደ ሰማይኑ የሐውር ፤

አራቱን መዓዝን ይዞራል አልህ፤ አንድም በአራቱ መዓዝን የሚሠራ ኃጢአትን አያውቅም አልህ ፤

፲፭፤ ፍኖቶሂ ዘለዓለም ተዓቅብ እንተ ኬድዋ ዕደው ጻድቃን ፤

ጻድቃን እነ ኖኅ፣ እነ አብርሃም ፀንተው የኖሩባትን ሕጉን ትጠብቅን እንዲህ እያልህ ስደበው እንጂ ፤

እለ ዓርጉ ዘእንበለ ይትዓወቅ ፤

ምን ምን ኃጢአት ሳይታወቅባቸው የኖሩባት ፤

ከመ ፈለግ ዘይውኅዝ መሠረታቲሆሙ ፤

አባትነታቸው በዝቶ ሳለ ፤

፲፮፤ ወእለ ይብሉ ምንተ ይሬስየነ እግዚአብሔር ፤

እግዚአብሔር ምን ያደርገን ይሆን የሚሉ ፤

ወምንተ ያመጽእ ላዕሌነ ዘኵሎ ይመልክ ፤

ሁሉን የሚገዛ እግዚአብሔር ምን ያመጣብን ይሆን የሚሉ፤

መልዐ ሎሙ አብያቲሆሙ በረከተ፤

ቤታቸው በረከትን የመላላቸው ጻድቃን ፀንተው የኖሩባት ሕግን ትጠብቅን እያልህ ስደበው እንጂ ፤

፲፯፤ ወምክረ ኃጥአንሰ ርኁቅ እምኔሁ ፤

የኃጥአን ምክር ግን ከሱ የራቀ ነው፤ እምኔሆሙ ቢል ለጻድቃን የኃጥአን ምክር ከጻድቃን የራቀ ነው ፤

፲፰፤ ወርእዮሙ ጻድቃን ሰሐቁ ወተሣለቁ ላዕሌሆሙ ንጹሓን ፤

ጻድቃን ንጹሐን አንድ ወገን ፤ ንጹሐን ጻድቃን የኃጥአንን ጥፋት አይተው ደስ አላቸው፤

፲፱፤ ወጠፍዐ ንዋዮሙ ፤

ገንዘባቸው ጠፋ ፤

ዘተረፈሙኒ በልዓት እሳት ፤

እሳት ወድቀት እምሰማይ ብሎ ነበርና የቀረውንም መዓት መቅሠፍት አጠፋው፤

፳፤ እስኩ ኩን እኩየ እመ ትፀንዕ ይሜንየከሁ ፤

እመ አበስኩ ብሎ ነበርና ፀንተህ ትኖር እንደሆነ እስቲ ክፉ ሁን?

ወእመሂ ይሜኒ ፍሬከ ፤

ልጆችህ ይበዙ እንደሆነ ፤

፳፩፤ ሕትቶ ለነገረ አፉሁ ፤

ይልቁንስ ይህን ትተህ ተናግሮ የሠራውን ሕጉን መርምር ፤

ወደይ ቃሎ ውስተ ልብከ ፤

ሕጉን በልቡናህ ያዝ ፤



፳፪፤ ወእመሰ ነሣሕከ ወአሕመምከ ርእሰከ ቅድመ እግዚአብሔር ፤

በእግዚአብሔር ፊት ንስሓ ገብተህ ራስህን ካሣዘንህ ፤

ወአርኃቀ እምልብከ ዓመፃ ፤

ኃጢአትን ከልቡናህ ካራቅህ ሕጉን መርምር፤ አንድም በደልሁ ካልህ ፤

፳፫፤ ይተክለከ ዲበ ኰኵሕ ፤

በጽኑ ረድኤት ይጠብቅሃል፤

ወከመ ዕብነ ፈለግ ይሰፍፍ ፤

እንደ ባሕር አሸዋ ይበዛል፤ አንድም በባብና በፋርፋ እንዳለ ዕንቍ ይሆናል ፤

፳፬፤ ወይረድአከ እምዐርከ ዘኵሎ ይመልክ ፤

ሁሉን የሚገዛ እግዚአብሔር ከጠላቶችህ ይረዳሃል ፤

ወያገብዕ ለከ ንጹሐ ከመ ብሩር ጽሩይ ፤

ባለ ዕዳ ለአበዳሪው የጠራውን ብር እንዲሰጥ ዋጋህን ንጹሕ አድርጎ ይሰጥሃል ፤

፳፭፤ ወትረክብ ሞገሰ በቅድመ እግዚአብሔር ፤

በእግዚአብሔር ፊት ባለሟልነትን ታገኛለህ ፤

ወትኔጽር ሰማየ ተፈሢሐከ ፤

እመኒ ጸደቁ ስዕንኩ አንቃዕድዎ ብሎ ነበርና ደስ ብሎህ ወደሰማይ ታያለህ ፤

፳፮፤ ወዘጸለይከ ኀቤሁ ይሰምዐከ፤

ከሱ ዘንድ የለመንኸውን ልመናህን ይሰማሃል ፤

ወይሁበከ ተምኔተከ ፤

የምትመኘውን ድኅነትን ይሰጥሃል ፤

፳፯፤ ወየዐሥየከ ፍዳ ጽድቅከ ፤

የምግባርህን ዋጋ ይሰጥሃል ፤

ወያበርህ ውስተ ፍናዊከ ፤

በሠራኸው ሥራ ብርሃነ ረድኤቱን ያበራልሃል ፤

፳፰፤ እስመ አሕመምከ ትብል ተዐበየ ፤

መከራ አምጥቶ አሳዝኖሃልና ተዓብየ ትላለህ እንጂ ማለት ያለ ኃጢአቴ አመጣብኝ ትላለህና ስለዚህ ነው እንጂ፤

ወያድኅኖ ለዘያቴሕት ርእሶ ፤

ራሱን የሚያዋርደውን ያድነዋል፤

፳፱፤ ወይባልሖ ለንጹሕ ፤

ንጹሕ ሰውን ያድነዋል ፤

ወትድኅን በንጽሐ እደዊከ ፤

በእጅህ መግደል በቃልህ መበደል ከሌለ ትድናለህ ።

www.ethiopianorthodox.org

# ምዕራፍ ፳፫

ሐዩ ሦስተኛው ምዕራፍ ይህ ነው ፡

ግብዬ

፩፡ ኀበ ተናገረ ኢዮብ ወተሰጥወ ወይቤ ፣

ኢዮብ ከተናገረ ዘንድ መለሰ፣ እንዲህ አለ ፡

፪፡ አእመርኩ እምእዴየ ውእቱ ዘለፋየ ፣

ይህ የመጣብኝ መከራ በተናገርሁት ቃል እንደሆነ አወቅሁ፡

ወአክበደ እዴሁ ላዕሌየ ወአግዓረኒ፣

እደ መዓቱን አፀናብኝ ፣ በመከራ አስጨነቀኝ ፡

፫፡ ምንት ውእቱ ዘኢየአምር ከመ እርከብ ወእብጸሖ እስከ ለዝሉፉ ፣

ከጥንት ያደረግሁትን ኃጢአቴን አገኝ እመረምር ዘንድ የማላውቀው ምንድን ነው ?

፬፡ ወይንግረኒ እመቦ ዘገበርኩ ፣

የሠራሁት ኃጢአት አለ እንደ ሆነ ይንገረኝ ፡

ወኢያረምም አፉየ እንዘ እወቅሥ፣

ያለ ኃጢአቴ አመጣብኝ እያልሁ ስናገር አፌ ዝም አይልም ፡

፭፡ ወአአምር ሊተሂ ከመ ይሁበኒ ፈውሰ ፡

ድኅነትን እንዲሰጠኝ አወቅሁ፡

ወለበውኩ ዘይሁበኒ ፣

የሚሰጠኝ ዋጋዬን አወቅሁ ፡

፮፡ ወእመሂ በብዙኅ ኃይል ይመጽእ፣

ምስለ ብዙኅ ሲል ነው፡ ምንም ከብዙ መጋፋት ጋራ ተቆጥቶ ቢመጣ ፡

ወኢይገብር እንከ በመዓቱ ላዕሌየ፣

ፈጽሞ አያጠፋኝም ፡

እስመ ግህል ወጽድቅ በኀቤሁ ፣

ይቅርታ ቸርነት በሱ ዘንድ ይገኛልና ፡

፯፡ ወየአርፈኒ ለዝሉፉ እምኮነኔየ፣

ከመከራዬ ፈጽሞ ያሳርፈኛል፡

፰፡ እስመ እገብዕ ኀበ ቀዲሙ ወኢይሄሉ እንከ ፣

ወደቀደመው ጥዒና እመለሳለሁና እንግዲህ ወዲህ በደዌ አልኖርም ፡

ወኢየአምር እንከ ደኃሪታ ፣

የዚችን ፍጻሜዋን አላውቅም፡

፱፡ እገብዕ እንከሰ መንገለ ፀጋም ወኢያደምዕ ፣

በስሕተት የተሠራ ኃጢአት እንጂ፣ ይኖራል ብዬ እመረም ራለሁ አላገኝም ፡



ወእትመየጥሂ መንገለ የማን ወአልቦ ዘእሬኢ ፣

ጽድቅ መስሎ የሚሠራ ኃጢአት እንጂ፣ ይኖራል ብዬ እመረም ራለሁ ፣ የማገኘው የለም ፡

፲፡ ወእደ አአምር ፍኖትየ ፣

ሥራዬን አውቅ እመረምር ዘንድ፡ አንድም ወድዓ አእመረ ፍኖትየ ሥራዬን ፈጽሞ አወቀ ፡

ወፈተነኒ ከመ ወርቅ ፣

እንደ ወርቅ በመከራ ፈተነኝ፡

፲፩፡ ወእወጽእ እምተግሣፁ ፣

ከቁጣው የተነሣ በሞት ከዚህ ዓለም እሄዳለሁ ፡

ወኢዓቀብኩ ፍናዊሁ ወኢተጋሕኩ ወኢኃለፍኩ እምትእዛዙ ፣

ሕጉን ጠብቄ ነበረ፣ ከሕጉም አልወጣሁም ነበረ ፡

፲፪፡ ወኃባዕኩ ውስተ ሕዕንየ ነገሮ፣

ሕጉን በልቤ ይገኖ ነበረ፣ ስለምን መጣብኝ ይሆን ?

፲፫፡ ወመኑ ውእቱ ዘይትዋቀስ በእንተ ኵነኔ እስመ ውእቱ ዘፈቀደ ይገብር ፣

ፈርዶ መከራ ቢያመጣ የሚከራከር ማነው? እሱ የወደደውን ያደርጋልና ፡

፲፬፡ ወበእንተዝ አነሂ በእንቲአሁ ጕጕዕኩ ፣

በእንቲአሁና በእንተዝ አንድ ወገን ነው፤ መሐሪ ወመስተሣህል መሆኑን አውቄ ስለዚህ ለመፈወስ ቸኮልሁ ፡

ወተገሣዕየ ሀለይኩም ፣

በመከራ ከተገሠጽኩ በኋላ ጌታን አሰብሁት ፡

፲፭፡ በእንተዝ ደንገጽኩ እምቅድመ ገጹ ፣

ከገጸ መዓቱ የተነሣ ስለዚህ ደነገጥኩ ፡

እኔልዮሂ ወይጌርመኒ ፣

መከራዬን አስበዋለሁ፣ ያስፈራኛል፣ ብሂሞትን የላከው እሱ ነውና ፡

፲፮፡ ወእግዚአብሔር መሰዎ ለልብየ፣

እግዚአብሔር ልቡናዬን በመከራ እንደ ሰም አቀለጠው ፡

ወዘኵሎ ይመልክ አኵኰዓኒ ፣

ሁሉን የሚገዛ እግዚአብሔር በሞት አስቸኮለኝ ፡

፲፯፡ በአይቴ አእመርኩ ከመ ትመጽአኒ ጽልመት ፣

መከራ እንድትመጣብኝ የት አውቅ ነበር ?

ወደፈነኒ ቆባር ውስተ ገጽየ ፣

ጽኑ መከራ ፊቴን ሸፈነኝ ።

www.ethiopianorthodox.org

## ምዕራፍ ፳፬

ሐያ አራተኛው ምዕራፍ ይህ ነው ፡

፩፡ ለምንት ይረስዮን እግዚአብሔር ለሰዓታትየ ፣

እግዚአብሔር ዘመኖቼን ለምን ዘነጋቸው፣ እሱ ስለተዘነጋባቸው ነው፣ አንድም በ፯ቱ፣ በ፲፪ቱ፣ በ፳፬ቱ ጊዜያት የማቀርበውልመናዬን፣ ጸሎቴን ለምን ዘነጋብኝ ፡

፪፡ ወተዓደዉ ኃጥአን እምወሰኖሙ፣

ፍጻ መቀበልማ በዚህ ዓለም ከሆነ ኃጥአን ከወሰነላቸው ትእዛዝ ለምን ወጡ ፡

ወመሠጡ ኖላዌ ምስለ መርዔቱ ፣

እረኛውን ከመንጋው ጋራ ነጠቁ፡ አንድም ጌታን ከሐዋርያት ጋራ ገደሉ ፡

፫፡ ወሖዱ አድገ ዕጓለ ማውታ ፣

እናት አባቱ የሞቱበት እየሸመተ የሚያመጣበት አህያውንም ቀሙት ፡

ወአኀዙ ላህመ ዕቤር ፣

ረጅ ልጅ የሌላት የባልቴቲቱን ላም ቀሙ ፡

፬፡ ወሚጥዎሙ ለድኩማን እምፍኖተ ጽድቅ ፣

ድኩማን አእምሮን ከውነተኛ ሕግ ለይዋቸው ፡

ወተጋብዑ ኅቡረ ፣

የውሃን ምድር ቦለዶች አንድ ሁነው ተሰበሰቡ ፡

፭፡ ወኮኑ ከመ አዕዱግ ገዳም ፣

እንደ ምድረበዳ አህያ ሆኑ ማለት ገገር የለንም አሉ ፡

በእንቲአየ ወጽኡ ፣

እኔን ስለመስደብ ወጡ ፡

ውነደጉ ምግባሮሙ ፣

ሥራቸውን ተዉ ፡

ወጥዕሞሙ እክል በንዕሶሙ ፣

በሕፃንነታቸው እህል ጨው ጨው አላቸው፡ አንድም በሕፃን አእምሮነት ሳሉ ኃጢአት ጨው ጨው አላቸው ፡

፮፡ አኮኑ ገራህተ ዘኢኮነ ዚአሆሙ አረሩ እምቅድመ ሰዓቱ ፣

እህል ጨው ጨው እንዳላቸው፡ አንድም ኃጢአት ጨው ጨው እንዳላቸው የሚያስረዳ ነገር ገንዘባቸው ያይደለውን ከጊዜው አስቀድሞ ዝርዝሩን ያጨዱ አይደለምን ? ወቅጠው አፍልተው ይጠጡታልና ፡

ወቀነይዎሙ ለባሕታውያን ዓፀደ ወይኖሙ ዘእንበለ አስብ ወዘእንበለ ሲሳይ ተዓገልዎሙ ኃጥአን ፣

ቀነይዎሙ ዘእንበለ ሲሳይ ተዓገልዎሙ ዘእንበለ አስብ ብሎ



መግጠም ነው፡ እናት አባት የሌላቸው ድሆችን ያለምግብ ገዟቸው፣ ያለዋጋ የወይኑን ቦታ ቀሟቸው ፡

፯፡ ወለብዙኃን ዕሩቃን አቤትዎሙ ዘእንበለ ልብስ ፣

ብዙዎችን ሰዎች ያለልብስ ዕራቁታቸውን አሳደሩዋቸው፡

ወሰለብዎሙ አራዘ ነፍስቶሙ ፣

ነታቸውን (ምንጣፋቸውን)፡ አንድም ሰናፊላቸውን ልብሳቸውን ገፈፏቸው ፡

፰፡ ወአርሐሰሙ ነፍኒፍ ወጠለ ገዳም ፣

እንቀማለን ሲሉ ካፊያ የምድረ በዳ ጠል ያርሳቸዋል፣ ያረፈርፋቸዋል ፡

እስመ አልቦሙ ከዳን ወተከድኑ ጸላዕተ ፣

ልብስ የላቸውምና ካፊያ ያርሳቸዋል፡ አንድም ልብስ የላቸውምና ዋሻውን ለብሰው አደሩ ፡

፱፡ ወመሠጡ ዕጓለ ማውታ እምውስተ ጥቡ ፣

እናት አባት የሌለውን ከጡቱ ለዩት ማለት አንዲት ላም ብትኖረው ወሰዱበት ፡

ወአሕመምዎን ለዕኑሳት ፣

የፀነሱትን ሴቶች መከራ አፀኑባቸው ፡

፲፡ ወገፍዕዎሙ ለዕኑሳን ወነጽሕዎሙ ፣

የተቸገሩትን ሰዎች ገፍተው ጣሏቸው ፡

ወሄድዎሙ አፍዕሞቶሙ ለርኁባን፣

የተራቡትን ሰዎች የሚጎርሱትን ቀሟቸው ፡

፲፩፡ ወአስርሕዎሙ ለምንዱባን ፣

በመከራ የተጨነቁትን አደከሟቸው ፡

ወተዓገልዎሙ ፣

ቀሟቸው ፡

ወኢያእመርዋ ለፍኖተ ጽድቅ ፣

የውነተኛውን ሕግ ሥራ አላወቋትም ፡

፲፪፡ ወሰደድዎሙ እምህገሮሙ ወእምአብያቲሆሙ ፣

ከሀገራቸው፣ ከቤታቸው አስወጥተው ሰደዱዋቸው ፡

ወአግዓሩ ነፍሰ ሕፃናት ፈድፋደ ፣

የሕፃናቱን ሰውነት አስጨነቁ፡ አንድም እነ ኄሮድስ ሕፃናቱን ገደሉ ፡

፲፫፡ ውእቱ እንከ ለምንት ኢገሠፆሙ ለእሉ ፣

መከራ መቀበል በኃጢአት ከሆነ እነዚህን ለምን አልገሠፃቸውም፡

www.ethiopianorthodox.org

አምጣነ ሀለዉ ዲበ ምድር ኢያእመርዎ ፤

በዚህ ዓለም ሳሉ አላወቁትም፡

ወርእይዋ ለፍኖተ ርትዕ ወኢሖሩ ውስተ መርህባ ፤

የቀናች ሕግን አውቀው በሥር ዓቷ ፀንተው አልኖሩም፡

፲፬፡ አእሚሮ ምግባሮሙ መጠዎሙ ውስተ ጽልመት ፤

ሥራቸውን አውቆ በመከራ ጣላቸው ፡

ወተረሲዮሙ ሌሊተ ከመ ሰራቂ ዘማውያን ፤

እንደ ሌባ ሌሊቱን ሽልማት አድርገው ኖሩ፤ አንድም ሌቦች ሌባ እንደመሆናቸው ሌሊቱን ሽልማት አድርገው ኖሩ ፡

፲፭፡ ዓይነ ዘማዊ ይጸንሕ ጽልመተ፤

ዘማዊ ጨለማውን ይጠብቃል፤ አንድም ሌባ ጨለማውን ይጠብቃል ፡

ወይብል አልቦ ዘይሬእየኒ ፤

ዘማዊ፡ አንድም ሌባ ሰው ስስርቅ የሚያየኝ የለም ይላል፡

ወይሜውር እምገጽ ፤

ገጸ ይላል ወለም ወለም ይላል፡

፲፮፡ ወይከሪ አብያተ በጽልመት ፤

ዘማዊ በጨለማ ወንዳ ወንዶውን ያነሣል፡ አንድም ሌባ በጨለማ ቤቱን ይቆፍራል ፡

መዓልተሰ ይትኃብኡ ወኢይሬእዩ ብርሃነ ፤

ዘማውያን፡ አንድም ሌቦች በመዓልት ግን ሰው እንዳያያቸው ይሠወራሉ ብርሃን አያዩም ፡

፲፯፡ ወእምከመ ጸብሐ ይመስሎሙ ጽልመተ ሌሊት ለኵሎሙ ፤

ከነጋ በኋላ ሁሉም ጭንቅ ይሆንባቸዋል ፡

እስመ የአምሩ ዘይከውን ሐከክ ፤

በሀገር የሚሆነውን ፀብ፣ ክርክር ያውቃሉና ፡

ወይትነዘብ መዊተ ፤

ዘማዊ ፡ አንድም ሌባ ሞትን ይጠራጠራል ፡

፲፰፡ ወይጼለል ዲበ ገጸ ማይ ፤

ዘማዊ በጀጀባው ይሠወራል ፡ አንድም ዲበ ገጸ ማይ ይላል ፡ ሌባ በፊቱ ውሀ ይመላበታል፡

ርጉም መክፈልቶሙ በዲበ ምድር፣

ዘማውያን፡ አንድም ሌቦች በዚህ ዓለም እድል ፈንታቸው ርጉማን መባል ነው ፡

፲፱፡ ወይሬእዩ እንዘ ይየብስ ተክሎሙ በዲበ ምድር ፤

ዘማውያን በዚህ ዓለም ልጆቻቸው ሲሞቱ ያያሉ ፡ አንድም ሌቦች እጃቸውን እግራቸውን ሲቆርጧቸው ያያሉ ፡



ወበርበርዎ ለዕጓለ ማውታ አስቦ ፤

እናት አባት የሞቱበትን ያለ ገንዘቡን በዘበዙት ፡

፳፡ ወእምዝ ይዜከራ ሎቱ ለኃጢአቱ ፤

ከዚህ በኋላ መከራ ሲመጣበት ኃጢአቱን ያስባታል ፡

ወይጠፍዕ ከመ ጊሜ ወጠል ፤

ጉም ጤዛ እንዲጠፋ ይጠፋል፡

ወይትፈደይ በከመ ገብረ ፤

እሱ እንደ አደረገ ፍዳውን ይቀበላል ፡

ወይትቀጠቀጥ ከመ ዕፅ ብኵብኑ ኵሉ ዓማፂ ፤

ዓመፀኛ ሁሉ እንደበሰበሰ እንጨት በመከራ ይቀጠቀጣል ፡

፳፩፡ ለመካንሂ ኢያሠነየ ፤

የሚረዳት ልጅ የላትም ብሎ ለመካኒቱ ይህ ልብስሽ ፣ ይህ ቀለብሽ ይሁን ብሎ በጎ ነገር አላደረገላትም ፡

ወለእንተ ትወልድሂ ኢመሐረ ፤

ለምትወልደውም ይህ ለልብስሽ ይህ ላንች ይሁን ብሎ አላዘነላትም ፡

፳፪፡ ወአንኃሎሙ በመዓቱ ለዕሑላን፣

የተቸገሩትን ተቆጥቶ አጠፋቸው ፡

ወተንሢኦ ኢይትአመና ለሕይወቱ፣

ቢድንም ሰውነቱን አያምናትም፡

፳፫፡ ወእመሂ ደወየ ኢይሴፎ ሐይወ፣

ቢታመምም እድናለሁ አይልም፡

ዳዕሙ ይወድቅ ውእቱ በሕማም ፤

እሱ በመከራ ይያዛል እንጂ ፡

፳፬፡ ለብዙኃን አመንደቦሙ በሢመቱ ፤

በተሾመ ጊዜ ብዙ ሰዎችን አስጨነቃቸው ፡

ወይጸመሂ ከመ መሎኬ በውስተ ሐሩር ፤

እንደ ሶሪት ቅጠል እንደ አመድማዶ በመከራ ይጠወልጋል ፡

ወከመ ሠዊት ዘይወድቅ ለሊሁ እምቀሪሙ ፤

ከጫፉ እንደወደቀ ፍሬ ይሆናል ፡

፳፭፡ ወእመ አኮ መኑ ውእቱ ዘይብለኒ ሐሣዊ አንተ ፤

ነገር እንደኔ ከሆነ እንዳንተ ካልሆነ እኔን ሐሰተኛ የሚለኝ ማነው ?

ወይሬስዮ ለነገርየ ከመ ወኢምንት፣

ነገሬን እንደ ኢምንት የሚያደርገው ማነው ?

www.ethiopianorthodox.org

## ምዕራፍ ፴፭

ሐዩ አምስተኛው ምዕራፍ ይህ ነው ፤

ጉባዔ

፩፡ ነበ ተናገረ በልዳዶስ ወአውሥአ በልዳዶስ አውኬናዊ ወይቤ ፤

በልዳዶስ ከተናገረ ዘንድ መለሰ፤ እንዲህ አለ ፤

፪፡ ቀዳሚሁ አኮኑ በነቢሁ ወውእቱ ግርማ ዘገብረ ኵሉ ዘውስተ አርያም፤

ጥንቱን መፈራት በሰማይ ያለውን ሁሉ የፈጠረ የሱ ገንዘብ አይደለምን ፤

፫፡ አልቦ ዘይመስል ከመቦ ዘይስሕት በነበ ሰራቂ ፤

በሌባ ፊት ያለ ገንዘቡን እንደሚስት የሚያስመስለው ሰው አይኑር ፤ እንደ ጎረቤት ሌባ ፤ አንድም የጠፋበትን ጊዜውን በማያውቅ ሰው የሚመስለው አይኑር፤ በቃ ቤት ያኖረውን ገንዘብ የጠፋበትን ጊዜውን አያውቅም፤ ባየው ጊዜ ያውቀዋል እንጂ ፤ አንድም እመቦ ይላል በሌባ ዘንድ ያለ ገንዘቡን የሳተ ሰው ቢኖር በዚያ የሚመስለው አይኑር ፤

ወለመኑሂ ዘኢበጽሐ እከዩ ፤

ኃጢአቱ መከራ ይዞ ያልመጣበት ማነው ፤

፬፡ ወእፎ ይከውን ጻድቅ ንጹሐ በነበ እግዚአብሔር ፤

ጻድቅ ነኝ ፤ ንጹሕ ነኝ የሚል ሰው በእግዚአብሔር ዘንድ እንደምን ንጹሕ ይሆናል ፤

ወመኑ ዘያነጽሕ ርእሶ ዘተወልደ እም አንስት ፤

ከሴቶች የተወለደ ራሱን ከኃጢአት የሚያነፃ ማነው ፤

፭፡ ወርኅኒ ይትኃባዕ ወኢያበርህ ፤

ጨረቃ ሕፀፅ ያደርጋል፤ አያበራም ፤ አንተም በፊት መከራ ትቀበላለህ ፤ እንግዲህ ወዲህ ተድላ ደስታ ታደርጋለህ፤ አንድም ያበርህ ወኢይትኃባዕ ፤ ያበራል ሕፀፅ አያደርግም፤ አንተም በተድላ በደስታ ኖርህ ፤ እንግዲህ ወዲህ መከራ ትቀበላለህ ፤ አንድም ኢያበርህ ወይትኃባዕ አያበራም ፤ ሕፀፅ ያደርጋል፤ እንደዚህም ሁሉ በመከራ ትያዛለህ፤ ከዚያ በኋላ ተድላ ደስታ ታደርጋለህ ፤ አንድም ይትኃባዕኑ ወኢያበርህኑ ጨረቃ ሕፀፅ ካደረገ በኋላ አያበራምን አንተስ መከራ ከተቀበልህ በኋላ ተድላ ደስታ አታገኝምን፤ አንድም ጨረቃ ካላበራ፤ ከተሠወረ ያንተም ከፋትህ ይሠወራል፤ አንድም ስንኳን አንተ ጨረቃ ያልፋል ፤



ወከዋክብትኒ ኢኮኑ ንጹሐነ በቅድሚሁ ፤

ከዋክብትም በፊቱ ንጹሐን አይደሉም ፤ እለፉ ጥፉ ቢላቸው በምን ዕዳችን አይሉም ፤

፯፡ ሕድግሰ ሰብአ መዋቴ ወዕሤያቲ፤

ፈራሽ፤ በስባሽ፤ ትል የሚሆን ሰውንስ ተውና ይትኃደግስ ሰብአ መዋቲ ፤ ፈራሽ በስባሽ ትል የሚሆን ሰውስ ይቅርና፤

ወዕፄለ እመሕያው በድን ፤

በድን የሚሆን ሰውስ ይቅርና ከዋክብትስ ስንኳን ንጹሐን አይደሉም ፤ እስመ አልቦ ንጹሕ በቅድሚሁ እንዲል ፤ በፊቱ ንጹሕ የለምና ንጹሕ ስለሌለ ንጹሐን አይደሉምና ፡፡

## ምዕራፍ ፴፮

ሐዩ ስድስተኛው ምዕራፍ ይህ ነው ፤

፩፡ ነበ ተናገረ ኢዮብ ወይቤ መኑ ትሠውቅ ፤

ኢዮብ ከተናገረ ዘንድ እንዲህ አለ፤ ማንን ትደግፋለህ የሚደግፉት ደካማውን ነው እንጂ ብርቱውን ይደግፉታል ?

፪፡ ወመኑ ትፈቅድ ትርዳዕ ፤

በነገርህ ማንን ልትረዳ ትወዳለህ ?

ቀዳሚሁ አኮኑ ዘብዙኅ ኃይሉ ወዓቢይ መዝራዕቱ ፤

አኮኑ በነቢሁ ግርማ ብሎ ነበርና ጥንቱን ዕውቀቱ ብዙ የሆነ፤ ሥልጣኑ ገናና የሆነ እርሱ አይደለምን ፤

፫፡ ወለመኑ ታመክር አኮኑ ሉቱ ጥበብ ፤

ማንን ትመክራለህ፤ ጥበብ የሱ ገንዘብ አይደለምን ፤

ወለመኑ ትትኃሠሥ አኮኑ ጽኑዕ ኃይሉ ፤

ለማን ትከራከራለህ፤ ኃይሉ ፅኑዕ የሚሆን እሱ አይደለምን ፤

፬፡ ለመኑ ታየድዕ ነገረ መንፈስ ፤

የዕውቀትን ነገር ለማን ትናገራለህ ፤

ወመንፈሰ መኑ ዘይወጽእ እምኔከ፤

ካንተ የተገኘ ዕውቀት የማነው? አንድም ብልጭ ብልጭ የሚልብህ ዕውቀት የሱ አይደለም ?

፭፡ እለ ያርብሁ ገፍዑኒ ፤

እሱ በደለኝ እንጂ አርበኞች በደሉኝ ?

ማይ ዘመትሕቱ ወዘውስቴቱ ፤

ውሃ ከበታቹ ያለው በውሀ በምልዓት ያለ እርሱ ነው ፤

www.ethiopianorthodox.org

፳፮፡ አኮኑ እግዚአብሔር ክሡት ሲኦል በቅድሜሁ ፤

መቃብር ሞት በፊቱ የተገለጠ እግዚአብሔር አይደለም ?

ወምንትኑ አልቦ ዘይሜወሮ እምኔሁ፤

ከሱ የሚሠወር ምንም ምን የለም፡ አንድም ሞትኒ ኢይሜወር እምኔሁ ሞትም ከሱ አይ ሰወርም ፡

፳፯፡ ዘሰፍሖ ለመስዕ ዲበ ወኢምንት፤

ጠፈርን በሕዋው የዘረጋው እሱ ነው ፡

ወሰቀላ ለምድር ዲበ ዕራቃ ፤

ምድርን ያለምሰሶ ያፀናት እሱ ነው፡ አንድም ሰማይን ያለባላ ያፀናው እሱ ነው፡ ምድርንም ያለ አዝርዕት፤ ያለ አትክልት ያፀናት እሱ ነው፡

፳፰፡ ወየአቀሩ ለማይ ዲበ ደመና፤

ውሀውን በደመና ቋጥሮ የሚያ መጣው እሱ ነው ፡

ወኢይሠጠጥ ደመናሁ በታሕቴሁ ፤

ከበታቹ ያለ ደመና እንዳይቀ ደድ የሚያደርግ ፡

፳፱፡ ዘውእቱ ብውህ ሎቱ ይንበር ዲበ መንበሩ ፤

በዙፋኑ ይቀመጥ ዘንድ የሥለ ጠነ እሱ ነው፡ አንድም በደመና በመዓልት ያለ እሱ ነው ፡ አን ድም በደመና ይቀመጥ ዘንድ ለዝናም ሥልጣን የሰጠ እሱ ነው ፡

ወይሠይም ላዕሌሁ ግብተ ለለሰዓቱ፤

በጊዜው ጊዜ ሊዘንም በደመና ላይ ዝናምን የሚያኖረው እሱ ነው ፡ አንድም ግብረ ይላል፤ ለዝናም ሥራን የሚሠጥ እሱ ነው፡ እንደ ወንፊት የተበሳሳ ደመና አለ ፤ ጥሩ ጥሩውን በዚህ አዝንሞ በረዱን ወስዶ በሰልሞን ያፈስዋል፡ አንድም ጌታ በደመና በምልዓት ይኖ ራል ፡

፴፡ ወሐፀሮ ለማይ በትእዛዙ ፤

ውሀውን በትእዛዙ ወሰነው ፡ እስከ ዝየ ብጽሒ ወኢትትዓደዊ እም ወሰንኪ ብሎ ፡

እስከ አመ የኃልቅ ይትባረይ ብርሃን ምስለ ጽልመት ፤

ዓለም እስቲያልፍ ድረስ ብርሃን ከጨለማ ጋራ ይፈራረቃል ፡

፴፩፡ ወሣረረ አዕማደ ሰማይ ፤

እሉ እሙንቱ ፬ቱ አዕማደ ሰማይ ያላቸውን አራቱን ነፋሳት የፈ ጠረ እሱ ነው ፡

ወድኀፀ እምትእዛዙ ፤

ከትእዛዙ የተነሣ ጠፈር በአድ ማስ ላይ አዘነበለ ፡ አንድም ምሕፀ ይላል፤ ከትእዛዙ የተነሣ ወደዚህ ዓለም ከመምጣት ሸሸ፡



ወይደነግፁ እምተግሣፀ ፤

ከተግሣፁ የተነሣ አሕዛብ አጋን ንት ይደነግጣሉ ፡

፴፪፡ ወበኃይሉ አኀድዓ ለባሕር ፤

ውቅያኖስን በኃይሉ አፀናው፡

ወነጽሐ ለአንበሬ በተግሣፁ ፤

ብሔሞትን በሥልጣኑ ወሰነው፡ አንድም ዲያብሎስን በመስቀሉ ድል የነሳው እሱ ነው ፡

፴፫፡ ወዓፀውተ ሲኦልኒ አድለዉ ሎቱ፤

ሄኖክ ፤ ኤልያስ አደሉለት ፤ በሞት ሞት፤ በመቃብር መቃ ብር ሁነውበታልና ፡ አንድም ጻድቃን አደሉለት፤ ይኄይስነ ናድሉ ለእግዚአብሔር ብለዋ ልና ፡ አንድም አጋንንት አደ ሉለት፤ አእመርናከ ከመ አንተ ቅዱሱ ለእግዚአብሔር ብለዋ ልና ፡

ወቀተሎ ለከይሲ ዓላዊ በተግሣፁ ፤

ብሔሞትን፡ አንድም ዲያብሎስን በሥልጣኑ ወሰነው፤ ዓላዊ አለው ገዥ የለኝም ብሏልና፡ አንድም ዲያብሎስ አነ ፈጣሪሆሙ ብሏ ልና ፡

፴፬፡ ናሁ ዝ መክፈልተ መዓቱ ፤

እነሆ ዕድል ፈንታው ይህ ነው፡

ወናዕምዕ ነገሮ እለ ተርፉ ፤

የቀሩትን ነገራት እንስማ፤ እነግ ረክሙ ምንት ውስተ እደ እግ ዚአብሔር፡ አንድም ብሔር እም ኀበ ይወጽእ ብሩር ብሎ እንዲ ያመጣው ፡

ወድምፀ ዐዓሁ መኑ የአምር ጊዜ ይገብር ፤

የብልጭልጭታውን ድምፅ የሚ ሰማበትን ጊዜ የሚያውቅ ማነው ::

## ምዕራፍ ፴፯

ሐያ ሰባተኛው ምዕራፍ ይህ ነው ፡

፩፡ ወደገመ ዓዲ ኢዮብ ወይቤ ፤

ኢዮብ ዳግመኛ ተናገረ፤ እንዲህ አለ፤ ተራው የሳፍር ነበርና ዳግመ አለ ፡ አንድም ተናገረ ሲል ነው፡ ወደገሞን ዝናም ፯ተ አውራኃ እንዲል፡ አንድም ዓዲ ዳግመ ሲል ነው፡ ዳግመኛ ሁለ ተኛ ተናገረ፡

፪፡ ሕያው እግዚአብሔር ዘኰነነኒ ከመዝ ፤

እንዲህ አድርጎ የፈረደብኝ እግዚአብሔር ሕያው ነው፡ አን ድም ሕያው እግዚአብሔር እን ዲህ የፈረደብኝ ነው ፡

ወዘኮሎ ይመልክ ፤

የፈረደብኝ ዘኮሎ ይመልክ ነው ፡ አንድም ሁሉን የሚገዛ እግዚአብሔር ሕያው ነው ፡

www.ethiopianorthodox.org

ዘአምረረ ለነፍስየ ፤

ሰውነቴን ያሳዘናት ሕያው እግ ዚአብሔር ነው ፤

፫፡ ሶበሁ ሀለወት ነፍስየ ፤

አእምሮየ ሳለች ፤

ወዓጺ መንፈሰ እግዚአብሔር ዘያስ ተናግረኒ ፤

ዳግመኛ የዕውቀትን ነገር የሚ ያናግረኝ መንፈስ ቅዱስ ሳለ እውነት ነገር ከመናገር ዝም አልልም ፤

ከመ ኢይንብብ አፉየ ዓመፃ ፤

አንደበቴ ሐሰት ነገር እንዳይ ናገር ሕያው እግዚአብሔርን፤ አንድም የሚያናግረኝ ሕያው እግዚአብሔር ነው ፤

ወኢትትመሐር ነፍስየ ኃጢአተ ፤

ሰውነቴ ኃጢአት የሚሆን ነገር እንዳትማር ሕያው እግዚአብ ሔርን፤ አንድም እንዳትማር የሚያደርጋት ሕያው እግዚአ ብሔር ነው ፤

፬፡ እትሐዘብሰ እምአርአይኩክሙ ጽድቀ ፤

እውነት ነገር እነግራችኋለሁ ብዬ አስባለሁ ፤

እስመ እመውት ወኢየኃድጋ ለሕይ ወትየ ፤

በሕይወት አልኖርምና ሰውነቴን በመከራ አልተዋትምና ፤

፭፡ እንዘሰ ጽድቀ እገብር ኢይትኃ ጉል ፤

በጎ ነገር ሳደርግ አልጠፋሁም ነበር ፤

እስመ ኢይትዓወቀኒ ዘገበርኩ እኩይ፤

ያደረግሁት ክፉ ነገር አይታወ ቀኝምና ፤

፮፡ ወባሕቱ ሶበ ኮኑ ጸላእትየ ከመ ድቀተ ኃጥአን ፤

ነገር ግን ጠላቶቼ እንደ ሰብአ ሰናኦር ቢጠፉ ባማረ በተገባ ነበር ፤

ወእለሂ ይትነሥኡ ላዕሌየ ከመ ሞተ ዓማፅያን ፤

በኔ ላይ በጠላትነት የሚነሱ ሰዎች እንደ ሰዶም፤ እንደ ገሞራ ቢሆኑ በአማረ በተገባ ነበር ፤

፯፡ ወምንተ ይጸንሕ ኃጥእ ከመ ይሴፎ ሐይወ ፤

በሕይወት ይኖር ዘንድ ኃጥዕ ሰው ምን ምግባሩን ደጅ ይፀና ዋል፤ አንድም ኃጥእ በሕይወት ይኖር ዘንድ ለምን ደጅ ይፀናል፤

ወዘኢተወከለ በእግዚአብሔር ይድኅ ንኑ እንጋ ፤

በእግዚአብሔር ያላመነ ሰው ይድናልን እንጃ ፤

፰፡ ወይሰምዖኑ ጸሎቶ ፤

ልመናውንስ ይሰማዋልን እንጃ፤



ወእመሂ መጽአ ምንዳቤ ይረክብኑ እንጋ ገጸ በነቢሁ ፤

መከራ ቢመጣበትስ በፊቱ ባለ ሟልነትን ያገኛል እንጃ፤

፱፡ ወእመሂ ፀውዖ ያወሥእኑ ፤

ቢለምነውስ ይመልስለታል ? እንጃ ፤

፲፡ ወባሕቱ እነግረክሙ ምንት ውእቱ ዘውስተ እደ እግዚአብሔር፤

ነገር ግን በእግዚአብሔር እጅ ያለው ምን ምን እንደሆነ እነ ግራችኋለሁ ፤

ወኢይኄሉ ዘሀሎ በኀበ ዘኵሎ ይመ ልክ ፤

ሁሉን በሚገዛ በሱ ያለውን ሁሉ ሐሰት አላደርግም ፤

፲፩፡ ተአምሩ ኵልክሙ ከመ እኪት ትመጽአሙ ለእኩያን ፤

በክፉ ሰዎች መከራ እንድትመ ጣባቸው ሁላችሁ ታውቃላችሁ፤

፲፪፡ ዝውእቱ መክፈልቱ ለብእሲ ኃጥእ እምኀበ እግዚአብሔር ፤

ከእግዚአብሔር ዘንድ ትእዛዝ የሚመጣበት የኃጥእ ሰው ዕድል ፈንታው ይህ ነው ፤

ወይበጽሕ ኀቤሁ ንዋየ ዓበይት እም ኀበ ዘኵሎ ይመልክ ፤

ሁሉን ከሚገዛ ከእግዚአብሔር ዘንድ የሰብአ ትካት የሰብአ ሰዶም መቅሠፍት ይመጣበታል፤

፲፫፡ ወእመኒ በዝኁ ደቂቁ ለሞስና ይከውኑ ፤

ልጆቹም ቢበዙ ለጥፋት ይሆ ናሉ ፤

ወእመሂ ፀንሁ ያስተፍዕሙ ፤

ቢጸኑም ቀላውጠ ለመብላት ይዞ ራሉ ፤

፲፬፡ ወአልቦ ዘይሜሕሮን ለዕቤራቲ ሆሙ ፤

ለባልቴቶቻቸውም የሚያዝንላ ቸው የለም ፤

፲፭፡ ወእመሂ አስተጋብአ ለብሩር ከመ መሬት ወከመ ዕቡር ወርቀ ዘገበ ፤

ብሩን እንደ መሬት፣ ወርቁን እንደ ጭቃ ቢሰበስብ ፤

፲፮፡ ዘኵሎ ጻድቃን ይነሥዕዎ ፤

ይኸን ሁሉ ጻድቃን ይወርሱ ታል ፤

ወይረክብዎ ራትዓን ለንዋዩ ፤

ገንዘቡን ቅንነት ያላቸው ሰዎች ያገኙታል ፤

፲፯፡ ወይከውን ቤቱ ከመ ሳሬት ፤

ቤቱ እንደ ሸረሪት ወተር ይሆ ናል ማለት ይጠፋል፤ አንድም የሸረሪት መወተሪያ ይሆናል ፤

ወከመ ብላዕ ቍንቍኒ ፤

ነቀዝ፣ ብል እንደበላው ይሆናል፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፰፡ ኖመ ባዕል ወአልቦ ነቂሐ ፣

ባለፀጋ በመከራ ተይዞ ድኅነት የለውም ፡

ወይከሥት አዕይንቲሁ ወያነክር ፣

ዓይኑን ገልጦ ያያል ፣ መከራ ውን ያደንቃል ፡

፲፱፡ ወይጠብቆ ሕማም ከመ ማይ፣

ውሀ ደሴቱን እንዲከብ መከራ ይከበዋል ፡ መከራ ከቦ ያስጨ ንቀዋል ፡

ወይነሥአ ዓውሎ በሌሊት ፣

በሌሊት መከራ ተይዞ ሳለ መቅ ሠፍት ይመጣበታል ፡

፳፡ ወይመሥጦ ሐሩር ወየሐልፍ ፣

መቅሠፍት ይመጣበታል፣ ይሞ ታል ፡

ወይልሕስ እምነ መንበሩ ፣

ከሚኖርበት ከሀገሩ ይሰደዳል፡

፳፩፡ ወይመጽእ ላዕሌሁ ዘኢየአምር ወኢይምሕኮ ፣

የማያውቀው አሕዛብ ዲያብሎስ ይመጣል አይራራለትም፡ እስመ ኢየአምር ሰብእ ዘይመጽእ ላዕ ሌሁ እንዲል፣ ሰው የሚመጣበ ትን አያውቅምና ፡

ወያመሥጥ እምዕዴሁ ወየኃልፍ ፣

ከእጁ ያመልጣል ፣ ኋላ ግን በሞት ይሄዳል ፡

፳፪፡ ወይጠፍሕ እደዊሁ በላዕሌሁ፣

በነዚያ ላይ እጁን ይጸፋል፣ ቢነ ደው ቢቆጨው ፡

ወይስሕቦ እምቤቱ ፣

ሞት ከቤቱ ስቦ ጎትቶ ያወጣ ዋል ፡፡

## ምዕራፍ ፳፰

### ሐያ ስምንተኛው ምዕራፍ ይህ ነው ፡

### ጉባዔ

፩፡ ቦ ብሔር እምነ ይወጽእ ብሩር፣

ብር የሚገኝበት አገር አለ፣ እንደ ሸዋ፡ አንድም ምዕመናን የሚበ ዙበት አገር አለ፣ እንደ እስክን ድርያ ፡

ለወርቅኒ ቦ ብሔር እምነ የአርርዎ፣

ወርቁን የሚለቅሙበት አገር አለ ፣ እንደ እናሪያ፡ አንድም ምዕመናን የሚበዙበት አገር አለ እንደ እስክንድርያ ፡

፪፡ ሐፂንሂ እምውስተ ምድር ይት ገበር ፣

ብረትም ከምድር ይሠራል ፣ እንደ ዛኪና፣ አንድም ሰማዕታት የሚበዙበት አገር አለ፣ እንደ አንፆኪያ ፡

ለብርትኒ ከመ ዕብን ይፈጽሕዎ ፣

ብርቱንም እንደ ደንጊያ እየፈ ለጡ ያወጡታል ፡



፫፡ ለጽልመትኒ አዘዘ ዕድሚሁ ፣

የጨለማውንም ሰዓት አዘዘ ፣ አሥራ ሁለት ሰዓት ሌሊት ይሁን ብሎ፡ አንድም የጽልመተ ነፍስ ጊዜው ፭ሺህ ካ፭መቶ ዘመን ይሁን ብሎ አዘዘ ፡

ወለኵሉ ውእቱ የሐትቶ ዕብነ ጽል መት ወጽላሎተ ሞት ፣

ሰውን ሁሉ ጽኑዕ መከራ አም ጥቶ ይመረምረዋል ፡

፬፡ ከመ ስጥቀተ ፈለግ ውስተ መሬት፣

ቱመ ስጡጥ ፈለግ ሲል ነው፡ ንፍቀ ታቦት ስጠተ ልብስ እን ዲል፣ ውሀ በመሬት ውስጥ እን ዲሄድ ያ መድከሙ ነው ፡

እለ ይረስዕዋ ለፍኖተ ጽድቅ ደከሙ በኃጢአቶሙ ፣

ከማሀ ያለበት ነው፣ እውነተኛ ሕግን የሚዘነጉት ሰዎች በኃጢ አታቸው ምክንያት ደከሙ ፡

፭፡ ለምድርኒ ይወጽእ እምኔሃ እክል፣

እህል የሚሆንበት አገር አለ፣ ደንቢያ በረንታ፡ አንድም ዕክለ ትምህርት የሚበዛበት ሰብእና ጻድቃን አለ ፡

በመትሕቲሃኒ ጠብለላ በእሳት ፣

ከታች በእሳት ጠቀለላት፡ ከታች ነፋስ ፣ ቀጥሎ እሳት ፣ ቀጥሎ ውሀ፣ ቀጥሎ መሬት ነውና፡ አን ድም ልበ መምህራንን በሀብተ መንፈስ ቅዱስ አማሟቃት ፡

፮፡ ቦ ብሔር ዘዕብነ ሰንፔር ፣

ሰንፔር የሚባል ዕንቀ የሚገኝ በት አገር አለ፣ እንደ ህንደኬ፡ አንድም ሊቃነ ጳጳሳት የሚበ ዙበት አገር አለ፣ እንደ ሮም፡

ወርቃኒ ከመ መሬት ፣

ወርቋ እንደ መሬት ብዙ የሆነ፣ አንድም ምዕመናን የበዙባት፡

፯፡ ወፍኖት ዘኢርእያ ዖፍ ወኢነጸራ ዓይነ ንስር ፣

ዖፍ ንስር አንድ ወገን፣ ዲያብሎስ ያላሳታት ሰብእና ጻድቃን፡ አን ድም ዲያብሎስ ያልገባባት ገነት መንግሥተ ሰማያት አለች ፡ አንድም ሰይጣን ያልጠበቃት ሕግ አለች ፡ ሕግ መሠራቱ ለሰው ነው እንጂ ለሰይጣን አይ ደለምና ፡

፰፡ ወኢኬድዋ ደቂቀ ዝኑራን በእ ግር ፣

ትዕቢተኞች፣ የትዕቢተኞች ልጆች በእግር ያልረገጧት ማለት አጋንንት ያላሳቷት ሰብእና ጻድ ቃን፡ አንድም አጋንንት ያልገቡ ባት ገነት መንግሥተ ሰማያት አለች፡ አንድም አጋንንት ያልጠ በቋት ሕግ አለች ፡

www.ethiopianorthodox.org

ወኢሐለፈ አንበሳ ውስቴታ ፤

ዲያብሎስ ያልጠበቃት፤ ሕግ ያላሳታት ሰብእና ጸድቃን አለች፤ አንድም ያልገባባት ገነት መንግሥተ ሰማያት አለች ፤

፱፡ ወአንሥአ እዴሁ በእኒዝ ፤

ለእኒዝ ሲል ነው፤ እኔን በመከራ ለመያዝ እደ መዓቱን አነሣ ፤ አንድም ምስለ እዝኅ ፤ ከመቅሠፍቱ ጋራ ሥልጣኑን አነሣ ፤

ወገፍትዖሙ ለአድባር እምሥርዎሙ፤

ተራሮችን፤ አንድም ነገሥታቱን ሥር መሠረታቸውን አጠፋ፤

፲፡ ወሠጠቀ አንቅዕተ አፍላግ ፤

የፈሳሾችን ምንጭ የፈጠረ እሱ ነው፤ አንድም ሀብተ መንፈስ ቅዱስን መጥኖ መጥኖ የሚሰጥ እሱ ነው ፤

ወርእየት ዓይንየ ኵሎ ክቡራተ ፤

ዓይኔ ክቡር ክቡር ነገርን አየች አለ፤ በዘመኑ የተደረገውን ፤

፲፩፡ ወሠጠቀ ቀላያተ ዘአፍላግ ፤

ፈሳሾች፤ ውሆች የሚሄዱበትን ወንዝ የፈጠረ እሱ ነው ፤ አንድም ሀብተ መንፈስ ቅዱስን የሚሰጥ እሱ ነው ፤

ወአርአየ ኃይሎ ውስተ ብርሃን ፤

በብርሃን ኃይሉን ገለጠ ማለት ለይኩን ብርሃን ብሎ ፈጠረ ፤

አንድም በወልድ ኃይሉን ገለጠ፤ ወልድ እለ ውስተ ሲኦል ሃሁ ብሎ ኃይሉን ገለጠ ፤

፲፪፡ ወእምአይቴ ተረክበት ጥበብ፤

ሕግ፤ አንድም ወልድ መንፈስ ቅዱስ ከወዴት ተገኘች ፤

ወአይቴ ብሔራ ለጥበብ ፤

የሕግ፤ አንድም የወልድ የመንፈስ ቅዱስ አገሯ ወዴት ነው ፤

፲፫፡ ወኢየአምራ መዋቲ ለፍኖታ ፤

ሟች ሰው ሕግን አይዛትም የወልድ የመንፈስ ቅዱስን ባሕርይዋን አያውቃትም ፤

ወኢሀለወት ኀበ ዕጓለ እመሕያው፤

ሕግ በሰው ዘንድ የለችም፤ አይጠብቃትም፤ አንድም መላእክት የወልድ የመንፈስ ቅዱስን ባሕርይዋን አያውቁምና ፤

፲፬፡ ቀላይኒ ትቤ ኢሀለወት ኀቤየሰ፤

ቀላይም ሕግ ከኔ ዘንድ የለችም አለች፤ ሕግ መሠራቱ ለቀላይ አይደለምና ፤ አንድም ወልድ መንፈስ ቅዱስ በውሳኔ ከኔ ዘንድ የለችም አለች፤ አንድም መቃብር ከኔ ዘንድ የለችም አለች ተነሥቷልና ፤ አንድም ሲኦል ከኔ ዘንድ የለችም አለች፤ በአካለ ነፍስ ወርዶ ነፍሳትን ባወጣ ጊዜ አጋንንት አልተቆራኙትምና ፤



ባሕርኒ ትቤ ኢነበረት ምስሌየ ፤

ባሕርም ሕግ ከኔ ጋራ የለችም አለች፤ ሕግ መሠራቱ ለባሕር አይደለምና ፤ አንድም ወልድ መንፈስ ቅዱስ በውሳኔ ከኔ ዘንድ የለችም አለች፤ አንድም መቃብር ሲኦል ከኔ ዘንድ የለችም አለች፤ ተነሥቷልና አጋንንትም አልተቆራኙትምና ፤

፲፭፡ ወአልቦ ዘተረክበ ዘከማሃ ፤

እንደ ሕግ ያለ የተገኘ የለም፤ አንድም እንደ ወልድ ፤ እንደ መንፈስ ቅዱስ የተገኘ የለም፤

ወኢይደልዋ ብሩር ተውላጣ ፤

ብር የሷ ለውጥ ሊሆን አይገባትም ፤

፲፮፡ ወኢትሠየጥ በወርቀ አፈር ፤

በህንድ ወርቅ አትሸጥም፤ ወርቅ ብር ተቀብሎ ሕግ ማፍረስ ፤ አንድም ወልድ መንፈስ ቅዱስን መካድ አይገባም ፤

ወኢበባላቅ ቅድው ወኢበሰንፔር ፤

በአማረ ባላቅ ሰንፔር በሚባል ዕንቁ ልትሸጥ አይገባም ፤

፲፯፡ ወኢይትማሰላ ወርቅ ወማኅው፤

ወርቅ ዕንቁ ዋጋዋ አይሆንም፤

ወቤዛሃኒ ንዋየ ወርቅ ፤

የወርቅ ወገን ሁሉ ዋጋዋ ሊሆን አይገባም ፤

፲፰፡ ዝሉፍ ወእንቡዝ ኢይዜከርዋ፤

ዝሉፍ እንቡዝ የሚባል ዕንቁ አይመስላትም፤ አንድም ዝሉፍ አውታታ እንቡዝ አእምሮውን የአጣ አያስባትም ፤

ወሰሐባ ለጥበብ እምዕንቍ በአምጣነ ኃይልከ ፤

ከዕንቍ ተሽለህ አሽለህ የሚቻልህ እንደሆነ በሚቻልህ መጠን ጥበብን ያዛት ፤

፲፱፡ ወኢይትኤረያ ተንከራ ዘኢትዮጵያ ፤

የኢትዮጵያ ሉል አይተካከላትም ፤

ወኢትሠየጥ በወርቅ ጽሩይ ፤

በጠራ ወርቅ አትሸጥም ፤

፳፡ ወጥበብ በአይቴ ተረክበት ፤

ሕግ፤ አንድም ወልድ መንፈስ ቅዱስ ወዴት ተገኘች ፤

ወአይቴ ውእቱ ብሔራ ለምክር ፤

የሕግ የወልድ የመንፈስ ቅዱስ አገሯ ወዴት ነው ፤

፳፩፡ እስመ ተረስዐት እምኵሉ ሰብእ፤

ሕግ ከሰው ተዘንግታለችና፤ አንድም ወልድ መንፈስ ቅዱስ ከሊቃነ አጋንንት ተዘንግታለችና ፤

ወተኀብዐት ዓዲ እምአዕዋፈ ሰማይ፤

ዳግመኛ ከአዕዋፍ ተዘንግታለችና ሕግ መሠራቱ ለሰው እንጂ

www.ethiopianorthodox.org

ለአዕዋፍ አይደለምና፤ እንድም ወልድ መንፈስ ቅዱስ ከሠራዊተ አጋንንት ተሠውራለችና ፤

፳፪፤ ሞትሂ ወሲኦል ይቤሉ ሰማዕነ ድምፃ ፣

ሂኖክ ኤልያስ የሕግ መሠራቷን ሰማን አሉ፣ በሞት ሞት፣ በመ ቃብር መቃብር ሁነውበታልና፤ እንድም ጻድቃን የሕግን መሠ ራቷን ሰማን አሉ፤ እንድም አጋ ንንት ወልድ እለ ውስተ ሲኦል ፃዑ ማለቷን ሰማን አሉ ፤ እን ድም የመንፈስ ቅዱስን ዜና ኀድረቷን ሰማን አሉ ፤

፳፫፤ ወእግዚአብሔር አሠነየ ፍኖታ፣

ሂኖክ ኤልያስ የሚሞቱ በሰማ ዕትነት ነውና የወልድን ትንሣ ኤዋን አበጀ ፤

፳፬፤ ወውእቱ ለሊሁ የአምር ብሔራ፣

እንዲህ መሆኗን ያውቃል አለ፣ ከሙሴ በኢያሱ፣ ከኤልያስ በኢ ልሳዕ ማደሯን እሱ ያውቃል፤ እንድም የወልድን ባሕርይዋን ያውቃል ፤

ወውእቱ ይሬኢ ኵሎ ዘውስተ ሰማይ ወየአምር ኵሎ ዘውስተ ምድር ፣

በሰማይ በምድር ያለውን ሁሉ እሱ ያውቃል ፤

፳፭፤ ዘለሊሁ ገብረ ነፋሳተ በመዳ ልው ፣

ነፋሳትን መጥኖ መጥኖ የፈጠረ እሱ ነው ፤

ወማየሂ በመስፈርት ፣

እስከ ዝየ ብጽሒ ወኢትትዓደዊ እምወሰንኪ ብሎ ውሀውን የወ ሰነ እሱ ነው ፤

፳፮፤ አመ ፈጠረ ከመዝ ኈለቋ ፣

እንዲህ አድርጎ ዓለምን በፈጠረ ጊዜ ሕግን ዐሥር ተብላ እንድ ትቈጠር አደረጋት ፤ እንድም በ፭ሽህ ካ፭መቶ ዘመን ወልድ ሥጋ እንድትሆን፤ እንድም መን ፈስ ቅዱስ በምዕመናን እንድ ታድር አውቆ ቈጠራት ፤

ወበፍኖት ያሜክርዎ ለቃል ፣

ፀሐይን በጎዳና ጸናን አልጸናን ብለው ይፈታተኑታል፤ እንድም ፀሐይን በጥላ ያውቁታል የበቃ በኬክሮስ ያልበቃ በጥላ ፤ እን ድም ሕግን ይፈታተኑታል፤ እን ድም አይሁድ ጌታን ይፈታተኑ ታል፤ ተአምራቱ ምትሓት ነው፤ ትምህርቱ ሐሰት ነው እያሉ፤

፳፯፤ ወርእያ አሜሁ ፣

ያንጊዜ ሕግን ሠራት፤ እንድም ወልድ መንፈስ ቅዱስን ሰደዳት፤

ወኈለቋ ፣

ዐሥር ተብላ እንድትቈጠር አደ ረጋት፤ እንድም በ፭ ሽህ ካ፭ መቶ ዘመን ወልድ ሥጋ እንድ ትሆን መንፈስ ቅዱስ በሰው እንድታድር አደረጋት፤



ወአስተዳለዋሂ ፣

አዘጋጃት ፤

ወአክበራ ወሰሐባ ፣

ሕግን የያዘ ሰውን አከበረ፣ ሕግን የያዘ ሰውን ወደሱ አቀረበው ፤

፳፰፤ ወይቤሎ ለዕጓለ እመሕያው ፈሪሃ እግዚአብሔር ውእቱ ጥበብ፣

እግዚአብሔር ሰውን ፈሪሃ እግ ዚአብሔር ይሉሃል ጥበብ ነው አለው፣ ጥበብ ይሉሃል እግዚአ ብሔርን መፍራት ነው ፤

ወተግህሦ እምእኩይ አዕምሮ ውእቱ፣

አዕምሮ ይሉሃል ከክፉ ነገር መራቅ ነው ::

## ምዕራፍ ፳፱

ሐያ ዘጠነኛው ምዕራፍ ይህ ነው ፤

ገባዔ

፩፤ ወደገመ ኢዮብ ዓዲ ቅድመ ወይቤ ፣

ኢዮብ ዳግመኛ ቀድሞ እንደተ ናገረው ተናገረ ፤

፪፤ መኑ እምአግብዓኒ ውስተ መዋ ዕለ አውራኅየ ዘትካት ፣

ቀድሞ ተድላ ደስታ አደርግ እንደ ነበረ ተድላ ደስታ አደርግ ዘንድ ወደቀደመ ዘመኔ ማን በመለሰኝ ነበር ፤

አመ ዐቀበኒ እግዚአብሔር ፣

እግዚአብሔር በረድኤት በጠበ ቀኝ ጊዜ እኖር እንደ ነበረ ወደመ ሆን ማን በመለሰኝ ነበር፤ እን ድም እኖር እንደነበረ እኖር ዘንድ ፤

፫፤ ከመ ከመ ይበርህ ማኅቶትየ በት ርዓስየ ፣

በራስጌዬ ፋና መብራት ይበራ እንደነበረ ጊዜ ወደመሆን፤ እን ድም በራስጌዬ መብራት ይበራ እንደ ነበረ ጊዜ እኖር ዘንድ ፤

አመ አሐውር በብርሃኑ ውስተ ጽል መት ፣

በጨለማ ከአዳራሽ ወደዕልፍኝ በፋና እሔድ እንደ ነበረ ጊዜ ወደመሆን ፤ እንድም ከመከራ በብርሃነ ረድኤቱ በጠበቀኝ ጊዜ፤

፬፤ አመ ሀሎኩ አነ ውስተ ኵሉ በረከት ፣

እኔ በበረከት ጸንቼ እኖር እንደ ነበረ ጊዜ ወደመሆን፤ እንድም እኔ በበረከት ጸንቼ እኖር ዘንድ ማን በመለሰኝ ፤

አመ እግዚአብሔር ይሔውጽ ቤትየ፣

እግዚአብሔር ወገኖቼን በረድ ኤት በጐበኛቸው ጊዜ እኖር እንደነበረ ወደመሆን፤ እንድም እኖር እንደ ነበረ እኖር ዘንድ፤

፭፤ ወአመ ጽፉቅ ንዋይየ ፣

ገንዘቤ በዝቶ ሳለ ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወበዓውድየ አግብርትየ ፤

ባሮቼ ዙሪያዬን ከበው ቆመው ሳለ ፤

፮፡ ወአመ ይውኅዝ ቅብዕ ውስተ ፍናውየ ፤

ቅቤው በጎዳናዬ ይፈስ እንደ ነበረ ጊዜ አለ ግብሩ ሲመጣ ፤ አንድም ተድላው ደስታው በዝቶ ሳለ ፤

ወአመ ይትከዐው ሀሊብ ውስተ አድባርየ ፤

ወተቱ በተራራ ይፈስስ እንደ ነበረ ጊዜ ወደመሆን ግቱ ሲመጣ፤ አንድም ከጡቷ ሲነዛ፤ አንድም ተድላ ደስታዬ ይበዛ እንደ ነበረ ጊዜ ወደመሆን ማን በመለሰኝ፤

፯፡ አመ እገይሥ በግርማ ሀገርየ ፤

በሀገሬ መፈራት በሄድሁ ጊዜ የኤዶምያስ ነገሥታት የሰው ደም እናፈስሳለን ሲሉ ቀይ ግምጃ ይለብሳሉ፤ አንድም ድል ነሥቼ ወደ ሀገሬ በመፈራት በተመለስሁ ጊዜ ፤

ወአነብር ውስተ መርህብ መንበርየ፤

ዙፋኔን በአደባባይ በዘረጋሁ ጊዜ ፤

፰፡ ወይሬእዩኒ ወሬዙት ወይትኀብኡ ፤

ወሬዙት ያር፤ አንድም ሌቦች እኔን አይተው ይሠወራሉ ፤

ወይጸንሑኒ ኵሎሙ ሊቃውንት ፤

ነገር የሚያውቁት ሁሉ ይጠብቁኛል ፤

፱፡ ወኃያላን ይትፌጸሙ ወኢይነብቡ፤

ኃያላኑም ዝም ይላሉ፤ አይናገሩም ፤

ወያጠውቁ አፉሆሙ በእደዊሆሙ፤

እጃቸውን በአፋቸው ጭነው ዝም ይላሉ ፤

፲፡ ወያስተበፅዑኒ እለ ይሰምዑኒ ፤

የሚሰሙኝም በአደነቁኝ ጊዜ፤

ወይጠግዕ ልሳኖሙ በጕርዔሆሙ ፤

አንደበታቸው ከጕሮሯቸው በተጣጋ ጊዜ ፤

፲፩፡ ወዕዝን ዘሰምዐተኒ ታስተበፅዓኒ፤

ስፈርድ ስተች የሰማችኝ ጆሮ ታደንቀኝ ነበር ፤

ወዓይን ዘርእየተኒ ትትሬስየኒ ፤

ስፈርድ ስተች ያየችኝ ዓይን አብነት ታደርገኝ ነበር፤ አንድም ትትገኃሠኒ ይላል፤ ስፈልጥ ስቆርጥ ታየኝ የነበረ የሌባ የቀማኛ ዓይን ትርቀኝ ነበረ፤

፲፪፡ እስመ አድኃንኩ ነዳየ እምእደ ዘይትዔገሎ ፤

ደኃውን ከሚቀማው እጅ አድኜ ዋለሁና ፤



ወረዳእኩ እጓለ ማውታ ዘአልቦ ረዳኢ፤

ረዳት የሌለው እናት አባቱ የሞቱበትን ረድቼዋለሁና ፤

፲፫፡ ወደኃረኒ ዘሂ ይመውት ፤

የሚሞት ሽማግሌ ሁሉ ይመርቀኝ ነበር፤ ስለምን መጣብኝ ይሆን የሚያልፍ ዝናም አይምታህ፤ የሚሞት ሽማግሌ አይርገምህ እንዲሉ፤

ወባረከኒ አፈ ዕቤራት ፤

የባልቴቶች አንደበት ይመርቀኝ ነበር፤ ስለምን መጣብኝ ይሆን፤

፲፬፡ ወለበስክዋ ለጽድቅ ፤

እውነተኛ ሕግን ገንዘብ አደርጋት ነበር ፤ ስለምን መጣብኝ ይሆን ፤

ወተረሰይኩ ርትዓ ከመ አጽፍ ፤

የቀና ፍርድን ገንዘብ አደርግ ነበር ፤

ወተቀጸልክዋ ለፍትሕ ፤

ፍርድን እንደ ዘውድ ተቀዳጅቻት ነበር ፤

፲፭፡ ወኮንክዎሙ ዓይነ ለዕውራን ፤

ለዕውራን ዓይን እሆናቸው ነበር አለ ፤ መሪ እየሰጠሁ ፤

ወእግረ ለሐንካሳን ፤

ለሐንካሳንም እግር እሆናቸው ነበር ማለት ፈረስ፤ በቅሎ እሰጣቸው ነበር ፤

፲፮፡ አነ ውእቱ አበ ምስኪናን ፤

የድኆች አባት እኔ ነበርሁ ፤ ስለምን መጣብኝ ይሆን ?

ወተኃሠሥኩ ለዘኢየአምር ቅስተ ፤

ፀብዕ ክርክር ለማያውቅ እከራከርለት ነበር፤ ድኃ ያመልክት፤ ዳኛ ይሟገት እንዲሉ ፤

፲፯፡ ወሰበርኩ ስነኒሆሙ ለዓማፅያን፤

አጽንተው የያዟቸውን ሥልጣናቸውን አጠፋ ነበር ፤

ወአንገፍክዎሙ እማዕከለ ጥረሲሆሙ ዘመሠጡ ፤

የነጠቁትን አስጥላቸው ነበር፤ ስለምን መጣብ ይሆን ?

፲፰፡ ወተሐዘብኩ እልሐቅ ወእርሳዕ ፤

እንዲህ ስላደረግሁ በተድላ በደስታ እኖራለሁ ብዬ አስብ ነበር፤

ወእኀየው ጕንዱየ ዓመተ ከመ ነዋህ በቀልተ ተመርት ፤

እንደ ዘምባባ ከብሬ ገንኜ እኖራለሁ ብዬ ነበር ፤

ወከመ ኆፃ አበዝኀ መዋዕለ ፤

ዘመኔን እንደ ባሕር አሸዋ አበዛለሁ ብዬ ነበር ፤

፲፱፡ ወይትከዓው ማይ ለሥርውየ፤

ለአባትነቴ ማየ ረድኤት ይሰጠኛል ብዬ ነበር ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወይወርድ ጠል ውስተ ማዕረርየ ፣

ጠል በአዝመራዬ ይወርዳል ብዬ ነበር፤ አንድም ጠለ ረድኤት በሰውነቴ ያድራል ብዬ ነበር፤

፳፡ ወክብርየ ሐዲስ ምስሌየ ፣

እንግዳ የሆነ ዘውዴ ከኔ ጋራ ይኖራል ብዬ ነበር፣ አያቶቼ ዘውድ አልደፉምና እንግዳ አለው አንድም ዘውዴ ከኔ ጋራ ጸንቶ ይኖራል ብዬ ነበር ንዑ ነሐድስ መንግሥቶ ለሳዖል እንዲል ፤

ወአሐውር እንዘ ቀስትየ ውስተ እዴየ፣

ሥልጣኔ እንደጸና እኖራለሁ ብዬ ነበር ፤ አንድም ቅስትየ ይላል ፣ ፀብዕ ክርክሬ በቃሌ ጸንቶ ይኖራል ብዬ ነበር ፤

፳፩፡ ኪያየ ያጽምዑኒ ወይሰምዑኒ፣

እኔን ይሰሙኝ ያደምጡኝ ነበር፤

ወያረምሙ በምክረ ዚአየ ፣

የሱ ምክር ይሁን ይሉ ነበር፤

፳፪፡ ወኢይደግሙ ነገረ በዲበ ነገርየ ፣

በኔ ነገር ላይ ዳግመኛ ነገር አይናገሩም ነበር ፤

ወይትሐሠዩ ሶበ እትናገሮሙ ፣

በተናገርኋቸው ጊዜ ደስ ይላቸው ነበር ፤

፳፫፡ ከመ ምድር ዕምዕት እንተ ትሴፎ ዝናመ ከማሁ እሙንቱ ለነገረ ዚአየ፣

የተጠማች ምድር ዝናሙን እንድትታመን፣ እንደዚህም ሁሉ ነገሬን ይታመኑት ነበር፤

፳፬፡ ወኢይትአመኑ እመ ሰሐቁ ምስሌሆሙ ፣

ከነዚያ ጋራ በሣቅሁ ጊዜ እኛን ደስ ይበላቸው ብሎ ነው እንጂ አሁን ስቆ ነው ብለው አያምኑኝም ነበር ፤

ወኢወድቀ ብርሃነ ገጽየ ፣

ተድላ ደስታዬ አይጠፋም ብዬ ነበር ፤

፳፭፡ ኃሢሥየ ፍኖቶሙ ነበርኩ እንዘ እኬንኖሙ ፣

ነገራቸውን መርምሬ ስፈርድላቸው እኖር ነበር ፤

ወነበርኩ ከመ ንጉሥ ባሕቲትየ ፣

እንደ ሌላ ንጉሥ፤ አንድም ንጉሥ እንደ መሆኔ ፤ አንድም እንደ ሰማያዊ ንጉሥ ብቻዬን ስፈርድላቸው እኖር ነበር ፤

ሶበ ይላህዉ ይትናዘዙ ብየ ፣

በአዘኑ ጊዜ በኔ ይረጋጉ ነበር፡፡



# ምዕራፍ ፴

ሠላሳኛው ምዕራፍ ይህ ነው፤

፩፡ ወይእዜሰ ትሑታን ይስሕቁኒ ፣

ዛሬ ግን ቦለጾች ይዘብቱብኛል፤

ወዮምሰ ይምዕዱኒ ለባሕቲቶሙ ፣

ዛሬ ግን ብቻቸውን ይመክሩብኛል ፤

እለ መነንክዎሙ ለአበዊሆሙ ወእለ ኢሀሰብክዎሙ ፣

አባቶቻቸውን የናቅሁዋቸው ከምንም ከምንም ትንሽ የጤፍ ያህል የማልቈጥራቸው ፤

ወኢከመ ከለባተ መራዕይየ ፣

መንገዴን እንደሚጠብቁ ውሾች የማልቈጥራቸው፤ አንድም መራዕየ ከለባት ይላል፣ ከንጉሥ ቤት ሶለጉ ብዙ ነውና ፤

፪፡ ወለምንት ሊተ ኃይለ እዴሆሙ፣

የዚህ ኃይለ ቃላቸው ለምኔ ነው፤

ወይመጽእ ላዕሌሆሙ ሞት ፣

በነዚህስ ሞት ይመጣባቸዋል፤

፫፡ ወያስተፍዕሙ እምረኃብ እንዘ ይልሕሱ ፣

ከረኃብ የተነሣ እየተሰደዱ ይቀላውጣሉ ፤

እለ ይመስጡ እምነ በድው ፣

በምድረ በዳ የሚቀሙ ፤

ትማልም በሥራህ ወበኃማር ፣

ትላንትና በዓዕር በገዓር ተይዘው የነበሩ ፤

፬፡ እለ ይዋሕዩ ወይስእሉ ወያስተፍዕሙ ፣

የሚቀሙ፣ የሚለምኑ፣ የሚቀላውጡ ኃይለኛ ቢሆን ይለምኑታል፤ ደካማ ቢሆን ይቀሙታል የቅሚያ መጀመሪያው ልመና ነውና ፤ አንድም እንጀራ በመሶብ፣ ጠላ በገንቦ ሲመጣ አይተው የሚጐመጁ ፤

እለ በተታሕሎ የሐይዉ ፣

ተለል ተለል የሚሉ ፤ አንድም በመቀላወጥ የሚኖሩ ፤

ኀሡራን ወአማዕያን ፣

ጉስቋሎች በደለኞች የሚሆኑ፤

ወዕኑሳን እምኵሉ ሠናይ ፣

ከበጎ ነገር ሁሉ የተቸገሩ ፤

እለ ሥርወ ዕፀ ይሜጽሩ እምዓቢይ ረኃብ ፣

በጽኑዕ ረኃብ ተይዘው ጅዋት እንጅሞን የሚያላምጡ ፤

፭፡ ተንሥኡ ላዕሌየ ሰረቅት ፣

ሌቦች እነዚህ በጠላትነት ተነሡብኝ ፤

እለ አብያቲሆሙ ውስተ ግበበ ኰኵሕ፣

ቤታቸውን በዋሻ ያደረጉ ፤

www.ethiopianorthodox.org

፮፡ ወይወውዑ ማዕከለ መጽአሞ ፤

በበረሀ የሚደነፉ ፧

ወይትኃብኡ ውስተ ሣዕረ ገዳም ፤

በምድረ በዳ ሣር ውስጥ የሚ ሠወሩ ፧

፯፡ አብዳን ውሉድ ፤

ሰነፎች ልጆች አባታቸው አይ ታወቅምና፤ እንድም እገሌ አባ ታችን አይሉምና ፧

ወአልቦሙ ስም ፤

ስም የሌላቸው ፧

እስመ ጥፉአን እምድር ፤

ከዚህ ዓለም ጠፍተዋልና ፧

ወጥበብ እንተ ጠፍዐት እምድር ፤

ከሳቸው የነበረች ጥበብ ከልቡ ናቸው ጠፍታለችና ሰነፎች ልጆች ፧

፰፡ ወይእዜሰ መሰንቆ ኮንክዎሙ ፤

ዛሬ ግን መሰንቆ ሆንኋቸው፧

ወአነ መሐደምቶሙ ፤

እኔ ተረት ሆንኋቸው ፧

፱፡ ወያስቈርሩኒ ወይርኅቁ እምኔየ፤

ይጸየፉኛል፤ ከኔ ይርቃሉ ፧

ወኢይትሐከዩ ወሪቀ ውስተ ገጽየ፤

በፊቴ እንትፍ ማለትን ቸል አይሉም ማለት ይንቁኛል፤ አን ድም ጌታ አይሁድ በፊቴ ምራ ቃቸውን እንትፍ ማለትን ቸል አይሉም ይላል፤

፲፡ ወከሠተ ምጕንጳሁ ወቀተለኒ ፤

መዓቱን አመጣ፤ አጠፋኝ ፧

ወፈነወ ልጓመ ለገጽየ ፤

በሰውነቴ ደዌ አመጣብኝ ፧

፲፩፡ ወተንሥአ በየማነ ኃይል ፤

በየማነ ኃይል ተነሣ ፧

ወሰፍሐ እገሪሁ ዲቤየ ፤

እግረ መዓቱን በኔ ላይ አመጣ፤

ወገብረ ፍኖተ ሞት ላዕሌየ ፤

የሞት ሥራ የሚሆን ደዌን አመ ጣብኝ፤ አንድም ሳይናበብ ሞት ጐዳናውን አደረገኝ ፧

፲፪፡ ወደምሰሰ አሠርየ ፤

ፍለጋዬን አጠፋ ፧

ወሰለበኒ አልባስየ ፤

ልብሴን ገፈፈኝ፤ ልብስና ቍስል አይስማማምና፤ አንድም ተድላ ደስታዬን አሳጣኝ ፧

ወደጐፀኒ በአሕፃሁ ፤

ከሠተ ምጕንጳሁ ወደጐፀኒ ወቀ ተለኒ ሲል ነው፤ ጕራንጕሬውን ገለጠ በፍላፃ ወግቶ ገደለኝ ማለት ሥልጣኑን ገለጠ አጠፋኝ ፧



፲፫፡ ወረሰየኒ ዘከመ ፈቀደ ፤

እንደ ወደደ አደረገኝ ፤ ጌታ ሁን እንዳሻህ ትሆን እንዲሉ ፧

ወአአይስ በሕማም ፤

በደዌ ተይዤ እዛብራለሁ ፧

፲፬፡ ውቱረ ይዋሕየኒ ነያራር ፤

ዘወትር ራስ ማዞር ይጎበኘኛል፤

ወትፍሕቅ ነፍስየ ወትልሕስ ወትፈ ልስ ፤

ሰውነቴ ስትጽር ሕቅ ሕቅ ትላ ለች በሞት ትሰደዳለች ፧

ኃለፈት ነፍስየ ከመ ደመና ዘተነጽሐ፤

ሰውነቴ እንደ ተበተነ ደመና ጠፋች ፧

፲፭፡ ወይእዜሰ ተክዕወት ነፍስየ በላ ዕሌየ ፤

ዛሬ ግን በኔ ላይ ያለች ሰው ነቴ እንደ ውሀ ፈሰሰች ፧

ወመልዐ መዋዕልየ ፃዕረ ፤

ዘመኔ ጻር ጋርን መላ ፧

፲፮፡ ኵሎ ሌሊተ ይነድድ አዕፅም ትየ ፤

ሌሊቱን ሁሉ አጥንቴ እንደ እሳት ይነዳል ፧

ወይትመሰው አሥራውየ ፤

ጅማቴ እንደ ሰም ይቀልጣል፤

፲፯፡ እምዓቢይ ኃይል እትሜጠዎ ለል ብስየ፤

ልብሴን በጭንቅ እለብሰዋለሁ፤

ወሐነቀኒ አፈ መልበስየ ፤

የቀሚሴ ቁልፍ አነቀኝ ማለት የቀሚሴ ቁልፍ ይውልበት በነ በረው ደዌ ዋለበት ፧

ወህባኔ ጸፈረ ውስተ ክሣድየ ፤

ተባት ቁልፍ ይውልበት በነበ ረው ደዌ ዋለበት፤ አንድም ወህ ብል ይላል፤ እንስት ቁልፍ ይው ልበት በነበረው ደዌ ዋለበት ፧

፲፰፡ ወኬዱኒ ከመ ዕቡር ፤

እንደ ጭቃ በመከራ ረገጡኝ፤

ሐመድ ወመሬት ኮነ መክፈልትየ፤

እድል ፈንታዬ አመድ ትቢያ ሆነ፤ ገል ደቀሰው፤ አመድ ነስን ሰው በሣጥን አስተኝተውታልና፤

፲፱፡ ገዐርኩ ኀቤከ ወኢሰማዕከኒ ቀዊምየ ወኢጠየቀኒ ፤

በፊትህ ቁሜ ለመንሁህ ልመና ዬን ሰምተህ አልተረዳኸኝም ፧

ደበዩኒ እለ አልቦሙ ምሕረት ፤

ርኅራኄ የሌላቸው አጋንንት፤ አንድም አሕዛብ ደበደቡኝ ፧ አንድም ዕዬያት አስጨነቁኝ፤

ወጸንዓት እድ እንተ ቀሠፈተኒ ፤

ያጠፋችኝ እደ መዓትህ ጸናች፤

፳፡ ጐደገኒ ውስተ ናሕክ ፤

በቅልቅል መከራ፤ አንድም ናዕክ ይላል፤ በዕኑዕ መከራ ጣልከኝ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወአርኃቀኒ እምሕይወትየ ፤

ከሕይወቴ ለየኸኝ ፤

፳፫፤ አአምር ከመሰ ሞት ይቀጠቅጠኒ ፤

የዛሬው መከራ ያሳዝነኛል እንጂ ኋላስ ሞት እንዳይቀርልኝ አውቃለሁ ፤

ወማኅደሩሰ ለኵሉ ዘሞተ ምድር ፤

ነገር ግን እኔ ብቻ አይደለሁም የሞተ ሰው ሁሉ ማደሪያው መቃብር ነው ፤

፳፬፤ ወእምፈተውኩ እትጐረዓይ ለልየ ፤

ታንቆ መሞት አይገባም እንጂ የሚገባ ቢሆን እኔ ታንቄ በሞትሁ ነበር ፤

ወእመ አኮ አስተበቍዕ ባዕደ ይግበር ሊተ ከማሁ ፤

ይኸም ባይሆን ሌላውን አንቀህ ግደለኝ ብዬ በማለድሁ ነበር አይገባም እንጂ ፤

፳፭፤ አንሰ በእንተ ኵሉ ምንዱብ አበኪ ፤

እኔ በመከራ ስለተጨነቀው ሰው ሁሉ አለቅስ ነበር ፤

ወአነብዕ እመ ርኢኩ ሰብአ ሕሙመ፤

የታመመ ሰው ባየሁ ጊዜ አለቅስ ነበር ስለምን መጣብኝ ይሆን፤

፳፮፤ አነሰ አጽናዕክዋ ለሠናይት ፤

እኔ በጎ ነገርን አጽንቼ ይገሮት ነበር፤ ስለምን መጣብኝ ይሆን?

ወናሁ ተራከባኒ መዋዕለ እኩያት፤

ክፉ ዘመኖች ተገናኙኝ ፤

ተሰፈውኩ ብርሃነ ወመጽአኒ ጽልመት ፤

ተድላ ደስታውን ተስፋ አደረግሁ፤ መከራ አመጣብኝ ፤

፳፯፤ ትፈልሕ ከርሥየ ወኢታረምም፤

ሰውነቴ ትናደዳለች አለ፤ ዝም አትልም ፤

ወበጽሐኒ መዋዕለ ተዕናስ ፤

ችጋር ያለው ዘመን ደረሰብኝ፤

፳፰፤ ወቦዕኩ ውስተ መዕብብ ወአልቦ ዘያስተግኅሥ ሊተ ኃጣዕኩ፤

ወደ ሣጥኑ ገባሁ፤ ሣጥኑን የሚያሰፋልኝ አጣሁ ፤ እንድም ወደ መከራው ገባሁ ፤ መከራውን የሚያርቅልኝ አጣሁ ፤

ቆምኩ ማዕከለ ብዙኃን ወአአወዩ ፤

በብዙ ሰዎች መካከል ቁሜ አለቅሳለሁ ፤

፳፱፤ ኮንኩ እኅዋሆሙ ለጽግነት ፤

ለሌሊት ያሮች ወንድማቸው ሆንሁ ፤



ወቢጸን ለአዕዋፍ ፤

ለጉጉትም ባልንጀራ ሆንሁ ፤

፴፤ ወያዝኃዝኃኒ በሕቁ ማዕስየ ፤

ሰውነቴ እርግፍ እርግፍ አለ፤

ተቀለጥኩ ፤

በመከራ ተቆላሁ ፤

ወተኃርጸ ኵሉ አዕዕምትየ ፤

አጥንቴ ተፈጨ፤ እንድም አጥንቴ ጅማቱን ተቀማ ፤

፴፩፤ መሰንቆ ኮነኒ ሕማምየ ፤

መከራዬ መሰንቆ ሆነኝ፤ መሰንቆ እንዲያጨዋውት አጨዋወተኝ፤

ወመዝሙረ ገብአኒ ብካይየ ፤

ልቅሶዬም በገና ወደመሆን ተመለሰብኝ ።

## ምዕራፍ ፴፩

ሠላሳ አንደኛው ምዕራፍ ይህ ነው ፤

ጉባዔ

፩፤ ሥርዓተ ገበርኩ ለአዕይንትየ ፤

ለዓይኔ ሥራት ሠራሁ ማለት የጐልማሳ ሚስት አቅንቼ አላየሁም ነበር ፤

ወኢነጸርክዋ ለድንግል ፤

ድንግሊቱንም አቅንቼ አላየሁም ነበር፤ ስለምን መጣብኝ ይሆን፤

፪፤ ወዓዲ ክፍለ እግዚአብሔር ኢበላዕኩ ፤

ዳግመኛ አሥራቱን፤ እንድም መሥዋዕቱን አልበላሁም ነበር፤

ወርስቶሂ ለኃያል እምአርያም ፤

በሰማይ ያለ የእግዚአብሔርን ቀዳማያቱን አላስቀረሁም ነበር፤ እንድም አምልኮቱን አልተውሁም ነበር፤ ስለምን መጣብኝ ይሆን ፤

፫፤ አሌ ሎ ለሞተ ዓማፂ ፤

ለዓመፀኛ ሞት ወዮለት ፤

ወተናክሮቶሙ ለእለ ይገብሩ ኃጢአተ ፤

ኃጢአት የሚሠሩ ሰዎች በሞት ይለያሉ፤ እንድም በሞት ስለመለያየታቸው ወዮላቸው ፤

፬፤ አኮኑ ውእቱ ዘይሬእያ ለፍናትየ ፤

እንዲህማ እንዳላደርግ ሥራዬን የሚመለከታት እሱ አይደለምን፤

ወኍለቈ ኵሎ ሥገሪትየ ፤

ወደ ኃጢአት መረማመዴን አካሄዴን የሚመለከት እሱ አይደለምን ፤

፭፤ ሶበሁ ሖርኩ ምስለ መሥተሣልቃን ፤

ዓይኑ በፈረጠ ፤ እጁ እግሩ በተቆረጠ ከሚዘብቱ ሰዎች ጋራ የኖርሁ ቢሆን ፤

www.ethiopianorthodox.org

ሶበሁ ተግኅሠት እግርየ እምፍኖቱ፣

እግረ ልቡናዬን ከሕጉ ያራቅሁ ብሆን በዚህ ምክንያት መጣ ብኝ ባልሁ ባላዘንሁም ነበር ፣ እግዚአብሔር ያውቃል ፤

፮፡ ወቆምኩ በመዳልው ጽድቅ ፣

በውነተኛ ሕግ ጸንቼ ኖርሁ ፤

ወየአምር እግዚአብሔር የውህትየ፣

በጐነቴን እግዚአብሔር ያው ቃል ፤

፯፡ ወእመሂ ተግኅሠት እግርየ እም ፍኖቱ ፣

እግረ ልቡናዬ ከሕጉ የራቀች ብትሆን ፤

ወእመ ተለወ ልብየ ድኅረ ዓይንየ፣

ባይኔ ያየሁትን በልቡናዬ ባደር ገው ፤

ወእመ ተመጠውኩ ሕልያነ በእዴየ፣

በእጄ መማለጃ ተቀብዬ ብሆን በዚህ ምክንያት መጣብኝ ባልሁ ባላዘንሁም ነበር፣ እግዚአብሔር ያውቃል፤ አንድም በእጄ መማ ለጃ ተቀብዬ እንደሆነ ፤

ዘዘራዕኩ ባዕድ ይብልዕ ፣

እኔ የዘራሁትን ሌላ ይብላው፤

፰፡ ወዘእንበለ ሥርው እኩን ዲበ ምድር ፣

በዚህ ዓለም ያላባትነት ልቅር፤

ወእመሂ ተለወ ድኅረ ልብየ ብእ ሲተ ብእሲ ፣

ልቤ የጐልማሳ ሚስት ተከትሎ ቢሆን ፤

ወእመኒ ወሐይኩ ኆኅተ ቤታ ፣

የቤቷን ደጅ ጐብኝቼ ቢሆን በአማረ በተገባ ነበር፤ አንድም እንዲህ አድርጌ እንደሆነ ፤

፱፡ ብእሲትየኒ ትትወህብ ለካልዕ፣

ሚስቴም ለሌላ ሰው ትሰጥ፤ አን ድም ተአድሞ ለካልዕ ብእሲ ይላል፣ ሌላውን ደስ ታሰኘው ፤

ወደቂቅየኒ ለይኅሡሩ በመቅሠፍተ መዓቱ ዘይእኅዝ ፣

ልጆቼም ተቆጥቶ በአመጣው መዓት መቅሠፍት ይጐስቀሉ፤

፲፡ አርኮሶ ብእሲተ ብእሲ እሳት ውእቱ ዘይነድድ ፣

እንዲህማ እንዳላደርግ የጐልማሳ ሚስት የሚያጐሰቁል እንደሚ ነድ እሳት እንዲጠፉ አላውቅ ምን፤

ወውስተ ኵሉ መለያልይ ኀበ፡ ቦአ ይሤሩ እምሥርዉ ፣

ከአደረ ዘንድ ሕዋሳቱ ሁሉ እን ዲጠፉ አላውቅምን ፤

፲፩፡ ወእመ ዐመፅኩ ፍትሐ ገብርየ ወአመትየ ሶበ ይትዋቀሱ በኀቤየ፣

ከኔ ዘንድ በተከራከሩ ጊዜ የሴት ባሪያዬን የወንድ ባሪያዬን ፍርድ



አድልቼ ብሆን በዚህ ምክንያት መጣብኝ ባልሁ ነበር ፤

፲፪፡ ወምንተ እሬሲ አመ ገብረ እግዚአብሔር ሐተታየ ፣

እንዲህ አደርግ ዘንድ፣ አይቴ ነበርከ ወምንተ ገበርከ ብሎ እግዚአብሔር በመረመረኝ ጊዜ ምን አደርጋለሁ ፤

ወእመኒ ቦ ዘሐወጸኒ እትዋሣዕኑ በቅድሜሁ ፣

በትንሣኤ ዘጉባዔ በጐበኘኝ ጊዜ አላደረግሁም ብዬ በፊቱ እከራ ከራለሁን ፤

፲፫፡ አኮኑ በከመ ተፈጠርኩ አነ በው ስተ ከርሥ እሙንቱሂ ከማሁ ኮኑ ፣

እንዲህማ እንዳላደርግ እኔ በማ ኅፀን እንደ ተፈጠርሁ እነዚያስ የተፈጠሩ አይደሉም ?

ወነበርነ ውስተ ይእቲ ከርሥ ፣

በዚች ማኅፀን የኖርነ አይደለ ምን ባሕርዩ አንድ ነውና ፤

፲፬፡ ትካትሰ ግብረ አደምዕ ዘፈቀ ድኩ ፣

ቀድሞስ የወደድሁትን ሥራ አገኝ ነበር ስለምን መጣብኝ ይሆን ፤

ወኢመሰውኩ ዓይነ ዕቤር ወዕጓለ ማውታ ፣

ገንዘቧን ወስጄ ባልቴቲቱን አስ ለቅሼ ዓይኗን አላጠፋሁም ነበር፤

ስለምን መጣብኝ ይሆን? እናት አባት የሌለውን አላስለቀስሁም ነበር፣ ስለምን መጣብኝ ይሆን፤

፲፭፡ ሶበሁ ባሕቲትየ በላዕኩ እክልየ፣

እህሌን ብቻዬን የበላሁ ቢሆን፤

ወኢወሀብኩ ለነዳይ ወለምስኪን ወለ ዕቤር ወለዕጓለ ማውታ ፣

ለድኃ፣ ለጦም አዳሪ፣ ለባልቴት፣ እናት አባቱ ጥለውት ለሞቱ ከዚህ ያልሰጠሁ ብሆን በዚህ ምክንያት መጣብኝ ባልሁ፣ ባላ ዘንሁም ነበር እግዚአብሔር ያው ቃል ፤

፲፮፡ ወአሐፅኖ እምንዕሱ ከመ አቡሁ፣

ከሕፃንነቱ ጀምሮ እንደ አባቱ አሳድገው ነበር ፤

ወአልሐቅዎ ከመ እሙ እምአመ ተወልደ ፣

ከተወለደ ጀምሮ እንደ እናቱ አሳድገው ነበር፣ ስለምን መጣ ብኝ ይሆን ፤

፲፯፡ ወእመኒ ርኢኩ ዕሩቀ ወኢያልበስክዎ እንዘ ይመውት በቍር ፣

በብርድ ሲሞት ራቁቱን አይቼ ያላለበስኩት ቢሆን በዚህ ምክ ንያት መጣብኝ ባልሁ ነበር ፤

፲፰፡ ወይድኅኑኒ ስኡናን ፣

ደካሞች ይመርቁኝ ነበር ስለምን መጣብኝ ይሆን ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወእምፀምረ ዓባግዕየ ሞቀ ዘባናቲሆሙ ፤

ከበጎቼ ብዛት የተነሣ ጀርባቸውን ሞቋቸው ነበር ስለምን መጣብኝ ይሆን ፤

፳፩፡ ወእመ አንሣዕኩ እዴየ ዲበ ዕጓለ ማውታ ተአሚንየ ከመ ብዙኅ ረድኤት ብየ ፤

ብዙ ረዳት አለኝ ብዬ ተአምኜ እናት አባት በሌለው እጄን አንስቼ ቢሆን በአማረ በተገባ ነበር፤ አንድም እንዲህ አድርጌ እንደ ሆነ ፤

ይትመተር መዝራዕትየ እመትከፍየ፤

ክንዴ ከትከሻዬ ይቆረጥ ማለት ሥልጣኔ ይጥፋ ፤

ወይትቀጥቀጥ እዴየ እምኵርናዕየ፤

እጄም ከክንዴ ይቆረጥ ማለት ሥልጣኔ ይጥፋ ፤

፳፫፡ እስመ ግርማ እግዚአብሔር አኀዘኒ ኢያመሥጥ እምእኒሁ ፤

ግርማ መዓቱ ይዞኛል ከመከራ አላመልጥም ፤

፳፬፡ ወእመ ደፈንኩ ወርቅየ ውስተ መሬት ፤

ወርቄን በመሬት ቀብሬ እንደ ሆነ ፤

ወእመ ተአመንኩ በዕንቍ ዘብዙኅ ሤጡ ፤

ዋጋው ብዙ በሆነ ዕንቍ ተአምኜ እንደሆነ ፤

፳፭፡ ወእመ ተፈሣሕኩ በብዙኅ ብዕልየ ፤

በብዙ ባለጸግነቴ ደስ ብሎኝ ቢሆን ፤

ወእመ ወደይኩ እዴየ ዲበ ዘአልቦ ኍልቍ ፤

ቍጥር ስፍር በሌለው ገንዘብ እጄን ጭኜ እንደሆነ ማለት አልሰጠሁ እንደሆነ ፤

፳፮፡ ኢይሬኢኑ ፀሐየ ዘያበርህ ወይጠፍዕ ፤

እንዲህማ እንዳላደርግ የሚያበራ ፀሐይን አላይምን እሱ ስንኳ ያልፋል ፤

ወርኀኒ ትበኪ ፤

ጨረቃም ታለቅሳለች ፤ ሰዎች የሚያለቅሱባት ስለሆነ፤ አንድም አጥብቀው ትበኪ በክ ትሆናለች በጠፍ ጊዜ አታበራም ፤

እስመ ኢትኬንን ርእሳ ፤

እለፊ ጥፊ ቢላት በምን ኃጢአቴ አትልምና ፤

፳፯፡ ወእመሰ ዘአስሐቶ ለልብየ በጽሚት ፤

ልቡናዬን ቀስ ብሎ ያሳተው አለ እንደሆነ ፤

ወእምወደይኩ እዴየ ዲበ አፉየ ፤

እጄን በአፌ ላይ ጭኜ እንደ ሆነ ፤



ወእመ ሰሚዓ ሰማዕኩ ወተጸመምኩ፤

ሰምቼ ዝም ብዬ እንደሆነ ፤

፳፰፡ ወዝኒ ይኩነኒ ዓቢየ ኃጢአተ፤

ይህ ጽኑዕ ኃጢአት ይሁንብኝ፤

እመ ሐሰውኩ ቅድመ እግዚአብሔር ልዑል ፤

በእግዚአብሔር ፊት ሐሰት ነገር ተናግሬ እንደሆነ ፤

፳፱፡ ወእመ ተፈሣሕኩ በድቀተ ጸላእየ ፤

በጠላቴ ጥፋት ደስ ብሎኝ እንደ ሆነ ፤

፴፡ ወእመ እቤ ዕንቋዕ ዕንቋዕ ለልብየ ለትስማዕ ዕዝንየ እኩየ ፤

በልቤ እሰይ እሰይ ስንኳ ብዬ እንደሆነ ጆሮየ ክፉ ነገርን ትስማ ፤

ወይሣዕ ሊተ ስም እኩይ በውስተ ሕዝብየ ፤

በወገኖቼ ዘንድ ክፉ ስም ይውጣልኝ ፤

፴፩፡ ወእመ ይቤሉ ነባሪየ መኑ እምወሀበነ ንብላዕ ሥጋሁ እንዘ ጥቀ እምሕሮሙ ፤

ቤተሰቦቼ ሥጋውን እንበላ ዘንድ ማን በሰጠን ባሉ ጊዜ የሰው ሥጋ አይበላም እንጂ የሚበላ ቢሆን በራራሁላቸው ነበር፤ አንድም ኢዮብ ያረደውን ሥጋ

እንበላ ዘንድ ማን በሰጠን ቢሉ እራራላቸው ነበር ፤

፴፪፡ ወበአፍአ ኢኀደረ ነግድ ፤

እንግዳ ከእዳሪ አላደረም ነበር፤ ስለምን መጣብኝ ይሆን ፤

ወለኵሉ ዘመጽአ ርኅው ኆኅትየ ፤

ለመጣ ሰው ሁሉ ደጄ የተከፈተ ነበር፤ ስለምን መጣብኝ ይሆን፤

ለእመ አበስኩ ዓቢየ ጌጋየ ወከበትኩ፤

ጽኑዕ ኃጢአት ሠርቼ ሠውሬ እንደሆነ ፤

፴፬፡ ወኢኃፈርኩ እምብዙኅ ሰብእ ተናጎዮ በኀቤሆሙ ፤

ተአምኖ አስተሥርዮ ሲል ነው፤ ከብዙ ሰዎች የተነሣ ኃጢአቴን ማመን ያላፈርሁ ብሆን ፤

ወእመ ምስኪን ይወጽእ እምኆኅትየ እንዘ ዕራቁ ፤

ድኃ ሳይለብስ ራቁቱን ከደጄ የወጣ ቢሆን በዚህ ምክንያት መጣብኝ ባልሁ፤ ባላዘንሁ ነበር፤

፴፭፡ መኑ እምወሀበኒ ዘያፀምአኒ ፤

ሲሰለቹት አይቶ የሚሰማኝ ማን በሰጠኝ ነበር ፤

ወእመ ኢፈራህኩ እደ እግዚአብሔር፤

የእግዚአብሔር እደ መዓቱን ያልፈራሁ ቢሆን በዚህ ምክን ያት መጣብኝ ባልሁ ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወእመኒ ብየ መጽሐፈ ዕዳ ዘይፈድ የኒ ፣

የሚከፍለኝ የገንዘቤ ደብዳቤ ቢኖር ፤

፴፮፡ እፀውር ዲበ መታክፍትየ ወአነ ብብ በቅድመ ብዙኃን ሰብእ ወእሠ ጥጠ ፣

ትከሻ ለእጅ አጋዥ ነው፤ በእጄ ይገፍ፤ አንድም የሚያነበው፤ አን ድም የሚነበበው ፊት ለፊት ነውና በምስክር አንብቤ ቀድጄ እጥለው ነበር ፤

ወአገብዖ እንዘ አልቦ ዘእነሥእ እም ኀበ ዘይፈድየኒ ፣

ከሚከፍለኝ ሰው የሚከፍለኝ ገን ዘብ ሳይኖር እመልሰው ነበር ፤

፴፰፡ ወእመ አግዓርክዋ ለምድር ፣

የምድርን ፍሬ ነስቼ ምድርን አስጨሂየት እንደሆነ ፤

ወእመ በከየ ትለሚሃ እምኔየ ፣

ድምበር አፍርሼ እንደሆነ ፤

፴፱፡ ወእመ በላዕኩ እክለ ባሕቲትየ ዘእንበለ ሤጥ፣

አሥራቱን በኵራቱን ያለዋጋ በልቼ እንደሆነ ፤

ወእመ ሰደድክዎ ለበዓለ ምድር ፣

አራሹን ውረድ ከማማ፣ ውጣ ከአውድማ ብዬ ሰድጄው እንደ ሆነ ፤

ወአሕመምክዎ ነፍሶ ፣

ልቡናውን አሳዝኜው እንደሆነ፤

፵፡ ህየንተ ሥርናይ ክርዳድ ይብ ቊለኒ ፣

ስንዴ በሚበቅልበት ክርዳድ ይብ ቀልበት ፤

ወህየንተ ሰገም ሕንዕዋል ፣

ገብስ በሚበቅልበት ሲናር ይብ ቀልበት ብዬ እንደሆነ ስለተድ ላው፣ ስለ ደስታው ፈንታ መከራ ይምጣብኝ ፤

ወኃደገ ኢዮብ ነገረ ፣

ኢዮብ መናገሩን ተወ ።

## ምዕራፍ ፴፪

ሠላሳ ሁለተኛው ምዕራፍ ይህ ነው ፤

፩፡ ወአርመሙ ፫ አዕርክቲሁ ፣

ሦስቱ ወዳጆቹ ዝም አሉ ፤

ወኢያውሥእዎ እንከ ለኢዮብ ፣

ለኢዮብ ዳግመኛ አልመለሱለ ትም ፤

እስመ ይጼድቅ ኢዮብ በቅድሜሆሙ፣

ኢዮብ በፊታቸው ይመጻደቅ ነበርና ተዉት፣ ቢሻው ይመጻደ ቅበት ብለው ፤ አንድም ይረታ ቸው ነበርና አልመለሱለትም ፤



፪፡ ወተምዓ ኤልዩስ ወልደ ብርክያል ዘቡዝ ዘሕዝበ አራም ዘብሔረ አው ስጢድ ፣

ኤልዩስ የእኅቱ ልጅ ነው፤ አን ድም ሰይፍ ጃግሬው ነው፤ ሁለ ቱንም ገሥጿቸዋል፤ ጌታም የሁ ለቱን ነገር ሲጠላ የሱን ነገር ወዶለታል ፤ የአውስጢድ ክፍል ከምትሆን ከአራም ወገን የሚ ሆን የብርክያል ልጅ ኤልዩስ ተቆጣ ፤

፫፡ ወተምዖ ለኢዮብ በሕቁ እስመ ይጼደቅ ቅድመ እግዚአብሔር ፣

በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ ነኝ ይል ነበርና በገቢር ባትሠራ በሐልዮ ሳትሠራ ቀረህ? ብሎ ገሠጸው ፤

ወተምዖሙ ጥቀ ለ፫ቱ አዕርክቲሁ፣

ሦስቱን ወዳጆቹን ገሠጻቸው ፤ እንደ ሌባ፣ እንደ ቀማኛ ኃጥዕ ነህ ለምን ትሉታላችሁ? በገቢር ባትሠራ በሐልዮ ሳትሠራ ቀረ ህን በሉት እንጂ፤

እስመ ስዕኑ አውሥአቶ ለኢዮብ ዘይትማሰል ፣

ዘይትማሰሎ ለነገሩ ዘይትማሰል ምስለ ነገሩ ብለህ ግጠም፣ ከነገሩ ጋራ የሚመስል ነገር መናገር መመለስ ተስኗቸዋልና ፤

ወረሰይዎ ከመ ዘኃጥዕ ፣

እንደ ሌባ እንደ ቀማኛ አድርገ ውታልና፤ አንድም በአጠገብ በአ

ጠገብ ለምን ትነግሩታላችሁ ገልጣችሁ ኃጥዕ በሉት እንጂ፤

፬፡ ወጸንሐሙ ኤልዩስ ያውሥእዎ ለኢዮብ እስመ ይልሕቅዎ በመዋዕሊ ሆሙ ፣

ለኢዮብ ይመልሱለት ዘንድ በዘ መን ይበልጡታልና፣ ኤልዩስ ኋላ ይመልስላቸው ዘንድ ጠበቃቸው፤

፭፡ ወርእዮ ኤልዩስ ከመ አልቦ ነገር ውስተ አፈ ፫ቱ ዕደው ወተምዖሙ በመዓቱ ፣

ኤልዩስ በሦስቱ ሰዎች አንደ በት ነገር እንደሌለ አይቶ ፈጽሞ ተቆጣቸው ፤

፮፡ ወተሰጥወ ኤልዩስ ወልደ በራክዩ ዘቡዝ ፣

በራክዩ አባቱ፣ ቡዝ እናቱ፤ አን ድም በራክዩ አያቱ፣ ቡዝ አባቱ፤ አንድም ለአንድ ሰው ሁለት ስም አለው፤ የቡዝ ወገን የሚሆን የበራክዩ ልጅ ኤልዩስ መለሰ ፤

ወይቤ ንዑስ አነ በመዋዕልየ ፣

እኔ በዘመን ታናሽ ነኝ ፤

ወአንትሙሰ ልሂቃን ወሊቃውንት፣

እናንተ ግን ሽማግሌዎች አዋቂ ዎች ናን ትላላችሁ ፤

በእንተዝ አርመምኩ ፈሪህየ ከመ እንግርክሙ ዘእሔሊ ፣

ያሰብኩትን ኋላ እነግራችሁ ዘንድ ስለዚህ ነገር ፈርቼ ዝም አልሁ፤

www.ethiopianorthodox.org

፯፡ ወእቤ ባሕቱ አኮ ዓመታት ዘያስ ተናግራ ፤

ነገር ግን ብዙ ዘመኖች የጥበ ብን ነገር የሚያናግሩ አይደለም፤

ዘአብዝኃኒ ክራማተ ኢየአምራ ለጥ በብ ፤

ዘመንን ያበዛ ሰው ጥበብን የሚ ያውቃት አይደለም ፤

፰፡ ዳዕሙ መንፈስ ዘሳዕለ መዋቲ፤

በሟች ሰው ላይ ያለ መንፈስ ቅዱስ ያውቃታል እንጂ ፤

ወመንፈስ ዘኮሎ ይመልክ ውእቱ ይሜህር ፤

መንፈስ ዘኮሎ ለማለት ደግሞ ታል፤ ሁሉን የሚገዛ የእግዚአብ ሔር ሕይወቱ መንፈስ ቅዱስ እሱ ያስተምራል ፤

፱፡ አኮ እለ አብዝኅኑ ክራማተ ጠቢ ባን ፤

ዘመንን ያበዙ ሰዎች አዋቆች አይደሉም ፤

ሊቃውንትኒ ኢየአምርዋ ለፍትሕ፤

ሊቃውንቱም ፍርድን አያውቋ ትም ማስተማር ተሰጥቷቸው፤ ስለማስረዳት ማስረዳት ተሰጥቷ ቸው ስለ ማስተማር አይሆንላ ቸውምና ፤

፲፡ ወባሕቱ እቤ ስምዑኒ እንግርክሙ ዘአአምር ፤

ነገር ግን እኔ የማውቀውን እነ ግራችሁ ዘንድ ስሙኝ አልሁ ፤

ወአፅምዑኒ ነገርየ ፤

ነገሬን አድምጡኝ ፤

፲፩፡ ወለክሙኒ አየድዓክሙ እስከ ትረክቡ ዘትነግሩ ፤

የምትናገሩት እስክታገኙ ድረስ ለናንተ እነግራችኋለሁ፤

፲፪፡ ወናሁ ተኃጥአ ዘይጌሥፆ ለኢ ዮብ ፤

ኢዮብን የሚገሥፀው ሰው ታጣ፤

ወዘያወሥእ ቃለ ለእንተ ነበበ እም ኔክሙ ፤

ከናንተ ለተናገረው ነገር የሚ መልስ ታጥቷልና ፤

ከመ ኢትበሉ ረከብነ ጥበበ እምነበ እግዚአብሔር ወአፈድፈድነ ፤

ጥበብን ከእግዚአብሔር አገኘን፤ አበዛን እንዳትሉ ከናንተ ጥበብ ታጣ ፤

፲፫፡ ወአባሕክምዎ ለሰብእ ይንብብ ዘከመዝ ነገረ ፤

እንዲህ እንዲህ ያለ ነገር ይናገር ዘንድ ሰውን አሠለጠናችሁት ፤

፲፬፡ ወፈራህክሙ ወኢያውሣእክሙ፤

ፈራችሁ አልመለሳችሁም ፤

ወበልየ ነገር እምኔክሙ ፤

ከናንት ነገር ጠፍቷልና ፤

፲፭፡ ጸናሕኩ ወኢነገርኩክሙ ፤

ቆየሁ አልተናገርኋችሁም ፤



እስመ አርመምክሙ ወኢያውሣእክ ሙኒ ፤

ዝም ብላችኋልና አልመለሳችሁ ምና ፤

፲፮፡ ኀበ ተናገረ ኤልዩስ አውሥአ ወይቤ ፤

ኤልዩስ ከተናገረ ዘንድ መለሰ፤ እንዲህ አለ ፤

ስማዕ ዘእነግረከ ካዕበ ፤

ስማዕ ካዕበ ዘእነግረከ ካዕበ ብለህ መግጠም ነው፤ ዳግመኛ የምነ ግርህን ነገር ስማ ፤

፲፯፡ ምሉዕ ነገር ኀቤየ ፤

ካዕበ ምሉዕ ነገር ኀቤየ ብሎ መግጠም ነው፤ ዳግመኛ ነገር እስከ አንገቴ መልቷል ፤

ወቀተለኒ መንፈስ ከርሥየ ፤

የልቡናዬ ዕውቀት እስከ አንገቴ ደርሶ ቀድጄህ ልውጣ ይለኛል፤ አንድም ወይሠጥወኒ ከርሥየ ዕውቀት ሰውነትህን ቀድጄህ ልውጣ ይለኛል ፤

፲፰፡ ወተአሥረት ከርሥየ ከመ ዝቀ ወይን ፤

ሰውነቴ እንደ ወይን ረዋት በዕ ውቀት ታሠረች ፤

ወትፈልህ ውዑየ ፤

ተናገር ተናገር ይለኛል ፤

፲፱፡ ወከመ ምብኳሐ ነሐቢ ስጡጥ እነብብ ከመ አእርፍ ፤

ስጡቅ ጥቁብ ይላል፤ እንደ ተቀ ደደ እንደ ተሰፋ እንደ ጃን ሽላሚ ወናፍ ያ ሲይዙት እንዲያኮርፍ ሲተዉት እንዲያርፍ ተናግሬ አርፍ ዘንድ ፤

ወእከሥት ከናፍርየ ፤

ከንፈሮቼን እገልጣለሁ ፤

፳፡ እስመ ኢየሐፍር እምዕጓለ እመ ሕያው ፤

ከሰው የተነሣ አላፍርምና ፤

ወኢይጌግዕ እመዋቲ ፤

ከሟች ሰው የተነሣ አልፈራም ተግ ተግ አልልም፤

፳፩፡ ወኢየአምር አድልዎ ለገጽ ፤

ለሰው ፊት ማድላት አላውቅም፤

ወእመሂ ቦ ዘየሐፍር እምሰብእ ፤

ከሰው የሚያፍር ሰው ቢኖር እኔ አላፍርም ፡፡

## ምዕራፍ ፴፫

ሠላሳ ሦስተኛው ምዕራፍ ይህ ነው ፤

፩፡ ወባሕቱ ስምዓኒ ኢዮብ ቃልየ፤

ነገር ግን ኢዮብ ነገሬን ስማኝ፤

ወአፅምዓኒ ነገርየ ፤

ነገሬን አድምጠኝ ፤

www.ethiopianorthodox.org

፪፡ ናሁ ከሠትኩ አፉየ ወነበበ ልሳንየ ፤

እነሆ አፌን ገለጥሁ፤ አንደበቴ እውነት ነገር ተናገረ ፡፡

፫፡ ወንጹሐ ይሔሊ ልብየ ፤

ልቤ እውነት ነገርን ያስባል፡፡

ወጥበበ ከናፍርየ ፤

ከንፈሬም ጥበብ የሚሆን ነገርን ይናገራል ፡፡

ወንጹሐ ይመክር መንፈስየ ፤

ልቡናዬ እውነት ነገርን ያስባል፡፡

፬፡ እግዚአብሔር ፈጠረኒ ፤

ሐሰት እንዳልናገር እግዚአብሔር ፈጥሮኛል ፡፡

ወመንፈስ ዘኰሎ ይመልክ ይሜህረኒ ፤

ሁሉን የሚገዛ የእግዚአብሔር ሕይወት፡ መንፈስ ቅዱስ ያስተምረኛል ፡፡

፭፡ እመ ትክል ታወሥአኒ በዝ ነገር ተአገሠኒ ፤

በዚህ ነገር ትመልሰኝ ዘንድ ይቻልህ እንደሆነ ታገሠኝ ፡፡

አነኒ እንግርከ አንተሂ አውሥአኒ፤

እኔ ልንገርህ፤ አንተም መልስልኝ ፡፡

፮፡ እምጽቡር ብሕባሔከ ከማየ ፤

ትላንትና ከተወለድህ ከአንተ ከመንጨረቁ ጋራ እከራከራለሁ

ትለኝ እንደሆነ ከመሬት፡ አንድም ከአዳም መፈጠርህ እንደኔ ነው፡፡

፯፡ ወእምኔሁ ቅሣሜኒ ኢያኀዝንከ፤

ከመሬት ከመፈጠራችን የተነሣ በሞት መለቀማችን፤ በአእምሮ መጣፈጣችን አያሳዝንህ ፡፡

ወኢትትሐዘበኒ ፤

አያውቅም ብለህ አትጠራጠረኝ ፡፡

ወእዴየኒ ኢያከብድ ላዕሌከ ፤

ቃሌን አላበዛብህም ፡፡

፰፡ ወባሕቱ እነግረከ ግፍዓከ ፤

ነገር ግን በደልህን እነግርሃለሁ፡፡

፱፡ ስምዓኒ ቃለ ነገርየ ፤

የተናገርኩትን ቃሌን ስማኝ ፡፡

እስመ ትቤ ንጹሕ አነ ወኢአበስኩ፤

እኔ ንጹሕ ነኝ አልበደልሁም ብለሃልና ፡፡

ወጻድቅ አነ ወኢገበርኩ ኃጢአተ ፤

እኔ ጻድቅ ነኝ ኃጢአት አልሠራሁም ብለሃልና ፡፡

ወረሰይከ ሎቱ ዘይነግር ፤

ነጋሪ ሽተህለታልና፤ ወነጸርከ ምክረ ረሲአን ብሎ ነበርና፤ ምሥጢሩ አላዋቂ አድርጎሃልና ሲል ነው፡፡ አንድም ወረሰይከ ሊተ ዘይነግር ይላል፤ ኃጢአቴን የሚናገር ደዌ አሕመጣህብኝ ብለሃልና ፡፡



፲፡ ወረሰየኒ ከመ ጸላዒ ፤

እንደ ጠላት አደረገኝ ብለሃልና፡፡

፲፩፡ ወዓቀሞን ዲበ ዳሕፀ ለእገርየ፤

እግሮቼን በዳሕፀ መከራ አቆማቸው ብለሃልና ፡፡

ወዐቀበ ኰሎ ፍናውየ ፤

ሥራዬን ሁሉ ተመለከተ ብለሃልና ፡፡

፲፪፡ እፎ ትብል ጻድቅ አነ ፤

እኔ ጻድቅ ነኝ እንዴት ትላለህ፡፡

ወኢይሰምዓኒ ዘለዓለም ውእቱ ዘላዕለ መዋቲ ፤

በሟች ሰው ላይ ለዘለዓለም የሚኖር እግዚአብሔር እንዴት አይሰማኝም ትላለህ፡፡

፲፫፡ እፎ ትብል ኢይሰምዓኒ ኰሎ ነገረ ጽድቅየ ፤

እውነተኛ ነገሬን አይሰማኝም እንዴት ትላለህ ፡፡

፲፬፡ እምከመ ምዕረ ነገረ እግዚአብሔር ፤

እግዚአብሔር በነቢያት አድሮ ከተናገረ በኋላ ፡፡

ዳግመሰ በሕልም ፤

ዳግመኛ በሕልም ይነግረዋል፡፡

ወእመ አኮ በነገረ ሌሊት ፤

በሕልም ነግሮት አልመለስም ቢል ደዌ ያመጣበታል ፡፡

፲፭፡ ወያመጽእ ዓቢየ ድንጋፄ ላዕለ ሰብእ እንዘ ይሰክብ ዲበ ምስካቡ ፤

በደዌው አልመለስም ቢል በመኝታው ተኝቶ ሳለ ጽኑ ድንጋፄ ያመጣበታል ፡፡

፲፮፡ ሶቤሃ ይከሥት ልቦ ለሰብእ ከመ ይርዓይ ግርማ ወይፍራህ ፤

የጌታን ግርማ መዓቱን አይቶ ይፈራ ዘንድ የሰውን ልቡና ያን ጊዜ ይገልጣል ፡፡

፲፯፡ ወይመይጦ ለሰብእ እምኃጢአት ፤

እንዲህ አድርጎ ሰውን ከኃጢአት ይመልሰዋል ፡፡

ወያድኅኖ ለሥጋሁ እምድቀት ፤

ሰውነቱን ከመከራ ያድነዋል፡፡

፲፰፡ ወይምህካ ለነፍሱ እሞት ፤

ነፍሱን ከሞት ይራራላታል፡፡

ከመ ኢይደቅ ውስተ ቀትል ፤

በመከራ እንዳይወድቅ ፡፡

፲፱፡ ወካዕበ ይጌሥፆ በደዌ በውስተ ምስካቡ ፤

በመኝታው ሳለ ዳግመኛ በደዌ ይገሥፀዋል ፡፡

ወይቈቀሎ ኰሎ አዕፅምቲሁ ፤

አጥንቶቹ ሁሉ ቋ ቋ ይላሉ፤ ይደርቃሉ ማለት ይከሳሉ ፡፡

www.ethiopianorthodox.org

፳፡ ወኢይክል ጥኢመ ኵሎ መብልዐ እክል ወትፈቱ ነፍሱ ትብላዕ ።

ሰውነቱ ትበላ ዘንድ ትወዳለች ምንምን የላመ የጣመ አይቀምስም ፤

፳፩፡ እስከ የሐልቅ ሥጋሁ ወያስተርኢ አዕፅምቲሁ ዕራቁ ።

ሥጋው እስቲከሳ አጥንቱ ባዶውን እስኪታይ ድረስ ፤

፳፪፡ ወአልጸቀት ነፍሱ ለሞት ወሕይወቱሂ ለሲኦል ።

ነፍሱ ለሞት ሰውነቱ ለመቃብር እስክትደርስ ድረስ ፤

፳፫፡ ወእመ ኮኑ ፲ቱ ፻ት መላእክተ ሞት ፩ እምኔሆሙ ኢይቀትሎ ።

ለመዓት የታዘዙ መላእክት ሽህ ቢሆኑ አንዱ ስንኳ አይገድለውም፤

ለእመ ኢሐለየ በልቡ ይትመየጥ ኀበ እግዚአብሔር ።

ወደ እግዚአብሔር ይመለስ ዘንድ ካላሰበ ሁሉም ይገድሉታል እንጂ፤ አንድም ለመርዳት የታዘዙ መላእክት ብዙ ቢሆኑ አንዱ ስንኳ ብቻ የሚቀር አይደለም፤ ሁሉም ይረዱታል እንጂ በልቡ ወደ እግዚአብሔር ይመለስ ዘንድ ካሰበ ፤

ከመ ይንግሮ ለሰብእ ኃጢአቶ ወያርእዮ ጌጋዮ ።

ኃጢአቱን ለሰው ይነግረው ዘንድ በደሉን ይገልጥ ዘንድ፤

ወይትዓቀብ ስመ ኢይደቅ ውስተ ሞት ።

በመከራ እንዳይወድቅ ይጠበቃል ፤

፳፬፡ ወይሔድሳ ለነፍሱ ከመ ምረገ አረፍት ።

ያረጀውን ምርግ አስለቅቀው እንዲያድሱ ሰውነቱን በንስሐ። በተድላ በደስታ ያድሳታል ፤

ወአዕፅምቲሁኒ ይመልዑ አንጕዐ ።

አጥንቶቹ ስቡን ይመላሉ ማለት ተድላውን ደስታውን ያገኛሉ ፤

፳፭፡ ወያደክሞ ለሥጋሁ ከመ ዘሕፃን ።

ሰውነቱን እንደ ሕፃን ገላ ያለሰልሰዋል ፤

ወይሬስዮ ጽኑዓ እምሰብእ ።

ያደክሞ ማለቱ ያለሰልሰዋል ሲል ነው እንጂ ከሰው ሁሉ ያጸናዋል ፤

፳፮፡ ወዘጸለየሂ ኀበ እግዚአብሔር ይትዌከፎ ።

ከእግዚአብሔር ዘንድ የለመነውን ልመና ይሰማዋል፤

ወይበውዕ በንጹሕ ገጽ እንዘ ይነግር።

በንጹሕ ልቡና ሥረይ ሊተ እያለ ይገባል ፤

ወይፈድዮ ለሰብእ ጽድቆ ።

ለሰው የምግባሩን ዋጋ ይሰጠዋል ፤



፳፯፡ ወሶበሂ የሐይስ ርእሶ ሰብእ ።

ያን ጊዜ ሰው ራሱን ይነቅፋል። ሰው ሁኖ ይህን ያህል ኃጢአት ብሎ፤ አንድም ሴላው ፤

ወለሊሁ ይብል ምንተ ገበርኩ ወኢመጠንየ ዘረከበኒ በጌጋይየ ።

እሱ ቅሉ ምን አደረግሁ በኃጢአቴ ያገኘኝ መከራ መጠኔ አይደለም። ኃጢአቴ ሲበዛ ነው ይላል ፤

፳፰፡ ወአድኅና ለነፍስየ ከመ ኢትሖር ውስተ ሙስና ።

ወደጥፋት እንዳትሔድ ሰውነቴን በቸርነቱ አዳናት እንጂ፤ አንድም ሰውነቴን በቸርነቱ አዳናት በለው ይለዋል ፤

ወትርዓይ ብርሃነ ሕይወትየ ።

ሰውነቴ ተድላውን ደስታውን ታይ ዘንድ ፤

፳፱፡ ዘኵሎ ይገብር ናሁ ኃያል ።

ይህን ሁሉ የሚያደርግ እነሆ ኃያል እግዚአብሔር ነው ፤

ወ፫ቱ ፍናዊሁ ለብእሲ ።

የሰው ሥራው ሦስት ነው፤ በፊት በሕልም ይነግረዋል። ኋላ በነቢያት አድሮ ይነግረዋል። ባይሰማ ኋላ ደዌ ያመጣበታል፤ አንተም ባትሰማ ደዌ አመጣብህ፤ አንድም ሐልዮ ነቢብ ገቢር ነው፤ አንተም በዚህ ሁሉ ኃጢአት ሠራህ። በዚህ ምክንያት መከራ መጣብህ ፤ አንድም የሰው ሥራው ሦስት ወገን ነው፤ ሕፃንነት። ጉልማስነት። ዕርግና ነው፤ በሕፃንነቱ ነበርህበት በጐልማስነቱም አለህበት። ኋላም ታረጃለህ፤ አንድም ጥዒና ደዌ ሞት ነው ፤ በጥዒናው ነበርህበት። በደዌውም አለህበት። ኋላም ትሞታለህ፤ አንድም ደዌ ሞት መቃብር ነው፤ በደዌው አለህበት። ኋላም ትሞታለህ። ትቀበራለህ፤ አንድም ሞት መቃብር ትንሣኤ ነው፤ ሞተህ ትቀበራለህ። ኋላም ትነሣለህ ፤

፴፡ ወባሕቱ አድኅና ለነፍስየ እሞት ከመ ትሰባሕ ሕይወትየ በውስተ ብርሃን ።

ሰውነቴ በተድላ በደስታ ትከብር ዘንድ ነገር ግን ሰውነቴን ከሞት አድናት ፤

፴፩፡ አጽምዓኒ ኢዮብ ወስምዓኒ ።

ኢዮብ ነገሬን አድምጠኝ ነገሬን ስማኝ ፤

ወጸጥ በል ወአነ እነግረከ ።

ጸጥ በል እኔ እነግርሃለሁ ፤

፴፪፡ ወእመሰ ቦ ዘትብል በል ንግር ዘትፈቅድ ጥቀ ትጽድቅ ።

በል ተናገር የምትል እንደሆነ እውነተኛ ትባል ዘንድ እወዳለሁ ፤

www.ethiopianorthodox.org

፴፫፡ ወእመ አኮሰ አንተ ስምዓኒ ፣

ነገር እንደ አንተ ካልሆነ እን ደኔ ከሆነ ስማኝ ፤

ወአርምም እምሀርከ ጥበበ ፣

ጥበብን አስተምርሀ ዘንድ ዝም በል ፡፡

## ምዕራፍ ፴፬

ሠላሳ አራተኛው ምዕራፍ ይህ ነው ፤

### ጉባኤ

፩፡ ወአውሥአ ኤልዩስ ወይቤ ስም ዑኒ ጠቢባን ፣

ኤልዩስ መለሰ፣ እንዲህ አለ፤ አዋቆች ነን የምትሉ ስሙ ፤

፪፡ ወአዕምዑኒ ሠናየ ማዕምራን ፣

በጎ ነገርን የምታውቁ፤ አንድም አዋቆች ነን የምትሉ እናንተ በጎ ነገሬን ስሙኝ ፤

፫፡ እስመ ዕዝን ነገረ ያሚክር ፣

ጆሮ በጎ ነገርን ያውቃልና ፤

ወጉርዔ እክለ ይጥዕም ፣

ጉረሮ የእኅል ጣዕም ያውቃልና የነገር ጣዕም በጆሮ ፣ የእህል ጣዕም በጉረሮ እንዲሉ ፤

፬፡ ደይኑ ንኅሥእ ለርዕስነ ፣

እመ ኢገሠዕኖ ለኢዮብ ያለበት ነው፤ ክፉና በጎ የምናውቅበት አዕምሮ ተሰጥቶን ሳለ ከእግዚአ ብሔር ጋራ በተከራከርሁ ሲል ዝም ብንለው መከራ ያገኘናል፤

ነአምር ምንት ይኄይስ በማዕከሌነ፣

በመካከላችን መከራከሩ እንዲ ሻል እናውቃለን ፤

፭፡ እስመ ይቤ ኢዮብ ጻድቅ አነ ፣

ኢዮብ እኔ ጻድቅ ነኝ ብሏልና፤

ወሠለጠ ሊተ እግዚአብሔር ኰነኔየ፣

እግዚአብሔር ደዌን አስጐረጐ ሰኝ ብሏልና ፤

ወሐሰወኒ ፍትሕየ ፣

እግዚአብሔር በሐሰት ፈረደ ብኝ ብሏልና ፤

ወአሐምም በግፍዕ ዘእንበለ አበሳ ፣

ኃጢአት ሳልሠራ በግፍዕ መከራ እቀበላለሁ ብሏልና ፤

፯፡ መኑ ሰብእ ከመ ኢዮብ ዘይሰ ትያ ለትዕግሥት ከመ ማይ ፣

ትእግሥትን እንደ ውሀ የሚጠ ጣት እንደ ኢዮብ ያለ ሰው ማነው? ፍና ተሣልቆ ነው፤ አን ድም በእውነቱ ፤

፰፡ ወኢአበሰ ወኢጌገየ ፣

ፈጽሞ ያልበደለ ፤

ወማሙራ ኢተሳተፈ ምስለ ገበርተ ዓመፃ ፣

ዓመፅን ከሚሠሩ ሰዎች ጋራ አንድ ያልሆነ ?



ወኢሖረ ምስለ ኃጥአን ፣

ከኃጥአን ጋራ ጸንቶ ያልኖረ እንደ ኢዮብ ያለ ሰው ማነው፤

፱፡ ወይቤ ኢይዌሕይዎ ለሰብእ በሩ ጸቱ ቅድመ እግዚአብሔር ፣

ሥላሴ ሰውን ፈጥኖ በሠራው ኃጢአት በመከራ አይገሥጹ ትም ያለ እንደ ኢዮብ ማን አለ? አንድም ሥላሴ ሰውን ፈጥኖ በሠራው ኃጢአት በመከራ አይ ገሥጹትም አለ እንጂ እንዲ ህማ ባይል ትዕግሥትን እንደ ውሀ አብዝቶ የሚጠጣት እንደ ኢዮብ ያለ ማነው ?

፲፡ ወይእዜኒ ስምዑኒ ጠቢባነ ልብ፣

አሁንም አዋቆች ነን የምትሉ ስሙኝ ፤

ወኢትፍቅዱ ተአብሱ ቅድመ እግዚ አብሔር ፣

በእግዚአብሔር ፊት ትበድሉ ዘንድ አትውደዱ ፤

ወኢትውሕከዎ ለጻድቅ በቅድመ ዘኵሉ ይመልክ ፣

ሁሉን በሚገዛ በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ ኢዮብን አታውኩት፤

፲፡ ወይፈድዮ ለኵሉ ሰብእ በከመ ምግባሩ ፣

ለሰው ሁሉ እንደ ሥራው ይከ ፍለዋል ፤

ወይረክቦ ለሰብእ በከመ ፍኖቱ ፣

ሰውን እንደ ሥራው ፍዳ ያገ ኘዋል፣ ለጻድቁ ዋጋውን ይሠ ጠዋል በኃጥኡ ይፈርድበታል፤

፲፩፡ ትሬስዮኑ ከመ እግዚአብሔር ይገፍዕ ፣

እግዚአብሔርን ገፋዒ ታሰኘዋ ለህን ፤

ወዘኵሎ ይመልክ ይዌልጥ ፍትሐ፣

ሁሉን የሚገዛ እሱ ፍርድን ይለውጣልን ፤

ዘውእቱ ፈጠራ ለምድር ፣

ምድርን የፈጠራት እግዚአብ ሔርን በሐሰት ይፈርዳል ትለዋ ለህን ፤

፲፪፡ መኑ ውእቱ ዘገብረ ዘታሕተ ሰማይ ፣

ከሰማይ በታች ያለውን የፈጠረ ማነው ?

ወኵሎ ዘውስቴታ ፣

በውስጥዋ ያለውን ሁሉ የፈጠረ ማነው ?

፲፫፡ ለእመ ፈቀደ ያጽንዕ ወየኃዝ መንፈሰ ዘእምኀቤሁ ፣

እሱ በሕይወት ያጸናው ዘንድ ቢወድ የሚገድለው ማነው ?

፲፬፡ ወይመውት ኵሉ ዘሥጋ ፣

ሥጋዊ ደማዊ ሁሉ አንድ ሁኖ ይሞታል ፤

www.ethiopianorthodox.org

ኵሉ መዋቲ ውስተ መሬት ይገብዕ እምኀበ ተፈጥረ ፤

ሟች ሰው ሁሉ ወደ ተፈጠረ በት ወደ መሬት ይመለሳል፤

፲፮፡ ወእመ አኮሰ ተገሠፅ ፤

ነገር እንደኔ ከሆነ እንደ አንተ ካልሆነ ተመከር ፤

ወስማዕ ዘንተ ወአፅምዕ ቃለ ነገርየ አንተ ፤

ይህን ስማ፤ የተናገርሁትን ነገር አንተ አድምጥ ፤

፲፯፡ ዝኩ ዘይጸልዕ ዓመፃ ፤

ዓመፅን የሚጠላ እሱ ነው ፤

ወዘያጠፍኦሙ ለእኩያን ዘለዓለም ጻድቅ ፤

ክፉዎችን የሚያጠፋቸው ለዘለ ዓለም የሚኖር እውነተኛ እሱ ነው ፤

፲፰፡ ጽሩፍ ዘይብሎ ለንጉሥ አበስከ፤

ንጉሡን ፤ አንድም ጌታን በደ ልህ የሚል የተነቀፈ ነው፤

ወእኩይሂ ብሂል ለመላእክት ፤

እኩያንሂ ሲል ነው፤ መላእክትን ክፉዎች ናቸው የሚል የተነቀፈ ነው፤ አንድም ሐዋርያትን ክፉ ዎች ናቸው የሚል የተነቀፈ ነው ፤

፲፱፡ ዘኢየሐፍር ገጸ ክቡር ፤

የደገን ሰው ፊት የማያፍር ፤

ወዘኢየአምር አክብሮ ዓቢይ ፤

ደገን ሰው ማክበር የማያውቅ፤

፳፡ ወዘኢይጌግዕ እምገጸሙ ከንቱ ይረክቦ ፤

ተግ ተግ የማይል መከራ ያገኘ ዋል፤ አንድም ከንቱ ነው ፤

ዘይጸርሕ ወኢያፀምዮ ለሰብእ ፤

የሚጮህ ሰውን የማይሰማ ፤

ወገብረ እኩየ ዲበ ምስኪናን ፤

በድሆች ላይ ክፉ ነገር የሚያ ደርግ ፤

፳፩፡ ለሊሁ ይሬኢ ምግባሮ ለሰብእ፤

ጌታ ምግባሩን መርምሮ ያጠ ፋዋል ፤

፳፪፡ አልቦ ምንትኒ ዘይትኃባዕ እም ኔሁ ፤

ከሱ ምንም ምን የሚሠወር የለም ፤

አልቦ ብሔር ኀበ ይትኃብዕዎ ገበርተ ዓመፃ ፤

ዓመፅን የሚሠሩ ሰዎች የሚሠ ወሩበት ቦታ የለም ፤

እስመ ኢያመሥጡ እንከ እምእግዚ አብሔር ዘኵሎ ይሬኢ ፤

ብርሃናትን፤ ነፋሳትን ከፈጠረ ከእግዚአብሔር አያመልጥምና፤

፳፫፡ ወዘየአምር ዘአልቦ አሠር ፤

ሁሉን የሚያውቅ ባሕርዩ የማይ መረመር እሱ ነው ፤



ክቡራተ ወመንክራተ ዘአልቦ ኍልቍ፤

ቍጥር ስፍር የሌላቸው የከበሩ ድንቅ ተአምራትን የሚያደርግ እሱ ነው ፤

፳፭፡ ዘየአምር ምግባሮሙ ፤

የኃጥአንን ሥራቸውን መርምሮ የሚያውቅ ፤

ወያገብዕ ሌሊተ ወየሐምሞሙ ፤

መከራ የሚያመጣ በመከራ የሚ ያስጨንቃቸው ፤

፳፮፡ ወያጠፍኦሙ ለኃጥአን ፤

ኃጥአንን የሚያጠፋቸው እሱ ነው ፤

ጻድቃንሰ ቅድሜሁ እሙንቱ ፤

ጻድቃን ግን በፊቱ በባለሟልነት ጸንተው ይኖራሉ ፤

፳፯፡ ወእለሰ ተግሕሡ እምሕገ እግ ዚአብሔር ፤

ከሕገ እግዚአብሔር የራቁ ሰዎች ግን ፤

ወኢየአምሩ ኵነኔሁ ከመ ያገብዕ ላዕሌሆሙ ዓውያተ ነዳያን ወይሰምዕ ገዓረ ምስኪናን ፤

የምስኪናን የነዳያንን ጩኸት ሰምቶ ፍርዱን ወደሳቸው እንዲ መልስባቸው አያውቁም፤

፳፰፡ ውእቱ ይሁቦሙ ዕረፍተ ፤

ልመናቸውን ሰምቶ ዕረፍትን ይሰጣቸዋል ፤

ወመኑ ውእቱ ዘይኴንን ወየኃብዕ ገጸ ፤

በሐሰት የሚፈርድ ሰውን ፊቱን በሞት የሚሠውር ማነው? አን ድም ሐሰት ፈርዶ፤ እንዳያየው ፊቱን የሚሠውር ማነው ?

ወአልቦ ዘይሬዕዮ በበሕዝቡ ወበበ ሰብኡ ኅቡረ ፤

በበያታሁ ሲል ነው፤ ጌታን በየ ወገኑ የሚያየው የለም ፤ አን ድም ከወገኖቹ እንዲያየው የሚ ያደርግ ማነው ?

፴፡ ወያነግሥ ብእሴ መደልወ በእ ንተ እከየ ሕዝቡ ፤

ወነበርኩ ከመ ንጉሥ ብሎ ነበ ርና ክፉማ ብሆን ያነግሠኝ ነበር? ትለኝ እንደሆነ ልማድ ነው፤ ስለ ሕዝቡ ክፋት ክፉ ሰውን ያነግሣል ፤

ዘይብሎ ለኃያል ነሣዕኩ ወአልብየ አኀዝ ፤

ኃይለኛውን ወሰድሁ፤ መያገ ፎን ያዝ የሚል እሱ ነው፤ አን ድም እግዚአብሔርን ወሰድሁ መያገፎን ያዝ የሚለው ማነው? አንድም እንዲህ የሚለውን የሚ ያጠፋ ማነው ፤

ወያነግሥ ብእሴ ራትዓ በእንተ ሠናየ ሕዝቡ ፤

ስለበጎዎች ሰዎች ግን ቀና ንጉሥ ያነግሣል ፤

www.ethiopianorthodox.org

፳፰፡ አነኒ ለልየ እሬኢ ወአንተኒ አርእየኒ ፤

እኔም ተናገርሁ፣ አንተም ተና ገር ፤

እመ ዓመፃ ገበርኩ ከመ ኢይድግም ተናግሮ ፤

ሐሰት ተናግሬ እንደሆነ ዳግ መኛ እንዳልናገር ፤

፳፱፡ ቦኑ እም፡ነቤከ ነሣዕክዋ ከመ ትትረኃቅ አንተ ፤

ጥበብ ትርቀኝ ዘንድ ከአንተ ተቀብያታለሁን ፤

እስመ አንተ ተሐሪ ወአኮ አነ ፤

የተበደልሁ እኔ ነኝ ብለሃልና እኔ አይደለሁምና ፤ አንድም ከሳሽ እኔ ነኝ ብለሃልና እኔ አይደለሁምና፤

፴፡ ወእመቦ ዘተአምር ንግር ፤

የምታውቀው ነገር አለ እንደ ሆነ ተናገር ፤

እስመ ጠቢባነ ልብ ይብሉ ከመዝ፣

ጠቢባነ ልብ ሳፍር በልዳዶስ ድኃ ያመልክት፣ ዳኛ ይሚገት ብለዋልና፤ አንድም ከሳሽ ይጠ ይቅ ፣ ተከሳሽ ይመልስ ፣ ዳኛ ሰምቶ ይፍረድ ብለዋልና፤

ወብእሲ ጠቢብ ይሰምዓኒ ቃልየ ፤

ብልህ ሰው ነገሬን ይሰማኛል፤

፴፩፡ ወኢዮብሰ አኮ ከመ ጠቢብ ዘይትናገር ፤

ኢዮብ ግን ብልህ እንደ መሆኑ እንደ ብልህ ሰው የሚናገር አይደለም ፤

ወነገሩሂ አኮ ከመ ምሁር ፤

ነገሩም የተማረ እንደ መሆኑ እንደ ተማረ ሰው አይደለም፤

፴፪፡ ወባሕቱ ተመሀር ኢዮብ ፤

ነገር ግን ኢዮብ አልተማርከ ምና ተማር ፤

ወኢታውሥእ ከመ ዓብዳን ከመ ኢትወስክ እንከ ዕበደ ዲበ ኃጣው ኢከ ፤

በኃጢአት ላይ ኃጢአት እንዳት ጨምር እንግዲህ ወዲህ እንደ አላዋቆች አትናገር ፤

ወይከውነከ ጌጋየ ነቢበ ብዙኅ ነገር ቅድመ እግዚአብሔር ፤

በእግዚአብሔር ፊት ብዙ ነገር መናገር ኃጢአት ይሆንብሃል።

## ምዕራፍ ፴፭

### ሠላሳ አምስተኛው ምዕራፍ ይህ ነው ፤

፩፡ ወአውሥአ ኤልዩስ ወይቤ ፤

ኤልዩስ መለሰ፣ እንዲህ አለ፤

፪፡ ወምንተ ትብል ተዋቂሠከ አንተ፣

አንተ ከእግዚአብሔር ጋራ በተ ከራከርሁ ትላለህ፣ በተከራከርህ ጊዜ ምን ትላለህ ፤



ወምንትኑ አንተ ከመ ትበል ጻድቅ አነ በቅድመ እግዚአብሔር ፤

በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ ነኝ ትል ዘንድ አንተ ምንድነህ ፤

፫፡ ወትብል ምንተ እሬሲ እመ አበ ስኩ ፤

ብበድልስ ምን አደርጋለሁ የም ትል ፤

፬፡ አነ አወሥእከ ለከ ወለ፫ቱ አዕር ክቲከ ፤

እኔ ለአንተ ለሦስቱ ወዳጆችህ እመልስላችኋለሁ ፤

፭፡ ነጽር ሰማየ ወአእምር ሚመጠን ርኁቅ እምኔከ ደመናት ፤

ስንኳን ከርሱ ከሰማይ ትደርስ እንደሆነ እይ፣ ደመና ከአንተ ምን ያህል ርቋል ፤

፮፡ እመሂ አበስከ ምንተ ትሬሲ ላዕ ሌሁ ፤

ይኄይሰከኑ እመ አበስከ የም ትል ብትበድል እሱን ምን ታደ ርገዋለህ ፤

ወእመኒ ጌገይከ ብዙኃ ምንተ ትክል ገቢረ ፤

ብዙ ኃጢአት ብትሠራ ምን ማድረግ ይቻልሃል ፤

፯፡ ወእመ ጻድቅ አንተ ምንተ ወሀብኮ ወምንተ ነሥአ እምኤከ ፤

ጻድቅስ ብትሆን ምን ሰጠኸው ከአንተስ ምን ተቀበለ ፤

፰፡ ለሰብእ ዘከማከ ኃጢአትከ ፤

ብትበድልስ እንደ አንተ ያሉ ሰዎችን ነው እንጂ ለሱ ምን ታደርግለታለህ፤ አንድም ብት በድልም ራስህን ነው፤ በጎ ነገር ብታደርግም ለራስህ ነው ፤

፱፡ እምብዝኅሞሙ ለመሥተዓግላን የአወይዉ ፤

ከቀማኞች ብዛት የተነሣ ድኆች ያለቅሳሉ ይጮሃሉ ከነዚያም አንዱ አንተ ነህ ፤

ወይግዕሩ እመዝራዕተ ብዙኃን ፤

ከብዙዎች ሰዎች ሥልጣን የተ ነሣ ድኆች ያለቅሳሉ፣ ከነዚያ አንዱ አንተ ነህ ፤

፲፡ ወኢይቤ አይቴ ውእቱ እግዚአ ብሔር ዘፈጠረኒ ፤

የፈጠረኝ እግዚአብሔር ወዴት ነው አይልም፤ አንድም ወይቤ ይላል፣ ደኃው መከራ ሲጸናበት የፈጠረኝ እግዚአብሔር ወዴት ነው ይላል ፤

ወይኤዝዝ ንዋመ ሌሊት ፤

በሌሊት ዕረፍትን የሚሰጥ እሱ ነው ፤

ዘያኄይሰኒ እምእንስሳ ምድር ፤

በነባቢት ነፍስ ከእንስሳት፣ በደ ማዊት ነፍስ ከዕፀው ከአዕባን የሚያሸለኝ እሱ ነው፤

www.ethiopianorthodox.org

ወእምአዕዋፈ ሰማይ ፣

ከአዕዋፍ፤ አንድም ከአጋንንት የሚያሽለኝ እሱ ነው ፤

፴፩፡ በህየ ይጸርሑ ወኢይሰምዖሙ፣

ስለ ሰው ኃጢአት ይጮሃሉ አይሰማቸውም ፤

ወእምጽዕለተ እኩያን ፣

ከክፉ ሰዎች ስድብ የተነሣ ፤

፴፪፡ እስመ ኢይፈቅድ እግዚአብሔር እኩየ ይርአይ ፣

እግዚአብሔር ክፉ ነገር ያይ ዘንድ አይወድምና ፤

፴፫፡ እስመ ውእቱ ዘኮሎ ይመልክ ማዕምር ውእቱ ኢይሰምዖሙ ለገበርተ ዓመፃ ፣

ሁሉን የሚገዛ እሱ አዋቂ ነውና ክፉ የሚሠሩትን ሰዎች አይሰማቸውም ፤

ተዋቀስ እስኩ አንተ በቅድሜሁ እመ ትክል ሰብሖቶ ከመ ውእቱ፣

ስንኳን መከራከር እንደ አምላ ክነቱ ማመስገን ይቻልህ እንደ ሆነ እስተ ተከራከር፤ አንድም ነዲገከ ሰብሖቶ ማመስገኑን ትተህ ፤ አንድም እመ ትክል መዋየቶ ፣ መርታት ይቻልህ እንደሆነ እሱ እንዲረታህ፤ አን ድም እመ ትክል አውሥኦቶ፣ መመለስ ይቻልህ እንደሆነ ከመ ውእቱ፣ እሱ እንዲመልስልህ፤

አንድም ውርድ ቢጠይቅህ ጭብጥ ትመልስለት እንደሆነ እሱ እንዲመልስልህ፤ አንድም እመ ትክል አድምዖቶ እሱን ማግኘት ይቻልህ እንደሆነ ከመ ውእቱ እሱ እንዲያገኝህ ፤

፴፬፡ ወይእዜኒ እስመ አልቦ ዘየአምር ጊዜ መዓቱ ፣

አሁንም የሚፈርድበትን ጊዜ የሚያውቅ የለምና ፤

ወኢይትሔዘባ ለኃጢአቱ ዓባይ ፣

ደገኛ ኃጢአቱን አያስባትም፤

፴፭፡ ወኢዮብሰ በከንቱ ይከሥት አፉሁ ፣

ኢዮብ ግን በከንቱ አፉን ይገል ጣል ፤

ወበኢያእምሮ ያከብድ ነገሮ ፣

ባለማወቅ ነገሩን ያበዛል ፡፡

## ምዕራፍ ፴፭

ሠላሳ ስድስተኛው ምዕራፍ ይህ ነው ፤

፩፡ ወአውሥአ ኤልዩስ ወይቤ ፣

ኤልዩስ መለሰ፣ እንዲህ አለ፤

፪፡ ተዓገሥኒ ዓዲ ኅዳጠ ወእሜህረከ፣

ዳግመኛ ጥቂት ታገሠኝ አስተ ምርሃለሁ ፤

ዓዲ ብየ ነገር ፣

ዳግመኛ ነገር አለኝ ፤



፫፡ እትሜጠዋ ለነገርየ እምርኁቅ ፣

ነገሬን ከሩቅ ስቤ አመጣታለሁ ማለት እንደ አንተ ጠለፍ አድ ርጌ አልናገርም፤ አንድም ከእግ ዚአብሔር አግኝቼ እናገራለሁ፤ አንድም ከአንተ አግኝቼ እናገ ራለሁ፣ ከእግዚአብሔር ጋራ በተከራከርሁ ብሏልና ፤

ምግባርየሰ ጽድቀ ዕበል ፣

ኢይደልወኒ ያለበት ነው፤ ምግ ባሬ በጎ ነው እል ዘንድ አይገ ባኝም ፤

፬፡ እሙን ነገርየ ዘኢኮነ ሐሰተ ፣

ሐሰት ያይደለ ነገሬ የታመነ ነው፤ አንድም ምንም የታመነ ቢሆን ፤

ዓመፃኑ ይሰምዕ ፣

በሐሰት ፈረደብኝ ብሏልና እግዚ አብሔር በሐሰት ይፈርዳልን ፤

፭፡ አእምር ባሕቲ ከመ ኢይገድፎ እግዚአብሔር ለየዋህ ፣

ነገር ግን እግዚአብሔር ደጉን ሰው በመከራ እንዳይጥለው እወቅ ፤

ኃያል ወጽኑዕ ውእቱ ፣

ኃያል ጽኑዕ እሱ ነው ፤

፮፡ ወኢየሐይዎ ለልበ ኃጥዕ ፣

የኃጥእን ልቡና ደስ አያሰኘውም ወሐይወ ልቡ ሊያዕቆብ እንዲል፤

ወይሁብ ፍትሐ ለነዳያን ፣

ለነዳያን ይፈርድላቸዋል ፤

፯፡ ኢየአትት አዕይንቲሁ እምጻድቅ፣

ዓይኑ ረድኤቱን ከድኃው አያር ቅም፤ አንድም ጻድቅ ጌታ ረድ ኤቱን አያርቅም ፤

ወየሐትቶ ለጻድቅ ፣

ድኃውን ይመረምረዋል ፤

ወያነብሮ ውስተ መናብርት ምስለ ነገሥት ፣

ከነገሥታቱ ጋራ በዙፋን ያስቀ ምጠዋል፤ አንድም ከጻድቃን ጋራ ፤

ወያነብሮሙ በዕልገቶሙ መልዕልተ ወይከብሩ ፣

በሰለባቸው ምክንያት በላይ ያስ ቀምጣቸዋል፣ ይከብራሉ፤ አን ድም ፍተወታት እኩያት ኃጣው ዕን ድል በመንሣታቸው ከሁሉ በላይ ያኖራቸዋል፣ ይከብራሉ፤

፰፡ ወእለሂ ሙቁሐን እደዊሆሙ በሰናስል ይትአኃዙ በሀብለ ንዴት፣

እጃቸውን በንፍገት ሰንሰለት የታሠሩ ሰዎች በችጋር ገመድ ይያዛሉ ፤

፱፡ ወይነግሮሙ ምግባሮሙ ወጌጋዮሙሂ እስመ ብዙኅ ፣

ኃጢአታቸው ብዙ ነውና ፍዳ ይነ ይገናኛቸዋል ያስፈርድባቸ ዋል ፤

www.ethiopianorthodox.org

፳፮፡ ወያሠርዕ ዘበልየ ፤

የደረቀውን ያለመልማል ፡

ወይከድን ደመና ዲበ መዋቲ ፤

በሟች ሰው ላይ ደመናውን ይጋርዳል ፡

፳፯፡ ወይትከዓው ዝናም ዘአልቦ ኍልቍ ፤

ቍጥር ስፍር የሌለው ዝናም ይዘንማል ፡

፳፰፡ ወየአምር ራኀበ ደመናት በአምጣነ ጽላሎቱ ወናሁ ይሰፍሕ አእምሮ ላዕሌሁ ፤

አካለ ደመናት ሲል ነው፡ ለሰው ጥላ በመሆኑ መጠን ዕውቀት ያሳድርበታል ማለት ለሰው ጥላ እንዲሆን ያደርገዋል፡ አንድም እንደ ወንፊት የተበሳሳ ነው፡ ጥሩውን ከዚህ አዝንሞ በረዱን በሰልሞን ያፈስሰዋል ፡

ወይደፍኖ በማዕበለ ባሕር ፤

ማዕበሉን ይሸፍነዋል ፡

፳፱፡ እስመ በሙ ይኴንን አሕዛበ፤

ዝናም ለዘር ጠል ለመከር እየሰጠ ሕዝቡን አሕዛቡን ይገዛል፡

ወይሁብ ሲሳዮ ለጽኑዕ ፤

ለልባም ምግቡን ይሰጠዋል ፡ አንድም ለዕኑስ ይላል፤ ለችግረኛ ምግቡን ይሰጠዋል ፡

፴፡ ወለእንተ ትብዕስ ይከድና ብርሃን፤

ጨረቃን በምልዓት በብርሃን የሚሸፍናት እሱ ነው ፡

ወአዘዘ ላቲ ዘይጸደቃ ፤

ኅፀዕን የሚያመጣባት እሱ ነው፡ አንድም ወለእንተ ትብዕስ፤ ከአራዊት ሁሉ በምትከፋ በእባብ ዕውቀትን ያሳደረባት፤ በትረ ብእሲን ያዘዘባት እሱ ነው ፡ አንድም ወበእንተ ትንዕስ ይላል በታናሽ ደመና ፀሐይን የጋረዳት እሱ ነው፡ በደመና ፀሐይን አዘዘባት ፡

፴፩፡ ወይነግር በእንቲአሁ አርኩ እንተ ረከቦ በዓመፃሁ ፤

ወዳጁ፡ አንድም ወዶ የሠራው ኃጢአቱ በዓመፃው ምክንያት ፍዳ ያመጣበታል ።

## ምዕራፍ ፴፯

ሠላሳ ሰባተኛው ምዕራፍ ይህ ነው ፡

፩፡ ወበእንተዝ ደንገፀተኒ ልብየ ወወድቀት እመካና ፤

ስለዚህ ነገር ልቡናየ ደነገጠችብኝ ከአፎቷ ተለየች ማለት ከዕውቀቷ ተለየች ፡

፪፡ ስማዕ ድምፀ መቅሠፍተ መዐቱ ለእግዚአብሔር ፤

እግዚአብሔር ተቆጥቶ ያመጣው የመቅሠፍቱን የመብረቁን ድምፅ ስማ ፡



ወዘይወጽእ ነገረ እምአፉሁ ፤

ከአፉ የሚወጣ ነገርን ስማ ፡

፫፡ ይዌርዎ ታሕተ ኵሉ ሰማያት፤

እርሱን ወደሰማያት ሁሉ ይሰደዋል ፡

ወብርሃኑ ዲበ ክንፈ ምድር ፤

ጽንፈ ምድር ሲል ነው፡ ብርሃኑ በጽንፈ ምድር ይታያል ፡

፬፡ ወበድኅሬሁ ይወጽእ ቃል ፤

በኋላ ነጐድጓድ ይሰማል ፡

ወያንጐደጕድ በቃለ መዓቱ ፤

በትእዛዙ የመብረቅ፤ የነጐድጓድ ድምፅ ይሰማል ፡

ወይሜህሮሙ እንዘ ይሰምዕ ቃሎሙ፤

ቃላቸውን ሰምቶ ይቅር ይላቸዋል፡ አምላከ አናንያ ወአዛርያ ቃል ሥጋ ኮነ ሰአሊ ለነ ፤ ቅድስት ይሉም እንደሆነ ፡

፭፡ ወያንጐደጕድ በዐዓዕ መደንግፅ፤

የሚያስደነግጥ የብልጭልጭታ ድምፅ ይሰማል ፡

ወይሬሲ ለእንስሳ በበጊዜሁ ፤

እንስሳ ገዳም በየጊዜው እንዲፀንሱ ያደርጋል ፡

ወየአምሩ ጊዜ ይሰክቡ ፤

የሚፀንሱበትን ጊዜ ያውቃሉ፡

በዝ ኵሉ ኢይደንግፅ ልብከ ፤

በዚህ ሁሉ ልቡናህ አይደንግጥብህ ፡

ወኢተወለጠ ልብከ እመኒ ሥጋሁ በዝ ኵሉ ፤

በዚህ ሁሉ ልቡናህ ከግዘፉ አልተለወጠም ፡

ወገብረ ዓቢያተ ዘኢነአምር ፤

ይገብር ሲል ነው፡ እኛ የማናውቀው ጽኑዕ ጽኑዕ፤ ገናና ገናና ሥራ ይሠራል ፡

፮፡ ወይኤዝዝ በረደ ይረድ ዲበ ምድር ፤

በረድ ይረድ ዲበ ምድር ብለህ ግጠም፤ በዚህ ዓለም በረድ ይዘንም ዘንድ ያዝዘዋል፡ አንድም ይወርድ ዘንድ በረድን ያዝዘዋል ፡

ወዝናመ ክረምት በኃይሉ ፤

ዝናም በዝቶ ይዘንም ዘንድ ያዝዛል፡ አንድም በሱ ኃይል ይዘንም ዘንድ ፡

፯፡ ወየዓቅብ እደ ኵሉ ሰብእ ፤

የሰው ሁሉ እጅ ዘርን በዕንቅብ፤ ምድርን በቅብቅብ ይዞ ይጠብቃል ፡

www.ethiopianorthodox.org

ከመ ያእምር ኵሉ ዕጓለ እመሕያው ድካሞ ፤

ሰው ሁሉ ደካማ ባሕርዩን ያውቅ ዘንድ ።

፰፡ ወቦኡ አራዊት ውስተ ጠፈር ፤

ይበውኡ ሲል ነው አራዊት ወደ ዋሻ ይገባሉ፡ አንድም አጋንንት በጠፈር አሉ ።

ወአዕረፉ ውስተ ምስካቦሙ ፤

የአርፍ ሲል ነው፤ ከመኝታቸው ያርፋሉ ።

፱፡ እምረ·ነብ ይመጽእሙ ሕማም፤

ከረሀብ የተነሣ መከራ ያገኛቸዋል፤ ምግብ ሲሹ አዳኞች ያገኟቸዋል ።

ወእማኅደሪሆሙ ይቈርሩ ፤

በማደሪያቸው ይበረዳሉ ።

፲፡ ወእምነፋስ ኃያል ይመጽእ አስሐትያ ፤

ከዕኑዕ ነፋስ የተነሣ ውርጭ ይመጣል ።

ወይከፍሎ ለማይ ዘከመ ፈቀደ ፤

እንደ ወደደ ውሀውን ይሽፍነዋል፡ አንድም ነፋስ ከውቅያኖስ ከፍሎ ያመጣዋል ።

፲፩፡ ወይሜውር ኅሩያነ በደመና ፤

ዝናማትን ፤ አዝርዕትን ፤ ፀሐይን፤ ጨረቃን በደመና ይሸፍናል፡ አንድም ጻድቃንን በክብር ይሠውራል፡ አንድም ሄኖክ ኤልያስን በጸጋ በክብር ይሠውራል፡

ወይዘርዎ ለደመና በብርሃኑ ፤

ጌታ ደመናውን በፀሐይ ይበትነዋል፡ አንድም ፀሐይ በብርሃኑ ደመናውን ይበትነዋል ።

ወውእቱ ይመይጦ በዓውዱ ፤

እሱ ፀሐይን በምዕራብ ገብቶ በምሥራቅ እንዲመለስ ያደርገዋል፡ አንድም ወንጌላዊ በዓውዱ ይመለሳል፤ ወንጌላዊ ዓውዱን የሚያገኘው በ፷፫ ዘመን ነው ይላሉ ።

፲፪፡ ምክሩ በምግባሩ በኵሉ ዘአዘዘሙ፤

በአዘዛቸው ሥራ ሁሉ ምክሩ አንድ ነው ።

ከመዝ ሥርዓት ዘእምነቤሁ በዲበ ምድር ፤

ከሱ ተገኝቶ በዚህ ዓለም የሚሠራው ሥርዓት እንዲህ ነው ።

፲፫፡ እመሂ ዘውስተ ገዳም ፤

ጐሽ አጋዘንም ቢሆን፡ አንድም ነጋድያንም ቢሆኑ ፡ አንድም መናንያንም ቢሆኑ ።

ወዘሂ ውስተ ምድር ፤

በዚህ ዓለም ያሉ እንስሳትም ቢሆኑ፡ አንድም ሰብአ ዓለምም ቢሆኑ፡ አንድም ከሚስቶቻቸው ጋራ ቈርበው የሚኖሩም ቢሆኑ፡



ወለዘሂ በሠናይ ይረክቦ ፤

ከነዚህ በበጎ የሚገኙ አሉ፤ መሥዋዕት የሚሆኑ፡ አንድም መናንያን ሰማዕታት አሉ ።

፲፬፡ አፅምዕ ኢዮብ ዘንተ ፤

ኢዮብ ይህንን አድምጥ ።

ወቁም ወተገሠፅ በኃይለ እግዚአብሔር ፤

አምጻኤ ዓለማትነቱን ፈጣሪ መሆኑን በማወቅ ጽና ።

፲፭፡ ነአምር ከመ እግዚአብሔር ሠርዐ ምግባሮ ፤

እግዚአብሔር ሁሉን አከናውኖ እንደፈጠረ እናውቃለን ።

ወገብረ ብርሃነ እምጽልመት ፤

ብርሃንን ከጨለማ ለይቶ ፈጠረ፡

፲፮፡ ቦኑ ተአምር ፈሊጦቶ ለደመና፤

በውኑ ዝናሙን ከደመና ለይተህ ታውቃለህን፡ አንድም እኛ የምናውቀው ፤ አንተ የማታውቀው ይህ ነው ።

ግሩም ድቀቶሙ ለእኩያን ፤

የክፉ ሰዎች ጥፋታቸው ጽኑዕ ነው ።

፲፯፡ ወለከሰ ምውቅ አልባሲከ ፤

ልብስህ የሞቀ ነው ማለት አንተ ግን ገላ ምሉ ልብስ ለብሰሃል ።

ወአርምም እንከ በዲበ ምድር ፤

እንግዲህ ወዲህ በዚህ ዓለም ሳለህ ዝም በል፡ አንድም ከምድር አብነት ነሥተህ ዝም በል ።

፲፰፡ ወእምአዜብ ያጸንዕ ምስሌሁ ተጋድሎ ፤

ከፀሐይ ከቀትር መጋደልን ከአጸና ከእሱ አብነትን ነሥተህ፡ አንድም እምአዜብኑ ትጸንዕ ለተጋድሎ፤ ከሱ ጋራ በተከራከርሁ ያልህ፤ ከፀሐይ ከቀትር አንተ ትጸናለህን፡ አንድም ከአዜባዊ ነፋስ፤ ከአዜባዊ መሬት፤ ከአዜባዊ ፀሐይ ይልቅ አንተ ትበልጣለህን እሱንስ ስንኳ እለፍ ቢለው ያልፋል ይለዋል ኤልዩስ ኢዮብን ።

ግሩም ራዕዩ በዲበ ብዙኅ ፤

እምነ ብዙኃን ሲል ነው፡ ከብዙ ሰዎች መልኩ ልዩ ነው ።

፲፱፡ በእንተ ምንት ንግረኒ ፤

የሱን ነገር ማወቅ ይቻልህ እንደ ሆነ ስለ ምን ንገረኝ ።

ወምንተ ንብሎ ወናርምም እንከ ፤

ምን እንበለው የሱን ነገር መናገር አይቻልምና ዝም እንበል ።

ወአንተሂ ኢትንብብ ብዙኃ ፤

አንተም ብዙ ነገር አትናገር፡

www.ethiopianorthodox.org

፲፱፡ ቦኑ መጽሐፍ ወጸሐፊ ሎቱ ከመ አርምም እንዘ ይቀውም ብእሲ ኀቤየ፣

ኢዮብ ከእግዚአብሔር ጋራ በተ ከራከርሁ ሲል ዝም እል ዘንድ በውኑ ለኢዮብ ኤልዩስ ዝም ይበል የሚል ጸሐፊ ደብዳቤ አለውን፣ አለው እንደሆነ ያሳየ ኝና ዝም ልበል፤ አንድም ኢልዩስ በነገር ሲነሳብኝ ዝም እል ዘንድ በውኑ ለእግዚአብሔር ዕዳዬን የሚያውቅበት ጸሐፊ ደብዳቤ አለው እንጂ፣ አለህ ብሎ ያጣላ ዋል፤ አንድም ቦኑ ጸሐፊ ሊተ ኤልዩስ በነገር ሲነሳብኝ ዝም እል ዘንድ በደሌን የሚነግር ጸሐፊ ደብዳቤ አለኝን ፤

፳፡ አኮ ለኵሉ ዘይትዓወቆ ብርሃን፣

ዕውቀት ለሁሉ የሚሰጥ አይደ ለም ፤

ወብርሃን ውእቱ ውስተ ዘይበሊ ፣

ዕውቀት በዚህ ዓለም መልቶ ሳለ ለሁሉ የሚሰጥ አይደለም፤

ከመ ዘእምነቢሁ ዘውስተ ደመና መስዕ ብሩህ ፣

ከመ ደመና ብሩህ ዘውስተ መስዕ ሲል ነው፤ ከሱ ጋራ ያሉ ጻድቃን እንዲያውቁ በመስዕ አጠገብ ያለ ደመና ብሩህ ነው ማለት ያ ለመስዕ ቀረብሁ ብሎ እንዲያበራ ወደሱም የቀረቡ ጻድቃን ያውቃሉ፤ አንድም በመ ስዕ ያለ ደመና ብሩህ እንደሆነ ከሱ ጋራ ያሉ ጻድቃን ያውቃሉ እንጂ፣ ዕውቀት ለሁሉ የሚሰጥ አይደለም፤ አንድም ከመ ደመና መስዕ ብለህ ግጠም፣ በመስዕ አጠገብ ባለ ደመና ላይ እንዳለ ብርሃን ያለ ዕውቀት በዓለም መልቶ ሳለ ዕውቀት ለሁሉ የሚሰጥ አይደለም ፤

፳፩፡ ቦኑ ዘከመዝ ዓቢየ ስብሐት ወክብር በነበ ዘኵሎ ይመልክ ፣

ሁሉን በሚገዛ በጌታ ዘንድ በውኑ እንደ ጌታ ያለ ዓቢየ ስብሐት ዓቢየ ክብር አለ ?

፳፪፡ ወኢንረክብ ካልአ ዘከመ ኃይሉ ዘጽድቀ ይኴንን ፣

እንደ ከሃሊነቱ እውነት የሚፈ ርድ እንደ ጌታ ያለ ሌላ አናገ ኝም ፤

እስመ ኢይፈቅድ ለብእሲ ኃጥዕ ፣

ኃጥዕን ሰው ይሰማው ዘንድ አይ ወድምና ፤

፳፫፡ ወባሕቱ ይፈርሆ ዕጓለ እመ ሕያው ፣

ነገር ግን ሰው ሁሉ ይፈራዋል፤

ወይፈርሕዎ ጠቢባነ ልብሂ ፣

ሳፍር በልዳዶስም ይፈሩታል፡፡



# ምዕራፍ ፴፰

## ሠላሳ ስምንተኛው ምዕራፍ ይህ ነው ፤

፩፡ ወእምድኅረዝ ኀደገ ነጊረ ኤል ዩስ ፣

ከዚህ በኋላ ኤልዩስ መናገሩን ተወ ፤

፪፡ ወተሰአሎ እግዚአብሔር ለኢዮብ በደመና ወበዓውሎ ፣

እግዚአብሔር በደመና በነፋስ ሁኖ ኢዮብን ጠየቀው፣ ደመና ብሩህ ነው፤ ጌታም ብሩህ ነውና፤ አንድም ደመና ግሩም ነው፣ ጌታም ግሩም ነውና፤ አንድም ደመና ልዑል ነው ፣ ጌታም ልዑል ነውና፣ ነፋስ ረቂቅ ኃያል ግሩም ምሉዕ ነው፤ ጌታም ረቂቅ ኃያል ግሩም ምሉዕ ነውና ፣ ሦስት ጊዜ ተናግሮታል፣ በመ ጀመሪያ ከደዌው ተፈውሷል፣ በሁ ለተኛው ኃይሉ ጸንቷል፣ በሦ ስተኛው በዮርዳኖስ ተጠ መቅ አለው ተጠመቀ ፤ እንደ እከክ ያለው ረግፎለታል፣ ኢዮብ፣ ንዕማን ፣ ጌታ ፣ የተጠመቁበት ወደቡ አንድ ነው ፤ የሚጠይቅ እየመሰለ ብዙ ሥነ ፍጥረትን ነግሮታል ፤

፫፡ ወይቤ መኑ ዘየኃብእ እምኔየ ምክረ ፣

ምክርን ከኔ የሚሠውር ማነው? አለ ፤

ወመኑ ይከብት ነገረ ውስተ ልቡ፣

ነገሩን በልቡናው ከኔ የሚሠ ውር ማነው ?

እምኔየሁ ይሤውር ፣

ቢሠውር ቢሠውር ከእኔ የሚ ሠውር ይመስለዋል ? አንድም ከእኔ ይሠውር ዘንድ መኑ ዘየኃ ብእ፣ የሚሠውር ማነው ?

፬፡ ቅንት ሐቌከ ከመ ብእሲ ፣

በዓለ አእምሮ እንደመሆንህ በአ እምሮ ጽና፤ አንድም እንደ ሰው ሁኖ ወየው አግኝቼው ቀኝና ግራ ዘብጥና ተራራ ሁነን ተከራክ ረን ብለሃልና መጣሁ ታጠቅ ፤

ወአነ እሴአለከ ወአንተ አውሥአኒ፣

እኔ እጠይቅሃለሁ፣ አንተ መል ስልኝ ፤

፭፡ አይቴ ሀሎከ አመ ሣረርክዋ ለምድር ፣

ከእግዚአብሔር ጋራ በተከራከ ርሁ ያልህ ምድርን በፈጠርኋት ጊዜ ወዴት ነበርህ ?

ንግረኒ እስኩ እመ ጠቢብ አንተ ፣

ብልህ እንደሆንህ እስቲ ንገረኝ?

፮፡ መኑ ሠርዐ አምጣኒሃ እመ ተአ ምር ፣

ታውቅ እንደሆነ ምድርን መጥኖ የፈጠራት ማነው? እኔ ነኝ አንተ?

www.ethiopianorthodox.org

ቅሉ እሱ ካላገዘው አይሆንለትምና፤ አንድም ሰደኒ እስኩ የሚለው ነውና፤ አንድም የብርሃን ነፍስ አገሩ ወዴት ነው፤ ገነት ነው አይለውም ቢሉ ይህንኑ ቅሉ እሱ ካላገዘው አያውቀውምና ፤

ወአይቴኑ መካኑ ለጽልመት ፤

የጨለማ ቦታው ወዴት ነው፤ አዜብ አይለውም ቢሉ ይህ ቅሉ እሱ ካላገዘው አይሆንለትምና፤ አንድም ሰደኒ እስኩ የሚለው ነውና፤ አንድም የጽልመተ ነፍስ አገሩ ወዴት ነው፤ ምንነው ሲኦል ነው አይለውም ቢሉ ይህንኑ ቅሉ እሱ ካልነገረው አያውቀውምና ፤

፳: ሰደኒ እስኩ ውስተ ደወሎሙ ፤

እስቲ ወደ አውራጃቸው ውሰደኝ ፤

፳፩: ወእመ ተአምር ፍኖቶሙ አአምር እንከሰ እምአሚሃ ተወለድከ ፤

ይህንን ብትነግረኝ ያን ጊዜ እንደ ተወለድህ አውቃለሁ ፤

ወብዙኀ ኍልቈ ዓመታቲከ ፤

የዘመንህ ቍጥሩ ብዙ እንደሆነ አውቃለሁ ፤

፳፪: በጸሐክኑ ኀበ መዛግብ በረድ፤

በረድ ካለበት ቦታ ደረስህን እኔ በምልዐት እንድደርስ ፤

ወርኢከኑ ምስያመ አስሐትያ ፤

ውርጭ የሚረጋበትን ቦታ አየህን ፤

፳፫: ወይትዓቀቡኑ ለከ ለጊዜ ፀርከ በዕለተ ፀብእ ወቀትል ፤

ጦርና ፀብዕ በሚደረግበት ቀን ጠላትህን ድል ልትነሣበት ይጠብቅልሃልን ፤

፳፬: ወእምአይቴ ይወፅእ ሐመዳ፤

እስቲ ታውቅ እንደሆነ ዋግ የሚወጣበት ወዴት ነው ፤

፳፭: ወይትመየጥኑ አዜብ ዘታሕተ ሰማይ ፤

ዐሐይ፤ አንድም ነፋስ በአንተ ትእዛዝ በምዕራብ ገብቶ በምሥራቅ ይመለሳልን ፤

፳፮: መኑ ውእቱ ዘያጸንዖ ለኃያል ዝናም በውስተ በድው ከመ ይዝንም ብሔረ ኀበ አልቦ ሰብእ በድው ኀበ ኢይነብር ዕጓለ እመሕያው ፤

በውስተ በድውና በድው አንድ ወገን፤ ኀበ አልቦ ሰብእና ኀበ ኢይነብሮ ዕጓለ እመሕያው አንድ ወገን፤ ሰው በማይኖርበት በሌለበት በምድረ በዳ ይዘንም ዘንድ ብዙ በረድን ያጸና ማነው ፤

፳፯: ከመ ያጽግብ ኀበ አልቦ ዕፅ ወአልቦ ዘይነብሮ ፤

እንጨት በሌለበት ሰው በማይኖርበት ዝናሙን ያዘንም ዘንድ፤



ከመ ያብቍል ሣዕረ ውስተ ገዳም፤

እህሉን ፤ ተክሉን በምድረ በዳ ያበቅል ዘንድ ፤

፳፰: መኑ አቡሁ ለዝናም ፤

ዝናምን የፈጠረ ማነው ፤

ወመኑ ይወልዶ ለሕንባባተ ነጠብጣብ ፤

ነጠብጣቡን የፈጠረ ማነው ፍሬ ፍሬ መስሎ ይወርዳልና፤

፴: ወእምከርሠ መኑ ይወጽእ በረድ፤

በረድስ ከማን ባሕርይ ይገኛል፤ ከአንተ ባሕርይ ነው ከእኔ ፤

ወመኑ ይወልዶ ለሐመዳ በሰማይ፤

በሰማይ ዋግን የሚፈጥረው ማን ነው ፤

ወይወርድ ዲበ ምድር ፤

ወደምድር እንዲወርድ የሚያደርገው ማነው? እኔ ነኝ አንተ፤

፴፩: ወውስተ አእባን ይትኃባኡ ማያት ፤

ውሃዎች በደንጊያዎች ውስጥ ይሠወራሉ፤ አንድም ጠፈር ይሆናሉ፤ አንድም የሐውሩ ማያት ይላል፤ መና በመሆን በረድ በመሆን ይጸናሉ፤

ወከመ ማይ ይውኅዙ ፤

እንደ ውሃነታቸው ፤ አንድም እንደ ውሃነታቸው ይፈስሳሉ ፤ አንድም ጠፈር እንደ መሆናቸው ያልፋሉ ፤

ወመኑ አኀሠሮሙ ገጸሙ ለኃጥአን፤

ሰብአ ትካትን ያጐሰቈላቸው ማነው፤ አንድም ኃጥኣንን ያጐሰቈላቸው ማን ነው አንተ ነህ እኔ ፤

፴፪: ወተአምርሁ ማዕሠሮሙ ለብዙኃን ፤

የሰብአ ትካትን ሞታቸውን ታውቃለህን ፤

ወአቀምከኑ ሙሐዘ ማይ ፤

ፈሳሹን ውሃ ያቆምኸው አንተ ነህን እኔ ፤

ወታርኁ ክረምተ በበዓመት ፤

ክረምቱን በዓመት በዓመት ታመጣለህን እኔ እንዳመጣው፤

ወታመጽኦኑ ለኃጋይ ድኅረ በዕድሜሁ ፤

በፍጻሜሁ ሲል ነው፤ ክረምቱ ሲፈጸም በጋውን የምታመጣው አንተ ነህን፤ አንድም በዕድሜሁ ይላል በጊዜው ጊዜ ታመጣዋለህን ፤

፴፫: ተአምርሁ ግዕዘ ለሰማይ ፤

በሰማይ የሚሠራውን ሥራ ታውቃለህን ፤

ወእመ አኮ ዘይከውን በመትሕተ ሰማይ ፤

ይህም ባይሆን ከሰማይ በታች በዚህ ዓለም የሚሆነውን ታውቃለህን ፤

www.ethiopianorthodox.org

፴፩፡ ትክልኑ ተአኅዛ ለትርያ ከመ ኢትሑር ፤

ዓቢይ ኮከብ ፤ አንድም ፈጣን ኮከብ አስታርቦሽሽ ኮከብ እንዳ ትሔድ ትይዛት ዘንድ ትችላ ለህን ፤

ወርኢከኑ ፍኖቶ ለደብራን ወሙጻአ፤

ንዑሳ ኮከብ ፤ አንድም ዳተኛ ኮከብ፤ አንድም እነሦስቶ የሚሄ ዱበትን ጐዳና አየህን ፤

፴፪፡ ተአምርኑ ጊዜሃ ለብላተነዓሽ ወሕዋዒሃ ፤

ጨረቃ ጠፍ የምታደርግበትን፤ ሠርቅ የምታደርግበትን ታውቃ ለህን እኔ እንዳውቀው ፤

፴፫፡ ትጼውዖኑ ለደመና በቃልከ ወያ ወሥእከኑ ማየ ብዙኀ እንዘ ይርዕድ፤

ደመናን ጠርተህ ታመጣዋለህ? ውሃውስ እየራደ ይመልስልሃ ልን ፤

፴፬፡ ወትፌኑ በዓዐ ወየሐውር ፤

ብልጭልጭታውን ልከህ የምት ስደው አንተ ነህ ፤

ወይብሉከ ምንት ውእቱ ፤

መጥቶ ምን ላድርግ ይልሃልን፤

፴፭፡ ወመኑ ወሀቦን ለአንስት ጥበበ ከመ ይእንማ ወዘዘኒአሁ ትምህርተ፤

በየአበላሉ ወርቁን ከሐር፤ ሐሩን ከወርቅ አስማምተው ይፈትሉ ዘንድ ለሴቶች ጥበብን ያስተማ ራቸው ማነው፤

፴፮፡ ወመኑ ኈለቆ ለደመና በጥበቡ፤

ደመናውን በባሕርይ ጥበቡ የቈ ጠረው ማነው ፤

ወአጽነና ለሰማይ ዲበ ምድር ፤

ሰማይን በደመና ላይ ያዘነበለው ማነው ፤

፴፯፡ ወተክዕወ ላዕለ ምድር ፤

በአድማስ ላይ በዚህ ዓለም የዘ ረጋው ማን ነው ፤

ወአስተጣበቅዋ ከመ ዕብነ ኩኰሕ፤

እንደ ዋሻ ደንጊያ አያያዟት ጠፈርና አድማስ እንደ ባጥና እንደ ግርግዳ፤ እንደ መሶብና እንደ መሶብ እፊያ ተያይዘዋል፡

፴፰፡ ወነዐውከኑ አናብስተ መስዕ ፤

በመስዕ ያሉ አናብስትን አዳን ሃቸውን እኔ እንዳደናቸው ፤

ወታጸምምኑ ነፍሰ አክይስት ፤

የእባብን ቀነስል የምታድን አንተ ነህ? እባብ ቁስል ይጸናበታል፤ ትንሽ የቆሰለ እንደሆነ እየሰፋ ይሄዳል፤ አንድም ወታጸግብኑ ነፍሰ አክይስት፤ እባብን የምታ ጠግብ አንተ ነህ እባብ ከእንግቱ እስከ ጅራቱ ሆድ ብቻ ነውና ፤

፴፱፡ ወቦኡ ውስተ ግበቢሆሙ ፤

ይበውዑ ሲል ነው፤ ወደጕድጓ ዳቸው ይገባሉ ፤



ወይነብሩ ውስተ ያም ወያስተሐይዑ፤

በዛፉ ውስጥ ሁነው ሰውን ይመ ለከታሉ፤ አንድም የቆላ እባብ ከዛፍ ተቀምጦ ሰው ሲመጣ ያየው እንደሆነ ተወርውሮ ይነድ ፈዋል፤

፵፡ መኑ ዘያስተዴሉ ሲሳየ ቋዓት፤

የቁራዎችን ምግብ የሚያዘጋጅ ማነው ፤

ወየዐወይዉ ኀበ እግዚአብሔር ዕጐሊሆሙ ወየኃሥሡ ዘይበልዑ ፤

ልጆቻቸው የሚበሉት ሲሹ ወደ እግዚአብሔር ይለምናሉ፤ እሱ ባወቀ ይለምኑታልና፤ አንድም ባሕርያቸው የሚያሻው ስለሆነ፤ ሐተታ ቁራ በተወለደ ጊዜ አካሉ ፍሕም ይመስላል፤ እናት አባቱ ፈርተው ትተውት ይሄዳሉ፤ ከአ ካሉ ወዝ አይታጣም፤ ተሐዋስ ያን ያንን ሲሉ ይመጣሉ፤ እነዚ ያን እየተመገበ ያድጋል አርባ ቀን ሲሆነው ጠጉር ያበቅላል እናት አባቱ ይመለሱለታል ፡፡

## ምዕራፍ ፴፱

ሠላሳ ዘጠነኛው ምዕራፍ ይህ ነው ፤

### ኀባኤ

፩፡ ተአምርሁ ጊዜ ይትወለድ ኃየል፤

ዋሊያ የሚወለድበትን ጊዜውን ታውቀዋለህን እኔ እንዳውቀው፤

ወዓቀብከኑ በውስተ ማኅምም ፤

በምጥ ጊዜ ጠበቅኸውን እኔ እንድጠብቀው ፤

፪፡ ውኈለቁኑ አውራኂሁ ማዕዜ ይትወለድ ፤

ወሩን ቈጠርኸው ? መች ይወለ ዳል የሚወለድበት ጊዜው መቼም መች እንደሆነ ቈጠርኸው ?፤

ፈታሕኮኑ እምሕማም ፤

ከምጥ ለየኸውን ፤

፫፡ ወሴሰይኮሙ ለደቂቁ ዘእንበለ ፍርሃት ፤

አጣለሁ ባለማለት ልጆቹን መገ ብሃቸውን ፤

ወተአትትኑ ሕማሞሙ ፤

መከራቸውን ታርቅላቸዋለህን፤

፬፡ ወያመሥጡ ዕጐሊሆሙ ወይትባ ዘኁ ወይትዋለዱ ፤

ልጆቻቸው ይሄዳሉ፤ በሄዱበት ይዋለዳሉ፤ ይበዛሉ ፤

ይወጽኡ ወኢይገብዑ ኀቤሆሙ ፤

ይወጣሉ ወደ እናት ወደ አባታ ቸው አይመለሱም፤ ሐተታ ይህ ዋሊያ ምጥ ይፀናበታል፤ እኪ ሌታ አካሉ ወጥቶ ሣር እየበላ መንፈቅ ይቀመጣል፤ የመብረቅ የነጐድጓድ ድምፅ በሰማ ጊዜ ፈትለክ ብሎ ወጥቶ ይሄዳል ከዚያ በኋላ አይመለስም ፤

www.ethiopianorthodox.org

፭፡ ወመኑ ዘአግዓዞ ለሐለስትዮ ፤

የምድረ በዳ አህያን ከአገዛዝ ነፃ የአወጣው ማነው ? አንተ ነህ እኔ ፡

ወመኑ ፈትሐ ማዕሠሮ ፤

ማሠሪያውን የፈታው ማነው? አንተ ነህ እኔ ፡

፮፡ ወረሰይኩ ሎቱ ገዳመ ንብረቶ፤

መኖሪያውን በምድረ በዳ አደረግሁለት ፡

ወማኅደሮሂ ውስተ ዔው ፤

ማደሪያውን በበረኃ አደረግሁ፡

፯፡ ወይስሕቆሙ ለብዙኃን አሕዛብ፤

በብዙ ሰዎች ይዘብትባቸዋል፡

ወኢይሰምዕ ድምፀ ዘያገርሞ ፤

የሚያስፈራውን ሰው ድምፅ አይሰማም ፡

፰፡ ወየዓይል ውስተ ገዳም ይትረዓይ ፤

በምድረ በዳ ይሰማራ ዘንድ ይዞራል ፡

ወኀበ ሐመልማል ይዴግን ፤

ልምላሜ ወደአለበት ይሄዳል፡

፱፡ ወይፈቅድኑ ይትቀነይ ለከ አርዌ ሐሪስ ፤

አውራሪስ ይገዛልህ ዘንድ ይወዳልን ፡

ወይቢት ውስተ ቤትከ ፤

በቤትህስ ያድር ዘንድ ይወዳልን ፡

፲፡ ወተአሥሮኑ በመዕመድ ወትወዲ አርዑተ ውስተ ክሣዱ ወየሐርስ ለከ ትልመ ገራውሂከ ፤

ቀንበሩን በላመ ገመድ በአንገቱ አስረህ እርሻህን ያርስልሃልን ፡

፲፩፡ ወትሰተፋ ላዕሌሁ እስመ ብዙኅ ኃይሉ ፤

ትትአመን ሲል ነው፡ ኃይሉ ብዙ ነውና ብለህ በእሱ ትታመናለህን ፡

ወተኀድግኑ ላዕሌሁ ተግባረከ ፤

ሥራህን በእሱ ላይ ትጥላለህን፡

፲፪፡ ወትትአመኖ ከመ ያእቱ ለከ ተግባረ ማዕረርከ ፤

መከሩን ይሰበስብልህ ዘንድ ታምነዋለህን ፡

ወያመጽእ ለከ እክለከ ፤

እኅሉን ያመጣልሃልን ፡

፲፫፡ ሰገኖ ዘታዘልፍ ወትነብር ውስተ ምድር እምከመ ኢፀንሰት ኢትፈቅድ ትብላዕ ፤

በበረኃ የምትኖር ሰጎን እንዲህ ናት ካልፀነሰች ትበላ ዘንድ አትወድም፤ ዝሙት ይፀናባታልና፡ አንድም እምከመ ፀንሰት ትፈቅድ ትብላዕ ከፀነሰች በኋላ ትበላ ዘንድ ትወዳለች ፡



ወታፀምዕ ውስተ ምድር ዕዘኒሃ ፤

የአዳኝ ድምፅ፡ አንድም የአውራውን ድምፅ ለመስማት ጆሮዋን ከምድር አድርጋ ታደምጣለች ፡

፲፬፡ ወተሐፅን ውስተ ምድር እጐሊሃ ፤

ልጆቿን በምድር ታሳድጋለች፡

ወተኀድግ ኀበ ወለደት ፤

ከወለደችበት ትተዋለች ፡

ወትከይድ አራዊተ ምድር ፤

በአራዊት ትሰለጥናለች ፡

፲፮፡ ወታልሕቅ ደቂቃ ወተኃድግ፤

ልጆቿን አሳድጋ ትተዋለች ፡

ወተሐምም ወለከንቱ ትፃሙ ፤

ታምጣለች በከንቱ ትደክማለች ፵ ቀን ዓይኗን ተኩራ እንቁላሏን ትመለከታለች፤ ዙራ ያየች እንደሆነ ደንጊያ ይሆንባታል፡

ወአልባቲ ፍርሃት ፤

ፍርሃት የለባትም ፡

፲፯፡ እስመ ወህባ እግዚአብሔር ጥበበ ወከፈላ ምክረ ፤

እግዚአብሔር ጥበብን ገልጦላታልና፤ ምክርንም ከፍሏታልና፤ አድሏታልና ፡

፲፰፡ በበዓመቱ ታነውኅ ደቂቃ ወታልሕቅ ፤

በዓመት በዓመት ልጆቿን ታሳድጋለች ፡

ወትስሕቅ ዲበ ፈረስ ወበዘይጼዐኖ፤

በፈረሱም በተቀመጠው ሰውም ላይ ትዘብታለች ፡

፲፱፡ አንተኑ ወሀብኮ ኃይለ ለፈረስ፤

ለፈረስ ኃይል የሰጠኸው አንተ ነህ እኔ ፡

ወአልበስኮ ግርማ ዲበ ክሣዱ ፤

በእምቢያው ግርማ ያሳደርህበት አንተ ነህ ?

፳፡ ወአስተረሰይኮ ለቀትል በንዋየ ሐቅል በግርማ እንግድዓሁ ፤

ግርማ ባለበት በደረቱ ለሰልፍ በጥሩር ያስጌጥኸው አንተ ነህ?

፳፩፡ እንዘ ይረውጽ ወየአምቅ ምድረ በእግሩ ፤

ሲሮጥ ምድሩን በእግሩ ያጎረጉደዋል ፡

ወይወጽእ ገዳመ በኃይሉ ፤

በኃይሉ ወደ ምድረ በዳ ይሄዳል ፡

፳፪፡ ወይስሕቆ ለሐፅ ዘይትቤቀሎ፤

የሚበቀለው ፍላጻውን ይዘብትበታል፡ አንድም ዘይትቄበሎ ይላል፤ የሚቀበለውን ፍላፃ ይዘብትበታል፤ አያገኘኝም ይላል፡

ወኢይትመየጥ እምሐፅ ፤

ከጦሩ የተነሣ አይመለስም ፡

www.ethiopianorthodox.org

፳፫፡ ወበሳዕሌሁ ያጸንዕ ቀስተ ወመጥባሕተ ፤

ፍላፃ ጦር በእሱ ይጸናል ማለት ያጌጠውን በለው ይላልና፡ አንድም ፈረሰኛ እየከበበ ለእግረኛ ይሰጣልና፡ አንድም ከእግረኛ ፈረሰኛ ሊወጋ ያጠብቃልና ፡

፳፬፡ ወበመዓቱ ያማስን ምድረ ፤

በኃይሉ ምድሩን ያጐደጕደዋል፡

ወኢይትአመን እስከ አመ ይትነፋሕ ቀርን ፤

ውጋ ውጋ የሚል ነጋሪት እስቲ ሰማ ድረስ ጦርነት ይሆናል ብሎ አያምንም ፡

፳፭፡ ወእምከመ ተነፍሐ ቀርን ይብል ዕንቋዕ ዕንቋዕ ፤

ነጋሪት በተመታ ጊዜ እሰ እሰ (እሰይ እሰይ) ይላል ማለት (ያዙኝ ልቀቁኝ) ይላል እንደ ወሎ ፈረስ ፡

ወእምርኁቅ ያጼንዎ ለቀትል ፤

ሰልፉን ከሩቅ ያሸተዋል፣ የወሎ ፈረስ ሰልፍ ባየ ጊዜ ያሽካካል ይላሉ ፡

፳፮፡ ወበጥበብከኑ ይቀውም ሆባይ ሰፊሆ ክነፊሁ ፤

አንጭት አሞራ ክንፉን ዘርግቶ የሚቆም በአንተ ጥበብ ነውን ፡

ወኢይትሐወስ ተሞይጦ መንገለ ደም፣

ወደቃውን ሲያይ ተመልሶ ደም ወደአለበት ለመሄድ አይንቀሳቀስም ፡

፳፯፡ ወበትእዛዝከኑ ይትሌዓል ንስር ሰማየ ፤

ንስር ወደ አየር ከፍ ከፍ የሚል በአንተ ትእዛዝ ነውን፡

፳፰፡ ወአውስትኒ ሐቂፎ ዕጕሊሁ ይበይት ውስተ ኵኵሕ ወህየ የኃብዕ፣

ጥምብ አሞራ ገላግልቱን ይዞ በዋሻ ያድራል፣ ከዚያ ይሠውራቸዋል ፡

፳፱፡ ወአንቢሮ የኃሥሥ ዘያበልያሙ፣

ልጆቹን ከዚያ አኑሮ የሚያበላቸውን ይፈልጋል ፡

እምርኁቅ ያስተሐይፃ አዕይንቲሁ፣

ዓይኖቹ ከሩቅ ይመለከታሉ፡

፴፡ ወዕጕሊሁ ይረውዩ ነበ ደም፣

ልጆቹ ወደ ወደቃው ይሄዳሉ፡ አንድም እገሪሁ ይላል፣ እግሮቹ ወደቃ ካለበት አያርፉም፣ በፊት ርቆ ያርፉል፣ ኋላ እያከበኰበ ወደወደቃው ይሄዳል ፡

ውነበ በድን ይበጽሑ ሶቤሃ ፤

ያን ጊዜ ገላግልቱ ወደቃ ካለበት ይደርሳሉ ፡

፴፩፡ ወአውሥአ እግዚአብሔር ለኢዮብ ወይቤሎ ፤

እግዚአብሔር ለኢዮብ መለሰለት፣ እንዲህ አለው ፡



፴፪፡ ምስለ ቢጽከኑ ትትዋቀስ አንተ ከመ ትትዋሣዕ እንዘ እግዚአብሔር ይዘልፈከ ፤

እግዚአብሔር በደዌ ሲዘልፍህ አንተ ትመልስለት ዘንድ ከባልንጀራህ ጋራ የምትከራከር ይመስልሃል ?

፴፫፡ ወተሰጥዎ ኢዮብ ወይቤሎ ለእግዚአብሔር ፤

ኢዮብ መለሰ፣ እግዚአብሔርን እንዲህ አለው ፡

፴፬፡ ምንት ብየ ዘአወሥእ እንዘ ትጌሥፀኒ ፤

ስታስተምረኝ የምመልሰው ምን አለኝ ? ምን እመልሳለሁ ?

ወምንትኑ አነ ከመ እትዋሣዕ ምስለ እግዚአብሔር እንዘ ዘንተ እሰምዕ ፤

ይህን ሰምቼ ከእግዚአብሔር ጋራ እከራከር ዘንድ እኔ ምንድ ነኝ ?

ወምንትኑ ዘአወሥእ አነ ዘእንበለ ዘእወዲ እዴየ ዲበ አፉየ ፤

እጄን በአፌ ላይ ጭኜ ዝም እላለሁ እንጂ እኔ የምመልሰው ምንድነው ?

፴፭፡ ምዕረ ነበብኩ ወኢይደግም እንከ ፤

አንድ ጊዜ ከእግዚአብሔር ጋራ በተከራከርኩ ብዬ ተናገርሁ ፤ እንግዲህ ወዲህ ዳግመኛ አልናገርም አልደግምም ።

# ምዕራፍ ፵

አርባኛው ምዕራፍ ይህ ነው፡

፩፡ ወዓዲ ተሰጥዎ እግዚአብሔር ለኢዮብ እምደመና ወይቤሎ ፤

ዳግመኛ እግዚአብሔር ለኢዮብ በደመና መለሰለት እንዲህ አለው ፡

፪፡ ዳዕሙ ቅንት ሐቌከ ከመ ብእሲ፣

ነገር ግን ባለ አእምሮ እንደ መሆንህ ወገብ ልቡናህን አጽና፡

ወአነ እሴአለከ ወአንተ አውሥአኒ፣

እኔ እጠይቅሃለሁ አንተ መልስልኝ ፡

፫፡ ወእመ አኮ ኀድግ ፍትሕየ ፤

ይህም ባይሆን ያለኃጢአቴ አመጣብኝ ማለትን ተው፡ አንድም ዳኛ አግኝቼ ተከራክሬ ማለትን ተው ፡

ይመስለከኑ ካልዕ ዘይኴንነከ ፤

ሌላ የሚፈርድብኝ ይመስልሃልን ፡

ዳዕሙ ከመ ያስተርኢ ጽድቅከ ፤

እኔ ነኝ እንጂ፡ አንድም በሌላው ኃጢአትህ የሚፈርድብኝ ይመስልሃልን፣ ጽድቅህ እንድትገለጥ ነው እንጂ፡ አንድም ሌላ የሚፈርድብኝ ይመስልሃልን፣ ጽድቅህ ናት እንጂ ፡

www.ethiopianorthodox.org

፱፤ መዝራዕትከኑ ከመ እግዚአብሔር፣

ከእግዚአብሔር ጋራ በተከራከ ርሁ ያልህ ሥልጣንህ እንደ እግዚአብሔር ነውን ፤

ወቃልከኑ ከመ ነጐድጓድ ፣

ቃልህስ እንደ ነጐድጓድ ያስፈ ራል ፤

፲፤ ልበስ እስኩ ኃይለ ዘእምዓርያም፣

ከእግዚአብሔር ጋራ በተከራከ ርሁ ያልህ ከሰማይ የተገኘ ኃይ ልን እስቲ ገንዘብ አድርግ ፤

ወተረሠይ በክብር ወበስብሐት ፣

ይቻልህ እንደሆነ በፍጹም ክብር ተጠረር ፤

፲፩፤ ወፈኑ መላእክተ መዓት ፣

ለመዓት የታዘዙ መላእክትን ስደድ ፤

ወአኅሥር ለጸላዒ ፣

ጠላትህን አጐስቍለው ፤

፲፪፤ ወአጥፍዖሙ ለዕቡያን ፣

ትዕቢተኞችን አጥፋቸው ፤

ወበጊዜሃ ድፍኖሙ ለረሲዓን ፣

ሕገ እግዚአብሔርን የዘነጉ ሰዎ ችን በጊዜዋ ጊዜ አጥፋቸው ፤

ወአብልዮሙ ኅቡረ ውስተ ምድር በአፍአ ፣

እኒ ዳታን አቤሮንን ከከተማ በአፍአ እንደ አጠፋኋቸው ከዚህ ዓለም አፍአ በሚሆን በመቃ ብር አጥፋቸው ፤

፲፫፤ ወኅብዮሙ ውስተ ምድር ኅቡረ በአፍአ ፣

ከዚህ ዓለም አፍአ በሚሆን በመቃብር አንድ አድርገህ ሠው ራቸው ፤

፲፬፤ ወአነሂ አአምነከ ከመ ትክል አድ ኅኖ ፣

ይኸነን ብታደርግ እኔም ማዳን እንዲቻልህ አውቃለሁ ፤

፲፭፤ ወናሁ አራዊት በኀቤከ ከመ እንስሳ ሣዕረ ይትረዓዩ ፣

እነሆ አራዊት በአንተ ዘንድ አሉ ? እንደ እንስሳ ወደ ሣር ይሰማራሉን ማለት ለኔ እንዲገ ዙልኝ ለአንተ ይገዙልሃልን፤ አን ድም አጋንንት ከአንተ ዘንድ አሉ? እንደ ኪሩቤል ወደቅዳሴ ይሰማራሉን ፤

፲፮፤ ወናሁ ኃይሉ ውስተ ሐቌሁ ፣

የዘንዶ የብሂሞት ኃይሉ በወገቡ ነው፤ አንድም የዲያብሎስ ጽናቱ በሠራዊቱ ነው ፤

ወፅኑዕ ውስተ ኅንብርተ ከርሡ ፣

የዘንዶ የብሂሞት ኃይሉ ጽናቱ በእንብርቱ ነው፤ አንድም የዲያ ብሎስ ጽናቱ በሠራዊቱ ነው ፤



፲፯፤ ወዓቀመ ዘነቦ ከመ ዕፀ ቄጽ ርስስ ፣

ጅራቱን እንደ ሶኖባ እንጨት አፀና ፤ አንድም ዘባኖ ይላል፣ ዲያብሎስ ሠራዊቱን አጸና ፤

ወሥረዊሁኒ ዕፉር ፣

የዘንዶ የብሔሞት ጅማቱ ንብ ብር ነው፤ አንድም የዲያብሎስ ሠራዊቱ ለማሳት ንብብር ናቸው፤

፲፰፤ ወአዕመ ገበዋቲሁኒ ዘብርት ፣

የጐኑ አጥንትም የብርት ነው ማለት ጽኑዕ ነው፤ አንድም የዲያ ብሎስ ሠራዊት ጽኑዓን ናቸው፤

ወዓዕመ ዘባኑሂ ዘሐፂን ስብኮ ፣

የጀርባው አጥንት ተመትቶ የተ ሠራ ብርት ነው ማለት ጽኑዕ ነው፤ አንድም የዲያብሎስ ሠራ ዊቱ ጽኑዓን ናቸው ፤

፲፱፤ ዘውእቱ ቀዳሚ ተግባሩ ለእግዚ አብሔር ፣

ቀዳማይ ሲል ነው፤ የእግዚአብ ሔር ደገኛ ፍጥረቱ ብሔሞት ነው፤ አንድም የእግዚአብሔር መጀመሪያ ፍጥረቱ ዲያብሎስ ነው ፤

ወተገቢሮሂ ሰሐቅዎ መላእክቲሁ ፣

ዘንዶ ብሔሞት በተፈጠረ ጊዜ መላእክት ይህን ደገኛ ፍጥረት የፈጠርህ ብለው አመሰገኑ ፤ አንድም መላእክት ዲያብሎስ ቀድሱኝ ቢል ዘበቱበት ፤

፳፤ ወዐረ ውስተ ደብር ነዋህ ፣

ብሔሞት ዘንዶ ተራራ ይወዳ ልና ብሔሞትም ወደ ረዢም ተራራ ሄደ ውነበ ሀለዉ. ፱ አድባር ህየ ሀሎ እንዲል፤ አን ድም ዲያብሎስ ልዑል አምላክ ነኝ አለ፤ አንድም ተራራውን የፈጠርኩ እኔ ነኝ አለ ፤

ወገብረ ብሔረ ለእንስሳሁ ውስተ ቈላ ፣

ቅዝቃዜ ባለበት በውቅያኖስ ለወ ገኖቹ አገር አቀና፤ አንድም ዲያ ብሎስ በአለበት በገሃነም ለወገ ኖቹ ለአጋንንት አገር አቀና፤

፳፩፤ ወይሰክብ ታሕተ ኵሉ ዕፅ ውስተ ሕለት ወሰማዝ ወብርዕ ፣

ከእንጨቱ ሁሉ በታች በፈላው በቄጠማው፣ በመቃው ውስጥ ይተኛል ፤

፳፪፤ ወይጼልሉ ዖመ ዳዕሮ ወአብ ትረ ልብኔ ፣

ዋርካ ልምጭ ልባንጃ ይጋርዳ ዋል፤ አንድም እኒህ ሁሉ ክፍት ክፍት ናቸው ፤ ዲያብሎስ አእ ምሮ መንፈሳዊ ባላደረበት ሰው ነት ያድራል፤

፳፫፤ ወለእመ መጽአ ማይ ብዙኅ ኢያነክር ፣

ብሔሞት ዘንዶ ብዙ ውሀ ቢመጣ ያስጥመኛል ብሎ አያደንቅም፤ አንድም ዲያብሎስ ብዙ ጥሙ

www.ethiopianorthodox.org

ቃን ቢመጣ ድል ይነሱኛል አይልም ፡

ይትአመን ከመ ይትሜጠዎ ለዮርዳኖስ በአፉሁ ፤

ዮርዳኖስን በአፉ እንዲቀበለው ይታመናል፤ አንድም ጥሙቃንን ድል እነሣቸዋለሁ ብሎ ይታመናል፤

፲፱፡ ወይትዌከፎ በዓይኑ ፤

ብሔሞት ዘንዶ ዮርዳኖስን በዓይኑ ይገድበዋል፤ አንድም ዲያብሎስ በሥልጣኑ ጥሙቃንን ድል ይነሣቸዋል ፤

ወይትመየጥ ወየዓቅብ አንፎ ፤

ተመልሶ አፍንጫውን ይጠብቃል፤ አንድም ዲያብሎስ ወደ አእምሮ ይመለሳል፤ ባሕርዩን ይጠብቃል ፤ ያዕቆብ ያዕቆብ አውአየተኒ ጸሎትከ እንዲል ፤

፳፡ ወታመጽኦኑ ለከይሲ በመሥገርት ፤

ዘንዶውን ራሱን በትርክዛ ወግተህ ታመጣዋለህ፤ አንድም ዲያብሎስን በመስቀል ድል ትነሣዋለህን ፤

ወትወዲ ሎቱ ዝማማተ ውስተ አንፉ፤

ትናጋውን በስተህ መሳቢያ ታበጅለታለህን ፤ አንድም በመስቀል ድል ትነሣዋለህን ፤

፳፩፡ ወተአሥርኑ ሎቱ ኀልቀተ ውስተ ሕልበቱ ፤

በጉንጩ ቀለበት ታስርበታለህን ፤

ወትሰቀሩሮ አንፎ በሕሮት ፤

አፍንጫውን በመሮ ትመታዋለህን ፤

፳፪፡ ወያወሥአከኑ እንዘ ይትጋነይ ለከ ወይየውሃከ ፤

ለአንተ ተገዝቶ ይመልስልሃልን ወይስ ያለዝብሃል እንደዚህ ሁሉ ዲያብሎስን በመስቀል ድል ትነሣዋለህ ፤

፳፫፡ ወይትካየድኑ ኪዳነ ምስሌከ ፤

ከአንተ ጋራ መሐላን ይማማላልን፤ የተመማለ ጽኑዕ እንደሆነ በአንተ ትእዛዝ ጸንቶ ይኖራልን፤ አንድም ዲያብሎስ ከአንተ ጋራ ይማማላልን፤ ብየ ማዕኩት ምስለ ዘፈጠረኒ እንዲል ፤

ወትነሥኦ ምስሌከ ይኩንከ ገብረ ዘለዓለም ፤

ከአንተ ጋራ ለዘለዓለም ተገዢ ሊሆን ትወስደዋለህን፤

፳፬፡ ወተአሥሮኑ ከመ ዖፈ ደቂቅ፤

ልጅ ዖፍን እንዲያሥር ታሥረዋለህን ፤

ወትትዋነዮኑ ከመ ዖፍ ፤

ልጅ በዖፍ እንዲጫወት ትጫወትበታለህ ፤



አሕዛብ ይከውኑ ሎቱ ፤

ይትኴነኑ ሲል ነው፤ አሕዛብ ለብሔሞት ይገዙለታል ፤ አንድም ለዲያብሎስ ይገዙለታል፤

፳፭፡ ወይትዌከፍዎ ሕዝበ ፊንቆን፤

ሕዝበ አረሚ ሲል ነው፤ የአረሚ ወገኖች ያምኑታል ፤

፳፮፡ ወእመ ኵሉ አዕዋፍ ተጋብኡ ኢያመጽኡ አሐተ እማዕሰ ዘባኑ ፤

አዕዋፍ ሁሉ ቢሰበሰቡ ከጀርባው ጠጉር አንዲት አያመጡም፤ አንድም ምዕመናን ሁሉ ቢሰበሰቡ ድል አይነሡትም ፤

ወኢመሠግራን በአሕማር ርእሶ ፤

ዓሣ ወጋሪዎች አጥማጆች በመርከብ ሁነው ራሱን በትርክዛ አይወጉትም፤ አንድም ምዕመናን በመስቀል ድል አይነሡትም፤

፳፯፡ ወትወዲ ሎቱ እዴከ ለገሚሃ ፤

እሱን ለመዳሰስ እጅህን ትዘረጋለህን፤ አንድም እጅህን ዘርግተህ ድል ትነሣዋለህ፤ እኔ ልጄን ሰድጄ ድል እንደነሣሁት ፤

ተዘከር ዘፀብዓከ በሥጋከ ከመ ኢትድግም እንከ ፤

ይህነንስ ትተህ በሥጋ የመጣብህን መከራ አስብ፤ ዳግመኛ እንዳትበድል ፤

፳፰፡ ርኢከሂ ወኢያንከርከ ፤

የኔን ነገር አይተህ አላደነቅህም፤

ወኢፈራህከ ነገሮ እስመ ሊተ አስተዳለውከ ፤

ያለ ኃጢአቴ አመጣብኝ ብለሃልና ነገሩን አላደነቅህም ።

## ምዕራፍ ፵፩

አርባ አንደኛው ምዕራፍ ይህ ነው ፤

### ጉባኤ

፩፡ ወመኑ ውእቱ ዘይትቃወመኒ ፤

የሚቃወመኝ ማን ነው ?

፪፡ ወመኑ ዘይትዋሥአኒ ወየሐዩ፤

የሚከራከረኝ በሕይወት የሚኖር ማን ነው ?፤

ኵሉ ዘታሕተ ሰማይ ዚአየ ውእቱ፤

ከሰማይ በታች ያለው ሁሉ የኔ ገንዘብ ነው ፤

፫፡ ወኢያረምም በእንቲአሁ ፤

ስለሱ ዝም አልልም ፤

ወቃለ ኃይል ይሣሀሎ ለዘከማሁ ፤

እንደ ብሔሞት ያለ ፍጥረቱን ጌታ ይቅር ይለዋል፤ አንድም ንግበር ሰብአ ብሎ የፈጠረውን ይቅር ይለዋል ፤

፬፡ ወመኑ ዘይቀፍጽ ግልባቤ ገጹ ፤

የዘንዶ የብሔሞትን ከንፈሩን የሚገልጠው ማነው ? አንድም

www.ethiopianorthodox.org

የዲያብሎስን ሠራዊት ድል የሚነሣ ማነው ?

ወመኑ ይበውእ ውስተ ማኅበርተ እንግድዓሁ ፤

ወደ ደረቱ የሚገባ ማነው? እንድም በማኅሳት ንብብር የሆኑ ሠራዊትን ድል የሚነሣ ማነው?

፭፡ ወመኑ ያርኑ መዓፁተ ዘቅድመ ገጹ ፤

በፊቱ ያለ መዝጊያውን የሚከፍት ማነው ማለት ሥልጣኑን የሚያርቅ ማነው ?

ወያዶ ለስነኒሁ ግርማ ፤

የብሔሞት የዘንዶን ጥርሱን መፈራት ከቦታል፤ አንድም የዲያብሎስን ጥርስ መፈራት ከቦታል ፤

፮፡ ወአማዑቲሁ አራዊት ዘብርት ፤

አንጀቱ የብረት ነው፤ ማለት ዕኑዕ ነው፤ አንድም ሠራዊቶቹ ጽኑዓን ናቸው ፤

ወቍዕረቱኒ ከመ ዕብነ ኰኵሕ ፤

ጀማቱ ቍጥርጥር ያለ ነው ማለት እንደ ዋሻ ደንጊያ ጽኑዕ ነው፤ አንድም ሠራዊቶቹ ጽኑዓን ናቸው ፤

፯፡ ወአሐዱ ምስለ ካልኡ ተማበቀ፤

እምተማበቀ ሲል ነው፤ ብሔሞትን ቢያይ አንዱ ከአንዱ ጋራ በተጨናነቀ ነበር፤ አንድም ዲያብሎስ አምስት ሺህ ከአምስት መቶ ዘመን ሰውን አስጨንቆ ኖረ፤

ወመንፈስሂ ኢይበርብሮ ፤

ነፋስ አይገባውም፤ አንድም ምግባረ ነቢያት ድል አይነሣውም፤

፰፡ ወያስተላክዕ ብእሲ ምስለ እኁሁ፤

እምተላክዐ ሲል ነው፤ ብሔሞትን ዘንዶን ቢያይ፤ ሰው ከወንድሙ ጋራ በተያያዘ ነበር፤ አንድም አምስት ሺህ ከአምስት መቶ ዘመን ወንድም ከወንድሙ ጋራ ተያይዞ ኖረ ፤

ወይማበቁ ወኢይትፋትሑ ፤

እምተተማበቁ ሲል ነው፤ በተጨናነቁ በአልተለያዩም ነበር፤ አንድም አምስት ሺህ ከአምስት መቶ ዘመን ተጨናነቁ አልተለያዩም ፤

፱፡ ወበዕጠሱ ይበርቅ ብርሃን ፤

ከብሔሞት ከዘንዶ በፊቱ እሳት ቦግ ይላል፤ አንድም ከዲያብሎስ ክፉ ዕውቀት ይገኛል ፤

ወአዕይንቲሁ ከመ ኮከበ ጽባሕ ፤

የብሔሞት የዘንዶ ዓይኖቹ እንደ አጥቢያ ኮከብ ናቸው፤ አንድም ዲያብሎስን በጥንት ተፈጥሮው ኮከበ ጽባሕ አለው፤ እሮ ወድቀ እምሰማይ ኮከበ ጽባሕ እንዲል፤



፲፡ ወእምአፉሁ ይወጽእ መኃትው ዘይነድድ ወይዌሩ አፍሐመ እሳት ፤

ከአፉ እሳት ይወጣል፤ የእሳት ፍም ይወረወራል ፤ አንድም ከዲያብሎስ ክፉ ዕውቀት ይገኛል ፤

፲፩፡ ወእምአንፉ ይወጽእ ጢስ ከመ ዕቶን ዘይነድድ በአፍሐመ እሳት ፤

በእሳት ፍሕም እንደሚነድ ምድጃ ከአፉ ጢስ ይወጣል፤

፲፪፡ ነፍሱሂ ፍሕም ይእቲ ፤

የብሔሞት ሰውነቱ እሳት ናት፤ አንድም የዲያብሎስ ተፈጥሮው ከእሳት ነው ፤

ነበልባል ይወጽእ እምአፉሁ ፤

ከአፉ እሳት ይወጣል፤ አንድም ከዲያብሎስ ክፉ ዕውቀት ይገኛል ፤

፲፫፡ ወውስተ ክሣዱ ኀደረ ኃይል፤

በዘንዶ በብሔሞት በአንገቱ ኃይል አድሮበታል ፤ አንድም በዲያብሎስ በሠራዊቱ ኃይል አድሮባቸዋል ፤

ወአለ በቅድሜሁ ሞት ለዘይሬእዮ፤

እምወአለ ሲል ነው፤ ብሔሞትን ለሚያየው ሰው ሞት በፊቱ በዋለ ነበር ፤ አንድም ፭ሺህ አምስት መቶ ዘመን ሞተ ነፍስ በፊቱ ተደረገ ፤

፲፬፡ ሥጋሁ ወነፍሱ ጥቡቅ ፤

የዘንዶ የብሔሞት ሰውነቱ ንብብር ነው ፤ አንድም ሠራዊቱ ለማኅሳት ንብብር ናቸው ፤

ወእመ ሦጡ ላዕሌሁ ዕብነ ኢይትሐወስ ፤

ዘንዶ ብሔሞት ደንጊያ በላዩ ላይ ቢጥሉበት አይንቀሳቀስም፤ አንድም ዲያብሎስን ድል የሚነሣ የለም ፤

፲፭፡ ልቡሂ ጽኑዕ ከመ ዕብነ ያላዕ፤

የዘንዶ የብሔሞት ልቡም እንደ ዋሻ ደንጊያ ጽኑዕ ነው፤ አንድም አሕዛብ ዲያብሎስን ድል አይነሱትም ፤

ወይቀውም ከመ ሕፃን ንሁስ ፤

እንደ ታናሽ ሕፃን ቀጥ ብሎ ይቆማል፤ አንድም ሕፃን ቢሠራ ቢሠራ እንዳይደክም ዲያብሎስም ቢያስት ቢያስት አይደክምም ፤

፲፮፡ ወእመሂ ተመይጠ ይሜምዑ ኵሎሙ አራዊት ወእንስሳ ወዘይትሐወስ ዲበ ምድር ፤

ዘንዶ ብሔሞት ቢመለስ በዚህ ዓለም የሚመላለሱ እንስሳት አራዊት ሁሉ ይሸሻሉ፤ አንድም ዲያብሎስ ቢመለስ ምዕመናን ድል ይነሣሉ ፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፯፡ ወእመሂ ጠበቆ ኲያንው አልቦ ዘይሬስዮ ፤

ብሔሞትን ዘንዶን ጦር ቢያስ ጨንቀው የሚጎዳው የለም ፤ አንድም ዲያብሎስን ምግባረ ነቢያት ድል አይነሣውም ፤

፲፰፡ ረምሕ ወልብሰ ሐፂን ከመ ሐሠር እሙንቱ በቅድሜሁ ፤

ዘገር ጥሩር በእሱ ዘንድ እንደ ገለባ ናቸው፤ አንድም ምግባረ ምዕመናን ድል አይነሣውም ፤

ወብርትኒ ከመ ዕፅ ብኑብኑ ፤

ብርቱም እንደ በሰበሰ ዕንጨት የተናቀ ነው፤ አንድም ምግባረ ምዕመናን ድል አይነሣውም ፤

፲፱፡ ወኢይሠቀሮ ቀስተ ብርት ፤

የብርት ቀስት አይወጋውም፤ አንድም ምግባረ ነቢያት ድል አይነሣውም ፤

ወዕብንኒ ከመ ኃሠር በቅድሜሁ ፤

በዘንዶ በብሔሞት ፊት ደንጊያው እንደ ገለባ የተናቀ ነው፤ አንድም በዲያብሎስ ፊት ምግባረ አሕዛብ የተናቀ ነው፤

ብርሀ ይመስሎ መፍጽሕ ፤

ድጅኖው ገለባ ይመስለዋል ፤ አንድም ምግባረ ምዕመናን ድል አይነሣውም ፤

ወይስሕቅ ላዕለ ዕብን ዓቢይ ፤

ዘንዶ ብሔሞት በታላቅ ደንጊያ ይዘብታል ማለት ይጐዳኛል አይልም፤ አንድም ዲያብሎስ በምዕመናን አሕዛብ ይዘብታል፤

፳፡ ወምስካቡሂ ሐውልት ዓቢይ ፤

ምኝታውም ታላቅ ደንጊያ ነው፤ አንድም አሕዛብ ማደሪያዎቹ ናቸው ፤

ወኲሉ ወርቀ ባሕር በኀቤሁ ከመ ዕቡር ዘአልቦ ኍልቈ ፤

ከባሕር የሚገኝ ወርቅ ሁሉ በሱ ዘንድ ቊጥር ስፍር እንደሌለው ጭቃ ነው፤ በወርቅ አሸዋ አስተኝቶታል፤ አንድም ወርቀ ባሕር ምዕመናን በዲያብሎስ ዘንድ እንደ ጭቃ የተናቁ ናቸው ፤

፳፩፡ ወያንሰአሥኣ ለሲኦል ከመ ዕሕርት ፤

ብሔሞት ውቅያኖስን እንደ ብረት ድስት ውሀ ያፈላታል ፤ አንድም ዲያብሎስ ሲኦልን ያነሣሳታል ፤

ባሕርኒ በድው ይመስሎ ፤

ለዘንዶ ለብሔሞት ውቅያኖስ ምድረ በዳ ይመስለዋል ፤ አንድም ለዲያብሎስ ገሃነም ምድረ በዳ ይመስለዋል ፤



፳፪፡ ወቀሩረ ሲኦልሂ ከመ ፂው ፤

የውቅያኖስ ቅዝቃዜ በረኃ ይመስለዋል፤ አንድም የሲኦል ቅዝቃዜ በረኃ ይመስለዋል ፤

ወረስዮ ለሲኦል ኀበ ያንሶሱ ፤

ብሔሞት ዘንዶ ውቅያኖስን መመላለሻ አደረጋት፤ አንድም ዲያብሎስ ሲኦልን መመላለሻ አደረጋት ፤

፳፫፡ ወአልቦ በዲበ ምድር ወኢምንትኒ ዘከማሁ ፤

በዚህ ዓለም እንደ ብሔሞት እንደ ዲያብሎስ ያለ ፍጥረት ምንም ምን የለም ፤

ወተፈጢሮ ተሣለቁ ላዕሌሁ መላእክቲሁ ፤

ብሔሞት በተፈጠረ ጊዜ መላእክት አመሠገኑ፤ አንድም ዲያብሎስ በተፈጠረ ጊዜ መላእክት ዘበቱበት ፤

፳፬፡ ወይሬኢ ኲሎ ነዋኀ ፤

ብሔሞት በሩቅ ያሉትን ያያል ዓይኑ ብሩህ ነው፤ አንድም ዲያብሎስ በጸጋ ዕውቀት መጻዕያትን ያውቃል ፤

ውእቱ ንጉሦሙ ዘውስተ ማይ ፤

ብሔሞት በውሀ ውስጥ ላሉት ንጉሣቸው ነው፤ አንድም ዘውስተ ሰማይ ይላል ዲያብሎስ ለአጋንንት ንጉሣቸው ነው ።

## ምዕራፍ ፵፪

አርባ ሁለተኛው ምዕራፍ ይህ ነው ፤

፩፡ ወተሰጥዎ ኢዮብ ለእግዚአብሔር ወይቤሎ ፤

ኢዮብ ለእግዚአብሔር መለሰለት እንዲህ አለው ፤

፪፡ አአምር ከመ ኵሎ ትክል ወኵሉ ይትከሃለከ ወአልቦ ዘይሰአነከ ፤

ሁሉን እንድትችል ሁሉን ማድረግ እንዲቻልህ የሚሳንህ እንደ ሌለ አውቃለሁ ፤

፫፡ መኑ ውእቱ ዘየኃብዓከ ምክረ ፤

ምክር የሚሠውርህ ማነው ፤

ወዘይምሕክ ነገረ ውስተ ልቡ ፤

ነገርን በልቡናው የሚሠውር ማነው ፤

እምኔከ ዘይሤውር ይመስሎ ፤

ከአንተ የሚሠውር ይመስለዋል፤ አንድም ቢሠውር ቢሠውር ከአንተ የሚሠውር ይመስለዋልን፤

መኑ ይነግረኒ ዘኢየአምር አቢየተ ወመንክራተ ዘኢርኢኩ ፤

ያላየሁትን ድንቅ ነገር የማላውቀውን ብዙ ነገር ማን ይነግረኝ ነበር፤ አንተ ነገርኸኝ እንጂ ፤

፬፡ ስምዓኒ እንግርከ እግዚኦ ፤

አቤቱ እነግርህ ዘንድ ስማኝ፤

www.ethiopianorthodox.org

አነሂ እሴአለከ ወአንተ መሀረኒ ፤

እኔ እጠይቅሃለሁ አንተም አስተ ምረኝ ፡

፭፡ ሰሚዐሰ ቀዲሙ ሰማዕኩ በእዝንየ፤

መስማቱንስ ቀድሞ በጆሮዬ ሰምቼ ነበር ፡

ወይእዜሰ ርኢኩ በአዕይንትየ ፤

ዛሬ ግን በዓይኔ አየሁ ፡

፮፡ ወባሕቱ በዘተዛለፍኩስ ተመሰ ውኩ ፤

ነገር ግን ከእግዚአብሔር ጋራ በተከራከርሁ ብዬ በመጣብኝ መከራ እንደ ሰም ቀለጥሁ ፡

አአምር ርእስየ ከመ መሬት ወሐ መድ አነ ፤

እኔ አመድ ትቢያ እንደሆንሁ ራሴ አውቃለሁ ፡

፯፡ ወእምድኅረ ተናገሮ እግዚአብሔር ለኢዮብ ዘ ነገረ ፤

እግዚአብሔር ለኢዮብ ይህን ነገር ከነገረው በኋላ ፡

ይቤሎ እግዚአብሔር ለኤልፋዝ ቴማ ናዊ አበስከ አንተ ወ፪ኤቱ አዕርክ ቲከ ፤

እግዚአብሔር የቴማኑን ሰው ኤልፋዝን አንተ በደልህ ሁለቱ ባለንጀሮችህም በደሉ አለው ፡

እስመ ኢተናገርክሙ ጽድቀ ቅድሜየ ከመ ኢዮብ ቍልዔየ ወኢአሐተኒ ፤

እንደ ወዳጄ እንደ ኢዮብ አን ዲትስ ስንኳ በፊቴ እውነት ነገር አልተናገራችሁምና ፡

፰፡ ወይእዜኒ ንሥኡ ፯ አልህምተ ወ፯ አባግዐ ፤

አሁንም ሰባት ላሞች ሰባት በጎች ይዛችሁ ፡

ወሑሩ ኀበ ቍልዔየ ኢዮብ ወይግ በር ለክሙ መሥዋዕተ ፤

ወደ ወዳጄ ወደ ኢዮብ ሒዱ መሥዋዕቱን ይሠዋላችሁ ፡

ወኢዮብ ቍልዔየ ይጼሊ በእንቲአ ክሙ ወእምገጸ ዚአሁ እነሥእ ፤

ስለናንተ ወዳጄ ኢዮብ ይጸል ይላችሁ ከእሱ እቀበላለሁ ፡

ወሶበ አኮ በእንቲአሁ እምቀተልኩ ክሙ ፤

እሱ ባይለምንላችሁ ባጠፋኋችሁ ነበር፤ አንድም የሱን ድኅነት ታያላችሁ ባልል ባጠፋኋችሁ ነበር፤ አንድም ትንቢቱ ይፈጸ ማል ባልል በአጠፋኋችሁ ነበር፤

እስመ ኢነበብክሙ ርትዓ ላዕለ ቍል ዔየ ኢዮብ ፤

ጽድቀ ሲል ነው ፡ በወዳጄ በኢዮብ ላይ እውነት ነገር አል ተናገራችሁምና ፡



፱፡ ወሖሩ ኤልፋዝ ቴማናዊ ወበል ዳዶስ አውኬናዊ ወሳፋር አሚናዊ ፤

የቴማኑን ሰው ኤልፋዝ የአው ኬን ሰው በልዳዶስ የአሚን ሰው ሳፋር ሂዱ ፡

ወገብሩ በከመ አዘዞሙ ፤

እግዚአብሔር እንደ አዘዛቸው አደረጉ ፡

ወሰረየ ሎሙ ኃጢአቶሙ በእንተ ኢዮብ ፤

ስለ ኢዮብ ፡ አንድም ኢዮብ ስለ ለመነላቸው እግዚአብሔር ኃጢአታቸውን ይቅር አላቸው፤

፲፡ ወአሕየዎ እግዚአብሔር ለኢዮብ እምደዌሁ ፤

እግዚአብሔር ኢዮብን ከደዌው አዳነው ፡

ወጸለየ በእንተ አዕርክቲሁ ፤

ስለ ወዳጆቹ ለመነ ፡

ወኀደገ ሎሙ ኃጢአቶሙ ፤

ኃጢአታቸውን ይቅር አላቸው፤

ወወሀቦ እግዚአብሔር ለኢዮብ ካዕበ ኵሎ ንዋዮ ዘቀዲሙ ፤

የቀደመ ገንዘቡን ሁሉ እጽፍ ድርብ አድርጎ እግዚአብሔር ለኢዮብ ሰጠው፤

ወአመክዓበ ሎቱ ፤

እጽፍ ድርብ አደረገለት፤ ከወ ዴት አምጥቶ ሰጥቶታል ቢሉ

ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር አለ፤ እም ኀበ አልቦ አምጥቶ ሰጥቶታል፤ አንድም እኒያ የዘረ ፉት አሕዛብ እንደረቡ አምጥ ተው ሰጥተውታል ፡

፲፩፡ ወሰምዑ ኵሎሙ አኃዊሁ ወአ ኃቲሁ ዘረከቦ ፤

እኅቶቹ ወንድሞቹ ሁሉ ያገኘ ውን ሰሙ ፡

ወመጽኡ ኀቤሁ ኵሎሙ እለ የአም ርዎ ቀዲሙ ፤

ቀድሞ የሚያውቁት ሰዎች ሁሉ ወደእሱ መጡ ፡

በልዑ ወሰትዩ ምስሌሁ ወአስተፍ ሥሕዎ ፤

ከሱ ጋራ በሉ ጠጡ፤ ደስ አሰ ኙት ፡

ወአንከሩ በእንተ ኵሉ ዘአምጽአ እግዚአብሔር ላዕሌሁ ፤

ሎቱ ሲል ነው፡ እግዚአብሔር በሱ ስላመጣበት ሁሉ አደነቁ፡

ወወሀብዎ ለለ፩፩ ዕምደ አልሕምት፤

አንዱም አንዱ ጥምድ በሬ ሰጡት ፡ አንድም ወወሀበሙ ይላል ፤ ለአንዱም ለአንዱም ጥምድ ጥምድ በሬ ሰጣቸው ፡

ወርቀ ወብሩረ በመድሎቱ ዘድድ ርከሚ ፬ ፤

አራቱንም ድሪም አንድ በሚያ ደርግ ሚዛን ወርቁን፤ ብሩን

www.ethiopianorthodox.org

ሰጡት፤ አንድም አራት አራት ድሪም ሰጣቸው ፡፡

፲፪፡ ወባረከ እግዚአብሔር ደኃሪቶ ለኢዮብ እምቀዳሚቱ ፡፡

ከቀደመው ይልቅ እግዚአብሔር ለኢዮብ የኋላውን ገንዘቡን አበ ዛለት ከብቱ ሁሉ እጥፍ እጥፍ ሁኗል ፡፡

ወእንስሳሁኒ ፲፻ወ፬፻ ፡፡

ሰባት ሺህ የነበሩ ከብቶቹም ፲፻ ከአራት (አሥራ አራት) ሺህ ሆኑ ፡፡

አባግዒሁ ፷፻ ፡፡

ወአመክዓበ ሎቱ ብሎ ነበርና በጎቹ ሦስት ሺህ የነበሩ ስድስት ሺህ ሆኑ ፡፡

ዕምደ አልሕምቲሁኒ ፲፻ ፡፡

አምስት መቶ የነበረው ጥማዱ ሺህ ሁኗል ፡፡

ወአዕዱጊሁኒ አዕኑስ ፲፻ ፡፡

አምስት መቶ የነበሩ ባዝሮቹ ሺህ ሁነዋል ፡፡

ወአግማሊሁኒ ፲፻ ፡፡

አምስት መቶ የነበሩ ግመሎቹ ሺህ ሆኑ ፡፡

፲፫፡ ወተወልዱ ሎቱ ፯ደቂቅ ወሠላስ አዋልድ ፡፡

ስድስት ወንዶች ሦስት ሴቶች ልጆች ተወለዱለት፤ ልጆቹን ግን እጥፍ አላደረገለትም ስለምን ቢሉ የሞቱት በነፍስ ሕያዋን ስለሆኑ ፡፡

፲፬፡ ወስማ ለቀዳሚት ዕለት ፡፡

የመጀመሪያዪቱ ዕለት ትባላ ለች ማለት ፀሐይ ማለት ነው፤ ኤልማማ ይላል ፀሐይ ማለት ነው፤

ወለካልዕታ ቃሲያስ ፡፡

ሁለተኛዪቱ ቃሲያስ ትባላለች ጨረቃ ማለት ነው፤ አንድም ቀስዋ ይላል ወርኅ ማለት ነው፤

ወለሣልስታኒ አሜልትያስቂራስ ፡፡

ሦስተኛዪቱ ኮከባ ትባላለች ፡፡ አንድም ቀርነፉሕ ይላል፤ ሥል ጣን በዲበ ሥልጣን ቀርን በዲበ ቀርን ሽቱ ማለት ነው ፡፡

፲፭፡ ወኢተረክበ ሠናይ በታሕተ ሰማይ ዘከመ አዋልደ ኢዮብ ፡፡

ከሰማይ በታች በዚህ ዓለም እንደ ኢዮብ ልጆች ያለ መልከ መልካም አልነበረም ፡፡

ወወሀቦን አቡሆን ርስቶን ምስለ አኃዊሆን ፡፡

መልከ መልካም ስለሆኑ አባታ ቸው ርስታቸውን ከወንድሞቻ ቸው ጋራ ሰጣቸው ፡፡

፲፮፡ ወሐይወ ኢዮብ እምድኅረ መቅሠፍቱ ፻ተ ወ፸ ክረምተ ፡፡

ከደዌው ከተፈወሰ በኋላ ኢዮብ መቶ ሰባ ዘመን ኖረ ፡፡



ወኵሎ ዘሐይወ ፪፻፵ወ፰ ዓመት ፡፡

በዚህ ዓለም የኖረው መላ ዘመኑ ሁለት መቶ ዓርባ ስምንት ነው፤

ወርእየ ኢዮብ ደቂቆ ወደቂቀ ደቂቁ እስከ ራብዕ ትውልድ ፡፡

ኢዮብ እስከ አራት ትውልድ ድረስ ልጁን የልጅ ልጁን አየ፤

፲፯፡ ወሞተ ኢዮብ ልሂቆ ወፈጺሞ መዋዕሊሁ ፡፡

ኢዮብ አርጅቶ በተፈጥሮ የተሰ ጠውን ዘመኑን ፈጽሞ ሞተ ፡፡

፲፰፡ ወጽሑፍ ከመ ይትነሣእ ካዕበ ምስለ እለ ያነሥኦሙ እግዚአብሔር፤

እግዚአብሔር ከሚያስነሣቸው ጋራ ዳግመኛ እንዲነሣ ተጽፏል፤

፲፱፡ ወከመዝ ትርጓሜሁ እመጽሐፈ ሶርያ ፡፡

ከሶርያ የመጣ የመጽሐፉ ትር ጓሜ ይህ ነው፤ ከሱርስት ወደ ዕብራይስጥ ተመልሷልና፤ ሙሴ ምድያምን በወጋ ጊዜ የደገ የኢዮብ መጽሐፍ ከዚህ አለ ብለው ነገሩት፤ እሱ ከሶርያ ወደ ዕብራይስጥ መልሶታል፤ አንድም ዳዊት ኤዶምያስን በወጋ ጊዜ ከዚያ አግኝቶ ይዞት መጥቷል፤

ብሔሩሰ ኀበ ይነብር አውስጢድ ዘደ ወለ ኤዶምያስ ዘዓረብ ፡፡

የሚኖርበት አገሩ ግን በምዕራብ በኩል ባለ በኤዶምያስ አውራጃ አውስጢድ ነበር አውስጢድ ከተማው ነው፤ መላው ኤዶም ያስ ይባላል ፡፡

፳፡ ወሰመይዎ ስሞ ኢዮባብ ፡፡

ስሙን ኢዮባብ አሉት፤ ኢዮብ ማለት አበባ፤ ጨረቃ ማለት ነበር፤ ፍሬ ፀሐይ አሉት ፡፡

ወአውሰበ ብእሲተ ዓረባዊተ ፡፡

አረማዊተ ሲል ነው፤ አረማዊት ሴት አገባ ፡፡

ወወለደት ሎቱ ወልደ ዘስሙ ኄኖን፤

ስሙ ኄኖን የሚባል ወንድ ልጅ ወለደችለት ፡፡

ወውእቱ አቡሆሙ ለዝኑራን ፡፡

የዝኑራን አባታቸው ነው ፡፡

ወልደ ወልዱ ለኤሳው ፡፡

ይኸውም ኢዮብ የኤሳው የልጅ ልጅ ነው ፡፡

ወእሙ ባሱራስ ፡፡

እናቱም ባሱራስ ትባላለች ፡፡

ወኃምስ ውእቱ ኢዮብ እምአብርሃም፤

አብርሃምን ትቶ ቢቈጥሩ አም ስተኛው ነው፤ ይስሐቅ፤ ኤሳው፤ ራጉኤል፤ ዛራ፤ ኢዮብ አምስ ተኛ ነው ፡፡

፳፩፡ ወእሉ ነገሥት እለ ነግሡ በኤ ዶም ፡፡

በኤዶምያስ የነገሡ ነገሥታት እኒህ ናቸው ፡፡

www.ethiopianorthodox.org

፳፬፡ ወውእቱ ኮነ በሐውርተ ቀዳሚ ባላቅ ወልደ ቤዖር ፤

መጀመሪያ የቢዖር ልጅ ባላቅ አገሩን ሁሉ ገዛ ፤

ወስመ ሀገሩ ዲናባ ፤

የሀገሩ ስም ዲናባ ይባላል ፤

፳፭፡ ወእምድኅረ ባላቅ ነግሠ ኢዮባብ ዘስሙ ኢዮብ ፤

ከሱ ቀጥሎ ስሙ ኢዮባብ የተባለ ኢዮብ ነገሠ ፤

ወእምድኅሬሁ አሶም ዘነግሠ በብሔረ ቴማን ፤

ከሱ ቀጥሎ ቴማን በሚባል አገር የነገሠ አሶም ነው ፤

፳፮፡ ወእምድኅሬሁ ለአሶም ነግሠ አዳድ ወልደ ባራድ ዘቀተሎሙ ለምድያም በሐቅለ ሞዓብ ፤

ከሱ ቀጥሎ በሞዓብ አውራጃ የምድያምን ሰዎች ያጠፋቸው አዳድ ወልደ ባራድ ነው ፤

ወስመ ሀገሩ ጌቴም ፤

የሀገሩ ስም ጌቴም ይባላል ፤

፳፯፡ ወእለሂ መጽኡ ኀቤሁ አእርክቲሁ ኤልፋዝ ዘእምደቂቀ ኤሳው ንጉሠ ቴማን ፤

ወደሱ የመጡ ወዳጆቹም በቴማን የነገሠ ከኤሳው ልጆች ወገን የሚሆን ኤልፋዝ ነው ፤

ወበልዳዶስ መስፍነ አውኬናዎን ፤

በአውኬን የተሾመ በልዳዶስ ነው ፤

ወሳፍር ንጉሠ አሜኔዎን ፤

የአሜኔዎን ንጉሥ ሳፍር ነው፤
ተፈጸመ መጽሐፈ ኢዮብ ጻድቅ በረከተ አምላኩ የሃሉ ምስሌነ፤

ወስብሐት ለእግዚአብሔር ፤

አነቃቅቶ ለአስጀመረን አተጋግቶ ለአስፈጸመን ለእግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይግባው አሜን ፤ በእውነት ፡፡

www.ethiopianorthodox.org